# ጉንጉን



ከ-ኃይለመለኮት መዋዕል

# ጉ ን ጉ ን

ልቦለድ

ከኃይለ መለኮት መዋዕል

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
[illegible]

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ / Tel. 11 27 19

ፖስታ ሣ. ቁ. / P. O. Box [illegible]

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
Ethiopia

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

የሽፋን ሥዕል — መስፍን ሀብተ ማርያም ግዘው

በሀሌ ማተሚያ ቤት ታተመ

ለእህቴ
ለበለጡ ስሜነህ ዓለሙ
እና
ለወንድሞቼ
ለደምመላሽ ስሜነህ ዓለሙ
ለአፈወርቁ መዋዕል መሐሪ

# ምዕራፍ  አራት

‘የቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ  የምርጫ ሳጥን በመሙላቱ ፣ ተጨማሪ ሳጥን እያስፈለገ ነው’ የሚል ወሬ እየተጋነነ በመወራቱ ደጋፊዎቻቸው ሁሉ ተደሰቱ ። እሳቸውም ዳመራን በችቦ ብርሃን እዩልኝ የማለት ያህል የሚሰሟትን ሁሉ እያጋነኑ ወሬ  መንዛት አበዙ ። ወ/ሮ ደጅ ይጥኑም እንኮይ መሳይ ፊታቸውን እያፍለቀለቁና ድብኚት የሚያህል ቂጣቸውን እንደ አዳል በግ ላት እያወዛወዙ ጉራቸውን ይነፉሉ ።

ቀኛዝማች ረዘም—ደልዳል ባለ ቁመናቸው ላይ ጥቁር የሱፍ ኮትና ሱሪ ለብሰው ከወዲያ ወዲህ ሲሉና በምርጫው ጣቢያ አካባቢ ሲጎማለሉ ‘ያለኔ ማን አለ ፣ እስቲ ልናይ አደል’ የሚሉ ይመላሰሉ ። ረዘም ያለው ገጽታቸውና ቀይ ዳማ ፊታቸው ከገብስማ ጸጉራቸው ጋር ደስ የሚል ግርማና ተወዳጅነት አለው ። ከግራና ከቀኝ እንደ ወሸመጥ ገባ—ገባ ያለው የጸጉራቸው በራ ግንባራቸውን በመጠኑ ሰፋ አድርጎታል ። ስልክክ ያለ አፍንጫቸው  መኻሉ ላይ እንደ ደጋን ጎበጥ ብሎ ከወደ ጫፉ የተንጠለጠለ ናዳ ይመስላል ።

ዘመድና ወዳጅ ነኝ ባዩ ሁሉ በስጡት ገንዘብ ጋብዞ እያስጋበዘ ተጨማሪ ሰው አጋበሰ ። እሳቸውም “እንደ ጤፍ የዘራሁትን ብር እጥፍ —በጥፍ አገኘዋለሁ” የሚሉት ፣ በዝምድና እየተሳበ ፣ እንዲሁም በስጦታና በመደለያ እየተንጋጋ የሚመጣውን ሕዝብ ጠባይ ስለሚያውቁት ነበር ።

ሌላው የአሸናፊነታቸው ምንጭና ብርታት አድርገው የሚመለከቱት ደግሞ የአንቃሩን ውቢት ሚካኤል ሲሆን ፣ ለእንዲህ ያለው ጊዜ አለሁልህ ካላላቸው ለሙቼም እንደማይሆናቸው በሳቸውም ፣ በነፍስ አባታቸው በመምሬ ተክለ ጊዮርጊስም ተነግሮታል ።ምንጊዜም እሱን ተተግነው ጠላቶቻቸውን እንደሚያሸንፉ ያምናሉ ። አንዳንድ ጊዜማ የሚፈሩትም ፣ የሚያከብሩትም ታማኝና ብርቱ ጓደኛቸው ይመስላቸዋል ። እንደዚያ ባለው ጊዜ “ቅሩበ የማንየ ሀሉ ወኢትቁም ርኁቀ” ይሉታል ።

እሱም ቢሆን ቆርቆሮ ቤት ውስጥ መግባት ይፈልጋል ። ከቀኛዝማች ጋር የተቀያየሙትና ለአጭር ጊዜም ቢሆን ችላ ያላቸው ፣

ምርና ቢወፍር ፣ ሞፈር አይሆን ድግር ። አየህ ፣ አሁን ለምሳሌ የማንም የገበሬ ልጅ ምንም ያክል ቢያውቅና — ቢማር ፣ ከየትም ብድግ አርገህ አማካሪ ወይም አገረ ገዢ እንዲሆን ብትሾመው ፣ ስንትና ስንት ነገር ያበላሻል ። እንዲያው ምንም ቢሆን ያላባቱ አይሆንም ። በትምርት የሚገኝ ሌላ—ሌላው ነው ።”

“አሁንም እኮ ጌታዬ” አለ ሰውዬው ደርበብ ባለ ፈገግታ ፣ “ማንኛውም ሰው በዘፈቀደ እንዳይገባና በስመ—መብት የሀገር ልማድና ወግ እንዳይፋለስ የተለየ ክትትልና ጥንቃቄ ይደረጋል ። በጽሑፍ ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ቢያሟላም ፣ ማንነቱና ምንነቱ ሁሉ ተጣርቶ ካልሆነ በቀር ዋጋ የለውም ። አለበለዚያማ ማንም ገብቶ ከታጎረ ነገር ተበላሸ ። ይኸ በየትም ያለ ነው ።”

ቀኛዝማች ሐሳባቸውን ለወጡና ፣ “ሰው ጠቃሚውን አያጣውም ፣ የሚያርሰውን መሬት ሰጥተን ፣ ይበላው ሲቸገር አለቅተን ፣ የዘንድሮን ቢያጣ እስከ ከርሞ አቆይተን ፣ ከባሰበትም ይቅር — ተወው ብለን ፣ ስንቱን ችለን ነው ። የምር አይምሰልህ ። እንግዲህ አንተም ሥር—ሥሩን አደራህን ። እኔም እንኳንና ይኸን ያክል ደግ ለሚውልልኝና ለትንሿ ነገርም እንቅልፍ የለኝ ።”

ቀኛዝማች ፣ እንደ ልማዳቸው ያመሰገኑትን እየነቀፉና የሰደቡትን እያመሰገኑ የገዛ ሐሳባቸውን ካምታቱ በኋላ ነገራቸውን አጠቃለሉ ።

“በኔ በኩል ግድ የለም ። ከብዙ አደራ መተማመን ይበልጣል” ብሎ የሞቀ ተስፋ ሰጣቸው ።

የምርጫው አስፈጻሚና ተቆጣጣሪ ማጀቴ ከገባ ጀምሮ ላይን—ያዝ ሲያደርግ በጓሮ በር በኩል ወደ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ቤት ዘው ይላል ። እሱም ቢሆን የራሱን ጉዳይ ያጠነጥናል ። በመጀመሪያ ሴትየዋ ላይ እንዣብቦ የነበረ ቀልቡ ክንፉን ከሰበሰበ ወዲህ ከዚያው ከቤት ሳይወጣ ያተር ፍልፍል በመሰለች ሸጋ ልጅ ውበት በመማረኩ ፣ የምርጫው ጊዜ ቢራዘምና የድምፅ ቆጠራው ቀን ቢጓተት ደስታው ነበር ። ወ/ሮ ደጅ ይጥኑም ይቺኑ ዐውቀው ፣ የጓሮ በራቸውን ከፍተው ፣ ከዚህም ከዚያም በርቱ ይላሉ ። እንኳን ይቺን ታህል አግኝተው ። አብራቸው የምትኖረው ላቀች ተገኜ ድረ— ገብ በመሆኗና ከቃላቸው እንደማትወጣ ስለሚያውቁ ፣ ነገሩ ለራሳቸውና ለቀኛዝማች የሚያስገኘውን ጥቅም በመመልከት ፣ አጥበውና አጥነው ቁርበት ከተነጠፈበት የጠፍር አልጋ ጋር ጀባ ይሉታል ።

ነጋ ጠባ ግብዣ ሆነ ። ሰውዬውም በመጣ ቁጥር ምናምን ኮልኮል ማድረግ ጀመረ ። ዓለማቸውን አዩ ።



ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ የዶሮውን ቅልጥም በእንጀራ ጠራርጎ ቀረብ ፣ በስንደዶ ተጠቅጥቆ ቅቤ የነሰረውን እንቁላል ፈርከስ ፣ እያደረጉ ማጉረስን ፣ ማወራረጃውን ባናት—ባናቱ መሙላትን ሥራዬ ብለው ተያያዙት ።

“ጠግቤአለሁ እኮ እሜትዬ ፣ በጣም ብዙ በላሁ” ይላል ሰውዬው ፣ የሴትዮዋን ማራኪ ዐይንና የብራ በረዶ የመሰለ ጥርስ ፣ እርስ—በርሱ በጥፊ የሚማታ ቂጥና ባዝቶ ገላ በጓጓ ዐይን እየተመለከተ ። ባይኑ ካመነዘረ ውሎ አድሯል ።

“በሞቴ ፣ አፈር ስሆን ፣ በኬብሮዋ ማርያም ! ይቺን ብቻ ፣ አልመለስብህም ፣ ምነው ? አዲሳባ ስትመጣ ታስቸግረኛለች ብለህ ነው” ይላሉ የመሔዱ ነገር እየታያቸው ።

“ኧረ በሆነና እንግድነትዎ ባስቸገረኝ — —”

“ቀኛማይ ከሔዱ አብሬ መሔዴ አይቀርም”

“እርግጠኛ ነኝ ! ይኸ ነገር እንደሚሳካ አይጠራጠሩ” ሲል ጉዳዩ ወዲያው ከፍጻሜ የደረሰ ስለሚመስላቸው ፣ ፊታቸውን ወደ ማጀቴ መድኃኔ — ዓለም ያዞሩና ፣ በርከክ ካሉ በኋላ ፣ መሬቱን ሲስሙ ቂጣቸው ቀሚስ የለበሰ ጋን መስሎ ይከመራል ። ይኸው ቂጥ ቀኛዝማችን አናውዟል ። ሰውዬውንም አማሏል ። በላቀች ላይ የነበረው ፍላጎት ባይቀንስም ሴትዬዋንም ተመኘቸው ።

አንዳንዱ ‘እንጉሡ ዘንዳ ደርሰው መጡ አሉ’ ይላል ። ሌላው ‘አንተ እዚያው ሆነህ አገርህን ጠብቅ ብለው ሾሟቸው አሉ’ ሲል ፣ ሌላው የከተማ ሰው ነኝ ባይ ደግሞ ‘አዲሳአባ ላሉት ዘመዶቻቸው መመረጣቸውን ሊነግሩ ነበር የሔዱት’ይላል ።

ለቅምጣቸው ከሻሹም ከሽቶውም ይዘው ሲመለሱ‘ እሷ እኮ ምላሷ ነው፡ ሆዷ ገር ነው’ ለሚሏቸው ለባለቤታቸው ግን ፣ በገጠር ተወዳጅና ብርቅ ነው የሚባለውን ልሙጥ ባለ አበባ ቀሚስ በተጨማሪ ገዝተዋል ። ምንዳዬ ካኪ ኮትና ቁምጣ ሱሪ ደረሰው ።

ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ታመነ ፣ ለጣውንታቸው የሚደረገውን ነገር ሁሉ አንድ ባንድ ያውቃሉ ። ቀኛዝማች ምንጊዜ ገብተው እንደወጡ ፣ ምን አሸክመውና አስነድተው እንደሔዱ ፣ ማን ተልኮ እንደሔደና እንደመጣ አሳምረው ያውቃሉ ። ብሶትና ችግራቸውን ፊት ለፊት ተጋፍጦ ከማቃለል ይልቅ ‘አህያውን ፈርቶ ዳውላውን’ በሆነ ዘዴ ገበሬና ሎሌ ፣ ገረድና የቤት ልጅ በሆነው ላይ ምላሳቸውን ይመዛሉ ። ድፍን አገር የሰማውን የጣውንታቸውን ጉዳይ ፣ እንኳን ባዕድና የሩቅ ሰው ፣ የገዛ ወገኖቻቸውም እንዲጠይቋቸው አይፈልጉም ። ዘመዶቻቸውም ‘እሷ ወዳና ጥሟት ዝም ያለችውን እኛ ምንዶለን’ ካሉ ከአራት—ካምስት ዓመት በላይ አልፏል ። ሴትዮዋም የባለቤታቸው ጠባይ የተጋባባቸው ይመስል ፣ ካንዳንድ አሉባልታ ከሚያመጡላቸው ወሬ አቀባባይ ሴቶች በስተቀር አንድም ወ/ሮ እከሌ የሚባሉ ምስጢረኛ የሏቸውም ። አንዳች ወሬ የሰሙ ዕለት ታዲያ በቅዝምዝም እንደ ተመታች ሚዳቋ ይዘሉ — ይፈርጡና ፣ “ምን ሰው አለኝና፣ እግዜሩም ዐይን የለው ። የሰው እጦቴ ነው ። ወገን የፈራ እንደሁ ገላጋይ ይሆናል አሉ ። የገዛ ዘመዶቼ ብሰዋል ። ሁሉም የሳቸው አደግዳጊ ሆነዋል ። ወይኔ ልጂት” ይላሉ አንጀታቸው እየተከነ ። አስቸግሮኛል የሚሉትን ማንኛውንም ሰው ለማጥቃት ሲነሡም ፣ አውጥተውና አውርደው ብቻቸውን ወይም አንድ ተጨማሪ ሰው ያዘጋጃሉ ። “ከዚህ በላይማ እዩልኝ ስሙልኝ ብሎ እማኝ የማስቀመጥ ያክል ነው” ይላሉ ።

ምንዳዬ አዲሱን ልብስ ለብሶ የቀኛዝማችን ጉልበት ሳመ ። ደስ አላቸው ። ከፊት ለፊታቸው ገለል ብሎ እንደ ቆመም ፣ “ይኸን ከተማ ይዘውት ቢገቡ አያሳፍርም ፣ አቋቋሙም አረማመዱም ቀልጣፋ ነው” አሉ ፣ ጠቅላላ አቋሙን እየገመገሙ ።



ከተመረጡ ወዲህ አብሯቸው በሚዘዋወርበት ወቅት ከቀድሞ የበለጠ ኩራት ይሰማው ጀመር ። አዲስ አበባ ሔዶ ሲመለስም ፣ እሱም እንደሳቸው ቀጭን ጌታ ሲሆን ይታየዋል ።

* * *

ሰውዬው ከጥቅምት 15 ቀን 1958 በፊት አዲስ አበባ መድረስ ስለ ነበረባቸው ለሣር—አምባ ጊዮርጊስና ለማጀቴ መድኃኔ —ዓለም ጥላቸውን ፣ ለኬብሮይና ለደብረ—ወርቅ ማርያም መጐናጸፊያቸውን ፣ ለካብ ሥላሴ ምንጣፋቸውን አደረሱ ። ሃጃ—ፊጅ ለሚገኙት ሁለት ሸሆች ደግሞ ከሙክቶቻቸው መኻል መርጠው ላኩ ። ስለ አንቃሩ ውቢት ሚካኤል ግን ፣ “የሱ እንዲህ በቀላሉ አይደለም ፣ ትልቅ ነገር ነው የተሳሉት”እያሉ ካህናትና ዲያቆናቱ ማስወራት ከጀመሩ ሰንበተዋል ። ቀኛዝማች ወደ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሔደው እንደ ተለመደው “ምቀኛና ጠላቶቼን አጥፋልኝ”ብለው ሲጸልዩ ፊት ለፊታቸው ቆሞ በፈገግታ የሚያያቸው ይመስላቸዋል ።

“ሊቀ መላኩ በደስታ ከሸኘኝ ንጉሡም በፈገግታ ይቀበሉኛል” ብለውም ፣ “ጌታዬ እኔ በድየህና አስቀይሜህ ይሆናል ። ሰው ነኝ ፣ ለራሴ አደላለሁ ። ሥጋ ያሳሳል ፣ ሁሉንም አይቼና ሰምቼ ይቅር ብየሃለሁ በለኝ ። አሳቤን ሁሉ ፈጽመህልኛል ። እኔም ቤትክን እሠራለሁ” ብለው ስለታቸውን አደሱ ። ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ሲሔዱ ሚካኤል እንደ ንስር እያንዣበበ የሚሸኛቸው መሰላቸው ።

"እጀባ! ሆዬ! እደይ ተኽምጦ ታሁን—አሁን ላሁልኝ ፣ ታሁን —ታሁን ላሁልኝ ፣ ታሁን —አሁን ጣሉልኝ እያሉ ዐሥረዬ ምራእን ተመዋጥ ፣ እዚህ በክብርት መቀመጥ ይሻላል ።" ይከላከላል ሌላው ።

"እንዲህ ፣ እንዲህ እያልክ ዐሥረዬ ራስክን አጥናናዪ ፣ ኋላማ ምን ታረግ ኮቸሮ አፌ ፣ — — ያንተ ቢጤው እኮ ነው አንድ ጅብ አሉ ፣ በላ ብሎ ባጥር ሾልኮ ይገባና ተወዲያ ተወዲህ ቲያይ ጊዜ አንዲት አህያ ቆማ ያያል ። ደስ ብሎት ሲቋምጥና ቲያዛጋ ፣ ታህያዋ ትንሽ ራቅ ብለው ሰዎች ያያል ። አይጠጋ ነገር እንዴት ፣ የጅብ ነገር ። ጥሎ አይወጣ ነገር አህያን ያክል ሲሳይ ልትቀርበት ኮነ ። ንድድ ሲለው ጊዜ ፣ ደሞ ለዚች ለጅማታሟ ነው ይህን ያክል መጨነኤ" አለ አሉ ።

"ይቺ ይቺን ተረቷንማ ታእባታለህ ! ይልቅዬ ሒድ በከዘራ እንዳ ይለምጡህ !" ይባባላሉ ።

ምንዳዬ ቀኛዝማችን እጅ ነሥቶ በዚያው በመጣበት አካባቢ ላንዳንድ ነገር ሽብ ማድረጊያ ተብሎ የተተከለውን ባላባልቾ እንጩት ተደግፎ ቆመ ። አደግድገው የቆሙትንም ሌሎች አራት ሰዎች አሳምሮ ያውቃቸዋል ። ርስት ጠባቂዎችና ወኪሎች ናቸው ። አንዱን ፣ ተጋዦችና ገባሮች ሁሉ ከስሙ ይልቅ እነሱው በድብቅ ባወጡለት ስም "እርም አይቀሬ" ይሉታል ። እሱም ያውቃል ። እረኞች ተደብቀውና ጢሻ ገብተው ፣

"እህያ መጣች ተጭና ጥሬ
አውድማ አስላሹ ፣ አያ እርም አይቀሬ" ይሉታል ። አዝመራ በደረሰ ቁጥር ክምሩን ከንድቶና ገበሬውን ተቆጥቶ ፣ "ለከርሞ ይቺን ማሳ አታርሳትም" ብሎ ዝቶ ከሔደ ፣ እሱ ሳይገኝ ፣ ወይም ምትክ ሳያስቀምጥ እህሉ ከተወቃ ጉድ ይፈላል ።

"ዐፈር—ብሉ ! ዐፈር ያስበላችሁ ! መናጢ! የመናጢ ዘር ሁሉ ! እንኳን የደበቃችኋትን ፣ የበላችኋትን አስተፋችኋለሁ ! እኔ ታልመጣ ማባከ አውድማ ለእልእ አለህ ? ይኸነዬ ሥር—ሥሩን እንደ ፍልፈል ቦጥቡጣችሁታል ። እንተዋወአለን ! አንተዋወእ መስሏችኋል ! ተሰኔ ሚካል ወዲያ ፣ ትበሉት አጣችሁ ልቆ ታልገባችሁ ፣ እጃችሁ ተልከስክሷል ማለት ነው" እያለ ሲሶ ሠፋሪዎቹን ሁሉ ያሸቀጠቁጣቸዋል ። መልስ ከመስጠት ይልቅ እውነተኝነታቸውን በዐይኖቻቸውና በአኳኋናቸው ሊያረጋግጡለት ይሞክራሉ ። የሱ እውነት ግን ምንጊዜም 'እጃችሁ ከምን' ነው ።



የገበሬ እጅ ለራሱ ከመብላቱ በፊት ለሰው አፍ ያጎርሳል ። ትልቁ የቀኛዝማች አፍ ከመከፈቱና ዘራፊ እጃቸው ከመዘርጋቱ በፊት ፣ የእርም አይቀሬ ጥርስ አግጦ ፣ እጁ ሊቀበል ይዘረጋል ። ፊቱ እሳት ፣ እጁ ረመጥ ነው ። በገበሬዎች ላይ የተጣበቀ የቀኛዝማች መኸገር ነው ። "የሳቸውስ የለየለት ነው ፣ ይኸ እኮ ሥር ሥሩን እንዳሞሌ ልሶ ጨረሰን" ይላሉ ገበሬዎቹ ።

ቀኛዝማች ፣ በልማድ ውልና ባዘዙ ፣ እርም አይቀሬ በዛተና ባስፈራራ መጠን ይዘርፋሉ ።

እርም አይቀሬ ፣ መምጫው የታወቀ ዕለት ገበሬው አይገቡ ገብቶና የነበረችውን አሟጦ ፣ አንጀቱ እያረረ ሥቆ ያስተናግደዋል። ወጠጤ ሽጦና እህል አቅንቶ ትንሽ ብር የቋጠረው ደግሞ ፣ "ምን የኛ ነገር አይሞላልን ፣ እንዲሁ ምንገድ አስመታሁሁ ፣ እስቲ ይቺን እጅሁ አርጓት" ብሎ ሦስትም—አራትም ብር ወሸቅ ያደርጋል ።

"እንዲያው መቼም የመሔጃ እጦት ነውዪ ፣ ከዚህ ከርም አይቀሬ ተሚሉ ከይሲ ሰውዬስ የጃራ ሴጣን ይሻላል ። ከገደለም ግልግል ነው ። ከማረም ምን ጣጣ አለ ። ይኸ ነውዪ ክፉ እጣቆ ፣ የድሃ መኸገር ፣ አውድማ አስላሽ" ይለዋል ገበሬው በየቤቱ ። እንደ ቤተኛና ታማኝ ሎሌ ከመታየቱ በፊት ምንዳዬንም በነገር እየወጋጋ አስደግድጎታል ። ከእርም አይቀሬ ጋር አብረው የቆሙትም የሱ ቢጤ መንጋጋ ናቸው ።

ከቆሙት ሁለቱ ቁምጣ ታጥቀውና አዳፋ ኮት ደርበው አዳፋ ነጠላ ሸው አድርገዋል ። ሌላው ጠባብ አረንጓዴ ሱሪ ታጥቆ እም ሳያውን ኮት ደርቧል ። የእግራቸው ንቃቃትና በእንቅፋት የተመነገለው ጥፍራቸው ከተለያዩ ጠማማና ጠፍጣፋ ቅርፅ ጋር እግር ሳይሆን ከረግረግ የመዘዙት የእንጨት ጉማጅ ይመስላል ። ከገበሬው ከፍ የሚሉት ላመል ታህል ነው ። ልብ የምታሳብጥ ሥልጣናቸውን አውልቆ ላስተዋላቸው ግን ፣ ገበሬው በቅሎ ፣ እነሱ ፣ እርካብ ፣ ኮርቻ ፣ አለንጋና ልጓም ናቸው ።

ገበሬውም ቢሆን ስም እያጣላቸውም ። አንዳንዶቹ ፣ "የቀኛማይ መጆች መጡ ፣ እነሱ ሲገረድፉላቸው ነው እሳቸው እሚሰልቁት ። እነሱንስ በሌላም አልነበር ፣ የገዛ ቀብራቸውን እያስማሱ ነበር ፣ እዚያው ዐፈር ማልበስ" እያሉ ከንፈራቸውን ይነክሳሉ ።

ቀደም ሲል ከነበሩት ርስት ጠባቂዎች መካከል ፣ ሁለቱ ተገድለው ሬሣቸው ፈፋ ውስጥ ተገኝቷል ። ያንዱ ገዳይ ይሙት በቃ ተፈ

ገሥፅ ታላቅ ወንድም ስለሚመለከቱት ፡ ጥፋታቸውን ተናዘው ይቅርታ ለመጠየቅ ጸሎትና ምልጃ ይበቃዋል ። ባንዳች አስቸጋሪ ግዴታ ካል ተያዙ በስተቀር ፡ ቢረቱም ማመን አይሆንላቸውም ። በሐሳባቸው የሚ ፈጥሩት ንዝንዝ አዲስ አበባ ድረስ ይዘልቅና ወይዘሮ ደጅ— ይጥኑ 'እዚያስ ይሁን ግድየለም ፡ የሰውን አፍ ፈርቼ ዝም ብዬ ኖርኩ ፡ እዚህ ደሞ ለምኔ ብዬ ነው መንቃቃቴ ፡ ኧረ ከማን አንሰና ነው ባጣ ቆዪኝ መሆኔ — ኧረ — ንሺ ! የቀረው ይቀራሊ ፡ ዛሬስ ቁርጡን ንገሩኝ ፡ አለያ — — " እያሉ ሲያስቸግሯቸው ይታያቸዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ ባለቤታቸው "የኔ ነገር እንዲህ ሆኖ ሊኸር ! — አሄሄ ! እከተማም እንዲህ ሆኜ ልኖር ! ተንግዲህስ መጫወቻሁን ፈልጉ—" — —እያሉ በገቡና በወጡ ቁጥር ሲነዘንዟቸው ይታያቸዋል ። ይህን ጉዳይ እንደ ተራ ነገር ችላ ይሉና ምኞታቸው ከፍ ሲል ደግሞ ፡ ከልዩ ልዩ እንደራሴዎች ጋር በመሰብሰብ ፡ እሳቸውም ስለ መጡበት አካባቢ አስረድተው ሲደነቁ ፡ ዝናቸውም በባለ— ሥልጣኖች ታውቆ ጉዳዩን ንጉሡ ሰምተው ሲያስጠሯቸው ይታያቸውና ልባቸው በደ ስታ ይንደቀደቃል ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱም ፡ በበኩላቸው ወደ አዲስ አበባ ሔደው እሳቸው የአዲሱ ተሿሚ የቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ሚስት እየተ ባሉ ፡ ባለ ጉዳዮች 'አማላጅ ሁኑኝ ፡ ተየሀ ተጉድ አውጡኝ ፡ ያላንቱ ማን አለኝ' እያሉ ደጅ — ሲጠኗቸው ይታያቸዋል ።

መምሬ ተክለ—ጊዮርጊስም የሚላክላቸውን ልብስና ስጦታ እንዲ ሁም እዚያው ድረስ ተጠርተው ፡ የቀኛዝማች ንስሐ —አባት መሆ ናቸው እየተነገረ ከወዳጆቻቸው ጋር ሲያስተዋውቋቸው ይታያቸውና በተስፋ ፈገግ ይላሉ ።

"እንደ ነገና ተነገ ወዲያ ሊነሡ ሲሉ ፡ እንዲህ እንደ ዛሬ ይላ ኩብኝ ፡ ሌላው ቢቀር ማጀቱ ድረስ እሸኝዎታለሁ" አሉ ቄሱ ።

"እንዴት ! ምን በወጣዎት ! እዚያ ድረስ ለምን ይደክማሉ ?"

"ለርስዎ ብዬ ሳይሆን ፡ እኔን ደስ ይበለኝ ብዬ ነው ። መጽሐ ፉም ሸኙ ይላል ።"

"ቢልም? — — —"

"እኔ እልክብኋላሁ ! እውነኩን ነው ። የሹም ምልክቱ ያጃቢው ብዛቱ ይባል የለ ?" አሉ ሴትዮዋ ።

"ታዲያ እሳቸውን አጃቢ ማድረግሽ ነው? ወዮ — —ጉድ!"



"ኧረ እኔ አልወጣኝም ! — አሁን ይኸን አጣሁትና ነው? አይ ያንቱ ነገር!?"

"ኧረ ይኸ ቀላል ነው! ብሸኝስ ምን ነውር አለበት ?! ሰው እን ኳንና የራሱን ፡ የሰው አገር ሹም ያጅብ የለ!" አሉ ለማግባባት ።

"ለምን ይንገላቱብኛል ብዬ ነውዬ ፡ ክብርና ማዕረጉማ ለኔው ነው ። እንዳለችው የሰው ብዛት ክብር ነው ። ታቦትስ ግርማ— ሞገስ የሚያገኘውና የሚያስፈራው ሕዝቡ ፡ ትልቅ — ትንሹ ሲያጅ በው አይደል ! " አሉ እየሣቁ ።

ቄሱ ተሰናብተው ሲወጡ ፡ ሴትዮዋ ተከትለዋቸው መሰስ አሉ ።

"እዬ ጉድ! እእ! ከገዛ ልቤ ጋር መክሬ ይሁን ካላልኩ የሚያስ ገድዱኝ መስሏታል" አሉ ሁለቱንም ከበስተጀርባቸው በንቀት እያዩ ።

ቄሱ በምንዳዬ ቤት አጠገብ ሲያልፉ ፡ ዘወርም አላሉ ። ካጥር ውጪ ገለል ብለው ከቀኛዝማች ጋር የተነጋገሩትን ነገር አንድ ባንድ ገለጹላቸው ። ሴትዮዋ ቀኛዝማችን በመጠራጠር በጣም ቅር ቢላቸ ውም ፡ ለጊዜው ሰው ከማሰልቸት ብለው ዝም አሉ ።

የቃጡትን ሌላውን የቂም በትር ግን አላነሡትም ። ስለ ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ መሔድና አለመሔድም ምን ተባለ ብለው አልጠየቁም ። ቄሱም በተንዛዛ ንግግራቸው ውስጥ የማጀቴዋን ቅምጥ ጉዳይ ከማጥ ላላት አልፈው እልባት አላስገኙለትም ። ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱ ንጉተው የጠበቁት የዚህን መልስ እንጂ ፡ ስለራሳቸው መሔድና አለ መሔድ አልነበረም ። ሆኖም የመሔዳቸው ጉዳይ በቀጠሮ ቢቆይም ይኸው ከፊል ድል አስደሰታቸውና ፡

"እስኪ ያቺን ትንሺን ልጅሁን ዘርትሁንን እንድልካት ፡ ቲመ ችሽ ብቅ በይ ብለውሻል በሉልኝ ። እሜቴንም በጎ ሰንብተኋል ወይ ? እንደምን ሰንብተኋል ብላለች ይበሉልኝ" አሉ ኮራ ባለ አነጋገር ።

ቄሱ ልጃቸው የምትጠራበትን ምክንያት ስለሚያውቁ ፊታ ቸው ፈካ ። የሚላክላቸው እህል ታያቸውና ፡ "እሺ እልካታለሁ" ብለው ሔዱ ። ሴትዬዋ ወደ ቤት ሲመለሱ የምንዳዬን ጎጆ አዩና የጨፋ—ሮቢቷ ጠንቋይ የነገረቻቸው ሁሉ ትዝ አላቸው ። 'የመጣው ይመጣሊ ፡ ያሰብኳት አትቀር' ብለው ጎጆዪቱን ክፉኛ ገላምጠዋት ወደ ቤታቸው ገብተው አዳራሹ ውስጥ እንደ ተቀመጡ ፡ የቆየ የቅናት ትዝታ ይዟቸው ከነፈ ። ከጥቂት ዓመታት በፊት ባልዮው ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑን እንደ ወሸሙ ሰሞን ፡ እንዴት ልባቸው ተቃጥሎ አንጀ ታቸው እንዳረረ አስታወሱ ። ነገሩ እውነትና ሐሰት እየተቀየጠበት

ለች ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ካዳሚዋ ትላልቅና የተለያየ ቀለማት ያላቸው ስኒዎች በዋንዛ ጥርብ እንጨት ረከቦት ላይ ደርድራ ወደ ውስጠኛው መጋረጃ ገባች ። ጀበናውም ያቦል ቡና እንፋሎቱን እያትጎለጎለ ከረከቦቱ ኋላ ካንገቱ ጎንበስ ፣ ከኋላው ፈንደድ ብሎ መስከን ይዟል ። ጊርጊራው ላይ አዲስ ፍምና ዕጣን ተጨምሮ ቤቱ እንኩቶ የተነኮተበት መሰለ ።

ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱ ከወሰዱት ልዩ ልዩ ቁጥርጣሪ ከፊሉ ቀርቦ “ጀባ” ተባለ ። በተጨማሪም በጆሮ ሹክ ተባለላቸው ። በካዳሚዋ የእጅ ምልክት ወደፊት ጠጋ ብለው ተቀመጡ ። ከዚያ ቀደም በተደጋጋሚ የሚያውቁት ነገር ስለነበር ፣ ለእንግድነት ያህል ፈርቶ የቆየው ሰውነታቸው አካባቢውን በመላመዱ ፣ አካላቸው ዘና ፣ ልባቸው ረጋ አለ ።

“ቀሃ ጀባ! አቦል ጀባ” አለች ካዳሚዋ ። ጠንቋዩዋ መቁጠሪያቸውን እያንሻሹ ፣ እጃቸውን እያሻሹና እየዘረጉ ፊታቸውን እያባበሱ መረቁ ። ቡናው በርጋታ ተቀድቶ ከሌሎቹ ስኒዎች በተለየ ቀይ ስኒ ለጠንቋዩዋ ተሰጠ ። ከዚያም ሌሎቹ በየተራ ያዙ ። በወ/ሮ እልፍ— ይከንዱ ትዕዛዝ ፣ ከቤት ውጪ የተቀመጠችው ሸዋርካብሽ ግን ፣ ምላሱን እያወጣ የላይ ከንፈሩን እንደሚልስ ሕፃን የበሩን ባጥ እየዳሰሰ በየቀዳዳው ከሚወጣው የዕጣን ጢስና የቡና ሽታ በቀር ያየችውም የሰማችውም ነገር አልነበረም ። ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱ ያሰቡና የጀመሩት ነገር ካላቃታቸው በቀር ለግል ጥቅማቸው የሚሠሩት ነገር ሁሉ እንዲታይና እንዲሰማባቸው አይፈልጉም ። አቦልና ቶና በዝምታ ተጠጡ ። በረካው ከመቀዳቱ በፊት የተወቀጠ ዕጣንና ጠጅ — ማር ፣ አዲስ ቡክቡካና ወይባ ማጨሻው ላይ ሲደረግ ዘንጎቹና ባላዎቹ በጉም ውስጥ የቆሙ አርጩሜዎች መሰሉ ።

ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱ የጠጡበትን ስኒ ፣ የቡና አተላ ቀስ በቀስ እያጋደሉ ካጠነፈፉት በኋላ ፣ ቀሪው አተላ ረግቶ የራሱን የመፋሰሻ ሽንተረራማ ሥዕል መሥራቱን እንዳዩ ከራሳቸው ተስፋና ፍላጐት ጋር ለካዳሚዋ አቀበሏት ። ስጠችላቸው ። ልባቸው እንደገና ተንደቀደቀች ። ምኞታቸው ተጠቃሎ ስኒው ሆድ ውስጥ ገባ ። ጠላቶቹ ናቸው የሚሏቸው ሰዎች ውድቀት ከስኒው ከርስ ውስጥ ሲወጣ ታያቸው ።

የጠንቋዩዋ ዐይን ስኒው ላይ ተተከለ ።

“አጀብኮ ነው እናንተ ሆዬ! እስቲ አሁን በሰው እርዚቅ እንዲህ ባይሆኑ ምን አለበት ? — — ከየት አገር ነው የመጣሽው?” አሉ ጠንቋዩዋ በክንብንባቸው ጠርዝ እያዩ ።



“ከማር — እምባ ።”

“ምነው በክፉ እሚያይሽ በዛ ? ምነው ምሰሶሽን ነእናኢው ግርግዳሽን ሰርሳሪው በዛ ? — —አጀብኮ ነው ! ዙሪያውን አሰፍስፈው ከበውሻል ? አንቺም ፣ ዝም ዝም ታበዣለሽ ? — —ለምንድነው ችላ ችላ እምትዪው!?”

“ምናባቴ ላርግ!? ቢቸግረኝ አደል ፣ ባንቱው መጀን ብዬ መምጣቴ” አሉ እንባቸው እየመጣና ድምፃቸው እየሰለለ ።

“አይዞሽ! አዛሽን ሁሉ እንጠራርግልሻለን ! እንደ ጤዛ እናረግፍልሻለን! ወፈር ያለች መልከ — መልካም ሴት ፣ ከሩቅ ቆማ በክፉ ዐይኗ ታይሻለይ !?”

ነገሩ ገባቸው ። መልከ —መልካም የሚለውን ቃል ግን ጠሉት ።

“ተጠንቀቂያት ! መርዛ ይዛሻለች ! የቤትሽን ዋልታ ትነኽንኸው ጀምራለች! አይዞሽ አታስቢ ! እጅ — እግሯን እኒዝልሻለን ! እህል — ውሃዋን እናደርቀዋለን! — —እዚያው እቤትሽ ጥግ የቆመ ሰው ይታየኛል ። ትልእ ዛፍ እበላው አለ ። ግንዱን ጥርቅም አርጎ ይዟል ። አጭርም — ረዥምም አይሉት ፣ እጅግም ላይን አይሞላ !ተወዲያ ወዲህ ይራወጣል! አይበጅሽም! ትልኡን ዛፍ አትንኪው ፣ ያገር አድባር ነው ! ዛፉን ሙጥኝ ማለቱ ለምን ብሎ ነው ? ወዲያ መንጭኤሽ ጣይው! አብሽሪ ! እሱን ተስሩ እንነእልልሻለን ! ሩህያው ተስነበተች አጥፊሽ ነው! አይዞሽ በልብሽ ያለውን ፈጥሚው ፣ አብረንሽ ነን ! አብሽሪ!” ብለው አስተማማኝነትን በሚገልጽ አኳኋን በጎርናና ድምፅ ተናገሩ ።

ወ/ሮ እልፍ — ይከንዱ ፣ ጎንበስ ብለው መሬቱን ከሳሙ በኋላ መጀመሪያ ወደ ነበሩበት ተመለሱ ።

ሁለቱ ሴቶች እጅ—ነሥተውና ተሰለው ሲወጡ ፣ ሁለት ወንዶች ተራቸውን ይጠብቁ ነበር ።

ሴትዬዋ ወደ ማር—እምባ ሲመለሱ ፣ ሌላ—ሌላ ወሬ ከማውራት በቀር ሳት ብሏቸው እንኳ ከጠንቋዩዋ የሰሙትን ነገር ለሸዋርካብሽ አላጫወቷትም ። እሷም ምን ተባሉ ብላ አልጠየቀች ።ልኳን ታውቃለች ።

* * *

ወ/ሮ ደጅ — ይጥኑም በበኩላቸው ጨፋ—ሮቢትዋ ጠንቋይ ዘንድ ሔደው የሚባሉትን ተብለው ፣ ደስ ብሏቸው ነበር ። ሰው ሁሉ በየተራ

ትናንት ቀኑን ሙሉ እንግዳ ሲቀበሉና ሲያስተናግዱ ፣ ለጉራና ለዝና ካንዱ ቤት አንዱ ቤት ሲሉ ሁሉ ፣ በአእምሯቸው ውስጥ አንድ ትልቅ ጉዳይ ሲጉላላ ውሏል ። ነገሩ ጭንቀት እየፈጠረባቸው በመሔዱ ፣

"እልከብሻለሁ ወይም እኔው እመጣለሁ ካሉኝ በኋላ እንዴት እንዲህ ዝም ይሉኛል ? ያፈለገው ይሆናሊ እንዲህ ጓዜ ተሰናድቶና ድፍን ማጀቴን ደህና ዋሉ ብዬ — — —" ይሉና በረዢሙ ይተነፍሳሉ ። ከወደ ማር — አምባ ይመጣል ብለው በርግጠኝነት የጠበቁት ሰው የውሃ ሽታ ሆኗል ።

የመነሻቸው ሰዓት እንደ ተቃረበ ፣ ቀደም ብለው ተነሥተው ተጣጠቡ ። የረሱት ዕቃ እንደሌለም አረጋገጡ ።

ባለቀይ ጥለት ኩታና ቀሚሳቸውን ለብሰውና ጥቁር ሻሻቸውን አስረው አዲስ ሰማያዊ ሸራ ጫማ አድርገዋል ።ላቀችም ቱር ብላ የታጠበች ቀሚሷን ለብሳ ጠንበለል መስላለች ። መጫሚያ ባይኖራትም አልቦዋና የሞቀችው እንሶስላ ዐይን ይስባል ። ባለ አራት ዓይነቱ ጥለት ረዢም መቀነቷ ሦስት ዙር ዞሮ ፊት ለፊት ተወዲያ ወዲህ ሲል ሽንጥና ዳሌዋን ለማሳየት የቀረበ አስተናጋጅ ይመስላል ።

ሸኚዎቹ የሴትዮዋን ጓዝ ተከፋፍለው ከቤት ሲወጡ ፣ ላቀች ጥቁሩን ጥላቸውንና የራሷን ጨርቆች በእምብርቢጣዋ ይዛ ከሴትዮዋ ኋላ ተከተለች ።

ወደ አዲስ አበባ በሚሔደው አውቶቡስ ዙሪያ ብዙ ሰው ተሰብስቦ የመንገደኞቹ ዕቃ ይጫናል ። የወ/ሮ ደጅ — ይጥኑም ዕቃ ተጫነ። ሸኚዎቻቸውን አንድ ባንድ ስመው ከተሰናበቱ በኋላ ፣ በፊት በር በኩል ፣ እበሩ ላይ የተለጠፈውን ብረት ጨብጠው ወደ ውስጥ ሲገቡ ፣ ቂጣቸው ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ወደኋላ ተቀልሎና እንድ ሁለቴ ተርገፍግፎ ሸኚዎቹን ሁሉ ተሰናብቷቸው ገባ ።

ተከትላ ገብታ የቆመችውን ላቀችን ፣ "እንዲያ ወደ ኋላ ቦታ አለልሽ ፣ ሒጂና ተቀመጪ" አሏት ። ጐረቤቶቻቸው ከውጪ "በቸር ያግባሁ ፣ በደህና ያግባሁ" እያሉ እንባቸውን በሸማቸው እያባበሱ አንጋጠው ሲያዩዋቸው ፣ እሳቸውም በተከፈተው መስኮት በኩል ብቅ ብለው ሲሰናበቱ ፣ አንድ መንገደኛ መጥቶ እጐናቸው ተቀመጠ ።



መለስ ብለው አዩት ። ትውውቅ ባይኖራቸውም የማር — አምባ ሰው መሆኑን ያውቃሉ ።

አውቶቡሱ ኮረኮንቻማውን ጥርጊያ እየረመጠጠና ወፍራም የአቧራ ጅራቱን እያቦለለ ሲንደረደር ፣ ከበስተኋላው የማጀቷ ከተማ ከትልቅ ቋጥኝ ሥር የወደቀች ቆርኪ መሰለች ። መኪናው ኮረኮንቻማውን መንገድ ጨርሶ ፣ የኑግ ልጥልጥ ከመሰለ ጎዳና ገባ ። ወ/ሮ ደጅ — ይጥኑ "ይህን የማር — አምባ ሰው ልጠይቀው ይሆን?" እያሉ ሲያቅማሙ መኪናው ካራቆሬ ደረሰ ።

## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

የቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ግቢ ታምቧል ። የጎረቤትና የአካባቢው ሰዎች ካጥር ውጪ ፣ በምንዳዬ ጎጆና በአዳራሾቹ ሰበሰብ ዙሪያ ተቀምጠዋል ።

ልኬለሽ ወገቧን በነጠላዋ ጥርቅም አርጋ ታጥቃ ደረቷን እየመታች ልብ በሚነካ አሳዛኝ ድምፅ ታለቅሳለች ።

ቀኛዝማች ፣ ውጥንቅጡ በወጣ ስሜትና ፣ ምክንያት ፍለጋ በሚባዝን ሐሳብ ተወጥረው እየተቅበጠበጡ ፣ "እኔ በላይነህ አይደለሁም! እንኳን ምልክቱ ብቻ ተገኘ ፣ የዚህ የደሃ ደም በከንቱ ፈሰሶ አይቀርም" እያሉ በንዴት ከስለው አልፍኞቻቸው ውስጥ ይንቆራጠጣሉ ። ብስጭታቸው ናር ሲል ደግሞ ምንዳዬ ቤት ደርሰው ይመለሳሉ ።

ወይዘሮ አልፍ — ይከንዱ ፣ ካንጀት ጠብ በማይል አጉል ደስታ ውስጥ ውስጡን ይቦርቁና ፣ ምንዳዬ ቤት ሲገቡ ደግሞ ሐዘን እንዳንገበገበው ሰው ያባይ እንባ ያነባሉ ። መለስ ብለው ቆርቆሮው ቤት ውስጥ ይገቡና ዐይኖቻቸውን ወደ ላይ ሻጥ ፣ እጆቻቸውን በፊታቸው አኳያ ሽቅብ ዘርጋ ያደርጉና ፣ "አይ አንተ ጌታ ! ፈጥረኸኛላ ! አለሃ !" እያሉ ያመሰግናሉ ።

የምንዳዬ ልጆች እቤታቸው ደጃፍ ተቀምጠው ፣ ትልቁ እንባው ፣ ልሃጩና ንፍጡ እየተዝረበረበ ፣ ትንሹ የእናቱንና የወንድሙን ልቅሶ እያየ ሆዱ ባብቶ እየፈራ ያለቅሳሉ ። አካባቢውን የሐዘንና የብስጭት ጥላ ጥሉበታል ።

* * *

ቀኛዝማች ፣ ከቅምጣቸው ጋር ከተገናኙ ከሳምንት በላይ ሆኗቸዋል ። ምኞታቸው በእግረ — ሕሊና ማጀቴ ተሻግሮ የልቡን ሲያደርስ ፣ አካላቸው ግን በዛሬ — ነገ እንደጓጓ ቀረ ። በዚያ ላይ በሴትዮዋ መልክና ዳሙጠ ገላ ከተማረኩ ጀምሮ ፣ ከገዛ ባለቤታቸው ጋር እያወሩ ወይም ጋደም ብለው በመደባበስ ላይ እያሉ እንኳ ፣ ሴሰኛ ነፍሳቸው ማጀቴ ትገባና ከቅምጣቸው ጋር ይላፋሉ ። በእንዲህ

ያለው ወቅት የላይ ገላቸው ይሞቅና መላ አካላቸው ይሰጠጣል ። ሰው በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ ላይ ሊገኝ የሚችል ቢሆን ምንኛ ደስ ባላቸውና ባንድ ጊዜ ማር — አምባና ማጀቴ በተገኙ ነበር ። ሚካኤል እንዲህ — እንዲህ ያለውን ነገር ለአምላክ እያቀረበ የሚያስፈጽም ቢሆን ፣ ለውለታው ምላሹ ሊቀ ሊቃውንት ቀጥረው አዲስ “ገድል ወይም — ተአምረ — ሚካኤል” ያጽፉለት ነበር ። ወይ ነዶ ! ሁለቱም ቀረባቸው! እሳቸው ግን ፣ አካላቸውን ሁለት ቦታ ላይ የሚከፍሉትና ምኞታቸውን የሚገልጹት በምንዳዬ ሰውነት እየሠረፁ ይመስላል ። እሱ በወይዘሮ ደጅ ይጥኑና በሳቸው መካከል አንድ እግሩ ማጀቴ ፣ ሌላው እግሩ ማር — አምባ የቆመ ቅርፀ ደጋን የሰው ተከል ነው ። የሁለቱ ሰዎች ሐሳብና ምስጢር ከወዲያ — ወዲህ የሚሸጋገረው በምንዳዬ እንደበት ነው ።

ቀኛዝማች ፣ ለመጨረሻ ጊዜ እነ — እርም — አይቀሬን አስከትለው ሚጨራና ሀገረ — ማርያም ያለውን ርስትና ይዞታውን ለመመልከት ሲሔዱ ፣ ምንዳዬ ግን ውጪኛውን አጥር የላላ — የላላውን እንዲያሳጥርና እንዲያጠባብቅ በመታዘዙ አብሮ አልሔደም ። የታዘዘውን ሠርቶና — አሠርቶ ዐረፍ ከማለቱ ቀኛዝማች አጃቢዎቻቸውን አስከትለው ፣ ገና ፀሐይ ሳታሽቆለቁል ስለገቡ ወደ እልፍኝ ተጠርቶ ሔደ ።

ሸዋርካብሽ ፣ የሰውዬውን እግር በገበቴ ውሃ ስታጥብ ከእርሱ ጋር የሚያወሩትን ሁሉ ጆሮዋን አቁማ ስትሰማ በማየቱ ፣ ከእግር — እስከ ራሱ ወረረው ።

“ደክሞሃል እንዴ?” አሉት ፣ በመጨረሻ ቢደክመውም ደክመኝ እንደማይላቸው እያወቁ ።

“ምን ሠራሁና ፣ እየሁ ደይ — ለደይ እኮ ነው የዋልኩት” አለ ድካሙን ደብቆ ።

“እንግዲያውማ አንዳፍታ ማጀቴ ደረስ ብለህ ብትመጣ ፣ እንዳሳቤማ ትላንትና በጊዜ እገባለሁ ብዬ ነበር ። አንተን'ንኳ ያላስከተልኩህ ለውሎ — ገብ መንገድ ብዬ ነበር ። ሰዉ አላላውስ አለኝ ። ገብቼ አድሬ ቢሆን ኖሮ ረፋዱ ላይ ትመለስ ነበር ። አሁንም ቢሆን ገና ነው ፣ ባንተ አረማመድ ፣ አንዳፍታ ትንደረደራታለህ ። ከመሸብህም ጧት ትመለሳለህ” ብለው እንደ ጨረሱ ሸዋርካብሽ ገበቴዋን ይዛ ወጣች ።

“ያው እንግዲህ ነገ መሔዱ ነው ። ለምን አልሸኘኝም ብላ እንዳታኮርፍ ወረድ ብለህ እዚህ አለማደሬን ንገራት ። እኔማ ብቅ ብዬ



እሸኛታለሁ ብዬ ነበር ። ሰው አሰበበት አይውል ። ሒጂ — ሒጂ ብሎ አጉል አረገኝ እንዳትል” ብለው ተንጠራሩና ፣

“ያልኩህን ሁሉ ልብ ብለህ ይዘኸው የለ ?”

“እም !”

“ትስተዋለህ ብዬ ሳይሆን ፣ ነገር ያበዛሁብህ መሰሎኝ ነው ። አዎ ንገራት ፣ መቼም የሷ ነገር ፣ እዚህ ያለው ጣጣ ሁሉ ጣጣ አይመስላት ።”

“የከፋት ታይሆን ፣ ባያኡት ነው ። ምን ሴቶቹ — — —” ብሎ ሳይጨርስ ፣

“የከፋትስ አይደለም ፣ እንዲያው ብቻ የራስ የራሷን ስታይ —”

“ምን እሳቸው ብቻ ፣ ሁሉም የራስ የራሱን ነው እሚያየው” አለ አፍ አድጦት ።

“ነው ብለህ ነው ? ኧረ ስንት አንገት ያለው ሰው አለ ፣ ብቻ እንደ የሰዉ ቆዳ ነው ።”

እዚያው እልፍኝ እንደ ቆመ ሸዋርካብሽ የእጅ ውሃ አምጥታ ከማስታጠቧ አረጋሽ ገበታ ይዛ ገባች ። ምንዳዬ ለመሔድ ቢያስብም ገበታ ሲቀርብ አይቶ ቢወጣ ደስ እንደማይላቸው ስለሚያውቅ ፣ ፈንጠር ብሎ እበሩ ጥግ ተቀመጠ ።

ቀኛዝማች ፣ ለወጉ ያህል ጉራርሰው መዓዱ እንደ ተነሣ ፣ አረጋሽ የነካ የነካውን በሌላ ገበታ ላይ አድርጋ አቀረበችለትና በቅራሪ እያወራረደ በልቶ ፣ እጅ ነሥቶ ወጣ ።

ወይዘሮ እልፍ — ይከንዱና ሸዋርካብሽ ካጥር ውጪ ሠዋራ ቦታ ላይ ቆመው ገልመጥመጥ እያሉ አፍ — ላፍ ገጥመው ይወያያሉ ። እንደ ተለመደው ስለ ባላቸው ጠባይ የምታውቀውን አንዳንድ ሁኔታ ከነገረቻቸው በኋላ ፣ ምንዳዬ ወደ ማጀቴ ሲሔዱ ለሴትዮዋ ይዞላቸው የሚሔደውን ነገር እንዲያዩና እንዲከታተሉ ነገረቻቸው ።

“መቼ ነው እንዲህ ያሉት ? አሁን ነው… ?”

“ገና ገባ እንዳሉ ፣ እግራቸውን እያጠብኳቸው …”

“ታዲያ እንዴት እንዴት አሉት ? ይኸነዬ በወጉ አልሰማሽም ይሆናል ?”

“ጣዩ በረድ ቲልልህ ፣ ሒድ ብለውታል ።”

“ከማ ጋ ሁነህ ሒድ አሉት ?”

“ከማም ጋ አላሉት ።”

ደሁ ነገ ጧት ይሽራል” ብለው የምንዳዬን እጅ በጥንቃቄ በቸርነት
ካስያዙ በኋላ፤ ከትናንሽ ጡሊዎቻቸው አረንጓዴና ግራጫ መሳይ ዱቄት
እያወጡ፤ ጥይት በገባበትና በወጣበት በኩል በጣታቸው ገፋ—እያ
ደረጉ ገና ደም በሚያዥው ትኩስ ቁስል ላይ መድኃኒት ደመደ
ሙበት ። ባመጡት አሮጌ የነጠላ ትልታይ ጨርቅ በክንዱና ባንገቱ
ዙሪያ እየጠለፉ አሰሩለት ። ከትከሻና ከሽንጡ ወደ ቀኝ ዘንበል
አድርገው የግራ ብብቱን የኋላ አካባቢ ደባበሱት ። የፈሰሰው ደም
ረግቶና ደርቆ ትናንሽ ቅርፊት ፈጥሯል ። ያንንም ለብ ባለው ውሃ
ውስጥ ጥጥ እየነከሩ የማጠብ ያክል ጠራረጉና አፏን ከፍታ ደም
የምታመነጨውን ሁለተኛዋን ቁስል አገኟት ። ረጋና ትኩር ብለው
የደሙን መፍለቂያ ካስተዋሉ በኋላ፤ ዙሪያዋን ነካ—ነካ፤ ጫን ጫን
እያደረጉ ቀጠን ብሎ የረጋውን ደም ሲያስወጡ ምንዳዬ፤ “እስስስ!
አ!” ብሎ የሥቃይ ድምፅ አሰማ ። የልኬለሽ ልብ ሥቃዩን በሰቀቀን
ትጋራ ። ፊቷ ቅጭም ብሎ ዐይኖቿ ፈጠጡ ።

“አይዞህ! አይዞህ በርታ! እንኳን የኔን የሽማግሌውን እጅ ጥይ
ቱን ችለኸዋል ። አንተ ደሞ አይቆጭህም፤ አንጀትህን አርሰሃል”
ብለው እንደገና ዙሪያውን እየጠራረጉ ካጸዱና የረጋውን ደም ካስ
ወገዱ በኋላ፤ ፈገግ ብለው ቀና አሉ ።

“እንዴት ያለ ልበ ንጡሕ ነው! በየህ በኩል የገባችውማ ምና
ምኒት አጥንት እሚሉ ነገር ሳትነካ ሥጋ—ለሥጋ ሾልካለች ። አዬ ዕድል
እናንተ ሆዬ! ጌታ ከወደደኮ ከፈላ—ውሃ ያወጣል! አሁን ያነዬ የዛሬ
ስንት ዓመት መሆኑ ነው፤ የንቅጥቅጡ ጊዜ እንዷ ዘመዴ የድንጋይ
ቤት ግንብ ተደርብቶባት ኡሉ ተባብለው ቲያወጧት፤ ለማላ ያክል
እንኳ ጫር አላረጋትም ። እስቲሽርልህ ድረስ እጅህን ማንቀሳኸሱ
ነው የሚቸግርሂ፤ ጡንቻህ መወጠሪያ ላይ ባለመሆኗ ደህና ነህ፤
የዛሬውን ቀን ባል—እንዳለው ባሉን ጠይኸህ ጠብለው፤ መሰንበቻ
ውን ደህና — ደህናይቱን ጉርስ — ጥጥት ካረከ ብድግ ትላለህ”
ብለው ወደ በሩ እያዩ፤ “ሌላ አሮጌ ነጠላ የለሽ ይሆን? ማ ሒዶ ያመ
ጣሊ እኔም ጋ ነበረ” አሉ ።

ልኬለሽ፤ ወደ ድብኝቷ ተንደርድራ ማጀቱ ገበያ ስትወጣና ቤተ
ክርስቲያን ስትሔድ የምትለብሳትን ነጠላዋን ሰጠቻቸው ።

“እንዴ፤ ይኸማ አይሆንም፤ ሌላ ነተብተብ ያለ እላሊ አልኩሺ
ይኸ—”

“ግዴለሁም—ሆን ብዬ ነው ። ለማባቱ ሊሆነኝ፤ እንዳፈቀደሁ
አርጉት ።”



“ተይ አይሆንም ኋላ ኸን” አሉ እንዳትጸጸቺ በሚል ስሜት ።

“በሉ ወዲህ በሉት እኔው ልጀምርልሁና” ብላ እጅዋን ስትዘረጋ
ወጌሻው የነጠላውን ጥለት በጥርሳቸው ነክሰው ቁልቁል ተለተሉት ።

“ና በል እንደ እድምህ ደህና አርገህ አብራልኝ” አሉት ባለ
ኩራዙን ። ከዚያም እንደ መጀመሪያው ሁሉ ከየቅሎቹ መድኃኒት
እያወጡ በመነስነስና ባውራ—ጣታቸው እየሰጎዱ ከሁለት አቅጣጫ
ደመደሙለት ። በነጠላውም ትልታይ በትከሻው አሻግረው ካንገቱ
በስተቀኝ በኩል ጠልፈው፤ በደረቱ በኩል በማሳለፍና በግራ ትከሻ
ውም በማዞር ካሰሩለት በኋላ በጥንቃቄ አስተኙት ።

“እንግዲህ እንደ ካካቴ አትንጫጪ ። ጥላ እንዳይሆንበት ሸማ
ቢጤ ጋርዱለት ። ሰው ቲንጋጋ ጥሩ አደለም ። ዛጎልም የብር ቀለ
በትም አበት አርጊለት ። መበርታት ተንግዲህ ነው ። የምትነጨዋንም
የምትጠጣዋንም መረኢ የሰጠሽው እንደሆነ መሰንበቻውን ይጠግለ
ታል ። ሰውዬው ግን በለስ ባይሰጠውና፤ የዚህም ቀኑ ባይደርስ ነውዬ
አተኳኮሱስ የዋዛ አልነበረም” ብለው እጃቸውን ከታጠቡ በኋላ፤ ቅላ
ቅልና መቃቸውን አንጠልጥለው ወደ ቀኛዝማች እልፍኝ ሔዱ ።

* * *

“እኔ ቅድሙንም ተናግሬያለሁ፤ ለዚህ ኖሯል እንዴ ስታንዘፋዝፉ
የመጣችሁት? እንዲች ብላችሁ እዚች እግቢዬ እንዳታገቡ ። ለሱ ብቻ
የመጣ መስሏችኋል፤ የተደገሰው ለኔ ነበር ። ባይገድለውም እኮ ገሎታል፤
የምንዳን ደም አፍሶ ነው የሱ ሬሣ እዚች እግቢ እሚገባው? ለካጥር
ውጪም ሰው ምን ይላል ብዬ እያንገበገበኝ ነው ። እኔ የሽፍታ
ሬሳ ማጎሪያ ነኝ እንዴ? ለኔ ብላችሁ እንደሁ ኮለሌ ጣሉት” ብለው
ካስጠነቀቁ በኋላ ቀኛዝማች ወደ ቤት ገቡ ።

አንዳንዶቹ እየተሾካሾኩ ሲያሙና ሲያወሩ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ
እጅግም ጮክ ሳይሉ፤ “የኖረ አህያ እንኳ ለጅብ ቲጣል ያሳዝናል፤
ዐይናችን እያየ አውሬ ይብላው ማለት ጡር ነው፤ ደግም አደል ።
ነገና ተነገ ወዲያን ነውዬ ማየት፤ ለክፉም ለደጉም ሰው የጁን አያ
ጣም ። ባይሆን እንደ ፈረደብን እዚቹ እብርድ ላይ ስንጠብእ እናድ
ራታለኒ፤ ሰው ሆነን ከሰው ተፈጥረን ላውሬ አንሰጠውም” እያሉ
አንድ ሽማግሌ ጅምራቸውን ሳይጨርሱ “አገር ማስደቡስ ቀላል ነወይ፤
እንዲህ ያለው ሰባራ—ስም ኧስተ ልጅ—ልጅ ይሻገራል ። ሣር—አም
ቦች ሰው ገለው ለጅብ ጣሉ መባልስ ውርደት አማደል ወይ?” ብሎ
አቋረጣቸው አንዱ ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

ሸዋርካብሽ ፡ በጓሮ በር ሹልክ ብላ ገብታ ዐውራ ጣቷ አዲስ ቁስል ላይ ዐመድ ነስንሳ ፡ ደም መጥጦ ያልተላከከውን እፍ እያለች ስታራግፍ ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ገቡ ። ዐውራ ጣቷን በምድጃው ጥላ ከልላ ቆም አለችና ፡

“እቴሜቴ!”አለች እሳቸውን ሳይሆን ጥላቸውን እያየች ።

“ምነው? ደሞ ምን ቀረሽ?” አሏት በግልምጫ ።

“ቲፈልጉሽ ነበር” አለች በሰባራ ድምፅ ።

“ማ?”አሉ ፡ በማን እንደሚፈለጉ እየታወቃቸው ።

“እሳቸው ናቸው” አለች ‘ስማቸውን ቄስ ይጥራው’ እያለች በልቧ ።

“አሁን ነው ቆዩ?” ብለው ወጡ ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፡ ካዳራሹ ወጥተው በስተጓሮ እግቢው መኻል ቆም አሉና ፡ ጐራ ወደ ከለለው ሚካኤልና ፡ አሻቅበው ወደሚያዩት ሣር—አምባ ጊዮርጊስ አዩ ። ችግራቸውን ለማንኛው እንደሚነግሩ ሐሳባቸው ዋለለ ። ትዝ ሲላቸው ለካ ሚካኤል የቀኛዝማች ምስጢረኛ ኖሯል ። እየፈሩ ፊታቸውን አዞሩና ወደ ራሳቸው ሰማዕት ወደ ጎርጊስ መለስ አሉ ። “እስኪ ምኗ ካዲያን ነኝ እስተዛሬ ያለሱ አለሁሽ ያለኝ ማን አለ? እንዲያውም እሱ ሰው ነበር አሉ ። የሰው ችግር ይገባዋል ። የኔ ጎዮርጊስ አንተው ታእልኛለህ” አሉት በመዋለላቸው እየተጸጸቱ ። ማርያምንማ በሴትነቷ“ ምን አቅም ይኖራታል ፡ እሷም ቢሆን ገና ለምና ነው” በሚል ግምት ፡ ሥላሴዎችን “እነሱም ቢሆኑ ያው ለወንዶች ታያደሉም አይቀሩ ። ሽማግሌው ሁሉ እሚያዳላው ለወንዶች ነው ። በያ ላይ ደሞ ሦስት ናቸው ። ሁሉንም ከመለመን አንዱ ጎርጊስ ይሻላል” በሚል እምነት ብዙም አይማጠኗቸው ።

“አይይ! !” አሉ እንባቸው እየተንቆረዘዘ ። “እስኪ የኔ በደል ምንድነው? እስኪ አንተ ፍረድ! አንተው ፍረደኝ ፡ ምን አባቷ እንዳታረግ ብለው ፡ በላዬ ላይ ሴት ያዙ ፡ የለፋሁበትንና የደከምኩበትን እየወሰዱ ሲሰጡ ፡ ላንተው ነግሬ ዝም አልኩ ። ይባስ ብለው እኔን እንደ

ቀብር ዐፈር እያድፋፉና ችላ—ችላ እያሉ ያዳሚን ጋለሞታ ይገፍ ታል
ሔድኩ አሉ ። ላንተው ነግሬ ዝም አልኩ ። ምን አባቷ እንዳታረገኝ
ብለው የገዛ ሎሌዬን ነገር አመላላሻቸው አርገው በገዛ ቤቴ ያንገ
በግቡኝ ጀመር ። ተነገ—ዛሬ ልብ ያበጃሉ ፣ እትልእ ሥርፋ ሲውሉ
ነውና ይተዋሉ ብል ቲብስባቸው ጊዜ ፣ አንጀቴ ድብን ብሎ ይኸው
አይገቡ ጣጣ ገባሁ ። አንተ እማታኸው ምን ነገር አለ” ብለው ግዙፍ
የጨለማ ክብር የመሰለውን የሣር—አምባ ጊዮርጊስ ተራራ እንጋጠው
እያዩ አለቀሱና ፣ “ኧረ ተው! እውነቱን ፍረድ! ኧረ ተው አሳየኝ!
አሁን ተዚያ ተዘንዶ የኚህ ታይብስ ቀርቶ ነውገ ችላ ያልከኝ”ብለው
ከዚያ ቀደም ከተሳሉት ስለት የበለጠ ተስለው ወደ እልፍኝ አመሩ።

በየብስጭታቸው ጊዜ ሁሉ የተሳሉትን ስለት በልቦናቸው ይዘው
ማስታወስ ስለማይችሉ ፣ ተኝተው በቅዠታቸው የተለያ ዩ አራዊትና
እንስሳት ካዩና ካሯሯጧቸው ፣ “ደሞ የማንኛው ስለት ተረስቶ ይሆን?”
በማለት በየአምባው ያሉትን ታቦቶች በሐሳብ ያስሳሉ ። ጥርጣሬአ
ችው ወዳጋደለበት ታቦት ፣ ወይ ከዕጣኑ ፣ ወይ ከስንዴው ይልካሉ ።
ከማንኛውም ጉዳይ ይልቅ በወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ላይ የተሳሉት ስለት
ከሁሉም ይበልጣል ። የጣውንታቸውን ጉዳይ ረጋ ብለው ባስታወሱ
ቁጥር በጣም ላጭር ቅጽበት እንኳ ቢሆን የወላጅ እናታቸው ሥራ
ትዝ ይላቸዋል ።

ብዙ ጊዜ ወላጅ እናታቸውንና ጣውንታቸውን በተመሳሳይ ዐይን
ስለሚመለከቱ ፣ የገዛ እናታቸውንም በጥላቻ ትዝታና ስሜት ያስታውሷቸ
ዋል ። የወይዘሮ እልፍ ይከንዱ አባት በወረርሽኝ በሽታ የሞቱት እሳቸው
ገና የስምንት ዓመት ልጅ ሳሉ ነበር ። እናታቸው ጸጉራቸውን ተላጭ
ተው ፣ ማቅ አገልድመውና ፣ መሬት ላይ የበግ ለምድ አንጥፈው
እየተኙ ከሁለት ዓመት በላይ ተኮራምተው አዘኑ ። የባልና ሚስቱን
መዋደድ የሚያውቁ የባልየው ዘመዶች ‘ከዚህ በላይስ ይበቃታል’
ከሚሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ ። በመጨረሻም ‘ተንግዲህስ ወዲያ ደግ
አደለም ፣ አጥንቱም አይወቅስሽ ፣ ነፍሱም አይከስሽ’ ብለው ሐዘ
ናቸውን እንዲተዉ ገፋፏቸው ። የገዛ ዘመዶቻቸውም ፣ “ምንድነው
እቴ ፣ አሁንስ በዛ! ማ ጎሽ ይለኛል ብለሽ ነውገ ተነሥቶ አያይልሽ
ነገር ፣ ሰው ሒዶ እንዲህ ያለች ውለተኛ ናት አይለው ነገር — — —”
ብለው ስለ ወቃቀሷቸውና ስለ ተቆጧቸው ፣ በሐዘን ተጨብጦ የነበር
ልባቸው ላልቶ ፣ የተጐሳቆለ ገላቸው እየሞላ ሔደ ። ብዙ ወንዶች በተ
ለያዩ አጋጣሚዎች ለትዳር ጠየቋቸው ። የወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ
እናት ግን ፣ ‘ከሟቹ ባሌ የማይስተካከል ከሆነ እንዲች ብዬ አላገ
ባም’ ብለው የመጡትን ሁሉ በሰበብ አስባቡ መለሱ ። ጠይቆ
የተመለሰው ወንድ ሁሉ ፣ ‘ይቺ ሴትዮ ምንድነው ብልሃቷ!? ቆብ



ታጠልቅ ከጀላት እንዴ?’ እስከ ማለት ደረሰ ። ‘እኔ ልጂት ከማ
ንም ሎግኒ ጋር አልነፋጠጥም ። ቢያስቀዝንም ጮማ’ ብለው እጅ—እግ
ራቸውን ሰብስበው እንደ ተቀመጡ ፣ ዝናቸውን የሰሙ አንድ የሳፍራ
ባላባት ደም— ግባታቸውንና ቁመናቸውን አይተው ስለ ወደዷቸው ፣
እምቢ የማይባል ዘመድ ባማጭነት ልከው ፣ በልጆቻቸው እናት
ላይ የወይዘሮ እልፍ ይከንዱን እናት በቅምጥነት አስቀመጧቸው ።
ባዘዙ ቁጥር እህል በያይነቱ ፣ ዓውደ—ዓመት በመጣ ቁጥር ሙክቱ ፣
ነጭ ከመያዣ እያቀረቡ በክብካቤ አኖሯቸው ። ሴትዮዋም ቢሆን በሙ
ያቸውና ባልጋ ላይ ችሎታቸው ተጠቅመው ፣ ሰውየውን እንደ ኩቲ
ጠርተው እንደ ላም አለቧቸው ። በመጨረሻም ከቆዩ ትዳራቸው አፈ
ናቅለውና አጣልተው ጠቀለሏቸው ። ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ያንን ሁሉ
የእናታቸውን ድርጊት አንድ ባንድ ያስታውሳሉ ። ሰውዬውን ለመጠቅ
ለል ሲሉ ያደረጉትን ጥረት ፣ የሠሩና ያሠሩትን ተንኮል ፣ የደረሱበትን
ጠንቋይና የገቡበትን ደብተራ ፣ ‘እህ’ ያሉትን የወሬ አመላላሽ ብዛት
ያውቃሉ ። ይህ ከሆነ አያሌ ዓመታት ቢያልፍም ትዝታው ግን
አልጠፋም ። የገዛ እናታቸውን ድርጊት እያሰቡም ጣውንታቸውን ፈርተ
ዋል ።

በቀኛዝማች የሚፈጸምባቸውን በደል ሁሉ ከእንጀራ አባታቸ
ቸው ከኃዲነት ጋር በማነጻጸር ፣ “አይ ልጅነት ፣ እኔ ደህና ሰው ይመ
ስሉኝ ነበር ። ለካስ ጉዳቸው ሁሉ አልገባኝም ኖሯል ። ዘልዛላ የሰው
ዘልዛላ! ያ መሳይ ቁመናቸው ቅሌት ብቻ ኖሯል” በማለት በወይ
ዘሮ ደጅ ይጥኑ ምክንያት በተናደዱ ቁጥር ከእንጀራ አባታቸው
ሚስት ጋር በዛሬው ሐሳባቸው በማበር ወላጅ እናታቸውን ያወግ
ዛሉ ። ዐልፎ ዐልፎም ፣ ‘የሷ ጡር ቀትን ጠብቆ በኔ ላይ ደረሰ’ በሚል
እምነት እናታቸውን ይራገማሉ ። በዚህም ምክንያት ከእንጀራ አባ
ታቸው ሚስት ዕጣ ለመዳን ሲሉ ፣ በጣውንታቸው በኩል ያለውን
ነገር ሁሉ በእልህና በበቀል ተያያዙት ። ወደ እልፍኝ የገቡትም
ከዚህ ትዝታ ቁንጣሪና ከተረበሸ አእምሮ ጋር ነበር ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሰባት

ሣር አምባ የዋለ ሰው ወደ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ቤት ጐራ ብሎ የሰማውን ሁሉ ነግሯቸው ሳለ፣ ልብ ብሎ እንዳላዳመጠና በምን ግዴ እንደሰማ ሰው፣

"ማን ነው የሞተው?" አሉ እንደገና ከድንጋጤአቸው መለስ ብለው።

"የየት አገር ሰው እንደሁ አልታወኸም መሰል" አላቸው ሰውዬው።

"ይኸ የኛስ ተጐድቶ ይሆን" አሉ ረጋ ብለው።

"ታይጐዳም አይቀር።"

"እሚያሠጋው ይሆን እንዴ!" አሉ ትኩር ብለው እያዩ።

"የጌታን ነገር ማን ያኸዋል — እሱ እንዳለ ነው" አለ ወደላይ እያየ።

"ቀኛማችስ?"

"ምነው ነግሬሁ፣ እሳቸው ምንም አልሆኑ፣ ያው እሰ እፊት — እፊት ቲል ተጐዳዩ፣ የሱ መኖር ነው የበጃቸው፣ አለያማ የዛሬዋ ጥይት የሳቸው ነበረች።"

"እሳቸውም እሚወዱት ለዚህ ነው፣ እንኳን ጠላትን ደስ ያላ ለው። ሺ—አውል ከሚሞት ሺ—ይሙት ይባል የለ!" ብለው ብድግ ሲሉ ሰውዬውም ተሰናብቶ ወጣ። እሳቸውም የጎረቤት ሰው አስከ ትለው ወደ ሣር አምባ ገሠገሡ። የመንደሮቹ መቀራረብ ጠቀማቸው። እንደ ደረሱም የቤቱ አቀማመጥና የአደጋው መጠን በቅድሚያ እን ዲገቡ ወደሚያስገድዳቸው ወደ ምንዳዬ ቤት ገቡ። የነበሩትን ጥቂት ሰዎች መስቀል አሳልመው፣ ስለ ደረሰው አደጋ እንደገና ጠይቀው ተረዱ። በተደጋጋሚ ከንፈራቸውን እየመጠጡ ተቆርቋሪነታቸውን ከገ ለጹ በኋላ፣ አደጋም ሆነ ሞት በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሚመጡ፣ ሰውም በጠላቱ ላይ ድል የሚቀዳጀው በሱው ፈቃድ መሆኑን ባጭሩ አብራርተውና አጽናንተው ወደ ቀኛዝዝማች እልፍኝ አመሩ።

እንኳን አተረፈሁ ከሚሉ ከሁለት ሽማግሌዎች በቀር ሌላ ሰው አልነበረም። እዚህም ከቀኛዝማች በመጀመር መስቀል አሳልመው፣

ከፍ ባለ አዛኝነትና የሃይማኖታዊ አባት ስሜት ቁጭታቸውን ገልጸው ፣ አምላክ የወዳጆቹን ጽናት ለማወቅ ዐልፎ ዐልፎ በዚህ ሁኔታ እንደሚፈትን መጠቃቀስ እንደ ጀመሩ ፣ ሁለቱ ሽማግሌዎች ፣ “በዚሁ ያሳልፈው ፣ የዛሬን ጥላ ከለላ ሁኖኋል ፣ ለወደፊትም ከክፉ ነገር ይከልልሁ ፣ እሱንም የውሻ ቁስል ያርግለት” ብለው ሔዱ ።

ቀኛዝማች ፣ ያን ብዙ ምስጢር አለበት የሚሉትን አገልግል ወደ ጎን ብለው ፣ ከዕለቱ ሁኔታዎች መካከል ገና የሚያጣሩትን ቸል እያሉና ፣ አልፎ አልፎ አንዳንድ ድርጊቶችን እየዘለሉ ፣ “ይኽ ነገር የታሰበው ለኔ ነበር” የሚለውን የግል ጥርጣሬአቸውን እያጎሉ ፣ የምንዳዬን ጉብዝና እንደ ራሳቸው ጀብዱ እያሰማመሩ አወሩላቸው ። ቀኛዝማችን እጅግም መቃወም የማይሆንላቸው ቄስም ፣ ጉራና ጥርጣሬውን ፣ እውነትና ውሸቱን ሁሉ ፣ ትክክለኛ ነገር እንደሰማ ሰው ራሳቸውን በአዎንታ እየነቀነቁ አዳመጡ ።

ቄሱ በዚያ በጨለማ ገስግሰው በመምጣታቸው በቀኛዝማች በኩል ምን ያህል እንደሚያስወድዳቸውና እንደ ታላቅ ውለታም እንደሚታይላቸው ልባቸው ያውቃል ። ቀኛዝማችም ያን ዕለት መጥቶ የጠየቃቸውንና ምንዳዬ ቤት እየደረሰ የሔደውን ሰው ልብ ብለው እያዩ ፣ ሌሎቹንም ማን እንደ መጣና ማን እንደቀረ ተመልክቱ ብለዋል ።

ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ፣ ቅዱስ ጊዮርጊስን ተማፅነውና ‘አደራህን’ ብለው ወደ እልፍኝ ሲገቡ ዐይኖቻቸው ባለቤታቸው ላይ ተሰኩ ። በጭንቀት ማዕበል የተናወፀው አእምሯቸው ያይናቸውን ንቃት ቢቀንሰውም ፣ እዚያው ከቀኛዝማች አጠገብ ቄሱንም አዩዋቸው ። ሁሉም ነገር አስጠላቸው ። በተለይም ከቀኛዝማች እግር አጠገብ ያለውን አገልግል ሲመለከቱ ፣ ሲሰርቅና ሲዋሽ እንደ ተደረሰበት ሰው ዐይንና ቅስማቸው ተሰብሮ ደነገጡ ። ‘እንኳንም የመጣሽልኝ ! ኧረ በምን አበሳዬ ነው እንዲህ መንገላታቴ ! እነማን ሲቀባበሉኝ እንደዋሉ አንድ ባንድ እናገር የለ?!’ የሚል መሰላቸው ። የጭንቀት ሃዕር አነቃቸው ።

“ደህና አመሸሽ ወይ? ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ” አሉ ቄሱ በርጋታ።

“እዝጊሐር ምስጌን ፣ እንዴት አመሹ አባቴ? ምነዬ መጡ ?” አሉ ወደሳቸው እያመሩ ።

“ጥኢት ቆየት ብያለሁ ፣ ምንዳዬ ጋ ገባሁና ‘እንኳን እግዚአብሔር አተረፈህ’ ብዬ ፣ ዋናው ሥጋቴ ደሞ እዚህ በመሆኑ መጣሁ ። —— በጎ ሰነበሽ ወይ?” ብለው ከጀጠባባቸው ደረት ኪስ በቀይ ግምጃ እራፊ የተሸፈነች ፣ ቡናማ ላብ — ጠገብ የንጨት መስቀል አውጥተው ሲያሳልሟቸው ፣ እንደ ወትሮው ‘ይፍቱኝ’ እንኳ አላሉም።



ቀደም ብለው ከልፍኝ ውጪ ሁለመናቸውን ለዚያው ለጊዮርጊስ በማስረከባቸው ፣ በቄሱ መስቀልና አማላጅነት የሚተላለፍ መልዕክት አልነበራቸውም ።

“ምነው ታዲያ ተመሸ ፣ ነገም እኮ ትደርሱ ነበር” አሉ ከፊል ልባቸው ‘እንኳን መጡ’ እያለ ።

“እንዴት ብሎ ሊነጋልኝ? አሳቡም አያሳድረኝ ፣ ቲጨነቁ ተማደርስ ይኽ ይሻላል ። እናንተ እንኳ አትቀየሙኝም ። እሱ ግን ፣ አንደዬ ከተቀየመ ሆዱ በቀላል አይፈታም ። ላንድ አፍታ መንገድ ብዬ ከሚያዝንብኝ እንዲህ መምጣቴ ይሻለኛል ። ቀስ ብዬ መስቀል ሳሳልመው እንኳ ደስ ብሎት አየኝ” አሉ ደስ እያላቸው ።

“እሱስ እውነኩን ፣ ፣ ደግ አርገኋል” ብለው ፊንጠር ብለው ተቀመጡ ።

“—— ምን ነበር የጀመርነው ወሬ ፣ አልጨረሱልኝም እኮ?” አሉ ቀኛዝማች ።

“—— አዎ ፣ አልጨረስኩልዎም ፣ እንዴት አመሸሽ ልበላት ብዬ ነው ልጄን ።”

“ውይ! ዐፈር በበላሁት ! —— አይ የኔ ነገር! አቋረጥኳችሁ ?”

“ኧረ ጠላትሽ ዐፈር ይብላ ! ምን በወጣሽ ! እንዳይጠወልግ ነው እንይደርቅ ?” አሉ ቄሱ ። የወሬው መቀጠል በጠንቀኛው ዕቃ ምክንያት የሚጀመረውን ንትርክ የሚያዘገየው በመሆኑና ፣ በተጨማሪም በመካከሉ ራት ቀርቦ ሌላ አዳዲስ ጨዋታ ስለሚቀጥሉ ፣ እንዲያው በባዶ ሜዳ በመጠኑ ደስ አላቸው ። ገደብ የለሽ ምኞታቸው ፣ ከዚህ ዐልፎ ፣ ራት ሲበላና የተንተተ ወግ ሲወጋ በጣም ይመሽና ፣ ስላገልግሉ ሳይነሣ ያድራል ። በማግሥቱም የምንዳዬና የሚቼ ነገር ስለሚኖር በዚህም በዚያም በመዘግየት ፣ በችላ—ችላ መረሳቱ አይቀርም በማለት ፣ ልባቸው እንደገና ረጋ ፣ አእምሯቸው ባጉል ተስፋ ተንፈስ አለ ። ወዲያው ‘የተቋረጠው ወሬ ስለምን ይሆን’ በማለት ቢሡጉም ፣ ከጥቂት ድምጫ በኋላ ግን ፣ ዱሮ ደርሶ ስለነበር ተመሳሳይ አደጋ መሆኑን ስለተረዱ ቀለል አላቸው ። ያም ሆነ ይህ አሳቸውንም እንደ አፈሳ ወስድ—መለስ ያደርጋቸው ጀመር ።

ሌላ አዲስ ወሬ ከመጀመሩ በፊት ፣

“ጥሯት ብዬ ልኬብሽ ነበር ፣ አልነገሩሽም ኖሯል እንዴ ?” አሉ ቀኛዝማች ፣ በርጋታ ከያዛቸው የሐሳብ ሰመመን ነቁና ።

“ቢማሽልን ብለን ፡ እምንዳዬ ቤት ቡና ተፈላና ፡ ያቺ እቴዋ ስንዴ ይቁና ጋሼ አፍራሳ ወሬ ጀመሩልን ፡ አቋርጣብን ሔደች ይሉኛል ብዬ ሳልወድ የግዴን ቆየሁ ፡ እሱ ደሞ ወሬ ተጀመረ ፡ ከፉ አመል አለበት አውርቶ አያበራም ።”

“በሉ እንግዲህ እህል ውሃ በሉንና እንተኛበት — በጣም መሽ” አሉ ቀኛዝማች ። ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ወደ አዳራሽ ሔደው እረ ጋሽና ሸዋርካብሽ ራት እንዲያቀርቡ አዝዘው ተመለሱ ። ፍርሃትና ሥጋት ባጣደፈው ስሜት ጭምር ተፍ—ተፍ ብለው እጅ አስታጥበው ራት አቀረቡና ፡ ሲጠሩ ቶሎ‘አቤት! እመት!’ ለማለት እንዲ አዳራሹ፥ ሌላዋ እልፍኙ በር አጠገብ ሰጠፍ ብለው ቆሙ ።

ቀኛዝማች ፡ ከዕለቱ ሁኔታ ሌላ የተለያዩ ሐሳቦች ሲያወጡና —ሲያወርዱ ፡ ቤትዮዋ ከራት በኋላ ወይም በማግሥቱ ጧት የሚሰሙትን ያገልግል መዘዝ እያሰላሰሉ ፡ ቄሱ በራሳቸው የሐሳብ ጓዳ ሲንጎዳጎዱ ፡ እጅግም ተከታታይ ወሬ ሳይወራ ራት ተበልቶና ‘ስብሐት ለአብ’ ተብሎ መዓዱ ከፍ አለ ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፡ ለቄሱ አዳራሽ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ተነጥፎላቸው ተኙ ።

ቀኛዝማችና ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ብቻ እልፍኝ ውስጥ እንደ ቀሩ ፡

“ይኸ አገልግል የማን ነው?” አሉ ቀኛዝማች ረጋ ባለ ሁኔታ አገልግሉን እንሥተው ። የቤትዮዋ ነፍስ ተሸብራ ልባቸው ተንዱዱች።

“የቱ?” አሉ ዐይናቸው ፈጦ እያየ ።

“ይኸን ነዋ ! — ምነው ? አይታይሽም እንዴ?” አሉ በማንገቻው እያሸከረከሩ ።

“እእ!—የኛ ነው ። ምን ያረግልሁ እዚህ አመጣሁት” አሉ አፋቸው እንዳመጣ ።

“በደንብ አየሽው?—እንዳትሳሳቺ ብዬ ነው ።”

“ኡኡ! የገዛ ንብረቴን እንዴት አጣዋለሁ ?!”

“እምሳያ እንዳይሆን ብዬ ነዋ! እንኳን የዕቃ የሰው መልክ ያሳስታል ።”

“እስቲ ወዲህ በሉት !?” ብለው አገላብጠው አዩት ።



አገልግሉን ሲያገላብጡ እሳቸውን ደግሞ ድንጋጤና ሥጋት አገላበጣቸው ።

‘የኛ እማይደል ብያቸው’ አለ አንዱ ደፋር ሐሳብ ፡

‘ቁርጥ የኛን አገልግል በይ’አለ ሌላው ቀላማጅ ሐሳብ ፡

‘ለሰውዬው እንደሁ እነ ሸዋርካብሽ አረጋግጠው ነግረዋቸዋል ፡ ይልቅዬ የኛ ነው ባልሽው ጥኚ’ አለ ሌላው አብሯቸው ያመሸ ሐሳብ ። ቤትዮዋ ከሐሳቦች ጋር ሲራኮቱ ፡

“ምነው ዝም አልሽ?—የኛ አይደለም እንዴ?”አሉ ቀኛዝማች።

“የኛማ—የኛ ነው ።”

“የኛ መሆኑን ብቻ ካረጋገጥሽ ይበቃል ። ለሌላው ግድ የለም” ብለው አገልግሉን እንደገና ለመቀበል እጃቸውን ዘረጉ ።

“ምን ያረግልሁ አስመጣሁት?” አሉ የነገርና የብልሃት አቅጣጫ ለመቀየር ።

“እኔማ ምን ያረግልኛል ፡ ከየት እንዳስመጣሁት ግን እነግርሻለሁ ። ‘እኔ ለሰው ሠርግ ሳንቀላፋ ያስረገዘኝ ጠፋ’ አለች አሉ ሴትዮዋ ። እኔ ከሰው እኩል እሆን ብዬ ጣጣ—መከራዬን አያለሁ ፡ እዚህ ደሞ ቤቴ ሥር—ሥሩን ይማሳል ። በሬ ካራጁ ይውላል አሉ ። በይ እዚሁ ደህና ቦታ ስቀይውና ጣጣውን ሲጨርስ እንደሆነ ይሆናል” ብለው ወደ መኝታቸው ሔዱ ። ቤትዮዋም አገልግሉን ወደ ድንኩ አልጋ ግርጌ ገፋ አድርገው ፡ አካላቸው እየተብረከረከ ወደ መኝታቸው አመሩ ።

ቀኛዝማች ጋደም እንዳሉ ነገሩን ለመጀመር ፡ ቤትዮዋ የሚቀርብላቸውን ጥያቄ ሁሉ በአሉታ ለመመለስ አቆበቆቡ ። ከትራስጌአቸው በላይ የሚበራው ፋኖስ ፡ መስተዋቱ ቆሽሾ ደብዘዝ ያለ ብርሃን ይሰጣል ።

“ቅድም እኮ ነገሩን ብቅ አርጌ ችላ ያልኩት በቅድሚያ ላጣራ ብዬ ነው”

“የቱን ነገር?”

“አገልግሉን ነዋ! ተምነዬ ረሳሽው?” አሉ በገረሜታ ድምፀት ።

“ደሞ ምን ቁም ነገር አለው ብዬ እሱን ላስታውስ?!” አሉ ለማም ታታት ።

"እእ! ኧረ እንዲህ ቀላል ነገርም አደል! —መዘዙ ሳያማዝዝም አይቀር!" አሉ ቆጣ ብለው ።

"የምን መዘዝ ልጄ? ባገልግል የሚመጣ መዘዝ!?" አሉና ደረቅ የስላቅ ሣቅ ሣቁ ።

"መዘዙንማ እያደር ታገኚዋለሽ! የዘንድሮ አገልግል እግር—አውጥቶ ዱር ለዱር እየሔደ ፥ እየጢሻው ውስጥ መገኘት ይዟል ። ያውም ሰው እየገደለ ———"

"አበስ ገበርኩ ጌታዬ! ምነው ባማን አሳድረን ብንልበት! ዛሬስ ደሞ ደጇም ቤቱም ነው እንዴ! ሰው በእንዲህ ያለው ቀን ተመስገን ብሎ ይተኛሊ — — —"

"የደጇም የቤቱም ያው ነው ፥ ሁሉስ ያንቺ ጉድ ሳይሆን ይቀራል ፥ አገልግልሽ ዱር ለዱር እየተገኘ ———" ብለው የፌዝ ሣቅ ሣቁ ።

"ኧረ ንሱ አባቴ ! እንግዲህ ደሞ ጀመረሁ ፥ ደሞ የምን አገል ግል ነው ዱር — ለዱር እሚገኝብኝ ?"

"ምነው ነገሩን ሁሉ እያየሽውና እያወቅሽው ባታደኸሚኝ?" አሉ ቆጣ ብለው ።

"ጎርጊስ አባቴ! ደሞ ምንድን ነው ያየሁትና ያወኩት?"

"የምንዳዬን መቁሰልና የሰውዬውን መሞት ነዋ ?" አሉ በቀልድ መልክ ።

"እኔ ታዲያ ምንድነኝ — የምን ቤት ነኝ ?" አሉ ኮስተር ብለው ።

"አሁን ገና ጥሩ ጠየቅሽ ! ያን ያየሽውን አገልግል የኛ ነው ካልሽ ፥ ሌላ ሌላውን ደግሞ ቀስ በቀስ እንተማመናለን ።"

"የዛሬውስ የጉድ ነው ! ተነሥቼ ልሒድልሁ እንዴ ? በሌላ ቢያእትሁ ደሞ በዚህ መጣሁብኝ ።"

"እኔማ ምን እመጣብሻለሁ—— — የጊዮርጊስን መገበሪያ የበላ ያስለፈልፈዋል አሉ — —"

"ምንድነው ብላትሁ አንተ ሰውዬ ? እንግዲህ ደሞ ቀኗ ደረሰች መሰል ! ያላወኩ አይምሰልሁ ።"

"እሂሂ ! ምኑን ከምን አገናኘሽው በይ ! ? እኔ በላይነህ ካስፈለገኝ ዐሥር ዐሥራምስቷን ብነዳት ማባቱ ይከለክለኝ መሰለሽ ? ይኸን ወግ ብለሽ አታውጊ ። ይልቅ ባገልግሉ ለማን ቋጥረሽበት ነበር ?" አሉ በስጨትጨት ባለ ሁኔታ ።



"ይኸው ነው የቀረሁ ?! 'ያብዬን እከክ ለምዬ' አሉ ። ብዬ ብዬ በስተርጅና ቅሌት ተራ ገባሁ ? አይ አንተ ጎርጊስ ! የለህማ ! የለ ህም! ወይ መቆየት ፥ ደሞ ብዬ ብዬ አገልግል አቀባይ ሆንኩና ዐረፍኩት ?! እኔ ደሞ ምን አረግሽው ሊሉኝ ነው ብያለሁ ? ለካስ ተደግሶልኝ ኖሯል ? ምንም ብትሉ ምን ፥ እኔ እንደሁ ሰበቡ ገብቶኛል ፥ 'ገር ልጅ እናቷ አትወዳትም' አሉ"

"ይኸ ሌላ ፥ ያ ሌላ ፥ አላሉ ሸማኔ ። አሁን ነገር ማዟዟሩን ተይና ፥ ፍሬ —ፍሬ ነገሩን እንነጋገር ። አንቺስ አልቋጠርኩበትም አልሽ — እሺ ይሁን በጄ ፥ ለሰውስ አላዋሽም ?" ብለው ቀና አሉ ።

"እኔ ለማንም አላዋስኩ" አሉ የሐሳባቸው ቋት ጠቦ ።

"እንዴት ያለ ነገር መጣ እባካችሁ ? አገልግል እንደ ሰው እግር አውጥቶ ይሔድ ጀመር እንዴ ?"

"እኔ ምን አቅልኳለሁ !?"

"ኋላ ምን ልበል ? ካላዋሽ ፥ ቋጥረሽ ካልሰጠሽ አገልግሉን ገንዳ ውሃ ምን ወሰደው ?"

"ማ ተወስዶ ነበር አለሁ?"

"ማ ይለኛል ? እኔው ራሴ አንጠልጥዬ ሳመጣው !"

"ማ? አንቱ ?"

"አዎ ! እኔው ራሴ ?"

"ምንዳዬ እቆሰለበት ሥርፋ ተገኘ ልትሉኝ ይሆን?"

"ጤናም አልያዛት እንዴ ይቺ ሴትዮ !? እንዴት ብዬ ልናገር — አዎ! እዚያው !"

"ምነው ብተዉኝ አንቱ ሰውዬ ! እልህ ቲይዝሁ ጊዜ በዚህ መጣሁብኝ ? ይኸስ ያንዳይ ነው ! ሰው ቢሰማስ ምን ይል ?" ብለው ትራስጌአቸው ሸጎጥ ያረጉትን ነጠላ አውጥተው ለበሱና ፊታቸውን ወደ ግድግዳው አዙረው ተቀመጡ ።

"እኔስ የገረመኝ ይኸው አደል ? እኔን ሆነሽ አንቺ እዚያ ብታገኚው ኖሮ ራስሽን ይዘሽ ነበር ኡኡ እምትዪው ።ይኸ እንዲህ በችላ ችላ እሚተው አይደለም" ብለው ጋደም አሉ ።

“አንቱ ደሞ! ላመጣልሁ አደል፣ ገና አሁን እኮ ነው ነገሩ ዝክር ያለኝ —— ልቤ ስንት ቦታ ረገጠ?!” አሉ ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ።

“ዳር—ዳሩን ስታንዣብቢ ምን ልበል — — ?”

“ያፈሳን ሚስት አገር ታኡት የለ እንዴ?”

“አሳምሬ፣ ለምን አላኧውም፣ መተር—ሆዴ አይደለም እንዴ?”

“ነው። ዞን—አምባና መተር—ሆዴ አፍና አፍንጫ ናቸው። እሷ ታዲያ የዋዛ ቤት አትምሰልሁ፣ የምንዳዬን ዘመዶችና ባላጋራዎቹን ልቅም አርጋ ታቃቸዋለች። እሱም የሆዱን እንጃዪ፣ ያገሬ ልጅ እያለ፣ መተር—ሆዴ ስቴጂ፣ አገሬን አሽቆልቁለሽ እዪልኝ ይላታል” አሉ ሥር—ሥሩን ትብተባቸው እየላላ።

“ምነው እቴ! ይኸን አማይመስል ወሬሽን ብተይኝ!? እኔ እንደሁ ነገርሽ ገብቶኛል —— ምን አለፋሽ? ተይው!” አሉ እየነደዳቸው።

“አይ ፍርጃ !አታስወሩ! — አንቱ የት ታቃለሁ! አንቱ እምታኡት ላይ—ላውን — —”

“እንዲያው ባፈለገሽ ሁኔታ እዪው፣ ባላጋሮቹ ጃራን ተሻግረው ይኸን ነገር አያረጉም።”

“በሉ ተዉት ወንድሜ! እኔም ቂል ሆኜ ነው ካንቱ ጋ መሟገቴ። እኔ ለምኔ፣ ነገ ጧት እውነቱን ትሰሙት የለ! አሁን የኛ አገር ሰው ነው ሆዱ እሚገኘው? እኔም እረዳሃለሁ፣ ቀስ ብለህ በድብእ ደመኛህን ዲብ አርገው ካሉት ይተዋል? አይተውም።”

“እስቲ በይ ቀጥይ ልስማሽ?—መቼም የሰው ነገር አይታወእ፣ ዛሬ ቢያምልጠኝ ነገ አያመልጠኝ፣ ይቺን ነገር እኔ አለሁላችሁ ብሎ ውሏት ከሆነ ——”

“አሁን ቢናደዱት ምን ያረጋል? ነገርን እያጣሩ ነው — ይልቅዬ ልንገርሁ፤ ታዲያ ይኸ የኔ ጉድ — — —”

“ማ?” አሉ ሳይታወቃቸው።

“አፈሣ” ብለው ቀጠሉና፤ “ለሱ ያለለትን ላያጣው የሰው አዱኛ እያየ ሲያከ ያድራል። ታዲያ ዛሬ ጀምበሯ ዘእዘቅ እንዳለች ይመጣና ‘ሚስቴ ወደ ሐጃ—ፈጅ ሔዳ ቆየችብኝ። እኔ ደሞ ወደ ኮለሌ እሚሔድ ሰው አግኝቼ፣ ቆላ አዝመራ ጥበቃ ለሚያድረው ልጅ ራት መላክ ፈልጌ ነበር’ ሲለኝ ጊዜ ሸዋርካብሽን ቋጥሬለት አልኳት። የሰው መሐጃው አይታወእ፣ ከምንዳዬ ባላጋሮች ጋር ውስጥ—ውስጡን መክሮ



አለያም ሰው ገዝቶ ሊያስገድለው ተኋሁኖስ እንደሁ ማን አወኤ? አገልግሉንስ ወስዶ ሰጥቶ እንደሁ ማ ተከትሎ አየው? የሰው ደም አይለቅ! እሱማ በየትኛው አሞቱ፣—አጀባ ሆዬ! ምን ሱሪ አለውና ይቺ ነገር ከዚህ ብታልፍ ጠጉር ተምላሴ!”

“እ! እንዲህ ኖሯል ነገሩ!? ‘ሚስቱን ገደለና አማቱ ቤት ተደበቀ’ አሉ!” አሉና በንዴት ቡግ ብለው ተነሡ።

“ኧረ ንሱ ሰዎች! አሁን ታዲያ ምን ልኮኑ ነው? ምን ታረጉ ከጀለሁ!”

“እማረገውንማ እኔ ዐቃለሁ! አስጠፈንገዋለኋ! አይዞህ ባይ እንዳለውስ ማን ያውቃል! አሁን ማ ይሙት እሱ ብቻውን ይቺን ሥራ ሊሠራት! ወግ ነው! የምንዳዬ መቅደሙን አትዪ፣ እኔንም ያስገደለኝ ያክል ቁጠሪው። ዛሬ እኮ አብሬ ያለመኖሬ ነዪ ሙቻለሁ” ብለው ጋቢ ለብሰው ወረዱና ሱሪያቸውን ታጠቁ። ሴትዮዋም ቀሚሳቸውን አጥልቀው እፊታቸው ቆሙ።

“ኧረ በምቶዱት ታቦት ይዤኋለሁ ወንድሜ! ኧረ አገር ጉድ ይላል! ኧረ የሰው መሳቂያ መሆን ነው? ምነው ይኸን ያክል? አይነጋልሁም እንዴ? ወዴት በሮ እንዳይጠፉ ነው? ነገ እንደ ሰሎግ ሰተት ብሎ ሲመጣልሁ ያደርስኋል። አሁንማ ነገር ማበላሸት ነው። ነገር ሲያውጣጡና ሲያጣሩ ቀስ ብሎ ነው። ከገነገነና ከሰማማ ምናቅላችኋለሁ ብሎ ይሸመጥጣል። እሱ ራሱ ከመጣም እሰየው! አለያም እዚቹ ጠርቶ ቀስ ብሎ ማስለፍለፍ ነው። እኔ በብላት ቢጠየቅ ይሻላል፣ ነው እምልሁ” ብለው የሚመልሱትን ለመስማት ዝም አሉ። ሁለቱም ከየራሳቸው ሐሳብ ጋር እየመከሩ አጠር ላለ ጊዜ ፊት ለፊት ተቀመጡ። ሰውዬው የጉዳዩን ሁኔታ ረጋ ብለው ለማሰላሰል ተመልሰው ጋደም ሲሉ፣ ሴትዮዋም ከተል አሉ።

“የሚገርም እኮ ነው” አሉ ውስጥ—ውስጡን በጀርባቸው ተኝተው ጣራ—ጣራውን እያዩ። “እስቲ የሰው አገር ሰው አደል፣ ባይልለትና መዘዘኛ ሰው ቢገጥመው ነውዪ፣ ላንድ ራሱና ለቤተሰቡ ያባቱ ርስት ይበቃው ነበር። አሁን ይኸ ነገር እውነት ሆኖ እሱ ገብቶበት ከተገኘና ምንዳዬ ካወቀ መተላለቃቸው ነው። እኔ ሒድ ብዬ ባላዘው ኖሮ ይኸ ሁሉ መከራ አይደርስበትም ነበር። እሱ ባልሰማና እኔ ብቻ አሳሩን ባስጨለኩት ——” አሉ በልባቸው። ይህንኑ እያሰላሰሉ እንቀላፉ።

ሴትዮዋም ነገሩ ተድበስብሶ የሚቀርበትን ብልሃት እህህ እንዳሉና የሚያመልጡበትን የሸር ምጥ እንዳማጡ ወፍ ተንጫጫ።

"እኔ እኮ ጥኢት መስላችሁኝ ነበር ፥ ለካ ብዙ ናችሁና — ያ እፊሣ እዚህ ነው አዳሬ ብሎኝ ነበር ፥ ወዴት ኬዶ ይሆን ? አላያችሁትም?" አሉ እየሣቁ ።

"እየሁ እኛው ጋ ነበር አሁን —— በዚህ ወደታይ ወረድ አለ መሰል" አለ አንዱ እየጠቆመ ።

"ምን ያለው ነው ወንድሜ ?! — እስቲ አደራህን ብየው ጥፍት ይበልብኝ" አሉ የተጋደመውን ቃሬዛ ማየት እየፈሩ ።

"ምናሻሁ ታዲያ ፥ እኔ በያው ነው ምንገዴ ፥ ታገኘሁት እነግርልኋለሁ" ብሎ አንድ ጕረምሳ ቁምጣ ሱሪውን እያራገፈ ቁልቁል ተንደረደረ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፥ ረጋ ብለው በዚያው አቅጣጫ ሲጓዙ ፥ ስንኳንስ አእምሮው ተሸብሮ ሐሳብ የገባው ሰው ሊመስሉ ቀርቶ ነገር የሚያሰላስሉ አይመስሉም ነበር ። ጥቂት ወረድ ብለው መንገድ እንደ ጠፋው ሰው ገላጣ ቦታ ላይ ፈዘው እንደ ቆሙ ፥ አንድ ሰላላ ድምፅ ከበስተጀርባቸው ፥ "እቴዋ!" ሲላቸው የናቱን ድምፅ እንደሰማ ሕፃን ተደሰቱ ።

"የት ኖረሃል ልጄ?" አሉት በጭምትርትር ፈገግታ ።

"እያው እደጅሽ ነው ያደርኩት ——"

"እሱንማ ሰምቼልሃለሁ! አሁን አልኩሂ ?"

"እንዲህ ወደታይ ወረድ ብዬ ነበር ። ብስጭቱ አላስቀም ፥ አላስቀምጥ አለኝ እቴዋ! ንዴቱ አንጀቴን ላስ አደረገው ——"

"ዋ—'ቴ! አሁን እንደንቧይ ቢፈርጡት ምን ያረጋል? ከኔና ካንተስ የሞተ ሰው ይሻላል!"

"ምነው እቴዋ? ምነው? እኛ ምናችን ተነካ ? እሚሆን መስሎን ——" ሲል ፥

"እሱን አታንሣ ። መበርታት አሁን ነው ። እንዲሁ ትንዘረዝረህ ጉዳችን መንተክተኩ ነው ። አንተ መቼም አሳበ—ቢስ ነህ —— ሰው እንዴት ቆሞ እጁን ይሰጣል?"

"ምነው ?ምን መጣ? ደህናም አደለሽ እንዴ?"

"ኧረ እንዲያው ሞተህ ባረፍከው አንተስ! ደሞ ደህናም አደለሽ ወይ ትለኛለህ?! አንተን ይገፎ ነው ደህና እምሆነው ? የዚያን ያገልግል ነገር ማታ በጭለማ መጥቼ አልነገርኩህም እንዴ?! እንዲቹ ቁጭ ብዬ ነጋልኝ — —"



"በምን ምክኛት? — — አትክዷቸውም እንዴ?"

"ኧረ—ወዲያልኝ አንተስ! ምን ብዬ ነው እምክዳቸው? እታእቸውምና ነው? አሁንማ ብለው—ብለው ፥ ያገልግሉ ጉዳይ ከሱ ራስ አይወርድም እያሉ — —"

"ከማ?"

"ካንተ ነዋ !" አሉት አፉቸውን ሞልተው ።

"ነው' ንዴ !! ኧረ—ንሱ! — እንተያያታለና! ዐርፈው ቢከበሩ ይሻላቸዋል ።"

"ኧረ ተው እንዳፍ አይቀናም! ይኸ አፍህ ዘረጥ—ዘረጥ አይበል! እማትወጣውን ዛፍ አትጠንቁል ። እኔ የሰሙትንም እንጃ ፥ ነገሩን ደርሼበታለሁ ቲሉ ነው ያመሹት — —"

"እኔ ቢያነጉስ ምን አሻኝ! — — እኔ የሳቸውን አገልግል አቅላቸዋለሁ እንዴ?"

"ማ ነገሩን አሳክቶ እንደ ነገራቸው ምን ዐውቄ ፥—— ዐሥረዬ እየተነሡ ይኸ ዘመድሽ ፥ እንዳሉ ነጋላቸውዬ ——"

"እንዴት አሳሬን አሳዬኝ ይኸ ዝምድና ወንድሜ!— አሁንማ ማ ችሏቸው ፥ ተሾሙ መሰል ፈረደብን ፥ እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ! ለመሆኑ ማ ነገረኝ ይላሉ?"

"ያቺ ቀላማጅ ምን ያልቀላመደችው አለ ? ሴላም ሰው ጠይቆዋል መሰል ማባቱ ሔዶ ሲሸረከት እንዳመሸ እንጃ ፥ እነዚያ ባላጋሮቹ ምንዳዬን ተዚህ ቢያበሩልኝ ፥ አለያም ቢገሉት ፥ ቀኛማይ ለሱ የሰጡትን ማሳ እቴዋ ለኔ ታስጠኝ ነበር ፥ እሱ ነው እንቅፋት የሆነብኝ እያለ ሲያወራ ሰምተነዋል ብለው ነግረዋቸዋል መሰል ።"

"እስቲ ሙት በይኝ! ደሞ ማ ይሆን እንዲህ አርጎ ስሜን ያጠፋው?"

"የት አባቴ ዐውቄ ! እኔስ አንጀቴ እርር ያለው በምን መሰለህ ?"

"ደሞ ወደኔ ዞሩ ?! እኔ መች ጉዴን አወኩ ?! አንቺ ታዲያ ምን አልሽ እቴዋ ?"

"ቀድሞ ነገር ማ አናግሮኝ? እሳቸው ለራሳቸው ነገር —ነገር ብሏቸዋል ። 'አንቺ ምን ታቂያለሽ' ብለው አፌን አስያዙኝ ።"

"እስቲ ምን እንደሚያረጉኝ አያለሁ ፥ አሁን ስተት ብዬ እሔድ የለ !"

"ማተብ እንዳለው ጫር — ጫር አርጌ ልይበት" ከማለቱ አንዱ አቀበለው ። የረጋውን ደም በስንጥሩ እየጫረ ማተቡን ፈለገ ።

"በደንብ ነሃ — ነሃ አርገው ፤ ምነው ፈራኸው?" አለ አንዱ ደፋር መሳይ ።

"ይቻት ክሩ! በደም ተለውሳ ነውቁ — ይቻት!" ብሎ ሁለት ሦስተቴ በስንጥሩ ወደ ላይ አነሣና ፤ "አማራ ነው! በሉ እንግዲህ ለቀ ኛማይ እንንገራቸው" አለ ቀና ብሎ ።

"ምን እንዲያደርጉልን ፤ እንዲያማምሱን ነው?" አለ ሌላው እየሣቀ ።

"ልንቀብረው ነው ብለን ነውቁ !" አለ ሁሉንም እያየ ።

"መሬት ለከተው እንዲያሰጡን ነው ወይስ ለቄሶቹ እንዲነግሩ ልን — ይልቅ አታሥቁብን ።"

"ለማንቻውስ ቢሆን ፤ አገሩ ሳይታወእና ሰው አይቶ ሳይለየው ፤ ማ ቅበሩ አላችሁ ቢሉንስ? በሰው ነገር ማ ጣጣ ይገባል? ቄሶቹም እሚሰሙት እሳቸውን ነው" አሉ ሽማግሌው ።

"እውነታቸውን ነው ፤ ማ ቅበሩ አላችሁና ቀበራችሁ ብንባልስ" አለ አንዱ ።

"እንደ ዐውሬ ጠባቂ ብርድ ሲፈዳፍደን አደርን — —አሁን ደሞ ምን ባረግን እንንገላታ?"

ሌላው ካፉ ልፎ "ሬሣውኮ የነሱ ነው ፤ እኛ ዐይናችን እያየና ጆሯችን እየሰማ እንዴት ዐውሬ ይበላዋል ብለን አደርኂ ፤ ምንዳዬ በገደለው እናንተን ምን ዶላችሁ ቢሉንስ ?" በማለቱ ተሣቀ ።

"እናንተ መማሻውን አምጡ ፤ እኔ ለቀኛማች እነግራቸዋለሁ ፤ ብላት አያጡም" አሉ ሽማግሌው ።

"ደግ ብለኋል ፤ ያደርነው አንሶ ስንንቃቃ እንዋል እንዴ!" አለ አንዱ ችኩል መሳይ ።

አንዳንዶቹ ዶማ ለማምጣት ወደየቤታቸው ሲሔዱ ፤ ሽማግሌው ወደ ቀኛዝማች እልፍኝ አመሩ ። ባዳራሾቹ መኻል አልፈው እልፍኙ አጠገብ እንደ ደረሱ ከወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ጋር ተገናኙ ።

"ምነው? የደህናሁን ነው?" አሉ ሴትዮዋ — እኚህ ደሞ 'ምን ሊሉ ይሆን' በማለት ።



"ደህናስ ደህና ነኝ ፤ ቀኛማይን ፈልጌ ነው ፤ ቅድም አፈሣን ስት ጠይኢ እነግርሻለሁ ስል ቶሎ ሔድሽብኝ — —አገኘሽው አደል— —"

"በሉ ግቡ! — ግቡ! አሁን የእድሙን ምን አነሣሣሁ" ብለው ገለል አሉላቸው ።

"አላገኘሽው እንደሁ ብዬ ነው" አሉና ገቡ ። ሽማግሌው እጅ ነሥተው ከቀኛዝማች ፊት እንደቆሙ ሰላምታ ተለዋውጠው ፤

"ምነው ? ደህናም አይደለሁ እንዴ ?" አሏቸው ባክብሮት ።

"እኔስ ደህና ነኝ ፤ እየሀ እደይ ያደረው ሬሣ" — —ብለው እን ደጀመሩ ፤

"የቱ ሬሣ?"

"እየሀ እደጅሁ ያለውን ሬሣ ነዋ !"

"እኔ ታዲያ ምን ላርግ?"

"ልጆቹ እየትኻራችን ልንሔድ ነው ፤ በጧቱ ቢቀበርስ ቲሉ ጊዜ—"

"ሀ! ታዲያ በላይነህ ታፈሰ ግቢ መቃብር አለ ያለው ማን ነው?"

"ኧረ ማንም አላለ ቀኛማይ ! አንቱ ሳትሰሙ ብለን ነውቁ —"

"እኔ ቀድሞውንስ መች አምጡልኝ አልኩና ፤ ሲያንዘፋዝፉ ያመጡት እነሱ ———"

"እነሱም አምጡ ብለውን ነው አላሉ አሁን ምናልባት እኔ ታልሰማ ማ አዘዛችሁ እንዳይሉ — — —"

"ለኔ ብለው ተሆነ ፤ ሟጨራ ገበያ ያስጡት ፤ — —እንዴት የጠ ቀመኝን ሰው አመጡልኝ !"

"ይሁን ፤ ለዚሁ ነበር አመጣጤ ። እኛማ ለቄሶቹም ትነግሩልና ለሁ ብለን ነበር ።"

"መይ ሥራ አጣሁና ፤ ቢሻቸው ይፍቀዱ ቢሻቸው ይከልክሉ ፤ ሰውዬው አማራ መሆኑ ከታወቀ ቤተስኪያን መቀበሩ አይቀር ፤ ዐፈር አይከለከልም ፤ ዐፈር ያባታችን ያዳም ነው" አሉ ሽማግሌ ውን ትኩር ብለው እያዩ ።

"ለምን አልነገራችሁኝም ብለሁ እንዳትቆጡ ብለን ነው" ብለው ሽማግሌው መሰስ አሉ ። "ዐውሬ የሰውዐውሬ! ደግነቱ ሁላችንም

እላይ ቤት እኩል መሆናችን ፣ እንኳንና የሰው ፣ ያሀያ ሬሣም እገበያ መኻል አይጣል — —ቲሾሙ ጊዜ ባሰባቸው ልበል ፣ ሒደው የመጡለትማ እንኳንና ሬሣ ደሃም ባይኔ አታሳዩኝ ሳይሉ አይቀሩ ። ክፉ —የሰው ክፉ — ስባት ላብ !" እያሉ ተመለሱ ።

"እ —ሀ ፣ ምን አሉ?" አሉ ሁለት ሦስቱ ።

"ሲያቀብጠኝ ሔጄ—ተዋርጄ ልምጣ?" አሉ ራሳቸውን እየነቀነቁ ።

"ተቆጡ እንዴ?"አለ አንዱ ።

"እኔ ያሉትን ቢሉ ምን አገኘኝ! ቀደው አያለብሱኝ ፣ ቆርሰው አያጐርሱኝ ፣ ሥራቸው በጣም ያሳዝናል" አሉ ሬሣውን አሽቆልቁ ለው እያዩ ።

"ተናገሩሁ እንዴ?" አለ አንዱ በቁጭት ።

"በምን ምክኛት ይናገሩኛል!? — — እኔ ቸግሮኝ አለቁኝ ልል አልሔድኩ ።"

"እንዴት ይሁን አሉ?"

"እንዲሀ አሉ ቢሉት ምን ያረጋል?"

"እኛስ ቢሆን ለነብሳችን ብለን ነውዪ — — — ማ የግድ ያዘን። ቄሶቹም ቢሆኑ ባፋቸው ነውዪ ለነፍሳቸው አላደሩም ፤ ይኸንዬ ከበ ርቲ ሞቶ ቢሆን እንደ ቀፎ ቀራጭ ጭሳቸውን እያምቧለሉና ምና ምኔአቸውን እያንቧሹ ከራስጌ—ከግርጌ ይሉ ነበር ፣ ላለው አፋሽ— አጎንባሹ ብዙ ነው ። ደሀና ገላገሉን ፣ በጧት ቀብረን ወደየ ምላዳችን እንሒዳለን" ብሎ እንደ ጨረሰ መማሻ ሊያመጡ የሔዱት በየተራ ብቅ ብቅ አሉ ። አንዲት ሴትዮ ሬሣው ላይ ሽማ ጣል አደረጉ ። አንዳንድ የመንደሩ ሴቶች ቀስ—በቀስ እየመጡ ፣ ድምፃቸው ሳይሰማ አለቀሱ።

* * *

ቃሬዛው ሊነሣ ሲል ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፣ አጥራቸው በር ላይ ቆመው በነጠላቸው ጫፍ እንባቸውን እያባበሱ ስቅስቅ ብለው አለ ቀሱ ። እሟሟቱና አወዳደቁ ሁሉ ክፉኛ ቆጠቆጣቸው ። የሚወዱትም የሚጠሉትም ጠፉቸውና ፣ "አይ ሰው መሆን! አሁን የኛ ነገር ምን መላ አለው!!"አሉና እንባቸውን አንዠቀዠቁት ። የነበራቸውንም ቃል ኪዳን አስታወሱ ። ተስፋና ምኞታቸው በመለምለም ፋንታ ሲደርቅ እየታያቸው ቢናደዱም ፣ ምስጢራቸውን የሚያውቀው ሰው አንዳችም ትንፍሽ ሳይል በመሞቱ እፎይ አሉ ።



## ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

አፈሣን እንደ ቀብር ዐፈር አድፋፍተው ከሸኙና የጠሉት ሬሣ ከደጃቸው ከተወሰደ በኋላ ፣ ወይዘሮ እልፍ ይከንዱ ልባቸው ዲዷታ ውን ቢቀንስም ፣ አእምሯቸው ከመሸበርና አካላቸው ከመርበትበት አላ ረፈም ። ከመሞት ፣ እያገገሙ መኖርን ይመርጣሉ ። ዋሽተውም ቢሆን የሚያማክሩት ፣ ለመጠቃቀም ሲል ተጠግቶና ምስጢራቸውን ጠብቆ ከቀኛዝማች ጋር የሚያስማማ ሰው ፣ ቢያስቡ ፣ ቢያሰላስሉ አጡ ።

"ወይኔ ልጂት!" አሉና አጥር ዘሎ ከሚወጣ ውርደት እቤታ ቸው ውስጥ መንበርከክን መረጡ ። ሁሉንም እርግፍ አድርገው ወደ ራሳቸው ተመለሱ ። ሌላው ቀርቶ በጭንቅና በጥቃታቸው ሰዓት ከዐይነ —ሕሊናቸው የማይጠፋው ጊዮርጊስ እንኳ ትዝ አላላቸውም ። ከቤት ንብረታቸው ይልቅ ስለ ስማቸው አሰቡ ። በተለይም ጣውንታቸውን ሲያስቡ ይብስባቸው ጀመር ። 'እኔን እታገል እጥል ብላ የገዛ ጉድ ጓዷን ማሰች ፣ የገዛ ሸሯ ተደረባባት' እያሉ የሚሳለቁባቸው መሰላ ቸው ። 'አንቺ እኔንም ከማስገደል አትመለሺ ፣ አሁንም ቢሆን ያረግ ሺው ያክል ነው ፣ እኔ ተንግዲህ ወዲያ ምንሽም ምንሽም አይሻኝ ፣ እጅሽ ባንጠለጠለና ጀርባሽ ባዘለ ያፈቀደሽን ይዘሽ ሒጂልኝ' እያሉ ቀኛዝማችም ሲያሰናብቷቸው ታያቸው ። ምኞታቸው እሳት እንደ ለቀቁበት የሣር ክምር ይሆንባቸውና እርር ድብን ይላሉ ።

ዕቃ እንደጣለ ሰው አጥር— ላጥር ሲዞሩ ቆዩና ፣ መምሬ ተክለጊ ዮርጊስ ወደ ምንዳዬ ቤት እንደ ገቡላቸው "ተንግዲህ በነገሬ ማንም አይገባበት ፣ ተፈርቶ የት ሊደረስ ነው ፣ እስታሁንም በቁሜ የገደለኝ ፍራቴ ነው ፣ የገዛ ነገሬንማ እንደ ሚሆን እንደሚሆን ማረግ ታቃተኝ የሰው መሳቂያ መሆኔ ነው" ብለው በቀጥታ ወደ እልፍኝ ገቡ ።

"የት ሔደሽ ነበር ? ቤተክርስቲያን ደርሰሽ መጣሽ እንዴ?" አሉ ቀኛዝማች በርጋታ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል እንደ ሰሙ እፎይታ ተሰማቸው ።

"አዎ" አሉ ያላሰቡትን ምክንያት በማግኘታቸው ደስ እያላቸው ። ሁለቱም ዝም አሉ ። ሴትዮዋ አፈሣን ከሸኙ በኋላ ያውጠነጠኗትን አዲስ መላ ለመናገር ተዘጋጅተው ሳለ ፣

"ያንን ሬሣ ወሰዱት—እስካሁን አለ?" አሉ ሰውዬው ድንገት ።

ብሎት አመሰገነ። መንገደኞች ከየቆዩበት ሲመለሱ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑም ተመልካቾቻቸውን እያስገረሙና ፣ የገላ ቅርፅ አይተው የሚቋምጡ ወንዶችን የስስና ምራቅ እያስዋጡ ተመልሰው ገቡ። ለላቀች ግን ፣ አውቶቡሱ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቆሎ ከሚሸጡ ልጆች መኻል አንዱን ጠርተው በምልክት ካሳዩት በኋላ የዐሥር ሣንቲም የገብስና የሽምብራ ቆሎ አዘዙላት። ለራሳቸው ከገዙት ሙዝም ሳኩላት። በትልቅ አገልግል ጥሰቅ ብሎ የተቋጠረው የዶሮ—ወጥና እንጀራ ግን ፣ አዲስ አበባ ለጉራና ለዝና ቀርቦ የሚበላ የባለሙያነት ማስመስከሪያ ነው።

ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ የሚበሉና የሚጠጡት ፣ የሚለብሱና የሚያጌጡበት ነገር ሁሉ ከሰው የበለጠ ቢሆንላቸው ደስታውን አይችሉትም። የሚያኮራ ስምና ዝና ይወዳሉ።

“ጥሎብኝ ፣ ከትንሽ ሰው ጋር መዋል አይሆንልኝም ፣ መብልም ቢሆን ጥፍጥ ያለች በትንሿ ትበአለች። አሰስ ገሰስ አልወድም” ይላሉ።

ቀኛዝማችን የወሸሙ ሰሞንም ፣ “እያዩ ነው መውደቅ ፣ ለንዲህ ያለው ሰው ቢበለጡም አይቆጭ ፣ ከማን ጋ ነው ቢባልም ስማቸው ብቻ ያኮራል። ካንድ ቁና ጓያ አንድ ቃጢ ስንዴ ይበልጣል” በማለት ከጐረቤቶቻቸው ጋር አውርተዋል። ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ የተነሡበትም ዋናው ምክንያት ፣ አዲስ የተመረጡት የሕዝብ እንደራሴ የቀኛዝማች በላይነህ ሚስት ናቸው በመባል የዝና ተካፋይ ለመሆን ነው። ይህ ፍላጐታቸው በሰውዬው በኩል ካልተሳካ ሌላ ብልሃት ከመፈለግና ከማስፈለግ ቸል አይሉም።



## ምዕራፍ ሐያ አንድ

የምንዳዬና የሞተው ሰውዬ ጉዳይ እንደ ሌሎች ተራ ወሬዎች ቶሎ በመቀዝቀዝ ፈንታ እንደ ፍግ ረመጥ ውስጥ—ውስጡን ተጋጋመ። የአፈሣ ቤተሰቡን ጥሎ መሔድ በየቤቱ በተለያየ ሁኔታ ተወራ።

አንዳንዱ ‘እቴዋ እያለች እንዴት የማንም ጋለሞታ ቀድማት አዲስ አበባ ወጣች’ ብሎ ከቀኛማይ ጋር ተጣልቶ ነው አሉ ሲል ፣ ሌላው ደግሞ ‘ሬሣ ጥባእ አድሮ ሊነጋጋ ቲል ፣ ምንዳዬን እጠይቃለሁ ብሎ ቲሔድ የምንዳዬ ሚስት ጨለማ ውስጥ ተቀምጣ ስታለቃቅስ ጥግ—ጥጉን ቲሔድ አይታ ፣ እሷም ለራሷ ፈርታ ሳታውቅ ብጠይቀው ይፈራና ይሸሻል ፤ በዚያ አፍሮ ነው የጠፋው አሉ’ ይላል። በጣም አውቃለሁ ባዩ ደግሞ ፣ ወሬውን ከየት እንደ ሰማና እንዳገኘው ሳይታወቅ ‘ከየቱ ፣ ነገሩ ወዲህ ነው አሉ ፣ ምንዳዬ የቆሰለ ለት ፣ አፈሣ ከቀኛማይ ቤት የተዋሰው አገልግል ሚቹ ሰውዬ ማሽመቂያ ላይ ተገኝቶ ነው አሉ። በዚህ የተነሣ ነገር እንዳይባባስ ብሎ ነው አሉ’ ይላል።

ሁሉም በየቤቱ የአፈሣን ነገር እያነሣ የየግሉን ጥርጣሬና ግምት ሲሰጥ ፣ የመጨረሻዋ ወሬ ግን በየት በኩል እንደ ተገኘች ማንም አያውቅ።

ቸርነት ፣ የወይዘሮ እልፍ ይከንዱን ወጠጤ እረፋዱ ላይ አርዶ ሥጋውን በቆሪና በሰዴቃ ላይ ከፋፍሎ ወደ ቤት ካስገባ በኋላ ምንዳዬ አጠገብ ዐረፍ ብሎ ፣

“እመመሀ መሰል ምንዳ?” አለው።

“አይ ደግ ነኝ ፣ ምንም አይለኝ ፣ እንደ ፈራሁትም አደል!”

“ሥጋ ለሥጋ መሆኑ በጀ ፣ አጥንትህንማ ቢጨርፍ ኖሮ —— መቼም የኛ ነገር ጥሎብን ፣ ኮርኮም ቢያረገንም ማማረራችን አይቀር —— ሞትስ አለ አደል? አብነቱ የጌትነቱ ነው! እኔማ እዚያ ፋፈ ውስጥ ወድቀህ በደም ተለውሰህ ቃይህ ፣ ልቤን ስውር ነበር ያረገኝ ፣ ያደነጋገጤን ነገር አታንሣ —— ”

“እኔ ደሞ ሰውዬው ባፍጢሙ ተደፍቶ ሳየው በጣም ደስ አለኝ። ትንሽም ንድድ ያለኝ እሱም ገድየዋለሁ ብሎ ይሆን እያልኩ ሳስብ

ሰው እያየና እየሰማ ከባለቤታቸው ጋራ ወደ አዲስ አበባ ለመሔድ በመብቃታቸው ልባቸው ፈንድቷል ።

"እንዲህ የልቤ ደርሶና እንጀቴ ርሶ ፥ ለምን ዛሬ ማምሸዬን አል ሞትም" እስከ ማለት ደረሱ ። አውቶቡሱ ሲንቀሳቀስ አብዛኛው ሰው በተደጋጋሚ እጅ ሲነሣ ፥ ቀኛዝማችም ባርኔጣቸውን አውልቀው ተሰናበቱ ። ሴትዬዋም ቶሎ—ቶሎ ራሳቸውን እየደፉና እያቀኑ "ደህና ሰንብቱ" አሉ ።



# ምዕራፍ ሐያ ሁለት

ወይዘሮ ደጅ ይጥኑ ፥ ከታላቁ ቤተ መንግሥት በስተ—ምሥራ ራቅ ረባዳው ቦታ ላይ ከተሠራው ከእናታቸው አጎት ግቢ ውስጥ አንድ ሰፊ ባለ ጓዳ ክፍል ተሰጥቷቸው ደህና ተቀምጠዋል ።

በአጎትነት ስም የሚጠሯቸው አቶ ወርቅነህ ደመቀም ከንጉሡ በስጦታ ፥ ከመኳንንትና ሹማምንቱ በመማለጃና በልመና ሰፊ የከተማ ቦታና የገጠር መሬት ይዘው ፥ ጥሪት ያበጁና ቋሚ ንብረት ያደራጁ የታወቁ የጽሕፈት ሚኒስቴር ሁለተኛ መዝገብ ቤት ዲሬክተር ናቸው ። የሽምግልናቸውን ምዕራፍ ከጀመሩ ሰንበትበት ቢሉም ዙሪያውን የቆመላቸው ረዳትና የገንዘብ ወጋግራ ቀጥ አድርጎ ስለ ደገፋቸው ፥ ዕድሜያቸው ተቀናንሶና ጠባያቸው ተኳኩሎ ገና ለብዙ ጊዜ የሚያ ገለግል ተፈላጊ ሹም አድርጓቸዋል ።

የሳቸው ደህንነትና ተስፋ በወዳጅና በውለታ ከፋዮች ሲጠበ ቅና ሲከበር ፥ እሳቸውም በበኩላቸው የደጋፊዎቻቸውንና የአይዞህ ባዮቻቸውን ደህንነትና ጥቅም ሥራዬ ብለው ይከታተላሉ ። ቢሆንም ፥ ላላከኩላቸው አያኩም ፥ ላልጋገሩላቸው አያነጉቱም ። በዙሪያቸውና ከበ ላያቸው ያሉት ሰዎች ኑሮ ተዋቅሮ የተጨመጨመው ፥ በአማግረኝ ላማግርህ ፥ በአካድነኝ ላካድንህ ፥ እንካ — በንካ ስልት በመሆኑ ቻል ታና ዝንጋታ የኑሮ መዕድን ያናጋሉ ። አፋቸው ለጉርሻ ፥ እጃቸው ለእጅ መንሻ የተከፈተና የተዘረጋ በመሆኑ ፥ ከዘንጉ መነጠቅ ፥ ችላ ካሉ መጨፍለቅ ስላለ ፥ የሁሉም የጋራ ምሳሌ 'የዘነጋ ተወጋ' ወይም 'ፍት ፍቱን እይተህ ተጎራረስ' ነው ።

አቶ ወርቅነህ ደመቀ ከተላላኪነት ወደ ተራ ጸሐፊነት ፥ ከዚ ያም ደረጃ በደረጃ ወደ ፪ኛ መዝገብ ቤት ዲሬክተርነት የደረሱት ፥ በሥራና በአገልግሎት ብቻ ሳይሆን ፥ ለአለቆቻቸው በሚያደርጉትና በሚያሳዩት ከፍ ያለ ኸር —ጉድና የተትረፈረፈ ትሕትና ሲሆን ፥ በተጨማሪም በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች እንደ ጠቃሚያቸው ሰው ፍላጐትና ሁኔታ ለተለያዩ አለቆቻቸው በሚያቀርቡት ገጸ —በረከ ትና 'ይኸ ምስጢር ነው' በማለት በሚያደርሱት ወሬ ጭምር ነበር ። በዚህም ምክንያት ከአያሌ ዓመታት ጀምሮ ጠባያቸውን አሳምረው የሚያውቁ የቅርብ የሥራ ባልደረቦቻቸው ፥ "ወርቅነህ መዘውር" በማለት ቅጥያ አወጡላቸው ።

ሕይወታቸው በተላላኪነት ሥራ ወዲያ — ወዲህ ካለችበት ጊዜ ጀምሮ በሠሩበት ቦታ ሁሉ ፣ አንዱ ባንዱ ላይ ተንጠላጥሎና ተሻግሮ ፣ ተጉትቶና ስቦ እንደሚኖር በማየታቸው ቋሚ ጠባያቸውን ዐውቆ ፣ እምነትና ጽናታቸውን ገምግሞ ለመተንበይ የሚያዳግት ባሕሪ አላቸው ። ካለ ነገራቸው ግን ፣ ተናግረው ሰው አያስቀይሙም ። ልባቸው ከፈቀደና እጃቸው ከተዘረጋ ፣ ለጋስና ቁም —ነገረኛ ሲሆኑ ፣ ቂም ይዘው በክፉ ዐይናቸው ካዩ ደግሞ ፣ የጥቃት ጦራቸውን አድፍጠው ይወረውራሉ ።

በሥራቸውና በጠጋ — ጠጋቸው ምክንያት የተነሣ ለም ከጠፍ የመንግሥት መሬት ያለበትን ፣ ሹመት የሚገኝበትንና የታጨለትን ፣ የደመወዝ ዕድገት የሚሰጥበትን ፣ የየትኛው ክፍል ባለሥልጣን በምን ዓይነት ጉዳይ እንደሚያግዝ በመንገርና በማማከር እንደምንም ጠቅሞ መጠቀም ልማዳቸው ነው ። ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ አዲስ አበባ በገቡ ሰሞን ፣ "አይዞሽ! የምትፈልጊውን ነገር ንገሪኝ ፣ ከሰው እንሶ መታየት አልወድም ፣ እ!" በማለት አኩራሯቸው ። ቀድሞውንም ዝናና አይዞሽ ባይ ወዳድ የነበሩት ሴትዮ ምኞታቸው ተሳክቶ ፣ በቀኛዝማችም ሆነ በሌሎች ወሬ ቃራሚዎች ፊት የሚያስከብሩና 'እኔ አለሁ' የሚሉ ዘመድ በማግኘታቸው ፣ ልባቸው በኩራትና በተስፋ ተለጠጠ ።

ላቀችም ገና ከማጀቴ ሳይነሡ እንደ ተነገራት አቶ ወርቅነህ ደመቀ ቤት ተልካ በገባች ቁጥር ፣ ካፏ ቆጠብ ፣ ካቀማመጧ ሰብሰብ ፣ ካንገቷ ሰበር ማለትንና የሚበላም ይሁን የሚጠጣ ሲሰጣት ፣ ካንገት በላይ መግደርደርን ሥራዬ ብላ ተያያዘችው ። ካደገችበት የገጠር ልማድ በባሰ ሁኔታ ፣ "እንዲህ እያልሽ ነው መናገር ፣ እንዲህ እያደረግሽ ነው መሥራት" እየተባለች በተደጋጋሚ በመነገሯ 'እሺ' እንጂ 'እምቢ' የሚል ቃል ከአንደበቷ የጠፋ መሰለ ። የኩተቱ ዓይነትም በዛባት ። የምታየው ዕቃ ሁሉ ሲነኩት የሚሰበር ፣ ሰው ሁሉ ቅን የማይናገር እየመሰላት ፣ ዕቃውን ሁሉ የምታነሣው በጥንቃቄ ፣ ሰውን ሁሉ የምታናግረው በፍርሃት ሆነ ። በጣም ያስደነቃት ዕቃ ግን ፣ ግድግዳው ላይ ረዢም ጥቁር የገመድ ጅራቱን ሽጉጦ ፣ ክብ ጠረጴዛ ላይ ማዕዘኑ ጥግ የተቀመጠው አነስተኛ ሳጥን መሰል ነገር ነበር ።

ጢት — ጢት ቡና ሲጠጣና ከምሳ በኋላ የአቶ ወርቅነህ ልጅ ነካ ስታደርገው ፣ እንደ ሰው ያወራራና በመኻሉ ደግሞ ዘፈኑን ያስነካዋል ። ማታም እንዲሁ ። ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ወጣ ሲሉላት ያንን ለፍላፊና ዘፋኝ ሳጥን ከወደ ቂጧ ሸሸት ፣ ከወደ ደረትና ራሷ ወደ ፊት ሰገግ ብላ ትመለከትና ፣ "እምኑ ጋ ይሆኑ ሰዎቹ?" ትላለች ።



አንድ ቀን ከወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ጋር ብቻቸውን ሲያወሩ ፣ "እቴዋ ፣ ይኸ ነገርዮ ምንድነው እልኋለሁ እያልኩ" አለች እያፈረች ።

"የቱ?" አሉ አካባቢውን እየቃኙ ።

"ያ እጠረንቤዛው ላይ ሆኖ እሚዘፍነው" አለች በጣቷ እያሳየች ።

"ያ ጠረንቤዛው ላይ ያለው?" አሉ እየሣቁ ።

"አዎይ!" አለች ስለተሣቀባት አፍራ ።

"ነካካሽው እንዴ?" አሉ ኮስተር ብለው ።

"እረ ምን ቅብጥ አርጎኝ"

"አዎ ፣ የማታኢውን ነገር አትንኪ ፣ ሬዲዮን ነው ።"

"እቴዋ? ዐፈር ስሆን አትሳኡብኝና እሚናገሩትና እሚዘፍኑት እምኑ ጋ ሆነው ነው?"

"ፈረንጅ እማይጠብበው ምናለ? እኔስ የት ዐውቄው ብለሽኝ" ብለው ስለ መለሱላት ፣ እሳቸውም እንደሷ ባለማወቃቸው "እረግ! ለካ የኔው ቢጤ ናቸውና" ብላ በልቧ ተደሰተች ።

ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ፣ ብዙ ጊዜ የተመኙትን ወርዳምና ቁመታም የቁም — ሳጥን መስታወት በማግኘታቸው ፣ ጀርባቸውን ወደ መስታወቱ አዙረው የአካላቸውን ቅርፅና አቀማመጥ አንገታቸውን እስኪያማቸው ተጠምዝዘው በተደጋጋሚ ያዩታል ። የተለያዩ የገጠር ቅድ ቀሚሶቻቸውን በመቀያየርም በየትኛው ወፍራም ፣ በየትኛው ደግሞ ልከኛ መስለው እንደሚታዩ ለማወቅ ዐሥሬዬ እያወለቁና እያጠለቁ ይመለከታሉ ።

ከአቶ ወርቅነህ ሚስት ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን በሔዱባቸው ቀናትም በአለባበስና በአረማመድ ፣ እንዲሁም ከወደ ቂጥና ዳሌአቸው ከሳቸው የሚበልጡና የተኩነሰነሱ ፣ አጣጣልና እርግፍጋፌውን የሚያሳምሩት አያሌ ሴቶች በማየታቸው በተበለጥኩ ስሜት ቀኑ ። "ሆሆይ! ለካ በያገሩና በየቤቱ ስንት መልከ መልካም አለ እናንተ ሆዬ!" እስከ ማለት ደረሱ ። ቀኛዝማች እንደሚወዷቸው ቢያውቁም ፣ የእንዲህ ዓይነቶቹን ሴቶች ቁመና በተደጋጋሚ ሲያዩ ልባቸው ይሸፍት ይሆናል በማለት ጠረጠሩ ።

ላቀች ሴትዮዋ ወጣ ባሉላት ቁጥር ፣ መስተዋቱ ፊት ትተክለች ። ቀጠን ፣ ለዘግ ያለው ቁመቷና አቀማመጠ መልካሙ የአካላቷ ቅርፅ ደስ ስለሚላት ፣ ቤቱ መስተዋት ብቻ ቢሆን ምኞቷ ነበር ።

* * *

ቀኛዝማች ፣ እሑድ ረፋዱ ላይ ወ/ሮ ደጅ ይጥኑን ሊጠይቁ በሔዱ ጊዜ አቶ ወርቅነህ ጥሩ አቀባበልና የመስተንግዶ ግብዣ አደረጉላቸው ። ከጥቂት ጭውውት በኋላ ቀኛዝማችና ሴትዮዋ ወደ ማረፊያቸው ሔዱ ። ተነፋፍቀዋል ።መኝታ ቤት ውስጥ ገብተው በመጀመሪያ ስለየራሳቸው ፣ ከዚያም በምንዳዬ ላይ ስለ ደረሰው አደጋ ባጭሩ አወሩ ። ሮውዬው አፋቸው እያወራ ፣ እጃቸው ይዳብሳል ። የሴትዬዋን ጣቶች ፣ ክንድ ፣ ጠፍጠፍ ብሎ አሮጌው ሶፋ ላይ የተጋደመውን ጭን እያሻሹ ፣ ስሜታቸውን ቀሰቀሱት ። ሴትዬዋም ነዝሯቸው ውስጣቸው ወከክ አለ ። ወዲያው የመኝታ ቤቱን በር በዝግታ መለስ አድርገው አንጀታቸውን አራሱ ። ረዘም ካለ ሰመመናም ቆይታ በኋላ በረድረድ ባለስሜት ወሬ ጀመሩ ።

“እንዲያው ያጨካከንሁ ነገር —” አሉ ሴትዮዋ ።

“ምን አጠፋሁ? ያጠፋሁት ነገር አለ እንዴ?” አሉ ውስጥ— ውስጡን እየዳበሱ ።

“መሔጃዋ ደርሷልና እንዴት ሆና ይሆን ብለሁ ብቅ አለማለትሁ።”

“የሞላለት ሰው ደስ ማለቱ እናንተ ሆዬ?! አዲስ አበባ ስመጣ እኮ የገጠር ንብረቴን በታትኜ አይደለም ። አደራ ብዬ ነው ። ምንዳዬስ በማን ሰበብ የቆሰለ መሰለሽ? አንቺው ጋ ተልኮ ሲመጣ እኮ ነበር — —ቢሞትስ ኖሮ ፣ ምንድን ነው የሰው ውለታ ማጥፋት — ”

“የእሱንማ ሰምቼ አዘንኩ ፣ የከዚያ በፊቱን ማለቴ ነውዪ!”

“ከዚያ በፊትማ ይኸን በዚህ አርጉት ፣ ይኸን በዚህ አርጉት ስል — —”

“ኡኡቴ! — —ማ አባቱ እንዳይነካው ፣ ያደራው ጋጋታ ደሞ ምን እንዳይመጣ ነው ?”

“ቢሆንም ፣ እንኳን ከዘመድና ከባዳ ፣ ከገዛ ልጆችሽም መኻል ታማኝ ታማኙን ትመርጫለሽ ።ሁሉም እኩል አደራ አይባልም ፣ ስንት አላቴና ስንት ቀስፋታ አለ መሰለሽ?”

“እኔንስ ከማን እኩል ታማኙኛለሁ?” አሉ እየሣቁ ።

“እንዴት ከማን እኩል?” አሉ ግራ ገብቷቸው ።

“እንደኔ ምንዳዬ ነውው — —”



“ይኸውላችሁ ስታሽቆለቁል! አንቺ ይኸን ይኸን ምን አጠያየቀሽ ? ይገርማል እኮ! ‘ብርንዶ ይዞ ሣምባ ቅልወጣ’ አሉ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ። እኔን ዋናውን ይዞሽ አደራ ጋ ምን ወሰደሽ?! ምን እንደምል ለመስማት ነው?” ብለው ሣቁ ።

ሴትዮዋ ለአንድ ቀን ዝናና ጉራ ያህል እንኳ እንዲያድሩላቸው ቢፈልጉም ፣ ወንድዬው ከባለቤታቸው ጋር አዲስ ንዝንዝ ላለመጀመር ስሜታቸውን ኮርኩመውና ነገር ፈርተው ወደ ቤታቸው ሔዱ ።

## ምዕራፍ ሐያ ሦስት

ምንዳዬ ፥ የቆሰለ ግራ ክንዱን አንገቱ ላይ ባጠለቀው የነጠላ ትልታይ ደግፎ እንጀራ ሲበላ ፥ ልኬለሽ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጣ አበላሉን እያየች ታጕርሰዋለች ።

"ብዬ እንጂ ልኬ ? አለያ እኔ መተዬ ነው ።"

"እየበላሁ አደል ! እኔ እኮ ስሠራም ጎረስረስ እያረኩ ነበር —"

"ደሞ የት ሆነሽ ነው የበላሽው? ሌላ የመብሊያ ሥርፋ ያለሽ ይመስል ?"

"እኔ ልሙት ! አላየኸኝሚ ስበላ ነበር ፥ አንተ በሽታ በሽታህን ስታዳምጥ" ብላ ልከኛ ጉርሻ ጠቅልላ እጅዋን ወደ ምንዳዬ ዘረጋች ።

"ቦጋለ ይሙት ፥ በቃኝ ጠግቢያለሁ" ብሎ ወደጐን ዞረ ። ወዲያው ፊቱን መለስ ከማድረጉ ፥

"ቢል ይኸው ስለማላህ ቀምሼልሃለሁ" ብላ ከጉርሻዋ አናት ላይ በፊት ጥርሶቿ በጥቃ ቀምሳ ፡ አፉ ሥር ደቀነችለት ። ፈገግ ብሎ ስለ ጎረሰ ደስ አላት ። እንደገና በእምቢታ የማያስመልስ ስም ስታስ ላስል ፥ የገዛ ስሟን አገኘች ።

"ዳግመኛ አልመጣብህም ፥ ይቺን ብቻ በልክዬ ሞት" ብላ ፋታ ሳትሰጥ አጎረሰችው ።

"አይ አንቺ ፡ እስካሁን የት ተደብቀሽ ነበር" ብሎ ሣቀ ።

ልኬለሽ የሞከከ —የሞከከውን ሥጋ እየመረጠች ስትሰጠውና ለራሷም ስትበላላ ቆይታ ፥

"ይቺን ብቻ ዐፈር ስሆን?" አለችው አዘናግታ ።

"አሁንስ አበዛሽው!" ብሎ ካንገት በላይ ሲቆጣ ፥

"እኔ በውሃ እበቅላለሁ እንዴ?" ስላለችው እየሣቀ ጎረሰላት ። እሱም ብድሩን መለስ ። መናዱ ሊነሣ ሲል "ልኬ!" አለ አንድ ሰው ከውጪ ።

"ይኸማ ጥሩ! እኔም ብሆን ደስ ይለኛል" አለ ቸርነት እየፈገገ ።
"እንግዲያውማ ይኸው፣ ልኬለሽ ትሙት !" ብሎ ማለ ።
ቸርነትና ልኬለሽ ትክዝ ብለው ተያዩ ።

ስለ አገልግሎ ገንዳ ውሃ መገኘትና ስለእነ አረጋሽ መጠየቅ እንዲሁም አፈሣ እንዴት ተውሶ እንደ ወሰደው ጭምር ያየና የሰማውን ነገረው ።

"ለዚች ኖሯል ያን ያክል የተጨነከው?"

"አይ አንተ! ምነው እኔን ሆንህ ባየኸው?"

"እኔኮ ለምጀዋለሁ ። አልሆን ቦታ ጠብኦው ሲተኩሱብኝ ስንቴን ጠርጥሬአለሁ ። ዞን —አምባ እያለሁ ፣ ታንደዜም ሁለተዜ ፈጣሪ አምላኽ ከልሎኛል ። ስንትና ስንት ነገርም አሜውቸሃለሁ ። አንተ ብቻ ተንኮል አታስብ፤ በሰው ላይ ነገር አትሥራ ። አንድ አምላኽ የሰጠህን ማንም አይነካብህ ። ብቻህንም ብትሆን እውነት እውነቱን ከሠራህ፣ ደመኛህ ሁሉ እግርህ ሥር ይለሽለሻል ። ጥላህ የሚቀለውና በጠላትህ እጅ እምትወድቀው ዙልመኛ ስትሆንና የሰው ሐቅ ስትሻ ነው ። ዋ! የምር አይምሰልህ፣ እንዲህ ኮነን እንቀር! ይቺ ቀን ታልፋለች!" ብሎ ራሱን ነቀነቀና ከንፈሩን ነከሰ ።

"ምነው ሙች ብለህ?! ምነው አልናደድም ስትል ምንዳ?" አለች ልኬለሽ እንባዋ እየመጣ ።

"አልተናደድኩም ልኬ ። ሞኝ የለቱን ፣ ብልህ ያመቱን ነው ። ብናደድስ ምን እንዳላመጣ? እሰው አገር ተቀምጬ፣ የሰው መሬት እያረስኩ ፣ ብቆጣና ብናደድ ማንን ልጎዳ ነው ? ሸዋርካብሽም ቢሆን አድርጊ ያላሏትን አታረግ፣ ትዋል —ትደሬ ይቺ ነገር ተደብአ አትቀር ! ያን ሽንታም አሞተቢስ ግን፣ ሱሪውን በጭንቅላቱ ባላስ ወልቀው እኔ ምንዳ አይደለሁም ! ምን ያረጋል፣ 'የዘነጋ ተወጋ' አሉ! በሉ እንዳትሠጉ — ምየላችሁ የለ? እኔም አልሰማሁ፣ እናንተም አልነገራችሁኝ" ብሎ ጋቢውን አጣፍቶ ካልጋው ላይ ወረደና መደብ ላይ ተቀመጠ ።

"አሄሄ! ይቺ ሁላ ዘዴ ነች ። እኔ ያንተን ልብ አጣኋትና ነው ። ሆደሰፊ ነህ ብዬ እፌን ስቀድ የነገርኩህ እንድትበሳጭ አልነበረም ። እንዲህ መሆንህን ባውቅማ — —" እንዳለ፣

"ምነው ቸርነት? ምነው? — ምነው እንዲህ ማለትህ? እኔስ እንደማደብኽኝ መች አጣሁት ። ቢቆጭህና ቢከነክንህማ ነው የነገርኩኝ ። አሁንም ቢሆን አልተበሳጩሁም ። ቸርነት ሙት! አልተናደድኩም!" አለው ። ፊቱ ግን እንደ ቀጨመ ነበር ።



## ምዕራፍ ሐያ አራት

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ፣ ጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ አዲስ አበባ ከደረሱ ጀምሮ ስለ ሕግ መምሪያና መወሰኛ ምክር ቤቶች አሠራርና ስለ መምሪያው ፕሬዚዳንትና ስለ ዐፃቤ ጉባኤው ሥልጣን፣ የሚገልጸውን ውስጠ ደንብ ጨርሰው የ1957ቱን ዜና ፓርላማ ሲያነቡ፤

"የተሻሻለውን ሕገ መንግሥት ካወጅንበት ከ1947 ዓ.ም. ጀምሮ ዛሬ ስምንተኛውን የፓርላማችንን ዓመታዊ ስብሰባ መክፈታችን ነው" በማለት ጀምሮ፣

"ዘላቂ የመሻሻል እርምጃ ሊገኝ የሚቻለው ጥልቅና ቀዋሚ የሆነ መሠረት ሲኖረው ብቻ መሆኑን ማስጠንቀቅ ይገባል ። እንደዚህ ያለውም ቀዋሚና ጥልቅ መሠረት ያገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያዳብርና የሚያጠናክር፣ ለሕዝቡም የተሻሻለ መልካም ኑሮ የሚያስገኝለት የተስፋፋ ፕሮግራም ሲኖረውና በየዕለቱም የሚያጋጥሙንን ችግርና መሰናክል ለማስወገድ የሚያስችለን ዘመናዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ዕውቀት እንዲሠራበትና የሕዝባችን የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ለማድረግ ሲሆን ነው" የሚለውን ሐተታ ሲያነቡ የሐሳቡ ይዘት ግራ ገባቸው ።

ቢሆንም ቀጠሉ ። "እናንተ የፓርላማ አባሎችና እያንዳንዱም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ማናቸውንም ጉዳይ ብሩህና አስተዋይ በሆነ አእምሮ ለመመልከትና ለመመርመር፣ የራሳችሁንም ሆነ የጓደኞቻችሁን ተግባር በማሻሻል ፍላጐት እንጂ፣ በጥፋት መንፈስ ለመተቸትና ለመንቀፍ አትሞክሩ" ከሚለው በታች እያሉ አንቀጾች አንብበው፣ "በመሬት ይዞታ መሻሻል ረገድ የሚደረገው ጥናት" የሚለውን አንቀጽ ሲጀምሩ፣ ዐይናቸው ፈጠጥ፣ ሁለመናቸው ነቃ ማለት ጀመረ ። "በልማድ የቆየውን አሠራር በመለወጥ የተሻሻለ ውጤት የሚገኝበትን ዘመናዊ ዘዴ ለመመሥረት በመሆኑ፣ የጥናቱ ሥራ እጅግ ከባድና መሠረት ያለውም መሆኑ ግልጥ ነው ። ለዚህም ተግባር አደራ የተጣለባቸው የመንግሥታችን ሠራተኞች ያለማቋረጥ በመሥራት ሥራቸውን በሁለት ደረጃ ከፍለው በመዠመሪያ ደረጃ እንዲፈጸም ካቀረቡት ውስጥ የርስተ ጉልት ግብር አከፋፈል ማሻሻያ ዐዋጅ

ቀርቦላችሁ መክራችሁበታል ። በፍትሐ—ብሔር ለወጣው የሰብል
አከፋፈል ሕግ ማሻሻያ የሆነው የጭሰኛና የባለ መሬት ግን
ኙነትና የሰብል ክፍያ ሕግ እንድትመክሩበት ቀርቦላችሁ እናንተው
ዘንድ ይገኛል ። በሚቀጥለው ደረጃ የሚወሰደውም ርምጃ ጥናቱ ተጠ
ናቆ ወደፊት ይቀርብላችኋል ። ባለርስት የሚገብረው ለማነው ? ለራሱ ፣
ለባለቤቱ ፣ ለልጁ ፣ ለአገሩ ነው ። ባለርስት በትጋት መሥራት አለ
በት” የሚለውን እንዳነበቡ መንፈሳቸው ረክቶ ፊታቸው ፈካ ። ከዚያ
ቀጥሎ የነበረውን ጽሑፍ ደስ ብሏቸው ቢያነቡትም አልገባቸውም ።

ቀኛዝማች ፣ እጅግ በጣም የጓጉለትና በሕይወታቸው ዘመን
እንደ መጀመሪያ ታላቅ ዕለት የቆጠሩት ኅዳር 3 ቀን አራት ሰዓት
ተኩል ላይ ቢቃለ—መሐላ ተጀመረ ። ከዚያም ልክ እኩለ ቀን ላይ
ታላቁ ቤተመንግሥት ውስጥ ከ3ኛ ጊዜ ተመራጮች ጋር ንጉሡ ዘንድ
ቀርበው እጅ ሲነሡ በተሰማቸው ኩራትና ራሳቸውም ጨማምረውና
አሰማምረው በፈጠሩት አድናቆት ተደስተው ዋሉ ። ደስታቸውን ሳይ
ጨርሱና ጋዜጣውን አንብበው ሳይጠግቡት ኅዳር 7 ቀን ደረሰ ።

አዲስ አበባ ከታላቁ ቤተ መንግሥት በስተሰሜን አራት ኪሎ
ሠፈር የሚገኘው የኢትዮጵያ ምክር ቤት ሕንፃ ፣ የሰዓት ደወል
ቤቱን እንደ ወፍራም ምርኩዝ እጐኑ ተክሎ እንደ ወርዳም
ትልቅ ቁምሳጥን ተጋድሟል ። ከልዩ ልዩ አቅጣጫ የሚጐርፈው የከ
ተማው ሕዝብ ከምክር ቤቱ በስተ ደቡብ ካለው ሕገ—መንግሥት
አደባባይ እና በስተምዕራቡ ካለው መንታ ጐዳና ላይ ፣ እንደ ጥምቀት
ባሕር ይተራመሰበታል ። ከምክር ቤቱ ውጪ ባሉት መንገዶች ላይ ፣
መሣሪያ ያነገቱ ወታደሮችና ተዘዋዋሪ ፖሊሶች ፣ በቁጣና በለዘብታ ፣
በግልምጫና በፈገግታ ሕዝቡ የመንገዱን ዳርና ዳር ይዞ እንዲ
ቆምና እንዲሔድ ወይም በያለበት ሥርዓት እንዲጠብቅ እያዘዙ
ያስተናብሩታል ። ሽማግሌና ባልቴት ፣ ጐረምሳና ኮረዳ ፣ ልጆችና
ጐልማሶች ይሰበሰባሉ ። ልዩ ልዩ ከረሜላ ፣ የሸንኮራ—አገዳ ፣ የአረን
ቻታና ሌላ ሌላ — — ነጋዴዎችና ሱቅ በደረቴዎች በሕዝቡ መኻል
እየተዘዋወሩ ይነግዳሉ ። አንዳንድ ሰዎች በዳንቴል ከርና በባለ አበባ
ጨርቅ የተሸፈኑ ትራንዚስተር ሬዲዮኖች አንግተውና አንጠልጥለው
የዕለቱን የፓርላማ መክፈቻ ንግግር ከማጉሊያና ከሬዲዮናቸው ለማ
ዳመጥ ቀዳሚ ሐተታውን ይከታተላሉ ። ትርምሱ እየበዛና ግፊያው
እያየለ ወደ መንገዱ ዳር ሲጠጋ ወታደሮቹ በቁጣም ፣ በዱላም ይከ
ላከላሉ ። ከወዲያ —ወዲህ የሚዘዋወሩት ፈረሰኛ ፖሊሶች ሕዝቡን
በፈረስ ኮቴና ዱላ እያስፈራሩ ከመንገዱ ገለል ያደርጉታል ።

ከምክር ቤቱ ሕንፃ ዋና ደቡባዊ በር አናት ላይ ፣ ሰማዕቱ ቅዱስ
ጊዮርጊስና ከግራ— ቀኙ ደግሞ ዘውድ ጭነው አንዱ በግራ ፣ ሌላው



በቀኝ ባንዳንድ የፊት እግራቸው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የያዙ
አናብስት ሥዕል አለ ።

በዚያው ትይዩ ከግዙፉ ባለሁለት ተካፉች የብረት በር ግራና—
ቀኝ ባራት ማዕዘን ቅርፅ የጥርብ ድንጋይ ዓምድ አናት ላይ ፊታቸውን
ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አዙረው የተገለጠ መጽሐፍ የያዙ የሁለት
ባለክንፍ አናብስት ሐውልት ይገኛል ። ከግርጌአቸው በጠባብ መቆሚያ
ውስጥ ቁመተ መለሎና አቋቋመ መልካም ፣ ትጥቀ ሸንቅጥ ቆፍጣና
ወታደሮች ይቆማሉ ።

ኅዳር 7 ቀን 1958 ዓ.ም. አራት ሰዓት ተኩል ላይ የኢትዮጵያ
ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሕግ መምሪያ ምክር ቤት የ3ኛ ጊዜ ተመ
ራጭ እንደራሴዎች የሥራ ጊዜ መጀመሪያና ንጉሡ ሁለቱን ምክር
ቤቶች በዙፋን ንግግር የሚከፍቱበት ዕለት በመሆኑ ፣ ከንጉሡ የኃ
ላፊነት ሥልጣን የተሰጣቸውና ከፍተኛ የመተዳደሪያ ንብረት ያላ
ቸው ፣ ሐረግ መዘውና ያጥንት ስንጣሪ ፈልገው የተሰባሰቡ ፣ የኃይል
አደራ የተቀበሉ ሁሉ በምድረ ግቢው ውስጥ በማዕረግና በሥልጣን
ተዋረዳቸው መሠረት በውስጣዊ የቅናት መንፈስና ፉክክር ሽብ—
ረብ ይላሉ ። በሰልፈኛውና በተመልካቹ ሕዝብ መካከል በተለያዩ
የአለባበስ ሁናቴና የኑሮ ደረጃ አቀራረብ እንደ ጥሬ የተዘሩት
ነጭ ለባሾች ደግሞ አምተው እያናገሩ ፣ አሽሚጠው እያሳደቡ ፣ ወሽ
ክተው እየነካኩ ፣ ወይም አሞግሰው እያስሞገሱ ፣ እንደ ንክ—ሰው
እየተቅበዘበዙና እንደ ዔሊ እየተንቀረፈፉ ይዘዋወራሉ ። የፓር
ላማው የደርብ ሰዓት ደወል አራት ተኩል ላይ እንደ ደወለ አካባ
ቢው በእልልታና በጭብጨባ አስተጋባ ። ግፊያና ጫጫታ በዛ ።
የሁሉም ዐይን ወደ ቤተ መንግሥቱ ሰሜናዊ ዋና በርና ወደ መን
ታው ጐዳና አተኮረ ።

በግዙፍ ልጥልጥ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው ፣ አጠር ባለ ሰንደቅ
ላይ በቢጫ ዘርፍ የተንቆጠቆጠች ሦሉስ ማዕዘን ባንዲራ የያዙ ፣
ባለ አንበሳ ጐፈር ቡሽ ባርኔጣ የደፉ ፣ ግራ ቀኝ ትከሻቸው ላይ ጐፈር
ያንዘረፈፉ ፣ ወፍራም ቢጫ ቋድ በደረትና በትከሻቸው በኩል ዐልፎ
እጐናቸው ላይ አናተ—ድብልብል ባለ—ዘርፍ ክሮች ያንዠረገጉ የክብር
ዘበኛ ፈረሰኞች ፣ አረንጓዴ ሽንጣም ውብ አቶሞቢል አጅበው በፓ
ርላማው ደቡባዊ በር በኩል እንደ ደረሱ ፣ በከፍተኛ ወታደራዊ ሥነ—
ሥርዓት የተሰለፉት ወታደሮች ረጂም የብረት ሰላምታ አቀረቡ ።

ንጉሡን ተከትለው እንዲገቡ የተፈቀደላቸው መሳፍንትና መኳ
ንንት ፣ ባለሥልጣኖችና ሹሞች ባስተናባሪዎች ቦታ ቦታቸውን ያዙ ።
ሁሉም ነገር የሚሽቆጠቆጥና የሚንሸቀሸቅ መሰለ ። ሕገ—መንግሥት

አደባባይ ከተሰበሰበው ሕዝብ መኻል ፤ ፍቅርና ጥላቻ ፤ ቂም በቀልና ውለታ ፤ ድጋፍና ጥርስ ነከሳ ፤ እርግማንና ምርቃት ፤ ብስልና ጥሬ ሐሳብ ጐን ለጐን ሲቆሙ ፤ አንዳንዱ በግልጽ ሌላው በስውር ውዴታና ጥላቻቸውን ይገልጻሉ ።

አጭር ፣ ቀጭን ፣ ፊተ እና አፍንጫ ሰልካካው ንጉሥ እጅግ ዘመናዊ የሆነ የሲቪል ልብስ እንደ ለበሱ ከአቶሞቢል ሲወርዱ የአካባቢው ሕዝብ በጭብጨባና በውካታ ድምፅ ተቀበላቸው ።

ንጉሡ ፈጠን ባለ አረማመድ በመሳፍንትና መኳንንቱ ፤ በታላላቅ የጦር —አለቆችና ባለሥልጣኖች ታጅበው ወደ ምክር ቤቱ ሲገቡ፤ በተለይ አንዳንዱ ለንጉሡ ያለውን ታማኝነትና ክብር ፤ መላ አካልና ሐሳቡን ለሳቸውና ለዙፋናቸው ደህንነትና ልዕልና የሰጠ መሆኑ እንዲታይና እንዲታወቅለት ይሯሯጣል ።

ጉባኤው አዳራሽ እንደ ደረሱ የሁለቱም ምክር ቤት አባላት ከፍ ባለ አስገምጋሚ ጭብጨባና የደስታ ስሜት ቆመው ተቀበሏቸው ። አብዛኛዎቹ የዘውዱ ሕልውና ጠባቂዎችና በዙፋኑ ዙሪያ የተማገሩ የበረከቱ ተቋዳሾች ሲሆኑ ፤ የሥዩመ እግዚአብሔርና የዘለዓለማዊነቱም መስካሪና አወዳሽ ፤ አውታርና ካስማዎች ናቸው ።

ንጉሡ ከመማክርቱ ፊት ለፊት ከፍ ካለ መድረክ ላይ ፤ መደገፊያው ረዘም ብሎ ፤ ከላይ መስቀል ባጎለለ ዘውድና ከግርጌው ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ፤ ከግራ — ከቀኝ ሰይፍ በያዙ መላእክትና በፍትሕ ዓርማ ታጅቦ ፤ በዳዊት ኮከብ ቅርፅ ካሸበረቀው መንበረ ዙፋናቸው ላይ ሲቀመጡ ሁሉም ነገር ጸጥ — ረጭ አለ ። ንጉሡ መደብ ጠርዝ ላይ እንደሚቀመጥ ልጅ ዙፋኑ ጫፍ ላይ ሲቀመጡ በአዳራሹ ውስጥ የነበሩት ዐይኖች ሁሉ ወደሳቸው አተኮሩ ።

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ፤ ከአድናቆታዊ ደስታ የተነሣ መላ— ቅጡ ጠፋቸው ። አንዳንድ ጊዜማ እንደ ሞኝ አፋቸውን ከፍተው ሲመለከቱ ፤ ዐይናቸው ይፈዝና እንቅልፍ የከበዳቸው ይመስሉ ነበር ። የንጉሡን የመጀመሪያ ቃል እንደ ሰሙም ፤ ወደ አንድ አዲስ ኑሮና አካባቢ እንደገቡ ታወቃቸው ።

የምክር ቤቱ መክፈቻ ንግግር ካንድ አንቀጽ ወደ ሌላ አንቀጽ በተሸጋገረ ቁጥር ከቀኛዝማች አስተሳሰብና ኑሮ ጋር ባለመገናኘቱ ፤ "ይኸ ምን ማለት ይሆን" እያሉ አንድ ቃል ወይም ሐሳብ ይዘው ሲያሰላስሉ ሌላው ያመልጣቸዋል ። በአዳዲስ ሐሳብና ፍቺው በማይገባ የቃላት ባሕር ተዘፈቁ ። ተገላገሉ ሲላቸው የግል ሐሳባቸውን ይዘው በእግረ —ሕሊና ሣር አምባ ገቡ ።



"ያገሬ ሰዎች ለዚህ ታላቅ ክብር መብቃቴንና ከመላ ኢትዮጵያ ተመርጠው ከመጡ የምክር ቤት አባላት ጋር ተቀምጨ የዙፋን ንግግር ስሰማ ቢያዩኝ እንዴት ጥሩ ነበር" በማለት ብዙ ሰዎች ትዝ አሏቸው ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱን ሲያስታውሱ ደግሞ ፤ "ይኸንማ ብታይ ፤ ተገርማም አታባራ ፤ እምድር ዓለም ያለሁም አይመስላት ፤ ይቺን አይታ ሣር አምባ ብትገባ ፤ ጃንሆይ ዘውድ ጭነውለት አየሁ ማለቷ አይቀርም ነበር" በማለት ኩራት ተሰማቸው ።

ሐሳባቸው ከሣር አምባ መለስ ሲል ፤ ንጉሡ ፤ ስለ ወቅቱ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ችግርና ትግል ፤ የተፈጥሮ ሕግና የሥራ ግዴታ ፤ የኅብረት ሥራ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ እንግዶች ጉዳይ አንብበው ፤ ሮዴሽያ ጉዳይ ላይ ደርሰው ስለነበር ፤ ቀኛዝማች ከማያውቁት የፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ ድንገት በመደንቀራቸው ፤ ስማ—በለው የሚያሻው ሰው መሰለው ተጎለቱ ። ደግነቱ የዕለቱ የፓርላማ መክፈቻ ንባብ በአጭር የምክር ቃላት በመጠቃለሉ ፤ 'እንዲህ እንዲህ ያለውን ቀላል ቀላሉን ቢናገሩ ምንነበረበት?' አሉ በልባቸው ። ያውም እየፈሩ ።

እያንዳንዱ የምክር ቤት አባል በስሜቱ ንረት መጠን እየተቁነጠነጠ ጭብጨባውን አቀለጠው ። አንዳንድ አባላት ግን የተደረገውን ንግግር ፤ "ምንም ዓይነት መሻሻል እኮ የለም ። ሀገር በዙፋን ዲስኩርና በተቀናበረ የቃላት ክምር አትቀናም ። የትግል ጊዜ ፤ የተፈጥሮ ሕግና የሥራ ግዴታ እያሉ ቢወተውቱት ምን ያረጋል ፤ እዚህ የተሰበሰበው ሁሉ የሚግጥ እንጂ የሚሠራ አይደል" በማለት የተደረገውን ንግግር በየልባቸው ነቀፉ ።

ንጉሡ ባጭር ቁመታቸውና በጠርጣሪ አመለካከታቸው እየተቆነኑ ፤ ወደ ምክር ቤቱ የውጪ ደቡባዊ ሰገነት ሲያመሩ ማጀብ የሚገባቸው ብቻ በዝግታ ተከትለው ሔዱ ።

ሕዝቡ እንጋጦ እያየ እልልታና ጭብጨባውን አቀለጠው ። ንጉሡ ላመል ታህል እንገታቸውን ስብር ቀና ፤ ቀኝ እጃቸውን ወለብለብ ፤ ጥርስ ሳይገልጡ ፈገግ እያሉ አሽቆልቁለው ተመለከቱ ።

ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ፤ የንጉሡን ችሎታ እያደነቁና የገባ የገባቸውን ሐሳብ ብቻ እያሰላሰሉ ፤ መንፈሳቸው በደስታ ተንበሸበሸ ።

ከቀኑ ሰባት ሰዓት ላይ ታላቁ ቤተ መንግሥት በተደረገው የምሳ ግብዣ ላይ 'ሲቪል ጠቆር ያለ" በሚለው የአለባበስ ደንብ መሠረት የታዘዘውን ለብሰው በቦታው ላይ ሲገኙ የተሰማቸውን እርካታ ፤ ያው የእንቃሩ ውቢት ሚካኤል ይገልጽላቸው እንደሆን እንጂ ፤ ሌላውንማ ችሎታ አለው ብለው አይገምቱም ።

ደግነቱ አራት ወራት ያህል እንደቆዩ ፣ እሚያድርበት ቤት ውስጥ በእንግድነት እየመጡ ሁኔታውን ያዩ የነበሩ አንድ የማር አምባ ገበሬ ፣ የእርሻ መሬት ሊጎልሙት ፣ ካነሳቸው ሊጋዙለት ፣ ለእርሻ ማረሻው ዓርብ ዕለትን ሊተዉለት ፣ ለሌሊት ልብሱ ዶዶ ፣ ለሥራ መሥሪያ ያቡጀዲ ቁምጣና እጀ—ጉርድ ሸሚዝ ሊገዙለት ተዋውሎ ተቀጠረ ። ሆዱን ባይርበውና ይለብሰው ባያጣም ፣ የሥራው ብዛት አስመረረው ።

እርሻ ውሎ ሲመለስ የበሬ ራት አጭዶ ፣ ወይም የማገዶ እንጨት ተሸክሞ ይገባል ። ይህን ከልጅነቱ ጀምሮ ለምዶታል ፤ ማታ ማታ ከቤት በታች በሬዎቹን እየጠበቀ ሣር ሲያበላ ፣ አገሩ ትዝ ይለዋል ። ወሎ ፣ ውጫሌ ወረዳ ድብል ማርያም እናት አባቱ ቤት ። ተወልዶ ያደገባት ቤት ፣ ተዘግታ እና ሆናለች ። ያደገበትን ቀዬ ዳዋ ወርሶታል ።

የአባቱ የአቶ ይመር አያሌው ርስት ከማነሷ ፣ ያካባቢው ባላባቶች ከወዲያ ከወዲህ እየኮረኮሟት ፣ አባቱም በተደጋጋሚ ደሴ ድረስ ላቤቱታ ሔደው ሰሚ በማጣታቸው ፣ በመጨረሻ የቀረቻቸው ሁለት ጥማድ አታውልም ነበር ። ቤተሰብ እየበዛ ፣ ይለበስና ይጎረስ እያነሰ ሲሔድ ኑሮ ያስመርራል ። የደረሰ ልጅ ያርሰው መሬትና ጎጆ ይቀልስበት ቦታ ሲያጣ ፣ የወላጅ ዐይኑም ልቡም ያነባል ።

የቸርነት አባት መሬት እየተጋዙና በጭሰኝነትም እያረሱ ኑሮን ታገሉት ። ባይንበረከኩም ተርገደገዱ ። የእኩሌታውንም ፣ የሲሶውንም ሞከሩት ። እርቦም ሰፈሩ ። ለሚያርሱት መሬት የሞፈር ማጋደሚያ ክፍያው ፣ ማርና ሙክቱ ፣ አጨዳና ውቂያው ፣ ጎተራ መጎተሩ ፣ ምርት ጭኖ ማድረሱ አንገፈገፋቸው ። ለከብት ሣር ግጦሽ ባመት በበሬ ሐያ ብር ደረሰ ። የኋላ ኋላማ ባለርስቱ አውድማ ላይ እየተገኘ ገለባውንም እኩል መካፈል መጣ ። በመጨረሻም ገበሬ እየቀጠሩ ጭሰኛውን ነቀሉት ።

ከዚያ በኋላ የቸርነት አባትና ጓደኞቻቸው ፣ ሊጫን የሚችለውን ኮተት ጭነው ከብቶቻቸውን እየነዱ ሐያ አራት ቀናት ከተጓዙ በኋላ ጎጃም ፣ መተከል ድባጤ ማርያም ገቡ ።

ለመንታ ወንዝ አካባቢ ገዢ ሐያ ብር የመሬት ግብር ከፍለው የሚበቃቸውን ያህል መሬት እንደያዙ ፣ ቸርነት ከአባቱ ጋር የእርሻ ሥራውን ቀጠለ ። ከሔዱት መኻል አንዳንዶቹ ዓመትና ሁለት ዓመት እየቆዩ ሲመለሱ ፣ ቆራጥ—ቆራጡ እዚያው ቀረ ። ቸርነትም ልቡ ተነሣ። ቢሉት ቢሠሩት አሻፈረኝ አለ ። የጎረምሳ ልቡን መግራትና ችኩል



ሐሳቡን መግታት ስላልቻሉ ፣ ተመልሶ አገሩ ገባ ። እዚያም ከሁለት ወር በላይ አልተቀመጠም ። "ደሴ ሔጄ ሸቃቅዬ እመለሳለሁ" ብሎ ቢወጣም አልተመለሰም ። እንዳሰበው ሥራ ባለማግኘቱ ከደሴ ጨፋ ሔደ ። ጨፋ—ሮቢትም ለማጀቴ አስረከበችው ። ቸርነት እንዳለው 'የሀል ውሃ ነገር ሆነና' ማር—አምባ በሎሌነት ተሻገረ ። ገበሬው ቤት አንድ ዓመት እንዳገለገለ ፋታ የለሹ ሥራ አንገሸገሸው ። "እዚህ ብቻዬን ከምንገላታ ፣ ብዙ ሎሌ ካለበት ቤት ይሻለኛል" በማለት ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ ዘንድ አማላጅ ልኮ ሎሌነት ገባ ።

ከምንዳዬ ረዘም ይላል ። ቀጠን ብሎ ሸንቀጥ ያለ የቀይ—ዳማ ወንዳወንድ ነው ። ሲሥቅ ጥርሱና ጉራማይሌው ደስ ይላል ። ደፋር ቢሆንም አይቸኩልም ። ዐልፎ—ዐልፎ ግን ድንገት ቱግ ይላል ። ቸርነትና ምንዳዬ ቀስ በቀስ እየተግባቡ ተዋደዱ ። ከተራ ትውውቅና ወሬ ፣ ሰፋ ወዳለ ወዳጅነትና ምስጢረኝነት ተሸጋገሩ ። ቀኛዝማች ቢወዱትም ፣ "ይኸን ልጅ አትበድሉት ፣ የሰው አገር ሰው ነው" ከማለት አልፈው እንደ ምንዳዬ ምስጢር ነክ መልዕክት አይልኩትም ።

ሸዋርካብሽ ቁመናና ቅልጥፍናውን አይታ ብትወደውም ፣ እሱ ግን ፣ ችላ ብሏት አረጋሽን ወደደ ። በተለያዩ ጊዜም በጠላውም በጉርሻውም ልትደልለው ሞከራ አልሆን ስላላት ፣ ያደረገ ፣ ያላደረገውን ለወ/ሮ አልፍ—ይከንዱ እየነገረች አስጠመደችው ። ሴትዮዋ በምኑም—በምኑም የተበሳጩና ሸዋርካብሽ ቅናቷ ያገረሸ ዕለት ፣ "ለኔ ሲል ነው እንዴ ከበእሎ ጋ ቲያዘጠዝጥ የዋለውን" በማለት ከእህል—ውሃ አቅም ያሳንሱበታል ። በእንዲህ ያለው ጊዜ "ዕድሜ ለልኬ" ብሎ ምንዳዬ ቤት ዘው ይላል ።

ምንዳዬ ቀስ በቀስ የቸርነትን ችግርና ታማኝነት ለቀኛዝማች አስረድቶ ጉልማ አሰጠው ።

# ምዕራፍ ሐያ ሰባት

የአፈሣ ከቤት እየራቀና ወሬው እየጠፋ መሔድ ከአስካደች ይልቅ ልኬለሽን አሥጋት ። "ይኸ ሰው እንዲህ አምርሮ ከጠፋ ነገር አለው ማለት ነው ። ምነው እንዲያ የጠላኋቸው ሰውዬ ፣ ይኸነዬ በመጡና ይዘውልኝ በሔዱ ። አፈሣ ገደለውም አስገደለውም የሞት ሞት ነው ። እዚያው ሔዶ ቢንገላታ ይሻላል" እያለች ትሸበራለች ።

ምንዳዬ የመበቃቀልን ጠንቅ በሚያስቀር የአካባቢ እርቅ ፣ ሿራን እንዳይሻገር ከባላገሮቹ ጋር እንዳደረገው የክልል ገደብ ፣ አፈሣም በገዛ ፍርሃቱ የከለለውን ድንበር ዐልፎ ወደ ሣር—እምባ ላለመዝለቅ አገር ቆርሮ አደፈጠ ። የሆነው እስቲሆን አዝመራውን ሰብስቦ ምር ቱን ጎተራ እሚከትለት ዘመድ አገኘ ። ሚስቱንም ጎራ ዞሮ አለሁልሽ አላት ።

ያለ ሥራ ውሎ እማያውቀውና ከሰው መዓድ ቆርሶ መብላት ያልለመደው እጁ ፣ ቦዝኖ እየዋለ 'ኑ ግቡ ገበታ ቀርቧል' እየተባለ መጠራቱ ክፉኛ አበሳጨው ።

አሞቱ የመረረ ወኔ አጎነቆለ ። "ነገሩን ከወዲያ ወዲህ አሳክራ ለዚህ ያበቃችኝ እሷ ናት" በማለት ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱን ያማር ራል ። አገልግል ጥሎ መሸሹን ግን ፣ "ደህና ቦታ ላይ መትቶት ቢሆን ኖሮ ይኸ ሁሉ ጣጣ አይመጣም ነበር" በማለት ፍርሃቱን እያድበሰ በሰ ራሱን ይሸነግላል ።

ከሬሣ ጠባቂዎች ጋር አብሮ ያደረለት ሌሊት ፣ ተረተኛው ሽማ ግሌ ስለ አንድ ፈሪ ሰው ተርተው እንደ ፈጸሙ "ጥንቸል አንበሳ ሆነ ፣ ቢዘል እማጀት ፣ ቢወጋ ምንቸት" በማለት የተናገሩት ምሳሌ ከራሱ ሁኔታ ጋር እየተመሳሰለ አስቸገረው ። አንዳንድ ጊዜ ብቻውን ሲያስብ ፣ ከሆነለት በግሉ ፣ አለበለዚያም አንድ ታማኝ ሰው ፈልጎ ምንዳዬን ለመግደልና ለማስገደል ይወስንና ፣ እንደገና ደግሞ ሆዱ ይባባና ሥጋትና ፍርሃቱ ይቀራመቱታል ። ሐሳቡ እየተለዋወጠና ጥርጣሬው እየተዘበ ራረቀ ስለሚያስቸግረው ፣ ጨርቁን ያልጣለ ንክ መሰለ ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፣ "እንዲህ ያለውን መዘዘኛ በሽማግሌ መታረቅም እኮ የማሸነፍ ያክል ይብቃው ። ጌታ ፈርዶብኝና ሰይጣን አሳስቶኝ አጥፍቻለሁ ። ሽማግሌ አቅሜን አይቶ በወሰነ እከሳለሁ ብዬ ለምድር — ለሰማይ

"ይኸን መላ ነው ብለህ ልብህን አታክር ። ይልቅዬ ከበረታህ በየትም—በየትም ብለን ከባላጋሮቹ ጋ እንነጋገርና እምናደርገውን እናርጊ ለማይሆን ነገር ንብረክን አታባህን ። ቀስ ብለው ታማክሯቸው እነሱስ ቢሆኑ ዝም እሚሉ መሰለህ ። ውስጥ ውስጡን እየነደዳቸው መቆጨታቸው አይቀርም" አሉት ።

በመጨረሻም ከባላንጦቹ ጋር ዶልቶ ፣ ምንዳዬን ለመግደል ፣ ካልተሳካም በዚህም በዚያም አዋክቦ አገር ጥሎ እንዲጠፋ የሚደረግ በትን ዘዴ ተነጋግረው እንዳበቁ ፣ የአፈሣ ልብ ዳግመኛ የተንኮል ጥንስስ ጠንስሳ ወደ ቤት ገቡ ። እፎይ ብሎ አደረ ።



## ምዕራፍ ሐያ ስምንት

ወይዘሮ ደጆ—ይጥኑ ፣ የአካባቢያቸውን ቤቶች አለባበስ በመመልከት 'ቱሉ ቶሎ ልበሽ' የተባሉ ይመስል ፣ ሦስት ቅያሪ ልብሶች ገዝተው ሲለዋውጡ ፣ የአካል ፣ የዳሌና የቂጣቸው ቅርፅ አብሮ የሚለዋወጥ መሰለ ። ቀኛዝማች የቤትዮዋን የእግር አጣጣልና አነጣሥ ተከትሎ ሽቅብ ቁልቁል የሚርገፈገፈውን የወገብ በታች መቀንዘሪያ እያዩ ቢጎመዡም እንደ ቀድሞው ፋታ አጡ ።

"እንኳንም ትቻት ያልመጣሁ ፣ ይኸነዬ አዳሜ ቀኛዝማች ባገር የሉም እያለ ያማግጧት ነበር" በማለት ራሳቸው በሚፈጥሯቸው ተቀናቃኞች ይቀናሉ ። ባስ ሲልባቸውም ፣ የተለያዩ የማጀቴ ወንዶችን ይወሽሙላቸዋል ። በመጨረሻ ግን ፣ እንደውኑ ዓለም ፍላጎታቸው ፣ ሁሉንም ገፈታትረው የግላቸው ያደርጓቸዋል ። እንደ ምኞታቸውማ ቢሆን ኖሮ የሚፈልጓቸውን ቤቶች እንደ ከብት አንድ በረት ውስጥ አጉረው ሲያስፈልግ ፣ ሲያስፈልግ በየተራ እያስጠሩ የልባቸውን ለማድረስ ምንኛ ስፊውን በረት ባስከለሉ ነበር ።

የቀኛዝማች በላይነህ ታፈስ ሕይወት ወደ አዲስ የኑሮ ክልል በመግባቷ ፣ የማያውቋት ጉዳይ እየበዛ ፣ ከራሳቸው ጋር የሚያነጻጽሯቸው ሰዎች በልዩ ልዩ ሁኔታዎች እየበለጧቸው ፣ አንዱን ሲያጡኑና ሌላውን ሲከተሉ ኑሮ ዐይን አዋጅ ሆነባቸው ። ምንም እንኳ በአመለካከትና አንድን ፍሬ ሐሳብ አጣጥሞ በመገንዘብ ረገድ ከሌሎቹ እንደራሴዎች እጅግም ባይለዩም ፣ "ካንዳንዶቹስ እሻላለሁ" የሚለው የግል ግምታቸው ግን ያሰቡትን ያህል አልነበረም ። ሆኖም ትክክለኛ ችሎታቸውን ለመገምገም ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም ። "አዳሜ እናቱ ሆድ አልተማረው ፣ እኔ አብዛኛው እድገቴ በግብርና ነው ። ነገር ሳደራና ስሸምን አልኖርኩ" ብለው ብልሃት አበጁ ። ይኸውም ልዩ ልዩ ሐሳቦችንና ጉዳዮችን ለመረዳት ካንዳንድ እንደራሴዎች ጋር መተዋወቅንና አብሮ መዟወርን አዘወተሩ ። በዚህ ምክንያትም ከሚስትና ከቅምጣቸው ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ እያደር ተጣበበ ።

ምንም እንኳ የወራቱ ማነስ ለትዝብት ባያበቃም ፣ በሁለቱም ቤቶች ውስጥ ተቀብሮ የኖረው ቅናትና ፉክክር በማገርሸቱ ፣ የከተማው ግብግብ ተጀመረ ።

# ምዕራፍ ሐያ ዘጠኝ

ቀኛዝማች ፣ የምክር ቤቱን የስብሰባ ደንብና ሥነ—ሥርዓት ፣ አርፍዶ መግባትን ፣ ለፕሬዚዳንቱና ለዓቃቤ—ንባዔው ነገር በሰበብ ባስባቡ መቅረትን ተላመዱት ። ሁሉም የየራሱን ኑሮ ለመገንባት የሚያደርገውን መደጋገፍና ትንቅንቅ ፣ በውጣ—ውረዱ ወቅት የሚውጠነጠነውን ብልሃት ፣ አንዱ በሌላው ላይ ተፈናጦ ሲንጠራራና ሲጨብጥ የሚፈጸመውን ግፊያና ትርምስ በሚገባ አስተዋሉ ። እሳቸውም ነባር የገጠር ልምዳቸውንና ከአዲስ አበባ ወዳጆቻቸው ያገኙትን ምክር አጣምረው ተቀላቀሉ ። ሆኖም ገና ተደላድለው ሳይቆሙ የገጠር ድግስ ውጣ—ውረድ ጣልቃ ገብቶ አዲሱን ጥረታቸውን እንዳያደክምባቸው በማሰብ ፣ ለአያሌ ዓመታት ያስለመዱትን የኅዳር ሚካኤልን ድግስ በሥራ ብዛት ምክንያት ወደ ሰኔ ማዛወራቸውን ለንስሐ አባታቸው በደብዳቤ ገልጸው ነበር ።

ሆኖም ሐሳቤን የሚፃረር ነገር ይመጣል ብለው እንኳ ሳይጠራጠሩ ፣ መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ የሚካኤልን ጉዳይ አስቀድመው ፣ እንጦጦ ማርያምን አነግሣለሁ በሚል ምክንያት ሳይታሰቡ ከአባ ተክለ አብ ጋር ከተፍ አሉ ።

"የለም ፣ የለም " አሉ አባ ተክለአብ ። "እግዚአብሔርንና ቅዱሳን መላእክትን መሸንገል አይገባም ። በዕድሚያችሁ ላይ አንዲት ደቂቃ መጨመርና መቀነስ አትችሉም ማለቱ ለምንድን ነው? እኛ ለእሱ ቀጠሮ ሰጪዎች መሆን እንደማንችል ሲገልጽልን እኮ ነው" አሉ።

"ምን ቢያቀብጠኝ! ሸንገላኮ አይደለም አባቴ ፣ ቀኑን መለወጤ፣ ድግሱን በሰፊው ለማዘጋጀትና ስለቱን በወጉ አጠናቅቄ ለማግባት ነው" አሉ ቀኛዝማች ። በልባቸው ግን ፣ 'እሱ በሕልሜ እንኳ ያልተቆጣኝን ፣ የነኝህ ምን ይባላል' እያሉ ። በቀላሉ እንደማይላቀቁ ግን ገብቷቸዋል ።

"እማይሆነውን! እረ በሊቀ—መላኩ! እኛ እንዳስፈለገን የምንል ከሆነማ ፣ ምኑን ለጌታ ተገዛነው? ስለትን በዕለቱ ፣ ጸሎትን በሰዓቱ ነው ። የኅዳር ሚካኤሉን ለሰኔ ፣ የጥር ሥላሴን ለሐምሌ ማዛወር የኛ ሥልጣን አይደለም ። የተለመደው ጊዜ በመተላለፉ ፣ ስንኳንና ቅዱስ ሚካኤልን እኛንም አሳዝኖናል ። የተቸገረና ሐሳቡ ያልተፈጸመለት ሰው ፣ ጉዳዩን

የዝምድናቸውን ደረጃና አስተዳደጓን ረጋ ብለው በጉራ እየኳኳሉ ከተናገሩ በኋላ፥ "አንድ አግብታ ፈታለይ" አሉ ሴትዮዋ።

"በምን ምክንያት ነበር የተፋታቺው? ቆንጆ ሴት'ኮ አትታመንም። የዚያ አገር ሰዎች ሴቱም ወንዱም ቀናተኞች ናቸው" አሉ አቶ ወርቅነህ።

"እሷ እቴ! የቆንጆ እመቤት ነች። በዚህ በዚህስ አትጠረጠርም። የሠራባትም አትመስል። የዚህ ዓመል ቢኖራትማ ስንቱ ነበር ይረግጠው እስቲጠፋው ያንዣበበው። ባሏ የሚረባ ሰው አልነበረም መሰል፥ አይታና ታዝባ ንቃው ምንጥቅ አለች።"

"እንዴት?"

"ምን ታርገው? ወይ በርትቶ ካላረሰ፥ ወይ ከቆላ ደጋ ብሎ እንደሚነግዱት ካልነገደ፥ ወጣ ገባ እያለ ዐይንና ከናፍሯን ቢያያት ምን ያረግላታል? ባንዲት ቀሚስ ተጣብቃ እስከ መቼ፥ ጥጡም ቢሆን ተሸምቶ ነው። ወይ ቁና ባኤላ ወይ ቁና ገብስ ታልሰጡ፥ አንድ ነጥር ጥጥ አይገኝም። እዚያው ቢጤህን ፈልግ ብላ ጥላለት ውልቅ አለቻ።"

"እ! ኮብልላ ነዋ?"

"ኧረ እሷ እቴ! —— ምን አስኮበለላት!"

"አሁንም ከነፈርማዋ ነች ማለት ነው?"

"እሱማ አንገራግሮ ነበር፥ በጭቃ ሹም ተገዶ ነው የቀደደላት።"

"በኋላስ ዝም አለ? ልተናኮልም አላለ?"

"ኧረ ንቪ ሰዎች! እተናኮላለሁ ቢል ማባቱ ይለቀዋል? እስና ዘራለሁ ካለም፥ ከሰማይ ወፍ የሚያረግፉ ወንድሞች አሏት። እኔም ጋ የተጠጋችው እሷው ትሻለኛለች በማለትና ቀኛማችንም ትልእትንሹ ስለሚያከብራቸው፥ ለክብርቱ ብላ ነወዪ ዘመድስ ሞልቷታል" ብለው ቆጠብ ያለ ሣቅ ሣቁ። ጉዳዩ ገፍቶ መምጣቱ ገብቷቸዋል።

"የጨዋታችንን አዝማሚያ ሳታውቂው አልቀረሽም" አሉ አቶ ወርቅነህ ባለቤታቸውንና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑን እያዩ። "ወጣ—ገባ ሲል ጉዳዩ ገብቶሽ ይሆናል። የእህል ውሃ ነገር አይታወቅም። ሰው ውሃ አጣጩን አያጣም። ሁለቱም አላሰቡት። ያንዳንዱ ሰው ዕድል ገና እንጥስ ሲል ነው የሚያምርለት። እንደምታዪው ስንትና ስንት ሥልጡንና የተማሩ የከተማ ሴቶች ሞልተው ተርፈው ሳለ፥ ገና ምንንም ምንንም ያላየችው ባላገር እንዲህ ያለ ድንቅ ዕድል ሲገጥማት በጣም ደስ ይላል። ቀን ይውጣልሽ ሲላት ነው። ዐይን የሚያሹበት ቤት



አይምሰልሽ። ካወቀችበትና ነቃ—ነቃ ካለች ሰው ሆነች ማለት ነው። እኔ ገና መጀመሪያ ሲነግረኝ፥ የሚቀልድ መስሎኝ ነበር። ይቺ ገና የምትበላው ብዙ እንጀራ አላት። 'አትሩጥ አንጋጥ' ይሉሻል እንዲህ ነው። እኔ ባልወልደውም የልጄ ያህል ነው" አሉ።

ሦስቱም ምሳ በልተው፥ በእግረ—ረጃጅም ሆደ ሰፊና አፈ—ጠባብ መለኪያ ኮኛክ ሲጠጡ፥ "ልጅቱም ብትሆን የምታስመሰግን ነች" አሉ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ፥ ፉት ያሉትን ኮኛክ ውጠው። "በያ ላይ ጥፍፍ ያለች የሰው ልጅ ነች። እስቲ ቀይ ዋል እደር በሉና ትታዘቡኛላችሁ፥ አሁን እንኳ ከምንየዋ የናንተን ልጆች ሥልጣኔ ልቅም አርጋ ይዛዋለች። ለያውም እኔ ፊት እየነሣኋት። ጥኢት ሰንበትበት ስትልማ ማንም አይታከላት። ያየችው ሁሉ አይጠፋትም። ለቀም ነው። አለመማሯን እትዩ። ልበ—ብሩህ ናት። ቀሚስ ያጠለቀችና መቀነት ያዞረች ሁሉ ሴት አይደለችም። ይቺ እኮ ካልመሰላት ወንዱ ሁሉ ወንድ አይመስላትም። እንዲህ የዋዛ፥ ነብር ነች! ይኸ ሞገስ ታዲያ እኔ ጋ እየመጣ፥ ወጣ—ገባ ሲል፥ ጠባዋን ሳያቅ ይናገራትና 'የሰው ሰው ታዋርድብኝ ይሆን ጌታዬ' እያልኩ ፍርያቴ አይጣል ነበር" ብለው ድጋሚ የተቀዳላቸውን ኮኛክ ጨለጡ።

"እውነትም ልበ ቅን ነች። ከስንት አንድ ነች እንዲህ በክብርት ደህና ባል የምታገኝ፥ የተማረ የከተማ ሰው የባላገር ሴት አይፈልግም። ደስ ካለችውም ላንድና ለሁለት ቀን ጉዳዩን ፈጽሞ ዞር በይ ይላታል" ብለው ወ/ሮ መንበረ ከሣቁ በኋላ፥ "ዘመዴ በመሆኑ ላስማምረው ብዬ ሳይሆን፥ እንዲህ እንደ ዘመኑ ሰው አይምሰልሁ። የዘመኑ ሰው ስንትና ስንት ዐመል አለበት መሰለሁ? አብሶማ የከተማ ወንዶች! አንቱም እያደር ትታዘቡኛላሁ። እንግዲህ ነገሩን ታነሣነው አይቀር፥ ግልጥልጥ አርገን ነው መነጋገር" አሉ ወደ ባለቤታቸው እያዩ። ባልዬው 'እውነትሽን ነው' ለማለት ራሳቸውን ሽቅብ ቁልቁል ነቀነቁ።

"ሁለተዬ አግብቶ ፈቷል፥ ይኸነዬ የትናየት በደረሰ! ባያድለው ነው። ያዲሳባ ሴቶች ምናቸውም፥ ምናቸውም አይታመን። እየዛቁ ቢሰጧቸው፥ በጎን ይቆነጥራሉ——" ብለው ንግግራቸውን ሳይጨርሱ፥

"ይቺ አፏም ላይ ማር አይሚሚባት፥ አትጠረጠጠርም፥ ለዚህስ እኔ አለሁ። ጥኢትም ቅር የሚለኝ ያው ኃይለኝነቷ ነውዪ፥ በስለትም አትገኝ። በያላይ ባለሙያ ነች። ወጡን የሠራችው፥ ጠላውን የጠመኀችው፥ እንጀራውን የጋገረችው እንደሁ —— ኧረ ተዉኝ እቴ! እኔማ ጥሎብኝ ስወዳት! ስንቷ እግሬ ላይ ስትነጠፍ፥ እሷን ይገፔ መምጣቴ በጠባዋና በሙያዋ ነው። በየህ ላይ ወዲያ — ወዲህ ወለም—ዘለም

# ምዕራፍ ሠላሳ ሁለት

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ "አልመጣም እንዴ? የታለ?" አሉ በቀስታ በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ ።

"መጥቷል እንዳ ነው ።"

"ምነዬ መጣ ልጄ?" ብለው ወደ ጓዳ ገቡ ።

"ገና ገባ ማለቱ ነው ። ጥኢት ቆየት ብሏል" ብላ 'ከፉ መታረሪያ እግር' አለች በልቧ ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱና አፈሣ ተሳስመው መደቡ ላይ ተቀመጡ ።

"እንዴት ብለህ በዛሬው ቀን መጣህ? ቴነግረኝ ከው አልኩ ።"

"መቼ ይሻል ይሆን ስል ሳእማማ ስነበትኩና ዛሬ ይሻላል ብዬ ብቅ አልኩ ። ቆይ ዛሬ ቆይ ነገ በማለት ነውዬ በማንቻውም ቀን እችል ነበር" አለ መድፈሩን ለመግለጽ ።

"አዬዬ! እንጃልህ? የዛሬን ይሻላል አንተ ታአለህ! እንደኔ እንደኔስ ——" ብለው ሳይጨርሱ ፣

"ኋላ እንዴት ይሁን ነው እምትዬውየ ይኸው ስንትና ስንትኤን አድፍጠን ጠበእነው ፣ ጠላትሽ እልም ይበል ፣ እልም አለ ። እኔ ምን እንደሚነግረው እንጃ ። ታዲያ እሱን እስተ መቼ መጣ አልመጣም ስንል እንከርማለን እቴዋ? ዛሬ ደሞ እንዲህ ሰዉ ተወዲያ—ወዲህ ጅር—ጅር ሲል የልብን ሠርቶ ሸተት ነው ደጉ —— ያምአደራህን ያልሸው ሰውዬ ፈራ መሰል —— እንደ ግመል ሽንት የኋሊት ሔደ ። እኔ አንቺ ብትዬና ደስ ይበልሽ ብዬ ነውዬ ፣ የሱን ሰውዬ ነገር አልወደድኩልሽም" አለ ጠበንጕውን እያሻሸና እያዟዟረ ። አስካደች ደገፍ ብላ በቁሟ ትሰማለች ።

"ማ?"

"ያ ጋሼ አስረስ ነዋ! —— እኔም እርም አይቀሬ ልበለውጂ ።"

"አዬዬ ምነው የሱን ነገር ብተወኝ ልጄ? 'ሰውን ማመን ቀብሮ ነው' አለች አሉ ቀበሮ ። ምነው እሱማ ይኸ ነገር የኋላ—ኋላ የተሰ

"እማደለሁ! ፈርቼ መሰለህ? ትወረውር ያዩኝና ይቆጡኛል ብዬ ነውዬ" ሲል የምንዳዬ ዐይን እንባ ከተረ ። አባት ቁልቁል ፣ ልጅ አንጋጦ እየተያዩ ፣

"ጎሽ! —— እንዳትፈራ !"

"እልፈራም እምፈራ መስሎህ ነበር?"

"ዐውቄ ነው ፣ የኔ ልጅ ፈሪ አይደለህም ። እንዲህ ጎበዝ ተሆን ከማ ጠበንጃ እሰጥሃለሁ" ብሎ አገላብጦ ስሞት ወደቤት ሲገባ "ደህና ዋላችሁ?" አለ ፊቱ እንደ ፈገገ ።

"እንዴት ዋልክ? በደህና ዋልክ?" አሉት ሁለቱም ኖር ብለው ።

"አባትና ልጅ ይኸን ያህል ወሬ ስታውሩ ሰው ዘወር ብላችሁም አታዩ?" አለ ቸርነት ።

"እንዴት ያለ ወሬ ይዘን ነበር ከዚያ ታች የጀመርን ስናወራ" አለና ምንዳዬ ጠበንጃውን ትራስጌ አስቀምጦ ከቸርነት ጐን ተቀመጠ ። አሻጋሪ የሸክናውን ውሃ በጣቶቹ አፈን አድርጎ በቀጭኗ በማንቆርቆር እንዳስታጠበው ልኬለሽ ምግብ ጨመረችላቸው ።

"በጎ ዋልኮይ? ቀለል ብሎህ ዋለ? አይ የኔ ነገር ፣ ሆዴ ባሰብኽኮ ! ሰው ይደክመዋልን እማያቁ ሰውዬ ከወዲያ ወዲህ ሲያንገላቱን ውለው" ብሎ ባዘኔታ አየው ።

"አሁንስ ደህና ነኝ ። ጢት ነበር ይኸን መኻል አናቴን በቅቶ የያዘኝ ። አሁንማ ቀለል ብሎኛል ። እህሉ አልበላልህ ብሎኝ ውሎ ፣ ይኸው አሁን ገና ወዳፌ አልኩ" ብሎ ልኬለሽን አያት ።

"እኔማ ከስንቱ ኮቸሮ አፍ ጋ የዋልኩ መሰለህ? ወሬአቸው ለቁ የለው ፣ ጨዋታቸው አይጥም ።"

"እንዲህ ታንዳንደዬ'ንኳ ማጉደሌን ዕወቀውዬ! 'በእጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል' ነው እሚሉት" ብሎ አሣቀው ።

"ምን ታረግ? ሰው እኮ እሚያመሰግነው ሰው ሲያጣ ራሱን ያመ ሰግናል ። ይልቅ ምን ሆነህ ነው ያመመህ? ይኸነዬ አረጋሽ ታሁን አሁን መጣች እያልክ ብርድ ላይ ተቀምጠህ ስትንቃቃ ፣ ይኸ የጠር ውርጭ ሳይታወቅህ ጠብሰቆ ጥሎህ ነው" ብሎ ከት ብሎ ሣቀና ፣ "ከጠራራ ጂኒ እኮ የውድቅት ጂኒ ይብሳል አሉ ! አጣፍሮህ እንዳ ይሆን" ብሎ ተንከተከተ ።



"ኤ—ድ! አንተ ደሞ ትለው አታጣም? የምን ጂኒ አመጣህብኝ? እኔን ያጣፈረ አንተንስ የት ያጣሃል?"

"እኔ ምን ፍለጋ ስሔድ ልጄ? ሁሉም መገናኛ መገናኛ አለው።"

"ምነው ታዲያ አንተን ያሾሾ ወንዝ ጂኒ አላጣፈረህ? አሁን ተዚያ እሚብስ አለ? እምን እንደምረግጥ አላእም ነበር አላልከኝም? የረሳሁልህ መሰሎሃል?" አለ በቀስታ እየሣቀ ።

"ያንተኮ ሥጋትም አለበት ። እኔ ማንን እሠጋለሁ ። የቤቶቼም ቢሆኑ ያቁኛል? አጠይቃትም እንዴ? እኔ እንዳንተና እንደ ቆጥህ ሰባንን አላድር! ያንተ ደሞ ስንቱ ይወራል" ብሎ ሣቀ ።

"ምነው ብተወው ልጄ? በሽታውን ቢያዳምጥበት ፣ አንተ እኮ!" ስትል ልኬለሽ ፣ ካፏ ነጥቆ ፣

"ኧረ ቆይ ተይው! የረሳሁለት መስሎታል — —" አለ ቸርነት

"ለምን እኔ አሳምሬ አልነግርህም? ይኸነዬኮ አልነገረህም ይሆ ናል? አንተ ብቻ የራስ የራስክን — —"

"አንቺ ደሞ ምን ልትዬ ነው? መረዳቱ ነው? አቤት!" አለ ምንዳዬ ቢወራበት እየተደሰተ ።

"ምነው አንድ ኸንለታ ላይን ያዝ እንዳደረገ ሳባይኔ ድረስ አስልተህ መጥተህ — —" ብላ ስትጀምር ፣

"ሳባይኔ ሩቅ እንዳይመስልህ — —"

"የሰው ወሬ አታቆርፍድ! ዐቀዋለሁ ።"

"በሉ ይሁንላችሁ ፣ ዛሬ በኔ ላይ አብራችኋል ።"

"አንተ እህ በል ልጄ ፣ — — እቴዋ ዘርትሁን ቤት ደርሼ ትመ ለስ ፣ ሰው የለም ይልልህና ፣ 'ልኬ! አንቺ ልኬ!' እያለ ጨበጥ ቲያረ ገኝ ጊዜ ደንግጬ ጩኸቴን ለቀኩበት ። ለካ አብዬ ታዬ ሰምቶልህ ኖሮ 'ምንድን ነው? ማነህ አንተ?' ብሎ ከመጣራቱ ፣ መጣብኝ ፣ ደረሰብኝ ይልልህና የፍሪያቱ ፍሪያት መንገዱን ጥሎ በጉራንጉር ውስጥ ———"

"ጐበዝ ተሆን አይከተለኝም ኖሯል?" አለ ምንዳዬ እየተንከተከተ።

"የተገላቢጦሹን ተወውና ፣ ጐበዝ ተሆንክ ቆመህ አጠብቅውም ኖሯል? ደሞ አንድ ቀን መሽቶብኝ ውሃ ወርጄ ስመለስ ፣ እኋላ—እኋላዬ እያለ አላስኬድ ቲለኝ ፣ ዝም ብዬ ስሔድ—ስሔድ ማንገቻውን ጥርቅም አርጎ ያዘና — —

ሉዬ ፥ አይመጡ ። አግባና ውለድ ፡ ወንድም ይሆንሃል" አሉና የተቀበሉትን ቃሙ ። በተደጋጋሚ ተነጋግረው ተስማሙ ። ሁለቱም ደስ አላቸው ። የወደዳትን ልጅ ባይነግራቸውም ቀስ ብለው ሰልለውና ጓደኞቹን ጠይቀው ዐውቀዋታል ። ወደዋታል ።

አንድ ቀን ማታ ራት ሲበሉ ፥ የተለመደው የጋብቻ ጥያቄ ቀረበ። ምንዳዬ አንገቱን ሰበር አድርጎ ፤

"ሳባይኔ ያብዬ ከተማ ልጅ ብትሆን ምን ይመስልሻል?" አላቸው ።

"የትኛዋ?"

"ትልኡዋማ አግብታለይ ። አንድ ናት እቤት ያለችው" አለ ቀና ብሎ ።

"በምን አየሃት ልጄ! እኔም እሷን ነበር ያሰብኩልህ ። ጥሎብኝ ፥ ውቃቢ —አምላኬ ይወዳታል ። በዚህ በኛ ደጅ ወደ ተክልዬ ስትሔድ፥ ጉትት አርገሽ አስቀሪያት አስቀሪያት ይለኛል ። ማለፊያ ፥ አንገተ— ሰባራ ልጅ ነች" አሉት ።

አጐቱና ሌሎች ሁለት ሽማግሌዎች ተጨምረው አቶ ከተማ ቤት ሽምግልና ተላኩ ። በሁለተኛው ቀጠሮ 'ይሁን' ተባሉ ። ቃል አስረው የተመለሱ ዕለት እናትና ልጅ ፈነጠዙ ።

ያቺ ባገኛት ቁጥር ውሃ የያዘ ገንቦዋንና እንስራቷን ፥ የግድ ተቀብሎ አቀበት ቁልቁለቱን የሸኛት ፥ እንጨት አሳብሮና ተሸክሞ የወሰደላት ፥ እያችሁብኝ ብሎ ዱላ የተማዘዘባት ፥ የቀልቡ ማረፊያና የልቡ መርኪያ የሆነችው ልኬለሽ ግን ፥ መታጨቷንም ይሁን ለባል መሰጠቷን አላወቀችም ።

ለጋብቻ የተስማሙበት የመጀመሪያ ዓመት ፥ "የዘንድሮ መኸር አላስደሰተም ፥ እንኳን ለልጅ መዳሪያ ለቀለብም አያቢቃ" በሚል በልኬለሽ አባት ችግር ተላለፈ ። በሁለተኛው ዓመትም ዋናው ሳቢ በሬአቸው ከበሬ ጋ ሲዋጋ ገደል ገብቶ በመሞቱና የመቀናጆ አዝመራም የማያወላዳ በመሆኑ በድጋሚ ሳይሳካ ቀረ ። እናትና ልጅ መክረው፥ ሽማግሌዎች እንደገና ተላኩ ።

"ተናንተ ፈቃድ አንወጣም ብለን ፥ ይኸው ድፍን ሁለት ዓመት ዐለፈ ። እናንተም ወዳችሁ አይዶለም ። ችግርና እክል እማይገባበት ቤት የለም ። እየሁላችን ጋ አለ ። ታዲያ በዚህ መኻል ደሞ ልጆቹ አጉል ሆኑብን ፥ ሰው መቼም ቲኖረውና እጁ ቲሞላ ነው በጅጉ ጠምቆ ፥ ጋግሮና አርዶ ጉዳዩን እሚያወጣው ። ተሌለ ምን ይደረጋል ። እንደ



ጊዜውና እንደ ወራቱ እየታየ ደሞ ባቅም—ባቅም ይደረጋል ። ይኸ ልጅ 'ዘንድሮን አታሳልፉብኝ' ብሏል ። 'ባይሆን እኔም ያእሚን እደግፋቸዋለሁ ። እናቴም እየደከማት ነው' ብሎ ልኮናል" አሉ ከተላኩት ሽማግሌዎች መኻል አንዱ ነገሩን ሲያጠቃልሉ ።

"እኔስ ደስ ቢለኝ መች ጠላሁ! ካምናው ዘንድሮ ፥ ከዘንድሮ ለከርሞ ይሻል ይሆን ስል ባናት ባናቱ ይመጣብኛል ። እኔስ መቼ አጣሁት ። ለዚያውም እናንተ ሆናችሁ ነው ። እሱም እምንገድ ባየኝና ባገኘኝ ቁጥር ተሳቆ ሞተ! ምናባቴን ሳርግ ብላችሁ ነው ። ተልጆቼ መኻል እምወደው እሷን ነው ። ዐይኔ ነች ። ለሷ ያልሆነ ለማን ሊሆንኝ ነበር ። እኔ እንግዲህ ተዚህ ወዲያ ምንም አላስቸግራችሁ ። ይህን አረጋለሁ ፥ ይህን እፈጥምበታለሁ የምለውም አቅም የለኝ ። እሷም ዕድሏ እስቲቀናና ቀን እስቲወጣልን ትቆይ ፥ እናንተም እንደ ወደዳችሁ አርጉ" አሉ የልኬለሽ አባት ፥ ያልታሰበ እጦት በሰበረው አንደበት ።

የአባትዬው መልስ ለምንዳዬ ሽማግሌዎች አጥጋቢ አማራጭ በመሆኑ ደስ ብሏቸው ተመለሱ ።

"ምነው ይኸን መልስ አምና በሰጡ ኖሮ! ወይ ነዶ!" አለ ምንዳዬ አንድ ዓመት በከንቱ አለፈብኝ ብሎ ።

ምንዳዬና ሽማግሌዎቹ ፥ ባገሩ ባህል መሠረት እርስ በርስ መክረው ተስማሙ ። የልኬለሽን እናት አነጋገሯቸው ። እናትዬዋም ጉዳዩን ካሰላሰሉ በኋላ ፥ "እምቢ ብልስ ምን መላ አለው?" ብለው በነገሩ ተስማሙ ።

የምንዳዬ እናትና ጐረቤቶቻቸው የድግሱን ሥራ በድብቅ ተያያዙት ። የእንጀራ እህሉ ማጀቴ ውሃ—ወፍጮ ተፈጨ ። የጠላ እህሉ ተዘጋጀ ። ቀኑ ተወስኖ መሰናዶው እንደ ተጠናቀቀ ፥ ሁለቱ ሽማግሌዎች እንደገና የልኬለሽን እናት አነጋገሯቸው ።

"በየት በኩል ይሻላል?" አሉ እናቷ ትክዝ ብለው ።

"ጉባ አክስትሽ ጋ ልላክሽ ብትሏትስ?"

"ከየቱ? በዚያስ አይሆንም! ትደነግጥብኛለች" አሉ እንባቸው እየመጣ ።

"ቁቁ ማለቷና መደንገጧማ የት ይቀራል? ይኸን አጣነው ብለሽ ነው?" አሉ አንዱ ሽማግሌ ። በመጨረሻ ባንድ ብልሃት ላይ ተግባቡ ። ይኸውም ልኬለሽን ከአንዷት ጓደኛዋና ከሌላ የጐረቤት ሴት ጋር

"ጤናም አልያዛት እንዴ ? በይ ልሒድልሽ እቴ ! ባልና ሚስት ታንድ ምንድን ነበር ይቀዳል እሚሉት ? — — ያኗትን ትታ ያላ ኗትን" ብሎ ብድግ አለ ።

"ካንድ ወንዝ ይቀዳል ነው ። መቼም ያለኔ አይሆንልህ" ብሎ ጣልቃ ገባና ፣ "ምንድነው ነገሩ? ለኔ ንገሩኝና ልገላግላችሁ ። ባይሆን የዳኝነቱን ትከፍላላችሁ ።"

"ማ ቢያቀምስህ? የምን ጠጋ—ጠጋ ነው — — — እኔና እሱ እንተዋወአለን!" ብላ ቸርነትን ጐትታ አስቀመጠችው ። እንደ ቆመ ችም ፣ "ጥሩ ነገር በማድረግህ ምን አስፈራህ? እንዲያውም ባንተ እጅ ያምራል ። እኔ በናንተ መኻል ምን ዶለኝ ።"

"ምንድነው ነገሩ? ይኸነዬ እኮ አርቲ—ቡርቲ ይሆናል — —"

"መስሎሃል? ምንም ይሁን ምን ፣ ምን አስቸኮለህ? — — ቀስ ብለን ኮርተን" አለች እየሣቀች ።

"አይ ያንቺ ነገር! ደሞ አደራሽን ስል መዋሌ ። ለዚህ—ለዚ ህማ ምን አለፋፋኝ" አለ ቸርነት ።

"እንዲያውም አልሰማ! ለምናችሁ ትነግሩኝ የለ! — — ያለኔ አይሆንላችሁ" ብሎ ምንዳዬ ሣቀ ።

"እንዴት ተጎዳን እቴ? አንተ አልሰማ አልክና ጉዳያችን አይነ ቅዝ ፣ እኛም ሳናስደገድግ አንነግር" አለችው ።

"ታዲያ ምን ልበል? እንዳንዳንደዬው የነቀኛማይ ወሬ ነገራች ሁን ጥፍትፍት ስታረጉት ፣ አቄላችሁኝኮ!"

"ይልቅዬ ቀልድህን ትተህ ፣ የምነግርህን እህ በልና —— እሺ በለኝ!"

"ብያለኋ! ያለኔ አይሆንላችሁ ። ለእሺውም ፣ ለእምቢውም እስቲ መጀመሪያ ይሰማ ነገሩ?"

"እምቢ ብሎ ነገርማ የታል? እማይባለውን! ለዚያውም ቢሆን በመጀመሪያ ልኬለሽ ሙች ብለህልኝ ነው ። እንዲህ በዋዛ እንላቀቅ መስሎሃል!" ስትል ቸርነት ቀና ብሎ አያት ።

"ወይ ጣጣዬ! ነገሩን ሳላኸው ፣ ሙችና አትሙቺን ምን አመ ጣው?"

"ነገሩማ ይነገርሃል — — — የት ይቀራል ።"



"አንትል አስምለሽኝ የማይሆን ነገር ተሆነስ? ይኸን እያስማሉ መንገር ተውኝ አላልኩምይ!"

"እዩ! ምነው በቁሜ ገበያ ባታወርዱኝ ። አሁን ማ ይሙት ቸርነት ቢጠይቅህ እምቢ ትለዋለህ?" አለች ኮስተር ብላ ።

"እሱ'ስ እውነሽን ነው እምቢ አልለውም ። ታዲያ እምቢ አይ ልም እያላችሁ እንደ ሞኝ — — —"

"እኛ ሞኝ ነህ አላልንም! ያውም አንተን? ምን ቅብጥ ቢያረገን! ይልቅዬ በይ ሙች በልና ይነገርህ ። ቀላል መስሎታል?"

"ግድየለሽም ስልሽ!"

"አይይይ! ምንድነው እቴ ምንችክ ማለት!"

"በይ ደስ ይበልሽ! እላለሁ ።"

"እላለሁ ከማለት አትለውም?"

"ልኬ ሙች!" አላት በቁም ነገር እየሣቀ ።

የቸርነት ልብ በደስታ ተከብባ ነፍሱ ተነፈሰች ።

"እንግዲያውማ ቸርነት እንዲህ አረገልህ — —" ከማለቷ ሁለ ቱም ትኩር ብለው አዩዋት ።

"ምን አረገ ልጇ?" አላት ቶሎ ብሎ ።

"ከሰውዬው ጋ አዲሳባ ልትሔድ ነው ማለትን ተሰማ ጀምሮ እብሶ ይኸን ሰሞን ግራ ግብት ብሎታል ። ስማይ መሬቱ ድፍት እሚ ልብት ነው የመሰለው ። ከኔ ብሶልሃል ። ዛሬ ሳያመው የውሸቱን አመ መኝ ይልልህና ያቺኑ ጤፍና ቀጠጦውን (ማሽላ) ሸጥ አርጎ ፣ ለምንዳ ስጪልኝ — — —" ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ እንባዋ ዝርግፍ አለ ። ቸርነት አቀረቀረ ።

"ተቀበልሽው እንዴ ?" አለ አሻቅቦ እያየ በዝግ ገጽታ ።

"እሱንማ ልነግርህ አደል? አይሆንም ብዬ ብለው ብሠራው ፣ እምቢ አለኝ ። እምቢ ሲለኝ ምን ላርግ ትለኛለህ ?" ብላ ወደ ጓዳ ስትገባ ሁለቱም ባይናቸው ተከተሏት ። እንደ ተመለሰችም ምንዳዬ ሳያስበው የተጠቀለለውን ገንዘብ አስጨበጠችው ። ደነገጠ ። ቀለላት ።

ምንዳዬ በሐሳብ ፣ ቸርነት በደስታ ተዋጡ ።

“እስቲ ና ቁጭ እንበልና ንገረኝ?” አለ ምንዳዬ እንገቱን ዘለስ አድርጎ ።

“ምኑን ልንገርህ? ለኔ እሚነገረውን ለሌላ ልንገር ስትል!”

“እስቲ አንዳፍታ ቁጭ በሉና ተነጋገሩ ። እሱም እንዳንተ ፈርቶ ነው ። ምነው እንደ ራስህ ብታየው” አለች ልኬለሽ ለማቀራረብ ።

“አንቺ ደሞ አታለባብሽለት ። የኔ ፍሪያት ሌላ ፣ ይሽ ሌላ ፣ እስቲ በይ ምንና ምኑ ይገናኛል? እኔ እንደናቴ ልጅ ሳየው እማደል ፣ እሱ እንደባዳ ያራቀኝ? እለያማ መች ሌላ ሰው ፈልግልኝ ይል ነበር? ሰው ተሚያምነው ባልንጀራው ምስጢሩን አይደብእም ። እኔ እያለሁ አንቺና ልጆቹ ጦማችሁን አታድሩ፣ እምቢ ይለኛል ብሎ ነው ሰው ማፈላለጉ ።”

“ቦጋለ ይሙት! ገና አሁን ነው ነገሩ የገባኝ! ፍቅርህን! እኔ ልሙትልህ ። ለምን ግልጥልጥ አርገህ አትነግረኝም ። ጥቅሙ ለማን ሆነና ነው? እሺ አንተ ባልክ ይሁን” አለና ከልኬለሽ ጋ ወደ መቀመጫው መለሰው ።

ቸርነት ሐሳቡን እጥር—ምጥን አድርጎ ገለጸለት ። ሣቀችባቸው ።

“ደስም አላለህ እንዴ?” አለው ቸርነት እየሣቀ ።

“እንዴት ብዬ ልንገርህ? የኛ የሰውዬ ተረት ትዝ ይልሃል?”

“የየቱ?”

“የሚሻእል ለት ማታ እኔና አንተን ያጫወቱን ።”

“እእእ! አባ ወርቅነህ ናቸዋ! ምን ብለው ነበር? ረሳሁት እኮ!”

“ሰውዬው አሉ ፣ አህያና በሬውን እየነዳ ተዱር ወደ ቤቱ ቲመለስ ፣ አፋፍ ላይ ይደርሳል አሉ ። በሬው ድንገት ይንሸራተትና ገደል መግባት ። ቁቂታውን ያቀልጠዋል ። ሰዎች ከያሉበት ተሯሩጠው ይደርሱና ፣ እንደ ምንም ተንፏቀው ወርደው ፣ ያንን ቲያጣጥር ያገኙትን በሬ ይባርኩታል ። ገፋፈው የቻሉትን ያህል ይበሉና ፣ የተቀረውን ቆራርጠው ፣ ታቹን በሜዳው ዞረው ያንን ያዋጡትን ሥጋ በበሬው ቆዳ ጠእለው አህያው ላይ ያጫጭኑታል ። መሽቶ ውርውር ሲል ፣ እቤቱ ሲደርስ ጥኢት ሲኸረው ፣ ወገቤን ልፈትሽ ይልና አህያዋ እየሔደች ከምንገድ ዳር ገለል ይላል ። ለካ የራበው ጅብ ገና ከጉሬው ወጥቶ ሱክ—ሱክ ይል ኖሮ ፣ አህያዋን ስታዘግም ያያታል ። ጠጋ ብሎ ሲመለከታት በቆዳ የተጠቀለለ ሥጋ ተጭናለች ። የልቡን ሲያገኝ ጊዜ



‘አንቺዬ! እንዲያው ለመሆኑ አሁን አንቺን ማ ብለው ይጠሩሻል? አንቺው ራስሽ ሥጋ ፣ የተጫንሽውም ሥጋ ፣ ተባረኪ! እሰዬው እሰይ!’ አላት አሉ” ብሎ ከት አለ ።

“እና የዚች ፍቺዋ ምን መሆኗ ነው?”

“እእ! እዩልኝ እንግዲህ! የልቤን የምኞቴን አገኘሁ ነዋ! ምን ቅሬታ አለ ፣ ሁለመናው አማረ ነዋ! አንተ እኔ አለሁ ስትለኝ ከዚህ ወዲያ ምን ይገኛል? አርሶ እሚያመርተው ቸሬ፣— ተቀባይዋ ልኬ ። ተየህ ወዲያ ምን ይምጣኝ” አለው ፊቱ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ።

“አይ የሷ ነገር ! እዚህ እበላይዋ የመሶቢት ሚካኤል እያለ ፣ በሉ እንግዲህ የዘንድሮን በርቱ ፣ ለከርሞ አዲስ አበባ ትማራላችሁ ፣ መሰንበቻውንም ልብስ እልክላችኋለሁ ። ደብተር መግዣ ያስፈልጋችኋል እንዴ?” ብለው ድፍን አምስት ብር አውጥተው ለትልቁ ሰጡትና ፣ “በጎ ነሽ ወይ? በደህና ሰነበሽ ወይ ብሎሻል በሏት ፣ ባለቤቷ የለም እንዴ? መቼም እሱ ዕረፍት እሚሉ ነገር አያውቅ ።”

“ከሚሴ እንደሔዱ አልመጡም” አለ ትልቁ ብሩን እያየ ።

እነ ቀኛዝማች ተመልሰው ሲገቡ ፣ ምንዳዬም ከተል ብሎ ገባ። አውቶቡሱ እንደናዳ ድንጋይ እየተንደረደረ ፣ ከካራቆሬ ወደ አጣዬ የሚወስደውን ጠመዝማዛ ቁልቁለት ተያያዘው ።

* * *

ምንደስይልና ዋሲሁን ፣ የቀኛዝማች የመጨረሻ ልጆቻቸው ሲሆኑ፣ ወንዶቹ እነርሱ ብቻ ናቸው ። ወይዘሮ እልፍ— ይከንዱ ከቀኛዝማች ስድስት ወልደው ፣ አራቱ ሴቶች ሲሆኑ አንዷ በሕፃንነቷ ስትሞት ፣ ሦስቱ ግን ፣ “የደምና ያጥንት አቻ ተገኘላቸው” እየተባለ በ13 እና በ14 ዓመታቸው አካባቢ ለባል ተሰጡ ። የቀኛዝማች ታናሽ እህት ወ/ሮ ጌጤነሽና ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ሲጀምር ጀምሮ እጅግም አይግባቡ ። ሁለቱም ቢጠየቁ ለወቀሳም ይሁን ለጥላቻ የሚበቃ ጉልህ ምክንያት አያቀርቡም ። ከአያሌ ዓመታት በፊት ግን ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ በተከታታይ ሴቶች በመውለዳቸው የተነሣ ፣ “ወንድሜን የስም ማስጠሪያ ወንድ ልጅ አሳጣቸው” ብለዋል ብለው ወሬ ስላደረሱላቸው ተቀይመዋቸው ኖረዋል ። በተጨማሪም ወ/ሮ ጌጤነሽ ማጀቴ ለጉዳይና ለገበያ ሲሔዱ በሹልክታ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ደረስ ይላሉ የሚል ያልተረጋገጠ ወሬ ከሰሙ ወዲህ ፣ “የባልን ዘመድ ሰብስቦ ነበር በእሳት መለብለብ” እያሉ ግንኙነታቸው ካንገት በላይ ሆነ ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ‘ያሉ’’ ወሬና አሉባልታ ስለነበር ሲገናኙም ሲለያዩም ይሳሳማሉ ። ደስ ሲላቸው ሞቅ ያለ ወሬ ያወራሉ ። እንደ ቀኛዝማች ሚስት ፍላጐት ቢሆን ልጆቹ ማጀቴ ቢማሩ ደስታቸው ነበር ። ነገር ግን ፣ ጣውንታቸውን ስለ ጠረጠሩና ፣ ‘በጅ—አዙር መዳኒት ብታቀምስብኝ ምን አባቴ እሆንዋለሁ’ በሚል ፍርሃት ፣ ልጆቹ አክስታቸው ዘንድ ተቀምጠው እንዲማሩ ተስማሙ ።

አባትዬው ግን ፣ “ጌጤነሽ የዋዛ ሴት አይደለችም ። ልጅ ማሳደግ ታውቃለች ። አንዳንድ ሰው ፣ ልጄን አሳድግልኝ ብለው ሲሰጡት ፣ ቀጥቶና ቆንጥጦ አያሳድግም ። ያባልገዋል። ልጆቿ ደብረ—ሲና ወጥተው



ለመማር የበቁት ፣ በሷ ብርታት ነው ። አባታቸውማ ሲበዛ የዋህ ነው። ሴቶቹንም ባለማስተማሯ ያንገበግባታል ። የኖረ ተማሪ ቤት ደግሞ ጥሩ ነው” በማለት ልጆቹን አልብሰውና ቀልበው ማስተማር ለሚችሉት ለወ/ሮ ጌጤነሽ በየጊዜው የልጆች ቀለብ እየተላከላቸው እንዲማሩ ተደረገ ። አራተኛና ሦስተኛ ክፍል ደርሰዋል ። የወ/ሮ ጌጤነሽ ባል ፣ ባንድ በኩል የሚያሳርሱ ፣ በሌላ በኩል ማር ፣ ቅቤና ጌሾ የሚነግዱ ሲሳይ ንብረታቸው የተትረፈረፈ ነው ።

* * *

አውቶቡሱ ፣ ሜዳ ሜዳውን ተግለብልቦና ቁልቁለቱን ተንደርድሮ ፣ ዳገት ሽቅብቱን እየተንጣጣና እየቃተተ ፣ አጣዬን ፣ ሰንበቴን ሸዋሮቢትንና አርማኒያን ዐልፎ አራት ሰዓት ላይ ደብረ—ሲና ገባ ። እነ ቀኛዝማች ከሾፌሩ ጋር ቡና ቤት ለመግባት መንገድ ሲጀምሩ ፣ ምንዳዬ ትዝ አላቸው ።

መንገደኞች በሁለቱ በሮች ሲወርዱ ፣ “ብዙ እንዳትቆዩ ! ቶሎ በልታችሁ ተመለሱ ! እዚህ እናንተን ሲጠብቅ እሚውል የለም ! ገና ስንትና ስንት መንገድ ነው እሚቀረን ፣ በጊዜ ካልገባን አዳሚ የዱርዬ መጫወቻ ትሆናለህ” አለ እበሩ ላይ ቆሞ የሚያስጠነቅቀው ጸጉረ—እንጭብር ቱታ ለባሽ ‘አውታንቲ’

“አንተ ማነህ ? እስቲ ምንዳዬ ብለህ ጥራልኝ እባክህ ?” አሉት ቀኛዝማች ።

ምንዳዬ ፈጠን ብሎ ወርዶ ስላልተከተላቸው ፣ ቅር ብሎት በሩ ላይ ደርሶ ነበርና ገና ከመናገራቸው ዱብ አለ ።

“ና እንጂ! ከእንግዲህ ወዲያኮ ሌላ ምሳ መብሊያ የለም” ብለው በፈገግታ አዩት ። ኃፍረትና የእንግድነት ስሜት እየተጫነው ፣ “እኔ እዚሁ እመኪናው ላይ እእያለሁ ፣ አንቱን እከተልሁ እንደሁዬ እሚበላማ ይሻለሁ” ብሎ አንገቱን ሰበር አደረገ ።

“መያዝህንማ መች አጣሁትና ፣ ና ግድ የለህም ፣ ከዚሁ አገር እየለመድክ ትሔዳለህ —— ና !” ብለውት መንገድ ሲቀጥሉ ፣ አለ አሳብ ተቀምጦ ያጨማደዳትን ዙሪያ ቅምቅም ፤ ወገበ ሽንሽን ፤ አፈ—ሰፊ ቁምጣ ሱሪውን እያወናወነና ፣ ከታጠበች ውላ ያደረች ነጠላውን አጣፍቶ ዱላውን እንደያዘ ከመንገድ በታች ወደሚገኝ ቡና ቤት ተከትሎ ገባ ፤ ቀደም ብሎ የገባው መንገደኛ እንደልቡ እያውካካ ይበላል፣

ይጠጣል ። እንቀኛዝማች ሲገቡ ደንገጥ ያለ ፣ ወይም ኖር ብሎ የተቀበለ ፣ ገለል ብሎ መንገድ የለቀቀ ፣ እንደ ሣር—እምባ ወይም እንደ ማጀቴ ሰዎች በተለየ አክብሮት እጅ የነሣ ሰው ባለማየቱ ምንዳዩ ተገረመ ።

ሾፌሩና እንቀኛዝማች በጠባብ ቁልቁለታማ የቤት ውስጥ መተላለፊያ አልፈው ፣ ግርግዳ ላይ በምስማር ተንጠልጥሎና ተለጥፎ የእጅ ውሃ ከሚያንቆረቁረው ገረወይና ላይ ተራ በተራ ሲታጠቡ ፣ ምንዳዩ ጠንቀቅ ብሎ ያያል ። እሱም ያንን ሲፋተግ የሚሰማ ሸካራ እጁን ታጠበ ። ሦስቱ ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ሲቀመጡ ፣ ምንዳዩ የት እንደሚቀመጥ ግራ ገብቶት አካባቢውን በኃፍረት እያየ ፣ “ምነው ባልመጣሁ ወንድሜ! እዚያው እንደ ቢጤቴ በበላሁ!” እያለ ቆም እንዳለ ፣ ቀኛዝማች ፣ “እህ? ታጠብክና መጣህ?” ብለው ባይናቸው ወንበር ፈለጉለትና “ያውልህ እዚያ ጋ ወንበር” ብለው በጣታቸው አሳዩት።

ግር እያለው ወንበሩ ጠርዝ ላይ ሲቀመጥ ፣ ዱላውን በጭኖቹ አጣብቆ በግራ እጁ አነቃት ። ትላንትና ከሣር—እምባ ወደ ማጀቴ ሲሔዱ ፣ ቸርነት ቀኛዝማችን ባለማጀቡ ዱላ ብቻ በመያዙና በኋላም ምንዳዩ ጠበንጃውን ሲሰጠው እሱም ዱላውን ተቀብሎ ስለነበር ፣ ዱላውን ሲያይ ባልንጀራው ትዝ አለው ። ወዲያው በጤፍ እንጀራ ሁለት ዓይነት የጾም ወጥ ፣ ሁለት ሾጣጣ ቃሪያ አስከትሎ ቀረበለት። ተስተካክሎ ሳይቀመጥ መብላት ጀመረ ።

ከነቀኛዝማች ጋር የተቀመጠው ሾፌር ፣ እግሩን አንፈራጦና ወደ ጠረጴዛው አቀርቅሮ በሚያበለጨልጭ ብርማ ማንኪያና ሹካ ፣ እያንዘላዘለና እየጠቀለለ ፣ ሹካውን ብድግ ያደርግና ወደሚዝለገለገው ነገር ጉንበስ—ጠጋ እያለ ሲበላ ፣ ምንዳዩ ድንገት ዐይኑን ወርወር ሲያደርግ በማየቱ ክው ብሎ ደነገጠና ፣ “አበስ ገበርኩ!” ብሎ ቶሎ ዘወር አለ። አንዳች ነገር ታይቶት ዝግንን—ስቅጥጥ አለው ። አንጀቱ ተቆለፈ ። “ምኑን ይሆን እያንዘላዘለ እሚበላው? እንካከተውብኝ ይሆን እምላኬ ?” ብሎ ብሽ አለው ። “እህሉ ላይ ምን አየህበት ቢሉኝስ? እነሱ የበሉትን እኔ መተየስ የሌላ ያስመስልብኝ የለ ?” በማለት እየተናነቀው በልቶ ቁራሽ ስትቀረው ፣ እጁን ወንበርና ጠረጴዛው እግር ላይ አባብሶ ተቀመጠ ። እንቀኛዝማች ሲታጠቡ ሲነሡም ፣ አብሮ ሔዶ ታጠበና ተመልሶ ሲወጣ ሾፌሩን ተጠየፈው ።

“በል ሒድ ግባ ፣ መጣን ——” አሉት በትዕዛዛዊ ድምፅ ። እጁን ዱላው ላይ እያሻሸ ወደ አውቶቡሱ ሲመለስ ፣ ቀደም ሲል ልብ ብሎ ያላያቸው መኪናዎች በዙበት ። ሙዝ ፣ ትርንጎ ፣ ሸንኮራ አገዳ ፣ ሎሚና ቆሎ የሚሸጡ ሰዎች ፣ ከወዲያ—ወዲህ የሚተራመሰው



መንገደኛ ፣ ተጓዦችን የሚጣራ የመኪና ጡሩምባ ፣ ልዩ ልዩ ዘፈን የሚያሰሙ ድምፅ ማጉሊያዎች — — —አካባቢው ጭምር ግር አለው ። ተሳፍሮ የመጣበት መኪና የትኛው እንደሆነ ጠፋው ። ዙሪያውን እየዞረ አንድ ባንድ አየ ። ሦስቱ እሽንጣቸው ላይ ፣ አፉን ከፍቶና ጥርሱን አሹሎ የሚዘል ጎፈራም አውሬ ተስሎባቸዋል ። “የኛ እንዲህ ያለ ስቅል አልነበረበትም ፣ እንዲያው ቅጠልያ ነው” ብሎ ያንበሳውን ሥዕል ትኩር ብሎ አየው ። ሌላ ቀይ ሻንጣም አውቶቡስ ላይ የሚጋልብ የነጭ ፈረስ ሥዕል አየና ፣ “ይኸም አዶል” ብሎ ዘወር አለ ። ወዲያው አረንጓዴ ቀለም የተቀባውን አውቶቡስ አግኝቶ ጠጋ ሲል ፣ ድንገት የኋላው በር ተከፈተና አጠገቡ የነበሩትን ሽማግሌ አያቸው።

“አሁን እኔ ነኝ ከተማ ገብቼ እምሠለጥነው” ብሎ ራሱን በትዝብት ገመገመ ። በሦስት መደዳ አዝራርና በትልቅ መርፌ ቁልፍ ከተቆለፈችው ከደረት ኪሱ ፣ በትንሽ እራፊ የተቋጠሩ ሳንቲሞች አውጥቶ ሙዝና ሎሚ ገዛ ። ለሽማግሌው ሁለት ሙዝና ሎሚ ሰጣቸው ።

የጣርማበር ተራራ ፣ ትላልቅ የአለትና የቋጥኝ ፍላጭ ንብብሩን ፣ ወጣ — ገባ ገጣጣ ተረተሩን አግጦና ቀዝቃዛ ጉማም እየሩን ተከናንቦ፣ ከደብረ—ሲና ከተማ በስተምዕራብ ራስጌ ፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ እየጓነ ፣ እየረበደና እየተዳፋ ተንሰራፍቷል ። ከተራራው እግር እስከ ደረቱ እየተጠማዘዘ የተዘረጋው የመኪና መንገድ ሰፊ እርከን ይመስላል ።

የደብረ ሲና ከተማ ጣርማ በርን አንጋጣ ስታይ ፣ ትልቅ ዔሊ ሥር ያረፈች ቢራቢሮ ስትመስል ፣ እሱም ግጥብጥብ ደረትና ደንደሳም አለቱን አንገልጦ ቁልቁል ይመለከታታል ። ዐልፎ—ዐልፎ ብትፈራውም ፣ እንደማይጨክንባት ታውቃለች ። እሷስ ምኗ ሞኝ ነው? የዘነጋ ተወጋ ብለው ያማከሯት ይመስል የባሕር ዛፍ አጥሯን ገጥግጣዋለች ። እሷ ያለ እሱ ፣ ግርማ ሞገሷ ተቀንሶ የምትቀል ፣ እሱም ያለ እሷ ዝናው ታውቆ ፣ ስሙ ጐልቶ የማይጠራ ይመስላሉ ። እኩያው አለመሆኗን ግን ማንም ይመሰክርለታል ።

ደብረ ሲና ፈጽሞ ሳትታሰብና ሳትታለም ፣ ሳትወለድና ሳትከተም የትየለሌ ዘመናት ቀድሟት ኖሯል! ደብረ ሲና እምትባል ትንስዬ ከተማ እግሬ ሥር ትቀረቆር ይሆናል ብሎ በሕልሙም በውኑም አስቦት አያውቅ ። የዛሬን አያድርገውና ያነዩ ከዘመናት በፊት የነበረውን የልምላሜ መጐናጸፊያውን ፣ ዛሬም እንደ ተከናነበ ቢኖር ኖሮ፣ እሱ ድንቅ ደብር ፣ እሷም ትራስጌዋ ያማረ ከተማ ትሆን ነበር ። ማን ያውቃል ፣ አንድ ቀን ይሆን ይሆናል እንጂ ዛሬማ ፣ ጨርቁን ጥሎ ፣ እላቂ ነጭ ሻሽ ሸብ ያረገ ንክ ደብተራ መስሎ በፀሐይና በውርጭ

አሳረ—መከራውን ያያል ። በጉም ሽንት ጠል የጸደቁ ቁጥቋጦና ጦስኝ ቢያጽናኑትም ፣ እርቃኑን ስላልሸፈኑለት ያለት ጎኑ ገጢል ።

ደብረ—ሲናም ዝናውን ሰምታለች ። እኩዮቹም ከሩቁ ይመሰክሩ ለታል ። እንዲህ ሁለመናው ተቆፍሮና ተነድፍሮ ያዳሜ መፈንጪያ ከመሆኑ በፊት ፣ ሰንቱን ጉረኛና 'ማ እንደኔ' ባዩን ሁሉ ወገቤን ሲያ ሰኘው ኖሯል ። አይቆጪውም ። ዛሬም ቢሆን 'ዕውቀት የተላበሰ ሰው ተራራ ይነድላል' እሉ ሆነና ተባብረው ቢነዳድሉትም ፣ ሰንቱ መኪና አልቅሶና ፈሱን ጠብሶ 'አውጣኝ ሞተሬ' እያለ ሲንፏቀቅና ሲያዘግም እንደሚውል ደብረ—ሲናም ትመሰክራለች ። ምን እቧ ብቻ! አይርቁና አይቀርቡ ቢጤዎቹም ያውቁለታል ። ደብረ—ሲና እግሩ ሥር እንደ ተቆረቆረችማ ፣ በሁለቱ ያልቀና ጋራና ሸንተረር ፣ አረህና ሸለቆ ፣ አሻ ግሮ ያላየ ተራራም አልነበረም ። መቆፈርና መደፍጠጡን እኮ ቢቀ ምሱት ፣ ከቀያሽ ዐይን ሰውረኝ ሲሉ !!

አውቶቡሱ ሲንቀሳቀስ ቀኛዝማች ፣ ምንዳዬን አሻግረው አዩት። መኪናው ወደ ተራራው ወገብ እየተጠጋ ሲሔድ ፣ የከተማዪቱ ቤቶች ባረንጓዴ ወረቀት ላይ የተረጩ የነጭና የቡናማ ቀለም ፍንጥቅጣቂ ዎች መሰሉ ። የዋሁና ታማኙ ጣርማ በር ከፉ አስቦና ፈጽሞ አያው ቅም እንጂ ፣ ከገላው ቆርሶና ከቋጥኙ ገምሶ ቢንድ ፣ ደብረ—ሲናም ደብረ—ሲና አትሆን ፣ እሱም ከንቱ የተራራ ቅሌታም ተብሎ ፣ ድን ጋይህ ላፈር በተባለ ነበር ። ታዲያ ካለ ነገሩ እንዲህ ያለውን ቅሌታም ናዳ ለቆ አያውቅም ።

ምንዳዬ ፣ በሁለቱ ትናንሽ ዋሻዎች ተደንቆ ሳያባራ ፣ አውቶቡሱ ከረጂሙ ዋሻ ዘው አለ ። ዋሻው ከወደሚገቡበት በኩል ሆነው ሲያዩ ፣ ከሌላው ጫፍ ያለው የመውጫ በር ጠበብ ያለ የፉካ ቀዳዳ መስሎ ይታያል ። አንዳንድ መንገደኞች ስለ ዋሻው እርዝማኔ ፣ የተጋነነ አስተ ያየት ይሰጡ ነበር ።

"አዬ ሥራ ሆዬ!" ሲል ምንዳዬ ተገርሞ ፣

"ጣልያን ምን ያልሠራው ሥራ አለ? እሱ ነው የሠራው" አሉት ያጠገቡ ሽማግሌ ሳይጠየቁ ። መኪናው ትንፋሽ መለስ ያደረገና አቅም ያገኘ ይመስል ፍጥነት ጨመረ ።

ምንዳዬ ፣ ደረቱ ላይ አንዳች ነገር እየተንተከተከና እየተጉላላ አቅል አሳጣው ። ታመሰ ። ሽቅብ—ሽቅብ አለው ። ሁኔታው ስለ ገባው ደነገጠ።

"ወይኔ ምንዳ! ገና ዛሬ ተዋረድኩ!" አለ ። ከፉኛ አጣደፈው ። ከፊት ለፊቱ ከመስኮቱ በኩል የነበረውን መንገደኛ ከወደ ትከሻው



ነካ ነካ አድርጎ ፣ "ወንድሜ፣ እንደዬ ብትቻገርልኝ ፣ ሊጣላኝ ነው መሰለኝ ይተናነኸኛል ። ሽቅብ—ሽቅብ ይለኛል ። የሰው መኪናና ሰው ታላበለሻሽ እንዳፍታ ብትነሣልኝ" አለ እየፈራ ።

"እኔም እንዳንተው ይጣላኛል ብዬ ነው ፣ መስኮቱን ሙጥኝ ብዬ ደይ—ደጁን እማየው" አለው ዘወር ብሎ ።

"ምን ያህል ብቆይ ብለህ ነው ፣ ሳንዳፍታው ነወዬ ፣ እያው ተኸምጨ አልቀር — — —" አለ ደረቱ ላይ እየተንተከተከበት ። እንደገና መለስ ብሎ አይቶት ፣ በርግጥም እንደ ተቸገረ ገባውና ተነሣ ለት ።

"ምን ያለው ሰውዬ ነው ወንድሜ፣ እንዳያመልጥህ አፍክን አፍኚ —— በል ቶሎ ዞረህ ና!" ሲል ፣ ሌሎቹም ፈጠን ብለው የጐን ዮሽ እየተንፏቀቁ ማለፊያ ለቀቁለት ።

ምንዳዬ ፣ በግራ እጁ አፉን ግጥም አድርጎ መርጎ እየተንገዳገደ እንደ ምንም መስኮቱ ጋ ደረሰና ፣ ራሱን በመስኮቱ አውጥቶ ደብረ—ሲና የበላትን ሙልጭ አርጎ ዘረገፋት ። ዐይኖቹ እንባ አቅርረው ላቡ ግን ባሩ ላይ ችፍ አለ ። ነፍሱ መለስ አለች ። እየተዥጎደጎደ የሚከተለበው ቀዝቃዛ አየር ላቡን አትንኖ አቀዘቀዘው ። ምራቁን በተደጋጋሚ ጢ—ቅ! ብሎና አፉን በነጠላው ጫፍ አባብሶ ዐረፍ አለ ።

"ጥኢት ቆየት በል ፣ በወጉ ይለይልህ ! ሙልይ ብሎ ቲወጣልህ ነው ደጉ !" አለው ቦታ የለቀቀለት ። በአቅራቢያው የነበሩት ሰዎች ፣ በተጠየፈ ስሜት አፍና አፍንጫቸውን በሸማቸው አፍነዋል ።

"መኪና ላይ እሚወጣ ሰው ዐመሉን ታወኸው ፣ ምናምኒት መእመስ የለበትም" አለ አንዱ ።

"አሂሂ ! መይ በሱ ሆነና ! እንዲያው አንዳንዱን እንዲሁ ይጣላ ዋሊ ፣ ይኸው ሰንቱ ሰው እማዶል ወይ እምብርቱ እስቲገለበጥ በልቶ አሁንም እሚያሻምደው !" አለ ሌላው ቀበል አርጎ ።

ምንዳዬ ፣ ቀለል እንዳለውና ሆድ ዕቃው እንደ ተረጋጋ ፣ ወደ ቦታው ተመልሶ ሎሚውን እያሻሸ ማሸተት ጀመረ ።

አውቶቡሱ ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ እንደ ደረሰ ፣ አንዳንድ መንገደኞች ሾላና ቀበና ወርደው ፣ ጉዞውን ቀጠለ ። ምንዳዬ "አዲስ አበባ ገባን" ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ከመንገዱ ግራና—ቀኝ ያሉትን ቤቶች አፉን ከፍቶ ሲመለከት ፣ አንዱን አጣርቶ ሳያይ ሌላው እየተተካ መኪናው ሲገሠግሥ የሚያየው ነገር ሁሉ ወደኋላ እየተፈተለከ

እያለ ፣ "አጠቃቀስኩ!!" ብሎ የሚመታው አስመስሎ ለቀልድ ያህል ሲቃጣው ፣ ምንዳዬ ከፉኛ ደንግጦ ባነነና ፣ "ምንዳ ገላግሌ!!" ብሎ በያዘው ዱላ ጀርባው ላይ አቦነነው ። ደህና አድርጎ አቅምሶት ኖሮ ፣ "አ!!" ብሎ ከትከሻው ልምጥ አለ ። ምንዳዬ አጠገብ የደረሰው ረጂም ቀሸረር ኩሊ ፣ እጅግም ባልከረረ ፈጣን ምት ምንዳዬን እጉንጩ ላይ ሲያቀምሰው ፣ ብዥ አለበት ። በነጠላው አንቆ ሊደግመው ሲል ቀኛዝማች ዘለው ወጡና ፣ "ልቀቀው!" ብለው ሽጉጣቸውን መዘዙ ። "እከካም ሁሉ! ማን አባቱ ነው እሚነካው? አንድ ባንድ አነጥፍሃለሁ!" ሲሉ ደንግጦ ለቀቀው ።

በመመታቱ ደንገጥ ያለው ምንዳዬ መለስ ስላለለት ፣ መኻል እና ቱን ሊከካው ሲል በዘዴ ወደ ጐን እመር ስላለበት ሳተው ። ኩሊዎቹ እየሣቁና እየዛቱ ሲሔዱ ፣ "ምን ይሆናል! አላገሩና አለቦታው ተገኝቶ ነው እንጂ ፣ በቁምህ ነበር ሽንትህን እሚያሸናህ" አሉ ቀኛዝማች ጮክ ብለው ። ምንዳዬ ከንፈሩን እንደ ነከሰ ቀኛዝማችን ተከትሎ ወደ ቤት ገባ። እነ አቶ ወርቅነህ ሳሎኑ ውስጥ ፎቴ ወንበሮች ላይ ተዝናንተው ሲቀመጡ ፣ እሱ ግን ፈንጠር ብሎ እንጨት ወንበር ላይ ፀረፍ አለ ። "ዋ ባዶ እጅ መሆን! ይኸነዬ በጥይት እማንጠራራውን!" አለና እንዴት በዱላው እንደ መታው ሲታወሰው ፣ 'አላስተረፍኩትም ፣ አንጀቱን አርሻለሁ ፣ እሳቸው ባይደርሱልኝ ግን ፣ ለሦስት አፈር መሬት ያስግጡኝ ነበር' አለ በልቡ እየሣቀ ።

የስንቁን ከረጢት እግሩ ሥር አኑሯታል ። ቀስ በቀስ ክፍሉን ተመለከተና ፣ ከወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ይበልጥ ተደነቀ ። ተወልዶ ያደገበት መንደርና አካባቢ ፣ ልኬለሽ ፣ ልጆቹና ቸርነት ታዩት ። ገና ካሁኑ ትዝታቸው ሰቦት ፣ አዲስ የናፍቆት ዘር በልቡ ውስጥ ተዘራ ።

* * *

"ከእንግዲህ ወዲያ መጠንከር ነው" አሉ አቶ ወርቅነህ ። " ሰው ሁሉ ተሻሽሎ ያደገው ፣ በብልጠትና በብልሃት ነው ። አዳዲስ ወዳጅና ዘመድ ባገኙ ቁጥር ፣ ጠቃሚ ጠቃሚውን መምረጥ ያስፈልጋል። ማግበስበስ አያስፈልግም ። ምንም ይሁን ምን የውለታ ትንሽ የለውም። አንድ ሰጥቶ ሁለትና ሦስት መቀበል ነውር አይደለም ። ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የሚያስበው ስለራሱ ነው ። ዋናው ቁም—ነገር ታዲያ ፣ እስኪይዙና እስኪደላደሉ ድረስ እንደ ሐረግ ቀስ ብሎ ነው መንጠላጠል" ብለው ወደ ኋላ ተለጠጡ ።

"እውነትዎን ነው! መቼም መስንበቻውን ፣ ብዙ ቁም—ነገር እሜውቶዎታለሁ ። ለእንደርስዎ ያለ ብልህ ሰው ደግሞ ፣ በመጠኑ



ከነገሩት ይበቃዋል ። በዚህ ላይ ከሩቅ ጮማ የቅርብ ቆሎ ይበልጣል ። መቼም ነገሬ ሳይገባዎት አይቀርም ። ሩቅ ቦታ ያለ ርስት የማንም መቀለጃ ነው" አሉ ቀኛዝማች ።

"ያ ያባት ርስት ፣ ያባት አገር መሬት ነው ። ለልጅ ፣ ለልጅ—ልጅ የሚተላለፍ ነው ። ሰው ጫማ ጠበበኝ ብሎ እግሩን አይከረክምም ፣ ባይሆን ጫማ ይለውጣሊ! እና ያኛው ፣ መሠረትና ማረፊያ ነው ። እኛ እኮ መነጽሩ ያለው በእጃችን ነው ። ጥሩ—ጥሩው መሬት የት ቦታ እንደሚገኝ እናውቀዋለን ። እያጣራ የሚነግረን ሰው ይዘናል ። መስነፍና ችላ—ችላ ማለት የለብንም ። እኔ እንኳ የያዝኩትን ይባርክልኝ ። እንኮይ የመሰለች ልጅ ጀባ ስንለው ፣ ውለታችንንማ ካልከፈለን ምን ዋጋ አለው?" አሉ አቶ ወርቅነህ ፈገግ ብለው ።

"እረ የውለታው ጋጋታ ቀርቶብኝ በገዛ ገንዘቤ!" አሉ ቀኛዝማች ውስጥ ውስጡን ተደስተው ፣ ላይ—ላዩን እየተኩራሩ ።

"በገንዘብዎም በኩል ቀስ ብለው ይደርሳሉ ፣ እሱን ለኔ ይተዉት" አሉ አቶ ወርቅነህ ፣ በወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ በሞገስና በላቀች ምክንያት የሚገኘው ጥቅም እየታያቸው ። ቀኛዝማችም ባላሰቡት ሁኔታ ስለሚገኘው ጥቅም እየተገረሙ ልባቸው ተስፋ አደተ ።

ከወደ ማድቤት በኩል ባለው በር የሚገባው አየር ፣ የቡናና የወጥ ሽታ እየወሰደ ቤቱን አወደው ። የግቢው የብረት በር አአአ! ኢኢኢኢ! የሚል ድምፅ ከማሰማቱ በጓሮ በር በኩል ወ/ሮ መንበረና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ተከታትለው ገቡ ።

አቶ ወርቅነህ መዘውር ፣ ካንገት በላይ ሣቅ—ፈገግ ቢሉም ውስጣቸው ተከፋ ። 'እስቲ ምን አስቸኮላቸው ፣ ባለቤትዬዋ ብትኖርስ?' አሉ በሐሳባቸው ። ሴቶቹ ከነቀኛዝማች ጋር ከተሳሳሙ በኋላ ፣ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ መለስ አሉና ፣ "ውይ ምንዳ! መጣህ? እሰይ! እሰይ! እንኳንም የመጣህ?" ከማለታቸው ተነሣና ተሳሳሙ ። ደስ አለው ።

"ምነዬ ገባችሁ?" አሉት ።

"ጥኢት ቆየት ብለናል" አለ ምንዳዬ እንደ ቆመ ።

"በል ተኸመጥ ፣ ሚስትህ ደህና ነች? ልጆችህስ?"

"ደህና ናቸው ። አንቱስ ደህና ነሁ?" አለ አቀርቅሮ ።

"ደህና ነኝ! እዝጊሐር እምስጌን! ተኸመጥ!" ብለው ተመለሱ ።

* * *

በኋላ ፣ ጣዕሙን ለመለየት ያህል ሁለት ሦስትዬ ቆንጥሮ ጐረሰና ወደ
አደገበት ወጥ መለስ አለ ።

ሠራተኛይቱ ለነቀኛዝማች ቡና ስጥታ ፣ ለሱም አነስ ባልቿ
ጀሯም ስኒ ከነመቀመጫው ወስዳ እግሩ ሥር አኖረችለት ። በሦስት
ፉትታ ጨለጣት ። በደንብ በልቶ ሳይጠግብ ፣ እጁን ወደ ወንበሩ
የኋላ እግር ሰደድ አድርጎ አባበሰና ደገፍ ብሎ ተቀመጠ ። ገና ላይን
ሳይዝ መብራቱ በራ ። ጣራው ላይ ተለጥፈው የሚበሩትን ቁመተ—
ዱላ መብራቶች እንዳየ ተደነቀ ። ሌላ ክፍል የበሩትን ድቡልቡሎቹን
ወደዳቸው ። 'እንዲህ ያሉት የጠፋ ከብት መፈለጊያ ቢገኙ ጥሩ
ናቸው' አለ በሐሳቡ ።

ቀኛዝማች ፣ አቶ ወርቅነህ መዘውርንና ባለቤታቸውን ለመሸኘት
አብረው ሲወጡ በማየቱ ፣ ምንዳዬ እሱና ቀኛዝማች በእንግድነት የገቡ
መስለውና ፣ ዱላና ከረጢቱን አንጠልጥሎ እስከ ግቢው መኻል እንደ
ደረሰ ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ባጋጣሚ መለስ ሲሉ ስላዩት ፣—

"ወዴት ትሔድ ልጄ? አንተኮ እዚሁ ነው ቤትህ" አሉት እየ
ፈገጉ ። ቀኛዝማችም ፣ "የኛኮ ቤታችን ይኸ ነው ። በንግድነት የገባን
መሰለህ እንዴ? በል ተመለስ!" አሉት ያ የሣር—አምባው ብልህና
አስተዋይ በማያውቀው አካባቢ በመሳሳቱ የጓደኛው ያህል ቅር እያላ
ቸው ።

የቀኛዝማች ዘበኛ ፣ የአቶ ወርቅነህን የልብስ ሻንጣና ደብረሲና
የተገዛውን ሙዝ ፣ ትርንጎና ሸንኮራ አገዳ የያዘ ባለ ማንጠልጠያ ቅር
ጫት ተሸክሞና አንጠልሎ ወጣ ። ቀኛዝማችና ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ
እነ አቶ ወርቅነህን በታክሲ አሳፍረው ሲመለሱ ፣ አቶ ወርቅነህ ደስ
አላላቸውም ። እቤታቸው እንደ ደረሱም ፣ "እሷስ የራሷ ጉዳይ ፣ አንቺ
ለምን አብረሽ ሔድሽ? ይህን ያህል ድፍረት ጥሩ አይደለም ። እስከ
ዛሬም መመላለሷን አልወደድኩላትም ። ከዚህ ሁሉ በርትታ አጠቃል
ላቸውም ። ካልሆነም እሷን የመሰለች ሴት ወይዘሮ ስንቱ ነው ፈላጊዋ ።
ቀስ ብለሽ ንገሪያት ፣ እኔም ዋል አደር ብዬ እመክራታለሁ" ሲሏ
ቸው አልመለሱላቸውም ።

ቀኛዝማችና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ጥቂት ካወሩ በኋላ ፣ የሕይወት
አካል የሆነውን ልፊያቸውን ለመላፋት መኝታ ክፍል ገብተው ከብ
ርድ ልብሱ ሥር ያልተጠበሰ ሸክላ መሰለዋል ።

ሠራተኛይቱ ፣ ለራሷና ለዘበኛው ራት ስታቀርብ ምንዳዬንም
ጠርታ "ራት እንብላ" አለችው ። እሱ ግን ፣ "እኔ ይበአኛል ፣ የበላሁትም
አልጎደለ" ብሎ ተግደረደረ ።



'ካእኛ ጋ ይሻልሃል ብዬ ነው እንጂ ፣ ለብቻህ ላቀርብልህ ነበር"
አለችው በችኮላ ።

"ተበላሁማ ተሰው ጋ ነው ደጉ ። እኔ አይሻኝም ብዬ ነውዴ!"

"ቢሆንም እኛን ደስ እንዲለን አብረኸን ብላ" አለ ዘበኛው ።

"ተምሬ ነው ፣ በእቶኝ ነው ። በያ ላይ መኪናው ሲያነዝጠኝ
ውሎ..."

"ባይሆን እንኳ ቅመሰው —— ራት አይደለም እንዴ?"
አለው ።

"ቅድም የበላኸው አልጣፈጠህም እንዴ?" አለችው እየሣቀች ።

"ኧረ ተየቱ —— ለጥፍጥናውስ ምንም አይወጣለት ።"

"ባይሆን አንድ ሁለተዬ 'ንኳ ጕረስ — — የገባ አይጎዳም"
ሲለው ዘበኛው እንደ ተባለው አደረገ ።

"የጌቶች ዘመድ ነህ?" አለ ዘበኛው ። በሥራው ላይ ጠርጥሮ
ታል ።

"አዎድ!"

"መቼ ተነሥታችሁ ነው?" አለችው በተራዋ ።

"ተቤት የወጣነውማ ትላንትና ነው ፣ ማጀቴ አድረን ነውዴ—"

"ዛሬ ሰባት ሰዓት አካባቢ ነው ስልክ ተደውሏል ብለው የላኩ
ብን" ስትለው ነገሩ ስላልገባው ዝም አለ ።

"ሴትዮዋስ? እዚያው መቅረታቸው ነው እንዴ?" አለ ዘበኛው
እያላመጠ ።

"የማ ሴትዮ?" አለ ድንገት ።

"ሚስትዮዋ!"

የወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ አመጣጥ ቶሎ ገባውና ፣ "መሰንበቻውን
ይመጣሉ" አለ የወንበሩን ጠርዝ እያሻሸ ። ምንዳዬ ከራት ጋ
የቀረበለትን ጠላ ወድዶ የብርጭቆውን ማነስ ስለ ጠላው ፣ "በዚህ
ምን ያህሉ ቢጠጣ ያጠግባል?" አለ በልቡ ።

ሠራተኛይቱ ፣ "ገበሬ ነበርክ?" አለችው ።

"አዎድ!"

የሰውዬውን ቅሬታ የሚያስወግዱበትን የንግግርም ሆነ የሩካቤ ብልሃት አሳምረው ያውቃሉ ። ወንድዬው የቤትዮዋን ትርፍስፍስ ገላ ሲያዩና ሲዳብሱ ፣ ይይዙ ይጨብጡት ይጠፋቸውና ሕሊናቸው ይነሆልላል ። በእሳት ዙሪያ በርራ—በርራ እላዩ ላይ እንደምትማገድ የሳትራት ፣ ቤትዮዋ ባዘቶ ገላ ላይ ተንፈላሰው ፣ ሩካቤ ምድጃ ላይ እንደስብ ሲቀልጡ ይረካሉ ። ከዚያ በኋላ የሚጠየቁትን እነሆ ፣ የሚታዘዙትን እሺ በማለት የልግስናቸውን ከረጢት ይፈቱታል ።

ወ/ሮ ደጅ ይጥኑ ፣ አንድ ነገር አስበው ካልጋ ላይ ወረዱና ፣ እዚያው መኝታ ቤት ውስጥ ግድግዳ ላይ ተለጥፎ በተንጠለጠለው ቁመተ ልከኛ መስተዋት ፣ ፊትና ደረታቸውን ፣ ሻሽና ክናዳቸውን እየደባበሱ ሲመለከቱ ፣ ጀርባቸው ወደ ሰውዬው በመዞሩ ፣ ሳሳ ባለው ልብስ በኩል የሚታየው ከመር ፣ ጠፍጠፍና ጋደም ያለው ዳሌና መቀመጫቸው ፣ የሰውዬውን ቀልብ መንጥቆ ወሰደው ። ባይናቸው የሠረፀው ገላ፣ እንደገና የሩካቤ አምሮታቸውን እንሸከሸከው ።

“ምነው መጥተሽ ብተኚና ዐረፍ ብንልበት ፣ አውቶቢስ ሲያንገላታኝ እኮ ነው የዋልኩት” አሉ በጋባዥ ስሜት ። ልፊያቸው ሲቀዘቅዝ ሁለቱም እፎይ አሉ ።

* * *

ቀኛዝማች ፣ የወ/ሮ ደጅ ይጥኑን ገላና ፣ የተለየ ነፍስ እንዳለው ፍጡር እሽከም እያለ የሚንቀሳቀስ ቂጥ ሲመለከቱ ፣ የልጅነታቸው ጊዜ ትውስ ይላቸዋል ። ባጁ ፣ አጠር ብላ ፈርጠም ያለች ፣ ጤፍ ስትሰልቅ ፣ አሻሮ ስትድስ ፣ ክክ ስትከካ ፣ ወይም አጎንብሳ ቤት ስትለቀልቅ ፣ የሚያዘበጥጥና የሚርገፈገፍ ቂጥ የነበራት ያባታቸው አገልጋይ ነበረች ። ካባታቸው ሎሌዎች መኻል ጥርሰ—ዘርዛራ ፣ ክንደ—ጠንካራና አካለ ደልዳላ የነበረው መርጦ የባጁ ወዳጅ ነበር ።

“ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነው” ይባሉ በነበረበት ጊዜ ካገልጋይና ከልጆቻቸው ጋር እንደልብ ይዛለሉና ይጫወቱ ነበር ። ያን ጊዜ መርጦ የበላይነህን ዕድሜ በማየትና ‘ቢያይስ ነገሩን የት ዐውቆት’ በማለት ባጁ በገባችና በወጣች ቁጥር ዙሪያውን መልከትከት ያደርግና ቂጧን ጠፍ—መታ ፣ ጡቷን ቆንጠር ያደርጋታል ። ይዋደዱ ነበር ። ቤቱ ጭር ካለ ደግሞ ድሪያው ይባባሳል ። ያቺን ሁሉ እንደ ቀልድ ተመልክተዋል።

ቀስ በቀስም ነገሩ ስለ ገባቸው ፣ ባጁ እና መርጦ የሚያደርጉትን ሁሉ ለማየት ይጓጉ ጀመር ። ዕድሜያቸው በጨመረ ቁጥር የባጁ ገላ አማራቸው ። የተመኙትን አላጡም ። መርጦ ቢከፋው ቢከረፋውም



በግኖ ዝም አለ ። ባጁ በልዩ ልዩ ሥራ እዚያው ቤት ለቤት ፣ ከጠላ ቤት ጐተራ ቤት ፣ ከበረት ጉረኖ ፣ እያለች ስታደዘድዝ ላያት የአካሏ እንቅስቃሴና ሙላት አጓጊ ነበር ። “ያላሳብ እየዋጠች ተውለከለከች” ቢተባለችበትና የወንድ ዐይን በሳበችበት ወቅት ፣ የበላይነህም ዐይን በባጁ ላይ ማረፉ ስለ ታወቀ ሁኔታው ተባብሶ ስም ከማስበሩ በፊት ፣ እንደ ጊዜው ‘የመኳንንት ልጆች ’ የአምሮት ማብረጃ ሴት በግርድና ስም ተቀመጠችላቸው ።

ያ በልጅነታቸው የተጠናወታቸው የትልቅ ቂጥ አድናቆት አብሮ አድጎ አብሮ ጐልምሷል ። ከጥቂት ዓመታት በፊትም ማጀቴ ተወልደውና አድገው ፣ ወደ ደጋው አገር ተድረው ሁለት ሴቶች ከወለዱ በኋላ ተፋትተው ከተመለሱ ወዲህ ፣ ከወደ ደሴ የመጡ ልብስ ሠፊ አግብተው ለሁለት ዓመታት የኖሩትንና ዳግመኛ የተፋቱትን መልከ—መልካሟንና ዠርጋዳዋን ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑን አግኝተው ፣ በመጀመሪያ ወሽመው የኋላ—ኋላም አስቀመጧቸው ።

ሁኔታቸውን አይቶ የሚገዝት ካህን ፣ ተገቢ አይደለም ብሎ የሚገሥፅ ሽማግሌ ሳይታጣ ፣ ‘ብንናገር ይብስባቸው ይሆናል ፣ ወይም ከልጆቻቸው እናት ይፋታሉ’ በሚል ሥጋትና ጥርጣሬ ፣ እንዲሁም በአካባቢው የተለመደው የቅምጥና የቀላቢት ማስቀመጥ ልማድ ተደጋግፈው የልብ ልብ ሰጣቸው ። ሚስትዬዋንም ፣ “አንቺ ቤት ንብረትሽን አጥብቀሽ ያዢ ፣ ማየት ያለብሽ ልጆችሽን ነው ። ምን አጥተሽ? ምን ጎሎብሽ? ከዚህ ካንቺ ተርፎ ለሚሔደው ነው ሽጉዱ! ለነዳይ የተሰጠ ያክል ቁጠሪው ። እሳቸው እንደሁ ዘለው ዘለው ሲቢቃቸው የት ይሔዱ መሰለሽ? የምር አይምሰልሽ ፣ ሁላችንም አይተነዋል ። ወንድና ብረት ምጣድ ቶሎ ይበርዳል” እያሉ የሚመክሩ የቅርብ ዘመዶች ቢበዙም የወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ልብ ግን እልህና ቅናት አረገዘ ።

* * *

ምንዳዬ ስሜቱ ተመሳቅሎ እንደ ባነነና በቅዠት እንደ ተንገላታ ነጋ ። ማለዳም ወጣ ብሎ አትክልቱን ፣ ግቢውንና የዘበኛውን ቤት ተመለከተ ። ከቁርስ በኋላ ቀኛዝማች ወደ ሥራ ለመሔድ ሲነሡ በማየቱ ግቢው መኻል ዱላውን ይዞ ጠበቃቸው ።

“ወዴት ልቴድ ነው?” አሉት አቋቋሙን አይተው ።

“ልከተልሁ ብዬ ነዋ! መሔድሁም አደል እንዴ?”

“የለም! የለም! ወደ ሥራ ስሔድ—ስሔድ ተከታይ አያስፈልግም”።

"እኔስ ደስ ብሎኝ መስለህ? ሰው እሰው አገር ተኾምጦ ——" ከማለቷ ፣

"ማነው የሰው አገሩ ሰወ? ይኸ ጀምበር ከጠለቀች እሚደረስበት አገርሽ ሩቅ ሆነና ነው እንዲህ እምትዪውን?" ብሎ ሲቀጥል ሲል ፣ አሻጋሪ ከወደ ደጅ ብቅ አለ ። "እየሁ ኖረሃል እንዴ አሻጋሪ" አለ ቸርነት ወደ ውጪ እያየ ።

"እማምይ ተየሀ ተግቢ ትወጣና —— ዋልሀ ብላኝ —— እየሁ ነው የዋልኩት" አለ ተናዶ ።

"ምነው ልጄ! ምን አጠፋ?"

"ምነው ነገሩን ስታኸው? ፈራኋ?" አለች ተከዛ ።

"እነማንን?"

"ካፈሣ ጋር የመጡትኮ የዞን አምባ ሰዎች ናቸው ፣ ባላጋሮቻችን አይደሉሚ!"

"እስቲ ሙት በይኝ! እኔ የታባቱ አወ ኩ?" ብሎ ወዲያው ተነሥቶ ሔደ ።

ጠበንጃውን ይዞ እንደ መጣ ፣ "አሻጋሪ! ና ሒድ ውጣና ተጫወት! ማባቱ እንደሚነካህ አያለሁ! ሱሪ አልታጠኩማ!?" ብሎ ካጥር ውጪ ይዞት ወጣና ፣ "ሒድ ከባልንጀሮችህ ጋ ተጫወት" አለው ። ልኬለሽ በአለኝታነቱ ተደሰተች ።

ቸርነት ከአፈሣ ቤት በታች ዱብ ላይ ተቀምጦ ፣ ረባዳው ጠባብ ሜዳ ላይ የሚጫወቱትን ልጆች ሲመለከት ደስ አለው ።



## ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

ምንዳዬ ፣ አንድ ሁለተዬ ቀኛዝማችን ተከትሎ በሔደበት ጊዜ ባየው የከተማ ሁኔታ በጣም በመገረሙ ፣ ሰውዬው ወጣ ባሉ ቁጥር ፣ "ምነው ና እንሒድ ባሉኝ" በማለት ተከትሎ ለማየት በጣም ይጓጓ ጀመር ። በተለይም አንድ ቀን ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ መዘውር ምንዳዬን አስከትለው በራስ ሙኮንን ድልድይ አልፈው ፒያሳ እንደ ደረሱ ፣ ስን ኳንና አዲስ መጤው ምንዳዬ ቀርቶ ፣ በተደጋጋሚ ተመላልሼ አይቻ ዋለሁ ሲሉ የኖሩት ቀኛዝማች እንኳ በሚያዩት ልዩ ልዩ ብልጭልጭ የዕቃ ዓይነትና ብዛት ፣ በየሱቁ የተደረደረውን ልብስና ፣ ሸክ አርገው አልብሰው ያቆሟቸውን አምሳለ—ፈረንጅ አሻንጉሊቶች ሲመለከቱ በጣም ገርሟቸዋል ። የሱማ ምኑ ተነግሮ! እነ ቀኛዝማች ከአንድ መደብር ፊት—ለፊት ቆመው ፣ "ይኸኛው ይሻላል ፣ ያኛው ይጠነክራል" እያሉ የሱፍ ጨርቅ ሲያማርጡ ፣ ምንዳዬ ግን ዳለቻ የሱፍ ልብስ ለብሶና ባርኔጣ አድርጎ ፣ አንድ እጁን እሱሪ ኪሱ ውስጥ ወሽቆ የቆመውን መጠነ—ሰው አሻንጉሊት ትኩር ብሎ ያይ ነበር ።

በመጀመሪያ ፣ "እንዴት አምሮበታል ይኸ ፈረንጅ! አዬ አቋቋም ሆዬ!" አለ ። ነገር ግን ፣ ቢያየው ቢያየው ንቅንቅ አይልም ። "አቤት አሠለጣጠን! እንዴት ሰው አንደዬ'ንኳ ንእንቅ አይልም!" እያለ ሲገረም ፣ ለካስ እነ ቀኛዝማች መንገድ ቀጥለዋል ። ደግነቱ አልራቁም ነበር ።

የሰዉና የመኪናው ብዛት ፣ የቤቱ ንጽሕናና አሠራር እየገረመው ሲከተል ሌሎች አሻንጉሊቶችም በማየቱ ፣ "እንዴት ፈረደበት ይሄ ሁሉ ፈረንጅ ወንድሜ" እያለ ሲያዝግም ፣ አንድ ሱቅ በር ላይ እንደ ደረሱ ፣ አንድ ሸማግሌ ፈረንጅ ብቅ አሉ ። ምንዳዬ ትኩር ብሎ አያቸውና ፣ እስከዚያች ቅፅበት ያልታየው በቀል ትዝ ስላለው ብልጭ አለበት ። ወዲያው ጉዞ በመቀጠላቸውና ከሌላ ትርዒት ጋር በመገናኘቱ ትዝታው ጥሎት ነጎደ ።

አንዳንድ ቀን ከቀኛዝማች ጋር ወደ ፒያሳ ወይም ወደ አራት ኪሎ ሲሔድ ፣ የገረመውን ነገር መለስ ብሎ ወይ አሻግሮ ሲመለከት ፣ ሳያስበው ከሰው ጋር ይጋጭ—ይጋፋና በጣም ይደነግጣል ። ገጠሬነቱን የተገነዘቡ ሣቅ ብለው ያልፉታል ። አንዳንዶቹ የየራሳቸው የቀድሞ

"እእ! እኝህኛዋ ጋ ምን አሳብ አለ ፡፡ የቤትዮዋ ዘመድ አሉ ፡፡ በያ ላይ አንቺ አለሽ ፡፡ ምን እሚያሳስብ ነገር አለ?" ብሎ ዐይኑን ስክት አድርጎ አያት ፡፡

"የኔ እየህ መቆየት'ንኳ ያጠራጥራል ፤ ብኖርስ ማ እንደ ወንድ ልጄ?" አለችው በዝግታ እየሣቀች ፡፡

"ወዴት ልኬጂ?"

"ባል ታላገባሽ እያሉ — —" ብላ ሳትጨርስለት ፤

"ማንን?" አላት ተገርሞ ፡፡

"አንድ ሰውዬ እዚህ ቲመላለስም አላየኸው?"

"የትኛው? — — መሰንበቻውን ብዙ ሰው አይቻለሁ ፡፡"

"ለዘግ ብሎ ግራ እግሩን ላመል ጎተት እሚያረግ ሰውዬ ፤ አፍንጫው አጠር ያለ ደፍጫ ቢጤ — — አላየኸውም እንዴ?"

"እኝህ ባለመኪናው?" አለ ባጋጣሚ ግምት ፡፡

"አዎድ!" አለች ፈገግታዋ እየጨመረ ፡፡ ያቺ የሚያውቃት ላቀች ድንገት የተለወጠች ፤ እዚያው በዚያው ከሱ በልጣ እንደ ቀኛዝማች የከበረችና የተሾመች ፤ እንዲያውም ከዘመዷ በላይ የሆነች መሰለውና "አንቺ ደህና ቀን ወጣልሽ" አላት ሣቅ ብሎ ፡፡ ረጋ ብሎ ጠየቃት ፡፡ ዘርዝራ ነገረችው ፡፡

በርግጥም ከሁለት ወር በኋላ ቀኛዝማችና ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፤ አቶ ወርቅነህና ባለቤታቸው ፤ እንዲሁም አንዳንድ የጐረቤት ሰዎች በተገኙበት ፡ በሞገስ በኩል አቶ ወርቅነህ ፤ በላቀች ወገን ቀኛዝማች በላይነህ ታፈሰ የውል አባት ሆነው ፤ እሱ በብርዕ ፤ እሷ ቀለም በተቀባ ዐውራ ጣት ፈርመው ፤ እሱ ለሦስተኛ ፤ እሷ ለሁለተኛ ጊዜ አገቡ ፡፡

ላቀች ጥበብ ኩታና ቀሚስ ለብሳ ፡ ጸጉሯን ተሠርታና ጥቁር ተረከዘ አጭር መጫሚያ አድርጋ ላያት ፤ ዋልካ ዐፈር ላይ የበቀለች የነጭ አበባ እምቡጥ ትመስል ነበር ፡፡ ያላንዳች ዕልልታና ጭፈራ ፤ ሞገስ በሁለት ተጨማሪ አውቶሞቢሎች ጓደኞቹን ፤ እነ ቀኛዝማችንና መቅረት የሌለባቸውን ጐረቤቶች ይዞ ወደ ቤቱ ሔደ ፡፡ እዚያው አብሮ የዋለው ምንዳዬ ወደቤቱ ሲያመራ ፤ "ወይ መእየት! እነ ቀኛማይኮ አጅበዋት ሔዱ!" አለ ተገርሞ ፡፡



## ምዕራፍ ዐርባ

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፤ ከዛሬ ነገ አዲስ አበባ ይገባሉ እየተባለ ዘበኛውና ምንዳዬ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በየዕለቱ ከዐሥር ሰዓት ጀምሮ ይጠባበቁና አለመምጣታቸው ተረጋግጦ ወደ ቤት ሲመለሱ ፤ ቀኛዝማች "ምን ሆና ይሆን?" ይሉና የማታ—ማታ ምንዳዩን ወደ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ቤት ይልኩታል ፡፡

ቤትዮዋም ከነባር የምኞትና የቅናት ሐሳባቸው ጋር ይጨቃጨቁ ይነታረኩና ፤ "መቼስ ምን አረጋለሁ" ብለው ይነሣሉ ፡፡ ምንዳዬን አስከትለው ሲሔዱ ምኞታቸው በተስፋ አብቦ ያሸትና ፤ ከቀኛዝማች ጋር እንደ ልባቸው ሲኖሩ ይታያቸዋል ፡፡ ምኞታቸው ከዘወትር ልምዳቸው ስለማይርቅ ፤ ከሰውዬው ጋር ቤተ ክርስቲያን እየሳሙ ፤ ግብዣና ድግስ ተጠርተው ከመኳንንት ሚስቶች ጋር ሲጋበዙ ፤ እሳቸውም ደግሰው ሲያበሉና ሲያጠጡ እየታያቸው ፤ አእምሯቸው በተስፋ ረክቶ ፡ ልባቸው በደስታ ይንደቀደቃል ፡፡ በዚህ የምኞትና የተስፋ ትርዒት መኻል ፤ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ውልብ ሲሉባቸው ፤ "መድኃኒዓለም አባቴ በዚያው ያስቀርሽ!" ብለው ይሳሉና አእምሯቸውን ያረጋጋሉ ፡፡

የቤትዮዋ መመላለስ ድንገት ተሰምቶ ፡ አዲስ እንካ ስላንቲያ እንዳያስከትልና ከቤት የሚነሣውን ወሬ አዳፍኖ ለማስቀረት ሲባል ፤ የቤት ሠራተኛዋና ዘበኛው በተለያዬ ተራ ሰበብ ከሥራ ተሰናበቱ ፡፡

ወ/ሮ መንበረ ፡ ለወደፊቱ ወሬ እምታቀብል ሠራተኛ ሲወስዱላቸው ፤ ምንዳዬም በዘበኛው እግር ተተካ ፡፡ ከሰነበተባት የጸሎት ክፍል የመኝታ ምንጣፉንና ዳለቻ ስስ ብርድ—ልብሱን ጠቅሎ ወደ ዘበኝነት ቤቱ ተዛወረ ፡፡ አታፈናፍንም ፡፡

ከጣራዋ ቅርበት የተነሣ ፤ እጠናይቱ አልጋ ላይ ቆሞ ልብስ ማውለቅ አይቻልም ፡፡ በሌሊት ቅዝቃዜና በቀን ሞ'ቃትነቷ የተነሣ የቀድሞው ዘበኛ ፡ "አምስሽ አሹቂኝ" ብሎ ስም አ ውጥቶላት ነበር ፡፡ ምንዳዬ ትልቅ ሳጥን ከምትመስለው ክፍል ሲገባ አእምሮው ይጨነቅና የሐሳብ አሸን ይወረዋል ፡፡

ዘበኝነቱን በጀመረ በሁለተኛው ሳምንት ፍጻሜ ላይ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ሸዋርካብሽን አስከትለው ፤ ካውቶቡስ ሲወርዱ በትሕትና ተቀብሎ ከሁለቱም ጋር ተሳሳመ ፡፡

ሞገስ እምባቸው፣ ስለ ምንዳዬ ማንነትና አኗኗር፣ ከገዛ ባለቤቱና ከቀኛዝማች ከሰማበት ዕለት ጀምሮ ያ ያንድ ሰሞን ቅናትና ጥርጣሬው ወደ ልባዊ ርኅራኄ ተለውጦ ወዶታል። ወደ ቀኛዝማች ቤት በሔደ ቁጥርም፣ አትክልት የሚያይና አካባቢውን የሚቃኝ መስሎ እንደዘበት በማውራት፣ የምንዳዬን ጠባይ ከተረዳ ወዲህ በወደደ ስሜትና በፈገግ ፊት እጁን ዘረጋለት። ሁለት አርጀት ያለ ካኪ ኮትና ሱሪ ከነሸሚዙ የሰጠው ዕለት እንኳን ተቀባዩ ቀኛዝማችም ደስ ብሏቸዋል።

“አሁን ምን አርጌልሁና በምን አቀሁኝ ነው ይኸን ኩላ አምጥተሁ መስጠትሁ?” ብሎ ሲያመሰግን፣ “እንደ ትልቅ ስጦታ አትየው፤ ቀላል ነገር ነው፤ ለወደፊትም እረዳሃለሁ” አለው።

ልብሱን ማደሪያው ውስጥ አስቀምጦ፣ አንዳንድ ቀን ሥራውን ሲጨርስ እየቀያየረ መልበስ ጀመረ። ቦላሌውን ታጥቆ ሸሚዙን ወደውጭ ይለቅና፣ ቁልፎቹን በሙሉ ይቆልፋቸዋል። ኮቱን ሲለብስበት ደግሞ ሸሚዙ እሱሪው ላይ ይለጠፍና ጠርዙ ይጠቀለላል። ይህን ዋል አደር ብሎ አረመ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፣ የሸሚዙ አንገትጌ ሸቅብ ታጥፋ ትቆምና የነጭ ፍየል ግልገል ጆሮ ትመስላለች።

ቀኛዝማች፣ ከላይ ደህና ለብሶ ያለ መጫሚያ የሚከተላቸውን ምንዳዬን ለማስደሰት ተረከዙ ባንድ ወገን የተበላ አሮጌ ጫማቸውን ሰጡት። ያን እንደልቡ እየተዘረጋ እንዳሻው ሲረግጥ የኖረ እግሩን አሮጌ ሽፍን ጫማ ውስጥ ያለ እግር ሹራብ ይደነቅርና ጥርቅም አድርጎ ያስረዋል። ልብሱን ቀይሮና ጫማውን አጥልቆ ቀኛዝማችን የተከተለ ዕለት፣ አንድ እጁን ሱሪ ኪሱ ውስጥ ከትቶ ሲሔድ በጣም ደስ ይለዋል።

ሸዋርካብሽ፣ ቀደም ብላ ምስጢሩን የማታውቀው የመልእክት ጉዳይ ያስከተለባት ችግር እያንገበገባት፣ ቀስ በቀስ መግባባትን ሊፈጥር በሚያስችል ሁናቴ፣ ከምግብና ከመጠጡ ደበቅና ጠቀም እያደረገች ትሰጠው ጀመር። በሴትዮዋ ሰበብም ያቄመባት ስለሚመስላት፣ እሷ እንዳሏት አዳሪና በይ እንዳሏት መስካሪ መሆኗን እንዲያውቅላት በሰበብ ባስባቡ ጠጋ ጠጋ አበዛች። አልሸሻትም። ሲወጡላት ሔዳ ማውራትና ሲያስቀይሟትም ጠጋ ብላ ማማት ጀመረች። እሱም ቀስ በቀስ ነገሩን እየተረዳ፣ ከቀን ወደ ቀን ልቡን አላላላት።

* * *

ቀኛዝማች በላይነህ፣ ኑሮአቸውን የማሻሻልና ከነእከሌ እኩል ወይም በላይ መሆን አለብኝ የማለቱን ውጣ—ውረድ አመኙ በመሰ



ላቸው ጊዜና ቦታ ሁሉ ተያይዘውታል። የከተማ ኑሮ ዕውቀትና ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር በተዋወቁ ቁጥር፣ እንዴት ባለ ብዙ ንብረት ለመሆን እንደቻሉ ለመስማትና ለማወቅ፣ ሁለመናቸው ጆሮና አእምሮ ይሆናል። ከዓላማቸው ጋር የሚጣጣም ሰው ካገኙ ደግሞ እጃቸው የልግስና መዓዱን ያወርደዋል።

በገጠር ያሳለፏቸውን አያሌ ዓመታት በከንቱ እንደ ባከኑ በመቁጠር፣ የኑሯቸው ሥርና ግንድ የሆነውን ሕዝብና አካባቢ እያማረሩ ይጸየፉታል። የፍላጐታቸውን ማከናወኛ መሰላል ግን እዚያው መሬት ላይ ተክለው፣ በገጠሩ ሕዝብ ትከሻ ላይ ይረማመዳሉ።

“ሰሙ ቀኛዝማች” አለ ሞገስ አቶ ወርቅነህ ቤት ተቀምጠው ሲያወሩ። “ዛሬ እርስዎን በጣም የሚጐዳዎት ይኸ በየወሩ የሚከፍሉት የቤት ኪራይ ነው። ቀላል ገንዘብ አይደለም። በአራትና በአምስት ዓመት ራሱን የቻለ ቤት ያሠራል። እናም የመጀመሪያ ሥራዎ የመኖሪያ ቤት መግዛት ቢሆን ጥሩ ነው” አለ።

“እኔም ቀደም ብዬ ነግሬያቸዋለሁ” አሉ አቶ ወርቅነህ ለማስታወስ ያህል።

“በሱማ ምነው ተስማምተን! አካባቢው የጨዋ ሠፈርና ውካታ የሌለበት እንዲሆንልኝ በማለት ነው ረጋ ያልኩት። አሁን ያለሁበትን ቤት የወደድኩት ስለ አካባቢው ነው” አሉ ቀኛዝማች።

“በኔ በኩል ሁለት ቦታ ተገኝቷል። የሚሻለንን መምረጥ የኛ መብት ነው። በዋጋም ረገድ የሚጎዳ አይደለም” አለ ሞገስ ኩራ ባለ ድምፅ።

ከተደጋጋሚ ምክክር በኋላ ጂማ፣ መንገድ የተገኘው መኖሪያ ቤት የተሻለ በመሆኑ ተገዛ። በአሠራር ደረጃውም ሆነ በቤቱ ስፋት መጠን ከተከራዩት ቤት ያነሰ ሲሆን፣ በምድረ—ግቢ ስፋት ግን ይበልጣል። ዋናው ቤት ከቀይ ጡብና ድንጋይ፣ የበስተጀርባዎቹ ትናንሽ ክፍሎች ከእንጨት የተሠሩ ናቸው። የዋናው ቤት ወለል በተላገ ሣንቃ የተነጠፈ ሲሆን፣ የፊት ለፊቱ ሰበሰብ ግን፣ በጠጠርና ስሚንቶ ድብልቅ የተስተካከለ ሻካራ ወለል አለው። ዋናው ቤት ቀለም ተቀባብቶ ከታደሰ በኋላ፣ የአዲሱ መኖሪያቸው ጐረቤቶችና ጥቂት እንግዶች በተገኙበት፣ ሰው ሳይበዛና ግብዣ ሳይንዛዛ ቤቱ ተመርቆ፣ ቀኛዝማች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ገቡ።

ቤቱ አነስ ያለ ሳሎንና የገበታ ቤት፣ ሦስት የመኝታ ክፍሎች፣ ከበስተጀርባም የዕቃና የሽንት ቤት፣ ሁለት ማድቤቶች፣ ተጨማሪ የዘበኛ ቤትና የሠራተኞች ማደሪያ አነስተኛ ክፍሎች አሉት።

## ምዕራፍ ዐርባ ሁለት

የቀኛዝማች ኑሮ በተስፋ ተከበበ ። ጥቅምና ዕድገት ማነፍነፍ ዋነኛው ተግባራቸው ሆነ ። ምክር ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው ሳለ ፣ ከልዩ ልዩ ባለሙያዎች የሚቀርቡ ጥናቶች ፣ ክርክሮችና ተቃውሞዎች ሲነበቡም ሆነ ሲነሡ በሙሉ ልብ አድምጠው አያውቁም ። አንዳንድ አባላት የሚያቀርቡት ሐሳብና ክርክር ከማናደድ ዐልፎ ፣ “እንዲህ ያሉትን ጋጠ ወጦች ለምን ያስገቧቸዋል ፣ ‘ጭሰኛ ተጎዳ ፣ የጭሰኛ ግብር በዛ ፣ ሥራ አጥ በረከተ ፣ ሴት አዳሪነት ተስፋፋ ፣ ሕግና ፍትሕ ተጓደለ ፣ የሕዝብ ገንዘብ ባከነ’ እያሉ መለፍለፍ ምን ይባላል? ንጉሡ ይኸ ሁሉ ጠፍቸውና ነው? ደህና ዐርፎ የሚገዛውንና ሰጥ—ለጥ ብሎ የሚያድረውን ሕዝብ አጓጉል ነገር እያሰሙ አገር ሊበጠብጡብን ነወዴ! እኔ ብሆን ሰብስብ አርጌ ወህኒ ነበር እማጉራቸው” ይላሉ በልባቸው ።

የምክር ቤቱን ጉዳይ ችላ ብለው ወደ ራሳቸው ሐሳብ ሲመለሱም ፣ “ምንጊዜም ራስን ከማስቀደም አለመቦዘን ፣ በማንኛውም ብልሃት እየገፈተሩና እየጐናነጡ ፣ ኑሮን ማቃናትና መካብ እንጂ ፣ ሰዎች ይቀየሙኛል ወይም አያ እንቶኔ ያስብልኛል ብሎ መዘናጋት እያደር መሸርሸርና ፍጻሜ ማበላሸት ነው” የሚለው የአቶ ወርቅነህ አባባል ቀልባቸውን ከመቀስቀስ አልፎ እንደ በቅሏቸው ይዟቸው ይሰግራል ። ወደ ከተማ ዘግይተው በመግባታቸውም ፣ “ዕድሜ ልኬን ከማንም ነሁላ ባላገር ጋር ታረመ እንዴ ተገመሰ እያልኩ ስነታረክና የስልቻ እህል ስቆጥር ፣ እዚህ ስንቱ ግፍንት ሸቅብ ወጣ! ”በማለት ይጸጸታሉ ። ዕድሜያቸውን ሲያስቡትማ ምን ያህል ቀረኝ በሚል ስሜት በንዴት ቢል ይላሉ ። አእምሯቸው ተረጋግቶ ቀልባቸው ሲሰበሰብ ደግሞ ፣ የፍላጐታቸው ማስፈጸሚያ ፈር በሁለት ይከፈላል ።

አንዱ ፣ ገንዘብና በገንዘብ አማካይነት በሚገኙ ሰዎች በኩል ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ በዝምድናና ባገር ልጅነት ድጋፍ ሊካሔድ የታቀደ ነበር ። ለመኖሪያ ቤት መግዣ የተከፈተው የብር ማሰሯቸው እያደር አፉ እየሰፋና እየተዘረገፈ የሚከራይ ሦስት ክፍል ቤት ገዙ ። ፓርላማው ለዕረፍት ከመዘጋቱ በፊትም የሦስት ክፍል ቤት ኪራይ ሲቀበሉ ፣ “እንዴት ተጎድቼ ኖሯል? የማትነጥፍ ላም ማለት ይቺ ነች! ቆይ—ቆይ—ቆይ—ቆይ!” አሉ ።

ጉዳዩ ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱን የማይመለከታቸውና መብታቸውም እንዳልሆነ ሁሉ ፣ ግዢው ሲጀመርም ሆነ ሲፈጸም አልተነገራቸውም ። ሴትዮዋም ቢሆኑ ሰውዬው ወይዘሮ ደጅ—ይጥኑን ከወሸሙ አንሥቶ ትዳራቸውን ሳይሆን ቅናታቸውን ስለሚያሰላስሉ ፣ "ሀብትና ንብረት ቢበዛ ለኔ ምኔ ነውን የማንም ጋለሞታ ተጋምሳ ልትበላው ለማባቱ ብዬ እለፋለሁ" ስለሚሉ ፣ እንዴት ሆነና ምን ተደረገ ማለቱን ትተውታል ። በዚህም የተነሣ ሞልቶ ቢከነበል ፣ ተጢያጢሶ ቢቃጠል ደንታ አልነበራቸውም ። እንዲያውም ለጣውንታቸው እህል መላኩን ከሰሙ ፣ እሳቸውም በድግስና በጠበል—ጠዲቅ ስም ጐተራ አስከፍተው አጠፌታውን በመዛቅ እልኻቸውን በገዛ ንብረታቸው ስርቆት ሲወጡት ቆይተዋል ። ብሶታቸውን አድምጦ ቁጭቱን ለገለጸላቸው አንዳንድ ተቆርቋሪም እጃቸው ዝቆ ጥርሳቸው ሥቆ ይሸኙዋል ።

ምንዳዬ ፣ የአዲሱን ቤት አትክልት ለማሳመር ዘወትር እንደ ኮትኮት ፣ ግቢውን በጨፈቃ ቢጤ እንደ ፎከተ ነግቶ ይመሽለታል ። በዚያውም ሐሳብና ብቸኝነት ፣ ትዝታና ናፍቆት በየተራ ይቀራመቱታል ። ያ እንዳሻው ሲዘዋወር የኖረ እግሩ ተሰንክሎ ፣ ያ የሚስት ፣ የልጅና የጓደኛ ፍቅር የለመደ ልቡ በመታፈኑ ፣ ስሜቱ ቀዝቅዟል ። በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ስለማያውቅ ሐሳብ ገባው ። ሴትዮዋም ሰው ሲኖር መፍካቱን ፣ ጭር ሲል ፊት መንሣቱን ያውቁበትና ይገላባበጡበት ጀመር ። ሁኔታቸውን የምታውቀው ሸዋርካብሽም ነገሩ ስለገባት ምሳውን አቅርባለት ዘወር ፣ ራቱን አድርሳለት መለስ ማለት ጀመረች ። እሳቸውም የምታቀርብለትን ምግብ ፣ የምትቆነጥርለትን ቆሎ አየት ያደርጉና ፣ "አንቺ እንደሁ አሳብ የለሽ ! ቢያልቅ—ባያልቅ አንቺ ምን አሻሽ? ምን አረግሽው ለማን ሰጠሽው እያሉ እሚያንገበግቡኝ እኔን ——" በማለት የሚሰጠውን ምግብ መገመት አበዙ ። ለሱ ግን ፣ አካባቢውን መልመዱ በጀው ። ያቺን ምንም ያህል ያልተቆነጠረላትን የራሱንና የቸርነትን ብር ፣ የከፋው ለት መመኪያ ፣ የራበው ዕለት መተኪያ እያደረገ ተጋደደ ። የኑሮው ማነቆ ግን እያደር ጠበቀ ።

አንድ ቀን ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱ ፣ ሸዋርካብሽን አስከትለው ዘመድ ጥየቃ እንደሔዱ ፣ ቀኛዝማች ባጋጣሚ ወደ ቤት ይመጣሉ። በተደጋጋሚ የተመኘው ቀን ነበር ። ተከትሎአቸው ገብቶ ስለነበር የቀድሞው ቀኛዝማች አልመሰልህ አሉት ። እየወደዳቸው ፈራቸው ። ሊናገር ያሰበውን ትቶ ሊመለስ ሲል የሚስትዬዋ ፊት ታየውና ከቀኛዝማች ፊት ለፊት ቆመ ። ቀና ብለው በጠያቂ ገጽታ አዩት። ዳሩ ምን ያደርጋል ፣ ይሉኝታና ያልታሰበ ፍርሃት አንደበቱን አፈነው ። የመጣበትን ጉዳይ ትቶ ፣ "አሁን መጣሁ ብለው ነው ከሷ ጋ ወጣ ያሉት ፣ እስታሁንም እቆያለሁ አላሉ ነበር" አለ በልልኝ ያላሉትን በመናገሩ ራሱን እየታዘበ ።

"ቆይታለች?" አሉ በደንታ ቢስነት ።

"ኧረ ጥኢት ነው ቆየት ያሉት ፣ ያጋጣሚ ሆኖ ወጣ ከማለታቸው — —"

"በል እንግዲያው ትንሽ ጋደም ልበል — — ደከሞኛል" ብለው ወደ መኝታ ቤት ገቡ ።

"እስቲ ምን አስፈራኝ? አልቀጠፍኩ ፣ አልሰረኩ ፣ ምን በወጣኝ ነው እንዲህ መሆኔ? ለዚያውም እኮ እንግልቱ ላይቀርልኝ! የህል—ውሃ ጉዳይ ሆኖ ነውዬ ፣ የትስ ይኖር አልነበር" ብሎ አጠና አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ተከዘ ።

* * *

ከአንድ ወር በኋላ ሌላ አጋጣሚ አገኘ ። እንደከዚያ ቀደሙ አልፈራም ። "ዛሬስ የልቤን ተናግሬ ይለይልኛል" ብሎ ከቀኛዝማች ፊት ቆም እንዳለ ፣

"ምነው ይኸን ሰሞን ደህና አይደለህም እንዴ? ቅር ያለህ ትመስላለህ?" አሉት ትኩር ብለው እያዩ ።

"አይ!—— ለደህንነቱስ ደህና ነኝ" አለ ቅሬታው በፊቱ ላይ እየታዩ ።

"ቅርስ—ቅር ያለህ ትመስላለህ ፣ —— ምን ሆነሃል? ንገረኝ!" አሉት ሁኔታውን እያጤኑ ።

"አንቱም አልተመቸሁ ብዬ ነውዬ ፣ ቅሬታማ ምን ይጠፋል ! እንዲያው ተዛሬ ተነገ እነግርኋለሁ ስል ——" ብሎ አንገቱን ሰበር አደረገ ።

"አትነግረኝም ኖሯል ታዲያ? —— ንገረኝ ምን የቸገረህ ነገር አለ?"

"ያው ስለ ራሴው ችግር ነው" አለ ።

"ምንድን ነው ችግሩ? —— ልጆችህ ናፈቁህ እንዴ?"

"መናፈቅማ የት ይቀራል? በያ ሰሞን ወረኸት እስጥፈ ልኬላቸው ነበር ። እነሱም ወዲህ የሚመጣ ሰው አጥተው ነው መሰል ፣

"ጤናም አልያዛት እንዴ ? በይ ልሒድልሽ እቴ ! ባልና ሚስት
ታንድ ምንድን ነበር ይቀዳል እሚሉት ? — — ያኗትን ትታ ያላ
ኗትን" ብሎ ብድግ አለ ።

"ካንድ ወንዝ ይቀዳል ነው ። መቼም ያለኔ አይሆንልህ" ብሎ
ጣልቃ ገባና ፡ "ምንድነው ነገሩ? ለኔ ንገሩኝና ልገላግላችሁ ። ባይሆን
የዳኝነቱን ትከፍላላችሁ ።"

"ማ ቢያቀምስህ? የምን ጠጋ—ጠጋ ነው — — — እኔና እሱ
እንተዋወአለን!" ብላ ቸርነትን ጉትታ አስቀመጠችው ። እንደ ቆመ
ችም ፡ "ጥሩ ነገር በማድረግህ ምን አስፈራህ? እንዲያውም ባንተ እጅ
ያምራል ። እኔ በናንተ መኻል ምን ዶለኝ ።"

"ምንድነው ነገሩ? ይኸነዬ እኮ አርቲ—ቡርቲ ይሆናል — —"

"መስሎሃል? ምንም ይሁን ምን ፡ ምን አስቸኮለህ? — — ቀስ
ብለን ኮርተን" አለች እየሣቀች ።

"አይ ያንቺ ነገር! ደሞ አደራሽን ስል መዋሌ ። ለዚህ—ለዚ
ህማ ምን አለፋፋኝ" አለ ቸርነት ።

"እንዲያውም አልሰማ! ለምናችሁ ትነግሩኝ የለ! — — ያለኔ
አይሆንላችሁ" ብሎ ምንዳዬ ሣቀ ።

"እንዴት ተጎዳን እቴ? አንተ አልሰማ አልክና ጉዳያችን አይነ
ቅዝ ፡ እኛም ሳናስደገድግ አንነግር" አለችው ።

"ታዲያ ምን ልበል? እንዳንዳንደዬው የነቀኛማይ ወሬ ነገራች
ሁን ጥፍትፍት ስታረጉት ፡ አቄላችሁኝኮ!"

"ይልቅዬ ቀልድህን ትተህ ፡ የምነግርህን እህ በልና —— እሺ
በለኝ!"

"ብያለኋ! ያለኔ አይሆንላችሁ ። ለእሺውም ፡ ለእምቢውም እስቲ
መጀመሪያ ይሰማ ነገሩ?"

"እምቢ ብሎ ነገርማ የታል? እማይባለውን! ለዚያውም ቢሆን
በመጀመሪያ ልኬለሽ ሙች ብለህልኝ ነው ። እንዲህ በዋዛ እንላቀቅ
መስሎሃል!" ስትል ቸርነት ቀና ብሎ አያት ።

"ወይ ጣጣዬ! ነገሩን ሳላኸው ፡ ሙችና አትሙቺን ምን አመ
ጣው?"

"ነገሩማ ይነገርሃል — — — የት ይቀራል ።"



"እንቱል አስምለሽኝ የማይሆን ነገር ተሆነስ? ይኸን እያስማሉ
መንገር ተውኝ አላልኩምይ!"

"አዬ! ምነው በቁሜ ገበያ ባታወርዱኝ ። አሁን ማ ይሙት
ቸርነት ቢጠይቅህ እምቢ ትለዋለህ?" አለች ኮስተር ብላ ።

"እሱ'ስ እውነሽን ነው እምቢ አልለውም ። ታዲያ እምቢ አይ
ልም እያላችሁ እንደ ሞኝ — — —"

"እኛ ሞኝ ነህ አላልንም! ያውም አንተን? ምን ቅብጥ ቢያረገን!
ይልቅዬ በይ ሙች በልና ይነገርህ ። ቀላል መስሎታል?"

"ግድየለሽም ስልሽ!"

"አይይይ! ምንድነው እቴ ምንችክ ማለት!"

"በይ ደስ ይበልሽ! እላለሁ ።"

"እላለሁ ከማለት አትለውም?"

"ልኬ ሙች!" አላት በቁም ነገር እየሣቀ ።

የቸርነት ልብ በደስታ ተከብባ ነፍሱ ተነፈሰች ።

"እንግዲያውማ ቸርነት እንዲህ አረገልህ — —" ከማለቷ ሁለ
ቱም ትኩር ብለው አዩዋት ።

"ምን አረገ ልጄ?" አላት ቶሎ ብሎ ።

"ከሰውዬው ጋ አዲሳባ ልትሔድ ነው ማለትን ተሰማ ጀምሮ
አብሶ ይኸን ሰሞን ግራ ግብት ብሎታል ። ሰማይ መሬቱ ድፍት እሚ
ልበት ነው የመሰለው ። ከኔ ብሶልሃል ። ዛሬ ሳያመው የውሽቱን አመ
መኝ ይልልህና ያቺኑ ጤፍና ቀጠጦውን (ማሽላ) ሸጥ አርገ ፡ ለምንዳ
ስጪልኝ — — —" ብላ ንግግሯን ሳትጨርስ እንባዋ ዝርግፍ አለ ።
ቸርነት አቀረቀረ ።

"ተቀበልሽው እንዴ ?" አለ አሻቅቦ እያየ በዝግ ገጽታ ።

"እሱንማ ልነግርህ አደል? አይሆንም ብዬ ብለው ብሠራው ፡
እምቢ አለኝ ። እምቢ ሲለኝ ምን ላርግ ትለኛለህ ?" ብላ ወደ ጓዳ
ስትገባ ሁለቱም ባይናቸው ተከተሏት ። እንደ ተመለሰችም ምንዳዬ
ሳያስበው የተጠቀለለውን ገንዘብ አስጨበጠችው ። ደነገጠ ። ቀለላት ።

ምንዳዬ በሐሳብ ፡ ቸርነት በደስታ ተዋጡ ።

ፀሐይዋ ዘቅዘቅ ፣ አየሩ በረድ እንደ ማለት ሲል ፣ የቀኛዝማች ጓዝ ተጭኖ መንገድ ገባ ። ወዲያው ሽኝና አጃቢው ሁሉ ከያለበት ተሰበሰበ። ልኬለሽ ገና አሁን ቁርጧን ያወቀች ይመስል በረዥሙ ተነፈሰች ። ልወደድ ባይና ዘመድ ፣ ኑሮ የፈጥኝ ያሰረው ተጋዥ ገበሬና ሎሌ ፣ በተለይም ዋና ቤተኛ ልምሰል ባዩ ፣ እነ ቀኛዝማች የሚቀመጡባቸውን በቅሎዎች እየሳበ ፣ ሌላው አጃቢ ጠበንጃውን ይዞ ካጥር ውጭ መደዳውን ተገጠገጠ ። እነርሱም ረጋና—ኮራ ባለ አረማመድ እያወሩ ዋናውን አጥር እንዳለፉ ፣ ምንዳዬም ጠበንጃውን አንግቶ ፣ ቸርነትን ፣ ልኬለሽንና ልጆቹን እስከትሎ ከኋላው ብቅ አለ ።

ልኬለሽ ፣ የቤቷን በር ስትዘጋ የእንባዋ በር ተከፈተ ። ማንም ልብ አላላት ። ሁለቱ ሰዎች በቅሎዎቻቸው ላይ እንደወጡ ፣ ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱና አንዳንድ ሰዎች እየተሰናበቱ ተመለሱ ። ሌላው ከበቅሎ ፊትና ኋላ እየሆነ መንገድ ገባ ።

ልኬለሽ ፣ ልጆቿን አስከትላ ጥቂት እንደ ተጓዘች ፣ ምንዳዬ ክንዷን ያዝ አደረገና ፣ "በይ ተመለሺ ። ለልቅሶና ለእንቅፋቱ ከሆነ ይበቃል!"

"ማ? ሀ! እኔ ነኝ ተመላሿ? ምነው በል ፣ ምንስ ቢሆን መኪና ላይ መውጣትህንና ከሳቸው ጋ በደህና ምንገድ መግባትህን ባይኔ ሳላይ ነው ፣ ነፍሴ በጇ ብላኝ እምመለሰው? እንቅፋትም አይመታኝ ፣ ራመድ—ራመድ እላለሁ ። ለልቅሶውም አታስብ ። እንዲህ ልኩን ሳቀው እርፍ እል የለ? ግድየለህም አታስብ ፣ ይልቅ ሒድ እንሒድ!"

"ቤቱን ለማን ትተሽው? ልጆቹስ?"

"እኛም አብረን እንሔዳለን ፣ አይደኽመንም" አለ ትንሹ ያባቱን እጅ እያሻሸ ።

"በሉ ኑ እንሒድ ፣ መንገዱስ ምንም አደል?" አለ ቁርጡን ዐውቆ።

ቸርነት የመለየት ስሜት አፋን ሸብቦት ፣ የምንዳዬን ስንቅ አንጠልጥሎ ይከተላል ። ከነሱ ኋላ ሌላ ሰው አልነበረም ።

ጥቂት እንደ ተጓዙ ፣ ምንዳዬ ትንሹን ልጇን እንኮኮ አለው ። መንገዱ ሳይታወቃቸውና የሔዱ ሳይመስላቸው ማጀቴ ደረሱ ። በመጀመሪያ ሁሉም ቀኛዝማች ከገቡበት የዘመድ ቤት ገብቶ ዐረፈ ። የማታ ማታም ወደየዘመዱና ወደየሚያውቀው ሰው ቤት ሲበተን ፣ ምንዳዬም ከጓደኛው ጋር የሚያድርበትን ቦታ ነግሮ አስፈቀደ ። ልኬለሽ ልጆቿን ፣ ምንዳዬንና ቸርነትን ይዛ ማጀቴ ዶር — አምባ ከሚኖሩት ዘመዷ ቤት ገባች ። ጥሩ መስተንግዶ ተደርጎላቸው ሲያወሩና ሲያወኩ ሌሊቱ ተጋመሰ ። ለሁለቱ ወንዶች አልጋ ተለቀላቸው ፣ ልኬለሽ ከነልጆቿ ጀንዲ ተነጥፎላት ከባለቤቲቱ ጋር ወለሉ ላይ ተኙ ።

ዶሮ ደጋግሞ እንደ ጮኸ ሴቶቹ ተነሥተው ፣ ባለቤትዮዋ ምጣድ፣ ልኬለሽ ድስት ጥደው ሲጣደፉ ወፍ ተንጫጫ ። ወገግ እንዳለ እነ ምንዳዬ ፊታቸውን ታጠቡ ። ካማን አውለኛቸው በኋላ ፣ ምንዳዬ ፣ ልኬለሽንና ቸርነትን ይዞ ወደ ጓሮ ዞረ ። ጠበንጃውን ባፈሙዙ ጨብጦ በእሱና በጓደኛው መኻል በሰደፉ ካቆመው በኋላ ፣ "ቸርነት" አለው ልብ በሚመስጥ ድምፅ ። "እንግዲህ የልኬንና የነአሻጋሪን ነገር አደራ! እኔ ብሔድ አንተ አለህ ። አንተ ካለህ ደሞ እኔ ያለሁ ያክል ነው ። ልጆቹን እንዳያስለቅሷቸው ። እሷንም እሱ ተሔደ ብለው እንዳያንከላፍቷት — አደራህን" ብሎ ዝም አለና ፣ "አንተም እንካ ዩኝን ቀኝ እጄን ፣ ጠበንጃዬን ። ወንድም የለኝም ወንድሜ ነው እንካ!" ብሎ በሁለት እጁ ሰጠው ።

ልኬለሽ ፣ ይሆናል ብላ ያልጠበቀችው ጉዳይ ቢሆንም ፣ የባለቤቷ ጠበንጃ ፣ እሷም ለምታምነውና እሱም ለሚወደው ባልንጀራው በመስጠቱ ምንዳዬ በከፊል አብሯቸው የቀረ ስለ መሰላት በጣም ደስ አላት። ቸርነት በጠበንጃው ሳይሆን በጓደኛው እምነትና ፍቅር ተመሰጠ ። የሚናገረው ጠፍቶት ዝም ሲል ዐይኖቹ እንባ ከተሩ ። ከቃላት የላቀ መልስ ነበር ። እየተለያዩ መዋሐጃ ፣ እየተዋሐዱ መኀልበቻ ።

"አታስብ ፣ እኔ እያለሁ ማባቱ ይነኻቸዋል ? —— አታስብ! አሁንማ ቀኝ እጅህን ወንድምህን ትተህልኛል ፣ ሁለዜም አብረኸኝ ነህ" ብሎ እንባውን ለማበስ ፊቱን አዞረ ። ምንዳዬ አንገቱን ሰበር ሲያደርግ ፣ የልኬለሽ ዐይን የእንባ ቦዩን ቀደደ ።

የአውቶቡሱ ጥሩንባ ፣ መንገደኞችን ለመቀስቀስ በተከታታይ ተነፋ ። ልኬለሽ ልጆቿን አስነሥታ አንድ ሁለትዬ አጉረሰቻቸውና አውቶቡሱ ወደ ነበረበት ገሠገሡ ። በመኪናው ዙሪያ ከተሰበሰቡት ሰዎች አንዳንዶቹ የሚጫን ዕቃ ወደ ላይ ሲያቀብሉ ፣ ሌሎቹ ኮተታቸውን እየቋጠሩ ፣ ካንዱ ወደ ሌላው እያጋቡ ያመቻቻሉ ።

ሞተሩ ተለኩሶ ፣ ጢሱ ቡልቅ—ቡልቅ ሲል ፣ መላ ብረታም አካሉ ተንዘፈዘፈ ። እነ ቀኛዝማች ወደ አውቶቡሱ ሲጠጉ ፣ አብዛኛው ሰው ገለል አለላቸው ። ምንዳዬና ቸርነት ጢጋ ብለው እጅ ነሡ ።

"ጥሩ ደርሰሃል ፣ እንግዲህ ነቃ—ነቃ ማለት ነው" ብለው ወደ አቶ ወርቅነህ ዘወር ሲሉ ፣ እነሱም ወደ ልኬለሽ መለስ አሉ ። ሊለያዩ ተያዩ ። አንዳንድ ሰዎች ወደ አውቶቡሱ መግባት ሲጀምሩ ፣

ያመልጠዋል ። በዚያን አኳኋን የሚያልፉት ልዩ ልዩ መኪናዎች ውልብ ሲሉ ትኩር ብሎ ያያቸዋል ። በሁለቱም አቅጣጫ የሚጓዘውን ሕዝብ አይቶ ፣ ‘እንዴት ያለ ትልቅ ገበያ ቢኖር ነው ቢጓዝ—ቢጓዝ እማያልቀው’ አለ በሐሳቡ ። አውቶቡሱ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሰሜናዊ በር ፊት—ለፊት ደርሶ እንደቆመ ፣ ጥቂት ሰዎች ጓዛቸውን እየያዙ ወረዱ ። እንደገና ወደ ቀኝ ታጠፈና ጥቂት ተጉዞ ቆመ ። እውታንቲው ወርዶ ወደኋላ ዞረና መኪናው ላይ ተለጥፎ የታዘለውን መሰላል ዘረጋው ። ቀደም ብለው የወረዱት ቀኛዝማች በተከፈተው የኋላ—በር ወደ ውስጥ ብቅ ብለው ፣

“ምንዳ! ደርሰናል እኮ! ናውረዲ!” አሉት ። ሲወርዱ ባለማየቱ ደንግጦ ተገረመ ። የስንቅ ከረጢቱን አንጠልጥሎ በፍጥነት ወረደና ዱላውን ይዞ ከበስተኋላቸው ቆመ ። የሚያየው ነገር ስለ በዛበት ግር አለው ።

ሁለት ዕቃ አውራጅ ሸቃዮች የቀኛዝማችን ጓዝ አውርደው አንድ ላይ ደበሩት ። “ይኸው ነው፣ የቀረ የለም?” አሉ አንጋጠው እያዩ ።

“የለም! ይኸው ነው!” አለ እውታንቲው ፣ ዕቃውን አስተካክሎ ሸራውን እየዘረጋ ። አውቶቡሱ ጉዞውን ሲቀጥል ፣ ምንዳዬ ትኩር ብሎ እያየ ባይኑ ሸኘው ።

በተቀለለው ጓዝ ዙሪያ የቆሙት ደረተ—ገላጣና ጭቅቅታም ጸጉረ እንጭብር ፣ አዳፋ ለበሶች ፣ ፍም የመሰሉ ዐይኖቻቸውን አጉርጠው ያያሉ ።

“በነዚህ በቀፈታሞቹ ይብሳል ፣ ምድረ—አባሕና !” ይላሉ እንደ ተለመደው ። የሦስቱም ሱሪ እተለያዬ ቦታ ላይ ተቀዳዶ ፣ በማይመሳሰሉ ጨርቆች ተጥፏል ። የጀርባና የትከሻቸው ላይ ልብስ ፣ የቀድሞ ቀለሙ ጠፍቶ ጤፍ መስሏል ። ምንዳዬ የቀኛዝማች ሎሌዎች መስለውት በአቀባበልና በሁኔታቸው ተገርሟል ። “ያዲሳባ አሽከር ጌታውን አያከብርም ማለት ነው? ምን ይመሳሰላሉ ደሞ ?” ብሎ በንቀት አያቸው ። አንደኛው ኩሊ የቀኛዝማችን ግቢ የብረት በር አንኳኩቶ አስከፈተ ። ዘበኛው መንገዱን ተሻግሮ እጅ ነሣና ገለል ብሎ ቆመ ።

“ቤቱ ይኸ የምታዩት ነው” አሉ ቀኛዝማች ።

“እኮ ስንት ይከፍላሉ? ከአውቶቡሱም ላይ አውርደናል” አለ አንዱ አሸቦ ፊት ።



“እናንተ ተናገሯ! ብታወርዱም ቤቱ ቅርብ ነው!” አሉ አቶ ወርቅነህ ኮራ ብለው ።

“ባንዳንዱ ስምንት—ስምንት ፍራንክ ትከፍላላችሁ!” አለ አጠር ያለ ቀይ ዳማ ደንደሳም ።

“እንጦጦ አድርሱልን እኮ አላልናችሁም! ቤቱ ይታይሃል!” አሉ አቶ ወርቅነህ ቆጣ ብለው ።

“እንጦጦ ድረስማ ሦስትና አራት ሰይቼንቶ ያስፈልጋችኋል” አለ አንደኛው የተመለመለ አጠና የመሰለ ከሲታ እየሣቀ ።

“የምን ንትርክ ነው! ትወስዳላችሁ አትወስዱም!” አሉ ቀኛዝማች ጮክ ብለው ።

ምንዳዬ ፣ ሰውዬው ሲቆጡ በማየቱ ዱላውን ጠበቅ አድርጎ ተመቻችቶ ቆመ ። ማንም አላየው ። ኩሊዎቹ እርስ በርስ ተመካከሩና ፣ “በሉ ስድስት—ስድስት ፍራንክ ትከፍሉናላችሁ” አለ ቀይ ዳማው ደንደሳም ።

“ትወስዱ እንደሁ ውሰዱ! አለበለዚያ ዞር በሉ ከዚህ! እንግዶች መሰልናቸው እንዴ ፣ ከነሱ እኩል ቆመን ስናወራ ጊዜ?” አሉ አቶ ወርቅነህ ደማቸው ፈልቶ ።

ኩሊዎቹ ተበሳጭተው ገለል—ገለል ሲሉ ፣ አንዱ ወደ ምንዳዬ ቀረብ በማለቱ፣ “ወሒድ ታጠገቤ!” ብሎ ዱላውን እዙሮ አፈጠጠበት።

“ይቺ ፋርጣ እንዳትነፋሽ! እነሱ ጋ ቀልድ የለም” አለ ቀጭኑ። እነቀኛዝማች ሣቅ አሉ ።

“በሉ እናንተ እንዳላችሁ ። ዛሬ ቤሽቲያ ቀን ነው! እናቱን! ጮርናቄና አቦስታ ከተገኘ ይበቃል” ብሎ አጠር ያለው ወፍራም ሊሸከም ጐንበስ ሲል ፣ አንዱን ስልቻ ጤፍ አሸከሙት ። ሦስት ሦስት ጊዜ ተመላልሰው አደረሱና ፣ ከዘበኛው ጋር አጥሩ በር አጠገብ ቆሙ ። እነቀኛዝማች ወደ ግቢ ገባ ብለው ፣ “በደንብ አስቀመጡት?” አሉት ዘበኛውን ።

“አዎ” አለ ባጭሩ ።

ምንዳዬ ፣ መንገዱን ከተሻገረ በኋላ አብሮ ወደ ግቢ በመግባት ፋንታ ፣ ካጥር ውጪ ግንቡን ተደግፎ ቆመ ። ኩሊዎቹ ገንዘባቸውን ተቀብለው ሲወጡ ፣ ወፈር ብሎ ዐመድ የነዛበት መሳዩ ፣ ምንዳዬ በማያውቀው አኳኋን ከእጅና ከትከሻው እንደ መናጥ መንዘር

"እኔስ ደስ ብሎኝ መስለህ? ሰው እሰው አገር ተኸምጦ — —" ከማለቷ ፣

"ማነው የሰው አገሩ ሰው? ይኽ ጀምበር ከጠለቀች እሚደረስ በት አገርሽ ሩቅ ሆነና ነው እንዲህ እምትዪው?" ብሎ ሊቀጥል ሲል ፣ አሻጋሪ ከወደ ደጅ ብቅ አለ ። "እየሁ ኖረሃል እንዴ አሻጋሪ" አለ ቸርነት ወደ ውጪ እያየ ።

"እማምዬ ተየህ ተግቢ ትወጣና — — ዋልህ ብላኝ — — እየሁ ነው የዋልኩት" አለ ተናዶ ።

"ምነው ልጄ? ምን አጠፋ?"

"ምነው ነገሩን ስታኸው? ፈራኋ?" አለች ተክዛ ።

"እነማንን?"

"ካፈሣ ጋር የመጡትኮ የዞን አምባ ሰዎች ናቸው ፣ ባላጋሮቻችን አይደሉሚ!"

"እስቲ ሙት በይኝ! እኔ የታባቴ አወ ኩ?" ብሎ ወዲያው ተነሥቶ ሔደ ።

ጠበንጃውን ይዞ እንደ መጣ ፣ "አሻጋሪ! ና ሒድ ውጣና ተጫወት! ማባቱ እንደሚነካህ አያለሁ! ሱሪ አልታጠኩማ!?" ብሎ ካጥር ውጪ ይዞት ወጣና ፣ "ሒድ ከባልንጀሮችህ ጋ ተጫወት" አለው ። ልኬለሽ በአለኝታነቱ ተደሰተች ።

ቸርነት ከአፈሣ ቤት በታች ዲብ ላይ ተቀምጦ ፣ ረባዳው ጠባብ ሜዳ ላይ የሚጫወቱትን ልጆች ሲመለከት ደስ አለው ።



## ምዕራፍ ሠላሳ ዘጠኝ

ምንዳዬ ፣ አንድ ሁለተዬ ቀኛዝማችን ተከትሎ በሔደበት ጊዜ ባየው የከተማ ሁኔታ በጣም በመገረሙ ፣ ሰውዬው ወጣ ባሉ ቁጥር ፣ "ምነው ና እንሒድ ባሉኝ" በማለት ተከትሎ ለማየት በጣም ይጓጓ ጀመር ። በተለይም አንድ ቀን ቀኛዝማችና አቶ ወርቅነህ መዘውር ምንዳዬን አስከትለው በራስ ሙኮንን ድልድይ አልፈው ፒያሳ እንደ ደረሱ ፣ ስን ኳንና አዲስ መጤው ምንዳዬ ቀርቶ ፣ በተደጋጋሚ ተመላልሼ አይቻ ዋለሁ ሲሉ የኖሩት ቀኛዝማች እንኳ በሚያዩት ልዩ ልዩ ብልጭልጭ የዕቃ ዓይነትና ብዛት ፣ በየሱቁ የተደረደረውን ልብስና ፣ ሽክ አርገው አልብሰው ያቆሟቸውን አምሳለ—ፈረንጅ አሻንጉሊቶች ሲመለከቱ በጣም ገርሟቸዋል ። የሱማ ምኑ ተነግሮ! እነ ቀኛዝማች ከአንድ መደብር ፊት—ለፊት ቆመው ፣ "ይኸኛው ይሻላል ፣ ያኛው ይጠነክ ራል" እያሉ የሱፍ ጨርቅ ሲያማርጡ ፣ ምንዳዬ ግን ዳለቻ የሱፍ ልብስ ለብሶና ባርኔጣ አድርጎ ፣ አንድ እጁን እሱሪ ኪሱ ውስጥ ወሽቆ የቆመውን መጠነ—ሰው አሻንጉሊት ትኩር ብሎ ያይ ነበር ።

በመጀመሪያ ፣ "እንዴት አምሮበታል ይኽ ፈረንጅ! አዬ አቋቋም ሆዬ!" አለ ። ነገር ግን ፣ ቢያየው ቢያየው ንቅንቅ አይልም ። "አቤት አሠለጣጠን! እንዴት ሰው እንደዬ'ንኳ ንእንቅ አይልም!" እያለ ሲገረም ፣ ለካስ እነ ቀኛዝማች መንገድ ቀጥለዋል ። ደግነቱ አልራቁም ነበር ።

የሰዉና የመኪናው ብዛት ፣ የቤቱ ንጽሕናና አሠራር እየገረመው ሲከተል ሌሎች አሻንጉሊቶችም በማየቱ ፣ "እንዴት ፈረደበት ይሄ ሁሉ ፈረንጅ ወንድሜ" እያለ ሲያዝግም ፣ አንድ ሱቅ በር ላይ እንደ ደረሱ ፣ አንድ ሽማግሌ ፈረንጅ ብቅ አሉ ። ምንዳዬ ትኩር ብሎ አያቸውና ፣ እስከዚያች ቅፅበት ያልታየው በቀል ትዝ ስላለው ብልጭ አለበት ። ወዲያው ጉዞ በመቀጠላቸውና ከሌላ ትርዒት ጋር በመገናኘቱ ትዝ ታው ጥሎት ነጎደ ።

አንዳንድ ቀን ከቀኛዝማች ጋር ወደ ፒያሳ ወይም ወደ አራት ኪሎ ሲሔድ ፣ የገረመውን ነገር መለስ ብሎ ወይ አሻግሮ ሲመለከት ፣ ሳያስበው ከሰው ጋር ይጋጭ—ይጋፋና በጣም ይደነግጣል ። ገጠሬነቱን የተገነዘቡ ሣቅ ብለው ያልፉታል ። አንዳንዶቹ የየራሳቸው የቀድሞ

ሞገስ እምባቸው፣ ስለ ምንዳዬ ማንነትና አኗኗር፣ ከገዛ ባለቤቱና ከቀኛዝማች ከሰማበት ዕለት ጀምሮ ያ ያንድ ሰሞን ቅናትና ጥርጣሬው ወደ ልባዊ ርኅራኄ ተለውጦ ወዶታል። ወደ ቀኛዝማች ቤት በሔደ ቁጥርም፣ አትክልት የሚያይና አካባቢውን የሚቃኝ መስሎ እንደዘበት በማውራት፣ የምንዳዬን ጠባይ ከተረዳ ወዲህ በወደደ ሰሜትና በፈገግ ፊት እጁን ዘረጋለት። ሁለት አርጀት ያለ ካኪ ኮትና ሱሪ ከነሸሚዙ የሰጠው ዕለት እንኳን ተቀባዩ ቀኛዝማችም ደስ ብሏቸዋል።

"አሁን ምን አርጌልሁና በምን አቀሁኝ ነው ይኸን ኩላ አምጥተሁ መስጠትሁ?" ብሎ ሲያመሰግን፣ "እንደ ትልቅ ስጦታ አትየው፤ ቀላል ነገር ነው፤ ለወደፊትም እረዳሃለሁ" አለው።

ልብሱን ማደሪያው ውስጥ አስቀምጦ፣ አንዳንድ ቀን ሥራውን ሲጨርስ እየቀያየረ መልበስ ጀመረ። ቦላሌውን ታጥቆ ሸሚዙን ወደ ውጭ ይለቅና፣ ቁልፎቹን በሙሉ ይቆልፋቸዋል። ኮቱን ሲለብስበት ደግሞ ሸሚዙ እሱሪው ላይ ይለጠፍና ጠርዙ ይጠቀለላል። ይህን ዋል አደር ብሎ አረመ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፣ የሸሚዙ አንገትጌ ሸቅብ ታጥፋ ትቆምና የነጭ ፍየል ግልገል ጆሮ ትመስላለች።

ቀኛዝማች፣ ከላይ ደህና ለብሶ ያለ መጫሚያ የሚከተላቸውን ምንዳዬን ለማስደሰት ተረከዙ ባንድ ወገን የተበላ አሮጌ ጫማቸውን ሰጡት። ያን እንደልቡ እየተዘረጋ እንዳሻው ሲረግጥ የኖረ እግሩን አሮጌ ሸፍን ጫማ ውስጥ ያለ እግር ሹራብ ይደነቅርና ጥርቅም አድርጎ ያስረዋል። ልብሱን ቀይሮና ጫማውን አጥልቆ ቀኛዝማችን የተከተለ ዕለት፣ አንድ እጁን ሱሪ ኪሱ ውስጥ ከትቶ ሲሔድ በጣም ደስ ይለዋል።

ሸዋርካብሽ፣ ቀደም ብላ ምስጢሩን የማታውቀው የመልእክት ጉዳይ ያስከተለባት ችግር እያንገበገባት፣ ቀስ በቀስ መግባባትን ሊፈጥር በሚያስችል ሁናቴ፣ ከምግብና ከመጠጡ ደበቅና ጠቀም እያደረገች ትሰጠው ጀመር። በሴትዮዋ ሰበብም ያቄመባት ስለሚመስላት፣ እሷ እንዳሏት አዳሪና በይ እንዳሏት መስካሪ መሆኗን እንዲያውቅላት በሰበብ ባስባቡ ጢጋ ጢጋ አበዛች። አልሸሻትም። ሲወጡላት ሔዳ ማውራትና ሲያስቀይሟትም ጢጋ ብላ ማማት ጀመረች። እሱም ቀስ በቀስ ነገሩን እየተረዳ፣ ከቀን ወደ ቀን ልቡን አላላላት።

* * *

ቀኛዝማች በላይነህ፣ ኑሮአቸውን የማሻሻልና ከነእከሌ እኩል ወይም በላይ መሆን አለብኝ የማለቱን ውጣ—ውረድ አመቺ በመሰላቸው ጊዜና ቦታ ሁሉ ተያይዘውታል። የከተማ ኑሮ ዕውቀትና ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር በተዋወቁ ቁጥር፣ እንዴት ባለ ብዙ ንብረት ለመሆን እንደቻሉ ለመስማትና ለማወቅ፣ ሁለመናቸው ጆሮና አእምሮ ይሆናል። ከዓላማቸው ጋር የሚጣጣም ሰው ካገኙ ደግሞ እጃቸው የልግስና መዓዱን ያወርደዋል።

በገጠር ያሳለፏቸውን አያሌ ዓመታት በከንቱ እንደ ባከኑ በመቁጠር፣ የኑሯቸው ሥርና ግንድ የሆነውን ሕዝብና አካባቢ እያማረሩ ይጸየፉታል። የፍላጐታቸውን ማከናወኛ መሰላል ግን እዚያው መሬት ላይ ተክለው፣ በገጠሩ ሕዝብ ትከሻ ላይ ይረማመዳሉ።

"ሰሙ ቀኛዝማች" አለ ሞገስ አቶ ወርቅነህ ቤት ተቀምጠው ሲያወሩ። "ዛሬ እርስዎን በጣም የሚጐዳዎት ይኸ በየወሩ የሚከፍሉት የቤት ኪራይ ነው። ቀላል ገንዘብ አይደለም። በአራትና በአምስት ዓመት ራሱን የቻለ ቤት ያሠራል። እናም የመጀመሪያ ሥራዎ የመኖሪያ ቤት መግዛት ቢሆን ጥሩ ነው" አለ።

"እኔም ቀደም ብዬ ነግሬያቸዋለሁ" አሉ አቶ ወርቅነህ ለማስታወስ ያህል።

"በሱማ ምነው ተስማምተን! አካባቢው የጨዋ ሠፈርና ውካታ የሌለበት እንዲሆንልኝ በማለት ነው ረጋ ያልኩት። አሁን ያለሁበትን ቤት የወደድኩት ስለ አካባቢው ነው" አሉ ቀኛዝማች።

"በኔ በኩል ሁለት ቦታ ተገኝቷል። የሚሻለንን መምረጥ የኛ መብት ነው። በዋጋም ረገድ የሚጎዳ አይደለም" አለ ሞገስ ኮራ ባለ ድምፅ።

ከተደጋጋሚ ምክክር በኋላ ጂማ፣ መንገድ የተገኘው መኖሪያ ቤት የተሻለ በመሆኑ ተገዛ። በአሠራር ደረጃውም ሆነ በቤቱ ስፋት መጠን ከተከራዩት ቤት ያነሰ ሲሆን፣ በምድረ—ግቢ ስፋት ግን ይበልጣል። ዋናው ቤት ከቀይ ጡብና ድንጋይ፣ የበስተጀርባዎቹ ትናንሽ ክፍሎች ከእንጨት የተሠሩ ናቸው። የዋናው ቤት ወለል በተላገ ሣንቃ የተነጠፈ ሲሆን፣ የፊት ለፊቱ ሰበሰብ ግን፣ በጠጠርና ስሚንቶ ድብልቅ የተስተካከለ ሻካራ ወለል አለው። ዋናው ቤት ቀለም ተቀባብቶ ከታደሰ በኋላ፣ የአዲሱ መኖሪያቸው ኰረቤቶችና ጥቂት እንግዶች በተገኙበት፣ ሰው ሳይበዛና ግብዣ ሳይንዛዛ ቤቱ ተመርቆ፣ ቀኛዝማች ቤተሰቦቻቸውን ይዘው ገቡ።

ቤቱ አነስ ያለ ሳሎንና የገበታ ቤት፣ ሦስት የመኝታ ክፍሎች፣ ከበስተጀርባም የዕቃና የሽንት ቤት፣ ሁለት ማድቤቶች፣ ተጨማሪ የዘበኛ ቤትና የሠራተኞች ማደሪያ አነስተኛ ክፍሎች አሉት።

እየመሰለው አይለያቸውም ። ሁሉቱም ልጆች ይከቡና አንዱ ከበስተ ጀርባው ትከሻውን ተደግፎ፥ ሌላው እግሮቹ መኻል ቆሞ ዐይን—ዐይኑን እያዩ ይላፋታል ። ቦታ ይቀያየሩና ይቀጥላሉ ። አይሰላቹም ። እንኳን የመታቸውን የሰደባቸውን ሲመቱ ይነግሩታል ።

"አንተ አብዬ ቸርነት፥ ይኸ ቀማቸው የጋሼ አፈሣ ልጅ ካልመታኋችሁ እያለ ያስፈራራናል ።"

"ለምን ልጄ? ምን አረጋችሁኝ ብሎ?"

"ምንም ታናረገው፥ እሱ ራሱ ነገር እየከጀለ ነው ።"

"ዝም አላችሁት እንዴ ታዲያ?" አለ ቸርነት ነደድ ብሎት ።

"ይቺ እማምይ የሱን ሳታይ እየተእጣችን ነውዴ —— እሳየው ነበር !" አለ ትልቁ በድጋሚ ።

"ልማታ ብሎ ሲመጣ አቀለጥመውም ኖሯል? ኧረይታባቱ! ከነካችሁ በሉት!"

"እሱ እኮ አባቱን እያየ ነውዴ እያእተኙም! የቀልድም የምርም ትንታግል እያነሣሁ አፈርጠዋለሁ! — —አባብይ ብሎ ቲጣራ እፈራና እሮጣለሁዴ!— —ሀሀ! አባቱ ከያዙኝ ይለቁኝ መስሎሃል? አንድ ኧንለታ ብቅ ቲሉብኝ ጊዜ — —" ብሎ ሳይጨርስ፥—

"እኔ እያለሁ ማባቱ ነው እሚነካህ! ፈሪ ከሆንክማ — —" ከማለቱ ቸርነት፥

"ምን ታረጋቸዋለህ?"

"እያረገውሚ!— —ካረገውማ እኔ ዐቃለሁ!" አለው ቸርነት ።

"ኧረ ተው እንዲህ — እንዲህ እያልክ የልብ ልብ አትስጠው?" አለች ልኬለሽ ።

"'ባለቤቱን ካልናቁ፥ አጥሩን አይነቀንቁ' አሉ ። ልጅኮ የወላጁን ፊት ነው እሚያየው፥ በኋቸው ይሉ እንደሆነስ ማ ያቃል? " አለ ከንፈሩን ነከስ አድርጎ ።

"እሱማ እውነክን ነው ። የሰው ሰው ሔደው እንዳይተነኩሱ ብዬ ነውዴ !"

"ይቺ እማምይ እኮ ነች፥ እንዲህ—እንዲህ እያለች እምታስፈራራን" አለ ትንሹ ።



"እናንተም ሳይነኳችሁ አትንኳቸው" አለ ቸርነት የልኬለሽን ፊት እየና ።

"የፈሪ ልጆች፥ አባታችሁ ሸሽቶ ሔዶ እያሉን አደል?" አለ አሻጋሪ በቁጭት ንዴት ።

"እየሽ! እየሽ ይኸን ነገር! ልጅ እኮ አይዋሽም! እነዚያም እቤታቸው ሲወራ የሰሙትን ነው ። የኛ አባት ሸሽቶ አያቅም! — — ውሸታሞች በኋቸው ። ሀ! 'የሳትን ልጅ ገለባ ጉበኘው አሉ!' " ብሎ ተናዶ ወጣ ።

* * *

እርም አይቀሬ ቤተሰቡን ይዞ አንደኛው አዳራሽ ውስጥ ከገባ ሰንብቷል ። አረጋሽ እልፍኙንና ሌላውን አዳራሽ ትዘናከትቢታለች ። ቸርነትም ለይስሙላ ቆጡን አጠባብቆ ሰው እያየው ወጥቶ ቢተኛም አካባቢው ጭር ሲልለት፥ እየወረደ ከአረጋሽ ጋ ማደር ከጀመረ ቆይቷል ። ድርጊቱን ቤተኛ ነኝ ባዩ ሁሉ ከመጠርጠር ዐልፎ ቢያረጋግጥም፥ አፍ አውጥቶ የተናገረ፥ ያገባኛል ብሎ "ሃይ!" ያለ ግን አልነበረም ። ቸርነት ቢናገሩት የሚመልስ፥ ቢቃጡበት የሚማታ በመሆኑ፥ ሁሉም አፉን ያዘ ። ምንዳዬ ቤትም እንደልቡ መግባት መውጣቱን፥ ማሳውን ማረሱንና ጠበንጃውንም መቀበሉን የተመለከተው አፈሣ የጎረጥ ይመለከተው ጀመር ።

# ምዕራፍ ዐርባ ሁለት

የቀኛዝማች ኑሮ በተስፋ ተከበበ ። ጥቅምና ዕድገት ማነፍነፍ ዋነኛው ተግባራቸው ሆነ ። ምክር ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው ሳለ ፣ ከልዩ ልዩ ባለሙያዎች የሚቀርቡ ጥናቶች ፣ ክርክሮችና ተቃውሞዎች ሲነበቡም ሆነ ሲነሡ በሙሉ ልብ አድምጠው አያውቁም ። አንዳንድ አባላት የሚያቀርቡት ሐሳብና ክርክር ከማናደድ ዐልፎ ፣ "እንዲህ ያሉትን ጋጠ ወጦች ለምን ያስገቧቸዋል ፣ 'ጭሰኛ ተጎዳ ፣ የጭሰኛ ግብር በዛ ፣ ሥራ አጥ በረከተ ፣ ሴት አዳሪነት ተስፋፋ ፣ ሕግና ፍትሕ ተንደለ ፣ የሕዝብ ገንዘብ ባከነ' እያሉ መለፍለፍ ምን ይባላል? ንጉሡ ይኸ ሁሉ ጠፍቸውና ነው? ደህና ዐርፎ የሚገዛውንና ሰጥ—ለጥ ብሎ የሚያድረውን ሕዝብ አጓጉል ነገር እያሰሙ አገር ሊበጠብጡብን ነወዴ! እኔ ብሆን ሰብስብ አርጌ ወህኒ ነበር እማጉራቸው" ይላሉ በልባቸው ።

የምክር ቤቱን ጉዳይ ችላ ብለው ወደ ራሳቸው ሐሳብ ሲመለሱም ፣ "ምንጊዜም ራስን ከማስቀደም አለመቦዘን ፣ በማንኛውም ብልሃት እየገፈተሩና እየጐናነጡ ፣ ኑሮን ማቃናትና መካብ እንጂ ፣ ሰዎች ይቀየሙኛል ወይም እያ እንቶኔ ያስብልኛል ብሎ መዘናጋት እያደር መሸርሸርና ፍጻሜ ማበላሸት ነው" የሚለው የአቶ ወርቅነህ አባባል ቀልባቸውን ከመቀስቀስ አልፎ እንደ በቅሏቸው ይዟቸው ይሰግራል ። ወደ ከተማ ዘግይተው በመግባታቸውም ፣ "ዕድሜ ልኬን ከማንም ነሁላ ባላገር ጋር ታረመ እንዴ ተገመሰ እያልኩ ስነታረክና የስልቻ እህል ስቆጥር ፣ እዚህ ስንቱ ግፍንት ሽቅብ ወጣ! "በማለት ይጸጸታሉ ። ዕድሜያቸውን ሲያስቡትማ ምን ያህል ቀረኝ በሚል ስሜት በንዴት ቢል ይላሉ ። አእምሯቸው ተረጋግቶ ቀልባቸው ሲሰበሰብ ደግሞ ፣ የፍላጐታቸው ማስፈጸሚያ ፈር በሁለት ይከፈላል ።

አንዱ ፣ ገንዘብና በገንዘብ አማካይነት በሚገኙ ሰዎች በኩል ሲሆን ፣ ሌላው ደግሞ በዝምድናና ባገር ልጅነት ድጋፍ ሊካሔድ የታቀደ ነበር ። ለመኖሪያ ቤት መግዣ የተከፈተው የብር ማሰሯቸው እያደር አፉ እየሰፋና እየተዘረገፈ የሚከራይ ሦስት ክፍል ቤት ገዙ ። ፓርላማው ለዕረፍት ከመዘጋቱ በፊትም የሦስት ክፍል ቤት ኪራይ ሲቀበሉ ፣ "እንዴት ተጎድቼ ኖሯል? የማትነጥፍ ላም ማለት ይቺ ነች! ቆይ—ቆይ—ቆይ—ቆይ!" አሉ ።

አዳፍኜ — —'' አሉ ወይዘሮ ደጅ — ይጥኑ ፣ ቀኛዝማች የከተማ ቤት እንደ ገዙና የገጠር መሬት እንዳገኙ በመደሰት ፈንታ ልባቸው በጥር ጣሬና በቅናት እየተኰማተረ ።

"አሁንስ ቢሆን ምን ጎደለብሽ? ዝናብ ሲጥል እኮ ነው ምንጭ በደንብ እሚመነጨው ፣ እንዲህ እምትጠራጠሪ ከሆነ በፊት ነበር መጠንቀቅ'' አሉ አቶ ወርቅነህ ነገር ሲጀምሩ ።

"ምን ጐደለሽ ትለኛለህ እንዴ ጋሼ? እስቲ ምን አገኘሁና ነው ምን ጐደለሽ የምባለው? ይኸን የማጀቴ ባቡር ፈጪ የማያጣውን ጹቄት አገኘሁና ነው ምን አጣሽ እምትለኝ? አበስ ገበርኩ እቴ! ይኸው ይኸ ቤትም ፣ ዕቃውም ያንተ ነው ። 'ዐይን አይቶ ልብ ይፈርዳል —' ለሳቸው ስል ስንቱን ሲሳዬን ትቼ —— ወይኔ!'' አሉ በምሬት ።

"እንግዲህኮ የናንተ ነገር ይኸው ነው ። እንደ ስብ ቶሎ ትቀልጡና ወዲያው ደሞ ወይኔ—ወይኔ! ምንድነው ባጭሩ መከንዳት? ሰውዬው ስንትና ስንት ነገር አስበዋል ። አንቺ ሌላ ነገር ታውጠነጥኛለሽ! እኔስ ምን እሠራ መሰለሽ? ላንቺም ቢሆን ብዙ ነገር አስበዋል ። እስቲ አሁን ላሚታ የሚያደርስ ምን ነገር ሠሩ? የኖሩት ገጠር ፣ ገና እየነጋላቸው ነው ። እዚያ ከኔ እኩል ማንም የለ ሲሉ ኖሩና እዚህ መጥተው ሲያዩት ጊዜ በጣም ተበሳጩ ። ገና ዛሬ አሐዱ ብለው መጀመራቸውና ያዝኩት ጨበጥኩት እያሉ ነው'' በማለት ቀኛዝማች በወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ላይ ያላቸውን እምነት ለማረጋገጥ በውክልና ቢጤ ፈገግ አሉ ።

"አንተ አታአቸውም ጋሼ! የዋዛ ሰው መሰለውሃል ። እኛ ሆድ ለሆድ እንተዋወቃለን ፣ አንተ ያየኸው ቆዳቸውን ነው ። እእእ! ሞኝ መሰለውሃል! እስቲደላደሉና እስቲመቻቹ ነው ። የያዙትን ሲይዙ ዐይናቸው ይባከናል ። እልህና ይሉኝታ ይዞኝ ነው በዳውላ እህል ዝም ያልኩት ። ስሙ ይቢቃኛል እያልኩ አብሬኖሬ ዐመላቸውን አጣሁትና ነው?'' አሉ የተሙኙት ሁሉ በከንቱ የቀረ እየመሰላቸው ።

"ግድ—የለሽም በኔ ይሁንብሽ! ትልቅ ግንድ ተፈልጦና ተማግዶ እሚያልቀው ቀስ በቀስ ነው ። አንቺ ብልሃቱን ሳታውቂበት እየቀረሽ ነው እንጂ ፣ ሚስትዬይቱንስ ማስወጣት መች ያቅትሽ ነበር! እልህ ያለ ብልሃት ምን ያደርጋል?'' አሉ መካሪና መሠሪነቱንም እየደባለቁ ።

"ሚስት ተብየዋማ ፣ አልሆን እያላትና የኔ መድካኒዓለም እየከለለልኝ ነውዪ — — ዋና ተብታቢ መተተኛ ነች ፣ እስተዛሬም በመሰንበቱ አገር ጉድ ይላል ፣ እሰው ቤት ሔጄ ተሰውጋ ታልሆን በቀር



እንዲች ብዬ አፌ አላረግ ! ጋኔኑን ቲያስለፈልፍና እንጨት ቲያስግዘው ፣ ውሃ ቲያስቀዳው እሚያድር ዘመድ እደጋው አገር ተጓሳው በላይ አላት አሉ ። እኔ ላይ ብቻ አልይዝልህ አለው መሰል ይኸው ደህና ነኝ ። ሰውዬው እንደሁ አሙን አሙን ሲሉ በምን ያገኛቸዋል ። አሽከርዬውም ቢሆን ጥፌት ቢጤ ታይኖረውና የእጅ—ስብ መከላከያ ሳይቀምስ አልቀረም'' አሉ ። እሳቸው ግን ፣ እዚያው ማጀቴ መድኃኔ—ዓለም በሚያውቁት አንገተ—ብርሌ በሚባል ደብተራ 'በስመ—አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ ጸሎት በእንተ መፍትሔ ሀፍት ወግርማ ሞገስ ፣ ወመድግ ወመስተፋቅር ፣ መድግ ፣ መጥቅ ፣ መትፍ ፣ አገጽጽያ አለሁማ ጅር—አላጅር ፣ መጅር ፣ ሰዓቦሙ ወአቅርቦሙ ወአራጎርኅ ልቦናሆሙ ፣ አሆ ! አሆ! አሆ! ይቤሉኒ ሰበ ከተማ ———' የሚል ጽሑፍ ያለበት ኪታብ በነጭ ፍየል ቆዳ አጽፈው እንደያዙ ልባቸው ያውቀዋል ።

"ለማንኛውም እኔ አለሁ — — ይኸ ቀላል ጉዳይ ነው ። 'ፌንጣ ብትቆጣ እግሯን ጥላ ሔደች' እንዳይሆን ፣ አንድ ደህና ነገር እጅሽ እስኪታገቢ ድረስ መታገሥ አለብሽ ። አለበለዚያ ነገር ታበላሻለሽ'' አሉ አቶ ወርቅነህ መዘወር ፣ የቤትዮዋ ለሁለት ማደር እየቆጫቸውና ለወደፊት አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባቸው እየወሰኑ ።

ወይዘሮ ደጅ — ይጥኑ ፣ በሰውዬው ምክርና ተግሣፅ እየተጽናኑና ተስፋቸውን እያለመለሙ ፣ ከቀድሞው በበለጠ ፈገግታና አቀራረብ የልብ ሰለባ ዘመቻቸውን እንደ ተያያዙት ፣ ለሳቸውም መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ !

* * *

የሞገስ አምባቸውና የላቀች ተገኔ ትዳር በሱ ፍላጐትና አስተሳሰብ እየተመራ ፣ በሷ ወደ አዲስ አካባቢ መግባትና ሰዎች ባደነቁላት ኑሮ ውስጥ መገኘት እየጠነከረ ፣ በፍቅር አብቦ በመግባባት ደመቀ። እሱም ባረማመድና ባለባበሷ ከተማ—አደግ እንድትመስልለት እንደ ቀልድ እየመከራት ፣ ቀድሞውንም የከተማ ልጅ ለመምሰል ከነበራት ፍላጐት ጋር ተጋግዞ የልቡ እየደረሰ ፣ የሷም መላ ወዘናዋ እያማረ፣ የቤት አያያዝንና የእንግዳ አቀባበልን ፣ የመኪና ውስጥ አቀማመጥንና የመልስ አሰጣጥን እያወቀችበት የአምስት ወር ነፍሰ—ጡር ሆና መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ !

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱም ፣ "አንፏቃቂ ሁሉ አንፏቆ አንፏቆ ቀረዪ ፣ እኔስ እልሄን ተወጥቻለሁ'' በማለት ራሳቸውን እያጽናኑ ፣

በስጨት ያሉ ዕለት ደግሞ ፣ ማር—አምባ ጊዮርጊስን እየተማፀኑ በዘልማድ ሲኖሩ ፤ ሽዋርካብሽም እንዳሏት እየሆነችና ባንዲት ቀሚስ እንደ ተወሰነች ፣ ትበላው ሳትቸገርና ታወራው ሳታጣ ቀኑ ቢገፋም ፣ ከተስፋዋ ይልቅ ትዝታዋ እየበዛ ፣ የመኩብለያ መንገድም እንደ ፈለገች፣ ለሁሉም መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ!

ልኬለሽ፣ በባለቤቷ ትዝታና ለምኖ ባጻፈው የደብዳቤ ተስፋ እየተጽናናች ፣ ልጆቿንም "ያባታችሁ መምጫ ደርሷል አሉ ፣ የሔደበትም መኺና ተበጅቷል" እያለች ፣ ቤቷ ሳይቀዘቅዝና መብራቷ ሳይደነግዝ ፣ ማሳዋ ታርሶና ቡቃያው አምሮ ባካባቢዋ እንደ ተከበረች ፣ ቸርነትም የባልንጀራውን አደራ እንደ ጠበቀና ከአረጋሽ ጋር የጀመረውን ፍቅር እንዳጠናከረ ፣ በመጨረሻም ምንዳዬ በሦስት ወር ደመወዙ ለልኬ ፣ ለልጆቹና ለቸርነት የላከላቸውን አዲስ ልብስ ለብሰው እንደ ተደሰቱ ፣ መስከረም ጠብቶ አደይ አበባ ፈነዳ!



## ምዕራፍ ዐርባ ሦስት

ቀኛዝማች ፣ የምክር ቤቱን ደንብና የአሠራር ሁናቴ ከዕለት ወደ ዕለት ስለ ለመዱት ፣ እንዴትና በምን ቀላል ዘዴ ሊያስፈቅዱና ያለ ፈቃድም ሊቀሩ እንደሚችሉ በሚገባ ዐወቁ ። እንዲያውም ለሦስትና ለአራት ወራት ያህል ከሥራ ገበታቸው የተለዩ አማካሪዎች ፣ ባሻቸው ጊዜ ሔደው ደመወዛቸውን እንደሚወስዱ ተረዱ።የወ/ሮ ደጅ—ይጥኑንም አንዳንድ ቅሬታ በልዩ ልዩ ስጦታና የማዘናጊያ ተስፋ ሰቅስቀው ጣሉት ። ድርጊታቸውን ሌት ተቀን የሚከታተሉት አቶ ወርቅነህ መዘውር ግን የሰውዬውን ለግል ጥቅማቸው ብቻ መራወጥ አንድ ባንድ ስለ ደረሱበት ለወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ያላቸው ተቆርቋሪነት ተጠናከረ ። የሴትዮዋን በጥበብ ልብስና በሉቲ ጨርቅ መደለል እያዩ ተበሳጩ ። "ለካ ሰው እንዳኖሩት አይገኝም ፣ ቁም—ነገረኛ እየመሰሉ የጊዜ ማሳለፊያ አደረጓት — — ቆይ! ቆይ! ቆይ! ቆይ! " አሉ ቀኛዝማችንም ለመዘወር ። የሰውዬውን ጠባይና ያላቸውን ወዳጅነትም በርጋታ ሲያሰላስሉት ፣ ቀኛዝማች አዳዲስ ወዳጆች ባገኙ ቁጥር ጨሌ እንዳየ በሬ ዘወር እንደሚሉ ታያቸው ። ስለዚህም ሴትዮዋን ቀስ በቀስ አራርቆና አላቆ ሌላ የመተዳደሪያ ዘዴ መስጠት አስፈላጊ ነው እስከ ማለት ደረሱ ። ሐሳባቸው ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርም ፣ ትልማቸውን ከጥቅማቸው ጋር በተያያዘ አዲስ ዕቅድ ውስጥ አስገብተው የመተግበሪያውን ስልት ማውጠንጠን ጀመሩ ።

*　　*　　*

ምንዳዬ ተስፋው እየጠወለገ፣ኑሮው በምሬትና በብስጭት ተቀነበበ። በቀድሞ ሥራው ላይ የቀኛዝማችን ልጆች ወደ ት/ቤት ማመላለሱም መረረው ። ሴትዮዋም ከግርመማ ወደ ግልምጫ በመሸጋገራቸው አካባቢና ኑሮው አስጠልቶት የትዝታው አድማስ ሰፋ ። ከራሱ ጋር ሙግት ገጠመ ። ሴትዮዋም የሳቸውን እጅና ፊት አይቶ አዳሪ ስለሆንላቸው እልሐቸውን የተወጡና የተበቀሉት እየመሰላቸው ፣ ከመደሰትም የልብ ልብ ተሰማቸው ።

"ምንዳ" ብለው ይጠሩና ፣ "እስቲ አታክልቱን ኮትኩተው? ምነው ግቢው ቆሸሸ? ምናለ ጠረግ—ጠረግ ብታረገው? ዛሬ ደሞ በሩን ከፍቱን ጥለኸው ወዴት ውለህ መጣህ? ምናለ አንዳንድ ቀን

ጨርቅ አጠባውንም ፣ ቤት ውልወላውንም አገዝ ብታረገን፣ ዛሬስ ብለህ—ብለህ ቀድመኸን ተኛህ እንዴ?" በማለት ያንገረግቡት ጀመር።

አንድ ቀንማ ሆን ብለው ፣ ያላያቸውና ያልሰማቸው አስመስለው፣ "ምን ጭብጥ ኩርምት ይልብኛል ፣ ኧረ ንሺ እልፍ ይከንዱ! ካልጣመው አይሔደውም፣ እኔ ናልኝ ብዬ አላመጣሁት፣ እከከከከከ!" ሲሉ በመስማቱ ፣ "ምናባቱ! ምነው ይህን ያህል መሽቆጥቆጤ! ቢሻው አሞራ ፣ ቢሻው አውሬ ይብላኚ እንዲህ ሆኜስ አልዘልቀውም" ብሎ ለመጨረሻ ጊዜ ቆረጠ ።

ቀኛዝማችን ለማነጋገር አጋጣሚ አልጠበቀም ። "እኔ እንግዲህ" አላቸው ግቢው መኻል ቆመው ወጥ እንዳይቀር የአበባ አትክልት ሲመለከቱ ። "እኔ እንግዲህ እያው አገሬ ልመለስ ፣ አለያም አንድ መላ ፈልጉልኝ ። እስተመቼ ሰው አስቸግሬ እዘልቀዋለሁ?" አለ የበጠቃትን ቅጠል እያልመዘመዘ ።

"የረሳሁ እይምሰልህ ፣ የሰው እጅ እማያሳይ ፣ ደህና ሥራ እስኪገኝልህ ብዬ ነው ። ለደህና ደህና ፍሬ ሰዎች ነግሬልሃለሁ ። ሁሉም ተስፋ ሰጥተውኛል ። እኔማ ከኔጋ ብትኖር ደስ ይለኝ ነበር ። ከሚስትና ከልጆችህ ነጥዬ ያመጣሁህም ——" ብለው ሳይጨርሱ ፣

"እኔስ እየሁ አንቱጋ መኖሬን መች ጠላሁት? ችግሩ ——"

"ያንተን መቸገር አጥቼው መሰለህ ። ካይንና ከግንባርህ ነው እማቀው ። ከኔጋ ወጥተህ እንዲሁ አገርህ አትመለስም ። ትልቅ ሐሳብ የሆነብኝ ደግሞ ፣ ሥራው ቢገኝስ እማንጋ ይቀመጠዋል እያልኩ ነው" ብለው የቀዘዘ ፊቱን ትኩር ብለው አዩት ።

"ኧረ የትም አስጠጉኝ ብዬ እድራለሁ ! ለለት ወስፋቴ ታገኙሁ ይበአኛል' አለ አቀርቅሮ ። 'እሳቸውን አስደስት ብዬ መንፈሬ ለምንድን ነው" እያለ በልቡ ።

"ግድየለህም ፣ እነሰም በዛ እንዱ ጋ አስቀጥርሃለሁ" አሉት ተስፋ ባለው ፈገግታ ።

"ተዚያ ሁላ ውለታና ቁም—ነገርሁ አይበልጥ ። እኔም የዕድሌ ነገር ሆኖ ነው መሰል ፣ ሁለዜ አንቱኑ እንዳስቸገርኩ ነው" ብሎ ከነገራቸው አያሌ ቀናት አለፉ ።

*   *   *



መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፣ ምንዳዬ ሽማግሌ ልኮ ከባላንጦቹ ጋር እንዲታረቅና የደም ማድረቂያ ወጀ ከፍሎ አገር እንዲቆረርለት (የተወሰነ የመኖሪያ ክልል) መኮይ ሽፍቶች መኖሪያ ድረስ ሁለት ጊዜ መልዕክተኛ ልከው ካስመጡት በኋላ ፣ ዞን አምባ ድረስ ሔደው የሚያስታርቁ ጉምቱ ሽማግሌዎች ለመኑ ።

ነገሩ የቆየና ሥር የሰደደ በመሆኑ በጥንቃቄ ተመከረበት ። መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ጉዳዩን በብልሃት ይዘው ከአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት ፣ ተሰሚነትና ታዋቂነት ያላቸውን መነኮሳትና ቀሳውስት አዘጋጁ ። ከካብ ሥላሴ አባ ተክለ—አብን ፣ ከከላይ ጊዮርጊስ መምሬ ማርዬን ፣ ከውቢት ሚካኤል አለቃ ዘነበን ፣ ከዞን አምባ ተክለሃይማኖትና ከየገልዳ ኢየሱስ መምሬ በየነንና አባ ምንውየለትን ለሽምግልና ሲያዘጋጁ ፣ በአካባቢው የተከበሩትን ቀኛዝማች በላይነህንም ለዚሁ ጉዳይ አማከረዋቸው ፣ እሳቸው በወቅቱ ባጋጠማቸው የርስት ክርክር ጉዳይ ስላልተመቻቸው ፣ በምትካቸው የገምዛ ወረዳ ጸሐፊና እንዲሁም የወረዳው ዳኛ እንዲገኙላቸው በማድረግ በዕርቁ ላይ ከፍተኛ ሜና የሚያሳድሩ ሰዎች ወከሉ ። የሁለቱ ባለሥልጣኖች በሽምግልናው መግባትም ዕርቅና ውሉን ሕጋዊ መሠረትና ጥንካሬ ሰጠው ።

ምንዳዬ ይህችን ሁሉ አንጠርጥሮ ያውቃታል ። ስለዚህም በማንኛውም ረገድ ቢሆን ፣ ቀኛዝማችን የሚያስቀይም ድርጊት ለማሰብ ሕሊናው ይጨነቃል ።

ምገስ የምንዳዬን የገጠር ኑሮና የነበረበትን ችግር ከገዛ ባለቤቱና ከወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ፣ እንዲሁም በሥራ ፈልግለት ሰበብ ከራሳቸው ከቀኛዝማች አንጠርጥሮ በመረዳቱ ፣ በሚያውቃቸው ሰዎች በኩል የዘበኝነት ሥራ ሲያጠያይቅለት ሰንብቶ ነበር ። ተስፋው አጐነቆለ ።

ምንዳዬ ወገገለት ።

ቀኛዝማች የሥራውን መገኘት እንደሰሙ የት እንደሚቀመጥ ሐሳብ ሆነባቸው ። ከወይዘሮ ደጅ—ይጥኑ ጋር እንዳይቀመጥ ፣ አቶ ወርቅነህ መዘወር የሱን ለቀኛዝማች ማድላት ስለሚያውቁና ከውጥናቸው ውስጥ አንዳንድ ወሬ ሊያቀብልብን ይችላል በማለት ስለሰጉ ፣ ለሁሉም ያሰቡ በመምሰል ፤

"እሱን የሚያህል ሰው ብቻዋን ከምትኖር ሴት ጋር ፣ አብረህ ተቀመጥ ማለት ያልታሰበ ችግር ያስከትላል ። ሰው ነውና ከብዙ ቀን አንድ ቀን ሊሳሳት ይችላል ። ምነው ስናውቀው ፣ ሴት ሆነን ባናየውም በወንድነታችን እናውቀዋለን ። ሥጋ ያሳስታል ። ሴላ እነስ

"ከመጣ ስንት ጊዜ አደረገ ?" አለ ምንዳዬን ከወደ ጐን እያየ ።

"ዓመት አልፎታል" አለ ሞገስ ፈጠን ብሎ ።

"ማኬ! ይኸም አገር ለምዷል ማለት ኖው —— ድንቄ !"

"ብዙ ወጣ—ወጣ አላለም እንጂ ፣ ለሥራስ ትጉኅ ነው" አሉ ቀኛዝማች ምንዳዬን እያዩ ።

"እዚህ እኛ አሎና በቀላል ይለምዳለ ፣ ዋና እሚፈለግ ያለ ነገር ከሱ ፣ እሙን ሰው ምኳን ቢቻ ኖው ። ላይ የሚያሸግር ነገር የለም ።"

"ስለሱ ግድየለም ፣ ለሚያደርሰው ማንኛውም ጥፋት ተጠያቂና ኃላፊ ነን" አሉ ቀኛዝማች ኮራ ብለው ።

"ድንቄ ! የሱ ሥራ ብጣዕሚ ቀሊል ኖው ፣ እንተኸነም ምጥንቃቕ እስፈላጊ ኖው ።"

ምንዳዬን ፣ ልዩ ልዩ የመኪና ቅባቶች ፣ የነዳጅ—ዘይቶችና የብየዳ ጢስ ሽታ አወከው ። ሕድሩ ፣ እነ ሞገስንና ምንዳዬን አስከትሎ ወደ ግቢው በር በመሔድ ፣

"ይኸ ኖው እሱ ይጠብቅበታል አቦስቶ ፣ የሥራ" ብሎ ዙሪያዋን በቆርቆሮ የተሠራች አነስተኛ ቤትና እበሯ ላይ የቅባት እባሽ የጠገበች ገዳዳ አግዳሚ አሳያቸው ። የምንዳዬን ባዶ እጅ መሆን አይቶ ፣ ገባ ብሎ የባሕር ዛፍ ዱላ ካወጣ በኋላ ፣ አገላብጦ አይቶ ሰጠው ። እጅ ነሥቶ ተቀበለ ።

"አይዞሃ ፣ የሚሸግረካ ነገር ዘበለ ፣ ለኔ ትነግረኛል!" ካለ በኋላ እነ ቀኛዝማችን ተሰናብቶ ወደ ሥራው ተመለሰ ።

ሞገስ ፣ "እንግዲህ ነቃ ነቃ ማለት ነው ። አይዞህ ። ሁሉም የለመደው እንዲህ እንዲህ እያለ ነው ። በል በርታ ! ያቅትሃል እንዴ ?" አለው ።

"ኧረ አያእተኝም ፣ ይኸ ደሞ ምኑ ያእተኛል" አለ ምንዳዬ ዱላውን በጥንቃቄ ጨብጦ ።

"በል እንግዲህ አይዞህ! አጅሬ እንኳን ለዚች !" ብለው ቀኛዝማች እየፈገጉ ተሰናበቱት ። ምንዳዬ ሆዱ ባባ ። ዐይኑ ቃበዘ ።

የጋራዡ ግቢ ሜዳ ጠጠር ፈሰስ ሆኖ ፣ በልም የመኪና አቧራርጋፊና ጥራጊ ፣ በቅባት ዝቃጭና ፍሳሽ ተለዋውሶ በመደምደሙ ፣ ቅጥራን ያፈሰሱበት ይመስላል ። ምንዳዬ ወለል ብሎ በተከፈተው



በር በኩል ወጪ ወራጁን እየት ያደርግና ፣ እንደገና ወደ ግቢ ዘወር ይላል ። እንዴት ዐይነቶቹ ሰዎች ሲመጡ እንደሚያስገባ ለማወቅ አሳብ ያዘው ። "በምን አቃቸዋለሁ ፣ ይግቡ ወይ ብዬ እጠይቅ እን ደሁዬ" አለ በሐሳቡ ።

ሠላሳ ያህል የሚሆኑት የጋራዡ ሠራተኞች ፣ በየተመደቡበት ሥራ ዓይነትና አካባቢ ተፍ—ተፍ ይላሉ ። ቅጥቀጣና ብየዳ ፣ እጠባና ጥገና ፣ ቅብና ሞተር ፍተሻ ይሠራሉ ። ምንዳዬም የዚያ ኑሮ አካል በመሆኑ እንዲት ኦፔል ሬኮርድ የቤት መኪና እየተገፋች ወደ ጋራዡ ልትገባ ፊቷን ወደ በሩ ስታዞር ፣ ዱላውን ይዞ ጠንቀቅ አለና ልክ በሩ ጋ ስትደርስ ፣ ኮስተር ባለ አነጋገር ፣—

"ቆይ! ቆሙ! ታይፈእዱላችሁ አትግቡ! መጀመሪያ ልጠይቃላችሁ" አለ ።

ማንም ነገሬ አላለው ። ከቁም—ነገርም አልጻፉት ። የመኪናዋ ከፊል አካል የበሩን ደፍ እንዳለፈ ፣ ነጂው ራሱን በመስኮት ብቅ አድርጎ ፣ "ምንድነው እምትለው ?" አለው በሲጋራ የበለዘ ዝርዝር ገጣጣ ጥርሱን እየገለፈጠና ጨምዳዳ ማዲያታም ፊቱን ይበልጥ እያጨማደደ ።

"ልጠይቃላችሁና ነው እምትገቡት ነው ያልኹት!" አለ ቁጣ—ቁጣ እያለው ። እየሣቁበት ገቡ ። የምትገፋውን መኪናና ሰዎቹን እያየ ነደደው ።

"ቢተዋወኡ ይሆናሊ ፣ እንዲያው ያለ ብላት ሰተት ብለው አይ ገቡ" አለ በግምት ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሕድሩ እየሣቀ ሲመጣ ፣ ቀጥ ብሎ ቆሞ ጠበቀው ።

"ማኪና ይዘው ሲመጡ ሳለ መግባት አይትከልክላሸው ፣ ሀዲሽ መሆንካ አይተው ኖው የሣቁብኸ ። አጆኻ ! አንተ መንም መንገደይና ልግባ ሲለካ አይታስገባ — ተረዳኸ?" አለው በሚያግባባ ፈገግታ እያየ ። ሕድሩ የተናገረው አማርኛ ግር ቢለውም ፣ ነገሩ ስለ ገባው "እሺ ! ማ አስገባቸው አለህ እንዳትሉ ብየ ነውዬ ፣ ሌላውስ አይጠፋኝም" አለ ምንዳዬ ። ሕድሩ ተመልሶ ሲሔድ ትክ ብሎ አየውና ፣ "እምኑ ውስጥ ዶሎ ቢለውሰው ነው ልብሱ እንዲህ አሙካ የመሰለው ? ያሽታተቱ ! ስባትላብ ጌታዬ!" ብሎ ቅልብሽ እያለው ተቀመጠ ። ቀስ በቀስ ስሜቱ ተረጋጋ ።

አሻግሮ ወደ ሠራተኞቹ ሲመለከት ፣ የሕድሩን ዓይነት ልብስ ለብሰው ከመኪና ሥር የተንጋለሉና እናት ላይ የወጡ ፣ ዙሪያውን እየ

ዩም ። ቀን በውኔ ሌት በልሜ ትታዩኛላችሁ ። በጣም ናፍቄአችኋለሁ ። እንደ እህልና ውሃ ነው የራባችሁኝ ፤ የጠማችሁኝ ። የሚያሠሩኝን ሰውዬ ፤ በሰውም ቢሆን አስለምኜ ፈቃድ ካገኘሁ ፤ ላንድ ቀን ጀምበርም ብትሆን መጥቼ አያችኋለሁ ። ስለኔ እንዲች ብላችሁ አታስቡ ፤ አይዟችሁ ፤ ጥቃት አይግባችሁ” የሚለው እንደተነበበ የልኬለሽ ዐይኖች አጤዙ ። ምራቋን ዋጥ አድርጋ ዐይኖቿን ከደን ስታደርጋቸው ጤዛው ኩልልታ ሆኖ ወረደ ። ፍቅር ፤ ምንዳዬ ፤ ትዝታ ፤ ም — ን — ዳ — ዬ ። የቧ እንባ ሳያባራና ፤ ቸርነት ዐይኑን ወረቀቱ ላይ እንደ ተከተለ ፤ ልጆቹ ሁሉንም ተራ — በተራ እንዳዩ ደብዳቤው ተነቦ አለቀ ።

ልኬለሽ ደስ ብሏት እንዳገሯ እንደ ሸንኩርት ውሃ ምንጭ እን ባዋን ለቀቀችው ። ቸርነት ደብዳቤውን ላነበበላቸው ሰውዬ ፤ “እስቲ ይቺን ለውሃሁ አርጓት” ብሎ ሐያ ሳንቲም ጨበጥ አደረገለት ።

እነ ልኬለሽ ተያይዘው እቤታቸው እንደገቡ ፤ በሉ እንግዲህ ተሳሳሙ ተብለው የታዘዙ ይመስል ፤ በልኬለሽ ጀማሪነት ተሳሳሙ ። ልጆቹ በደስታ ፈነደቁ ።

“ይህን የዛሬውን ደስታ ማ ያገኘዋል ?” አለች ዐይኗ እንባ እያረገዘ ።

“እስቲ እሱ ለራሱ ምን አለውና ነው እንዲህ ማረጉ ? በሰው አገር እየተንከላፈተ?” አለ ቸርነት ።

“የሱን ልብ ማ ያገኘዋል? እንዳይከፋን ብሎ ነው ። እነዚያ እነዚያ እምናአቸውንም ደስ አይበላቸው ብሎ ነው — ዋዛ መስሎሃል! ምንም ብሆን አለሁ ማለቱ ነው” አለችው ።

“ያጣንና የተቸገርን ይመስለው ይሆን እንዴ? መርሳትማ በየት ኛው አንጀቱ ይረሳናል? ምንስ ቢሆን ሚስትና ልጅ አይረሳ!?” አለ ቸርነት ለቀልድ ያህል እየሣቀ ።

“መስሎሃል! ሚስትነቱን አትይ! ተኔ አስበልጦ ነው እሚወድህ ። እንዲህ ወረኸት መላኩ ታልቀረ ፤ አሁን ምን አለበት እሱም እንደቀኛማይ ፤ ያን ኮቶግራፍ ሚሉትን ተነሥቶ ቢልህልን ፤ በትንሿ ትበአን ነበር ፤ ይኸ ትልልኡ ለሹሞቹ ነው መሰል?” አለች እየፈገገች ።

“እስቲ ደሞ ሰንበትበት ብለን እምናየውን በምን እናቀዋለን ። አቦ የሱ ሥራ!” አለ እየሣቀ ።

“ይኸ አባብይ መይ እመጣለሁ አለ እማምይ?” አለ አሻጋሪ የለበሰውን ጐመኔ ካኪ እያየ ።



“ቲነበብም አልሰማህ እንዴ ሽታዬ? መሰንበቻውን እመጣለሁኮ አለ” ስትል እንባዋ ወረደ ።

“ይቺ እማምይ ደሞ! ያልሰማሁ መስሎሻል? ምነው እያሣች ሆነን አብዬ ቸርነት ነግሮኝ!”

“ምን ብዬ ነገርኩህ አሻጋሪ? ፈቃድ ቲሰጡኝ መጥቼ አያችኋለሁ ብሏል ነው ያልኩህ!—አለያም እኔና አንተ ሔድ ብለን እናየዋለን!” አለ የምሩን በሚያስመስል አንደበት ።

“አቤት ይኸ አብዬ ቸርነት !!”አለ እየሣቀ ።

* * *

ቸርነት ፤ የራሱንና የባልንጀራውን ማሳ እያረሰ ፤ ልኬለሽና ልጆችዋ ሳይቸገሩ ፤ ጐተራዋ እንደ ሞላና ገበታዋ እንደ ከበደ ፤ ምድጃዋ ሳይቀዘቅዝና ማንም ወስላታ ቀና ብሎ ሳያያት ፤ ታፍራና ተከብራ ተቀምጣለች ።

አፈሣም ቢሆን ልቡ አላረፈም ። ምንዳዬ ባልታሰበ ቀን መጥቶ ጉድ እንዳያፈላበት እየሠጋና ውስጥ ውስጡን እየፈራ ፤ ከነቤተሰቡ እጃቸውን ሰብስበው አፋቸውን ከርክመዋል ።

መምሬ ተክለ ጊዮርጊስ ፤ ለምንዳዬ ቤተሰብ የወሰዱት ደብዳቤና ልብስ ፤ እጥፍ በእጥፍ ተጨማምሮበት ፤ ያልተባለው እየተባለና ያልተዛተው እየተዛተ ፤ ወሬው ውሎ ሳያድር ጃራን ተሻግሮ ዞን—አምባ ዘመተ ። ልኬለሽ ይህን በመስማቷ ፤ “እንዲህ እያሳመሩና እየጨማመሩ ያውሩለታ!” ብላ ካንገቷ ቀና ፤ ከልቧ ዘና አለች ።

ቸርነትም የሚወዱት እንዲያደንቁለት ፤ የሚጠሉት እንዲያዩለት ፤ ምንዳዬ የላከለትን ሙሉ ልብስ አዘወተረው ። አንዳንድ አሽሟጣጮችና ነገረ— ሠሪዎች ፤ “የሎሌነቱን ፤ የሚስትና የቤት ጠባኢነቱን፤ ጥብቆ ቢጤ ገዝቶ ላከለት ። ዋል አደር ብሎ ሚስቱን ቲቀማው ተጐኑ ያገኘዋል ። ‘ነፈዝ ባል የሚስቱን ውሽማ ይቀልባል’ እሚሉ ተረት ለካ አሰትም አዶል?” እያሉ አሰወሩ ። አሉባልታው ግን ፤ ከእርሱ በፊት ስንትና ስንት ጊዜ እየተወሩ እንደ ሞቱት አሉባልታዎች ሁሉ ፤ በየዕለቱ እየማቀቀ ሞተ እንጂ ፤ እንደ አንዳንድ ሽምድምድ ውሽቶች እንኳ ፤ የአሟሟት ወግና ግናዝ አልደረሰውም ።

የልኬለሽ ፤ የልጆቿና የቸርነት መንፈስ ግን ፤ በሚታፈስ እውነትና በምንዳዬ ይመጣል ተስፋ እየለመለመ — —ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፤ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — — ፍቅር ፤ ምንዳዬ ፤ ትዝታ ፤ ናፍቆት — — — — —ልኬለሽ — — — ምንዳዬ — — እነአሻጋሪ —— ቸርነት — — —

ራረብና መተዛዘንን ቀሰመ ። ከመሰንበትም የገጠር አነጋገርና ግትርነቱ እየተሻሻለ ፣ የሠራተኞችን ባሕሪና ሁኔታ መላበስ ጀመረ ። የልዩ ልዩ ዕቃዎችንም ስም ፣ ቀድሞ እንደሚያውቃቸው ሞፈርና ቀንበር ፣ ድግርና ወገል ፣ ዋልታና ምሰሶ ፣ መንሽና ላይዳ—ከማወቅ ዐልፎ አንዳንድ የሚሠሩ ነገሮችን ፣ ማጠባበቅና ማላላትን ፣ መቆራረጥና ማቃናትን ፣ ቀስ በቀስ ለመደ ። ቀድሞውንም በእርሻና በተጨማሪ የጉልበት ሥራ የጠነከረ አካሉ ፣ በመንገድ ብዛት የከረረ ጡንቻና ጅማቱ ዛሬ ደግሞ ከብረታ ብረት ጋር በሚደረግ ትንቅንቅና ሥራ እየጠነከረ ፈረጠመ ።

የቀኛዝማች ውዴታቸው ሳይሆን የገንዘብ ድጎማቸው ፣ "ከእንግዲህስ ምንም አይል ፣ ራሱን እየቻለ ነው" በሚል ግምት ፣ "በአይዞህ በርታ" ተተካ ። በርግጥም የወር ደመወዙ ከዘበኝነት ጊዜ ክፍያው ጋር ሲነጻጸር ከሁለት እጥፍ በላይ አድጓል ። ሽቅብ ተንጠራርቶ እነ ቀኛዝማችንና ሞገስ እምባቸውን ለመጋበዝ ባይቃጣውም፣ እሱም በድረጃው ፣ በቢጤዎቹ ተጋብዞ መጋበዝንና ውለታ መመለስን ፣ ከዋል—አደርም ለወ/ሮ ደጅ— ይጥኑ "እስኪ ይቺ ለቡናሁ ትሁንሁ" እያለ ጨበጥ ማድረግን ጀመረ ።

ከቀኛዝማችና ከሞገስ ፣ ወይም ከሌላ ሰው ጋር ሲነጋገርም አንደበቱ ዘና ፣ አነጋገሩ ፈጠንና ኀላ ማለት ያዘ ። ስለ መኖሪያው ጉዳይ የማሰላሰሉ ነገር ግን እየጨመረ እንጂ ፣ እየቀነሰ ባለመሔዱ ፣ "እስከ መቼ ድረስ ሰው አስቸግራለሁ ፣ እንኳን ባዳና ዘመድም ቢሆን ይሰለቻል" በማለት አውጥቶና አውርዶ የራሱን ውሳኔ ወሰነ ።

በቅድሚያ ቀኛዝማችን አማከረና ላቀችንም አዋያት ። ሰውየው ሐሳቡን ደግፈው የመቋቋሚያ ድጎማ ሲሰጡት ፣ ላቀችም አንዳንድ የማሰናጃና የመመገቢያ ዕቃዎች አዘጋጀችለት ። ሞገስም የበኩሉን ሰነዘረ ።

ምንዳዬ ፣ ከአንድ የጋራዥ ሠራተኛ ጋር በደባልነት ለመኖር ቤቱን ለቆ ሲወጣ ፣ ከፍ ያለ ልባዊ ምስጋና አቀረበ ።

በበዓላትና በዕረፍት ቀናት ወደ ቀኛዝማች ቤት ሲሔድ ፣ ሚስትዮዋ ያቺኑ እንዳቅሙ የሚያደርጋትን ጫማ ፣ የሚለብሳትን የተተኳኮሰች ካኪ ልብስና ተራ ሸሚዝ ሲያዩ ዐይናቸው ይቀላና ፣ "ይኸ ጥፍራም ባላገር እከኩን አራገፈ አይደል ! እኔ ተጎዳሁዪ ፣ አዳሜማ ተጠቃቀመ ችብኝ ። እዚያ ስንቱ የለፋላቸው አሳረ—መከራውን ያያል ፣ ይኸ በደህና ጠጠር ጣይ አስጠንቁሎ ፣ ሰላ ብሎ ገባና ሰው ሆነ ። አንዳች ነገር አበስ ብያደርግባቸው ነውዪ ፣ እስቲ ምን አርጎላቸው ነው ፣ እሱን እዚህ ሥራ ዶለው ፣ እዚያ ደሞ ሚስትህ እርሻዋን ታሳርስ ማለታቸው ? ሙቻ



ታለሁዋ ! ያቺን መሬት አስመንጭቄ መቅኖ ባላሳጣው" እስከ ማለት ደረሱ ።

ሽዋርካብሽ ግን ምንዳዬ ሲመጣ ፣ ዐልፎ — ዐልፎ ልኩን ባልሳተ ድፍረት ፣ የሴትዮዋን ሁኔታ እየገመተች ታጫውተዋለች ። "እኔስ እንደሱ የሚያልፍልኝ መቼ ይሆን?" በማለት ራሷንም ፣ እምላኳንም ትጠይቃለች ። መልስ አታገኝም ፤ የሩቅ ተስፋም አይታያት ።

"እሁንማ ያዲስአባ ሰው መሰልክ ምንዳ?"አለችው ።

"ከዋል አደር የት ይቀራል?"

"እስቲ ለኔም ቀስ ብለህ ሥራ ፈልግና እሰው ቤት ዱለኝ"አለችው ዙሪያዋን አይታ ።

"በያ ደሞ ደህና ተንፈስ ያልኩትን ፣ እንደገና ጥርስ አስገቢኝ — —እኝህ ቤሽቲያ ዘመድሽ ነገሩን አዙረው የቡና ማከተሚያ ነው እሚያረጉኝ ። "

"እውነትም በሽተኛ "አለች ነገሩ ስላልገባት ።

ምንዳዬ ከት ብሎ ሣቀና ፣ "እኔማ ለጓደኞቼም ነግሬ ቢሆን አፈላልግልሽ ነበር — — አንቺ ግን" ከማለቱ ፣

"አይለፍልሽ ብሎኝም እንደሁ ፣ የላይኛው ጌታ ያቃል ። ላመድ ያለው ቂጥ ለኮርቻ አይሆንም ይባላል ፤ እዚሁ ዐመድ ላመድ ተርመጥምጠሽ ቅሪ ካላለኝ — —"

"ለምን አገሬ መልሱኝ አትያቸውም ። ምን ዕዳ አለብሽ!!"

"ኸረ በምን ሥራ አጣሀልኝ ! አበስ ገበርኩ! ለዕድሌም አላሳየው ፣ ይልቅ አንተ የወንድምነትክን ዋልልኝ! የኔን ዘመድ አታንሣ! ከዘመዱ ገዳይ ናት! መጨበጫም የላት ። አሁንማ እንዳለፈው ቅዳሜ ጣል አርጋኝ ፣ ባንዲት ጨርቅ ተጣብቄ ቀረሁ" ብላ እንባ ሲተናነቃት ፣ እዘነ ።

ምንዳዬ ሊጠይቃቸው በሔደ ቁጥር አንዳች ተስፋ ይሰማታል ። ባጋጣሚ ሴትዮዋ ሳይኖሩ የደረሰ ዕለት ብሶቷን ስትነግረው ቀለል ይላታል ። እሱ ግን ፣ ሆን ብሎ የሚመላለሰው ሴትዮዋን ለማበሳጨትና መሻሻሉን ለማሳየት ነበር ።

ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ግን ፣ እሱ የገመተውን ያህል አልተበሳጩም ። በተገናኙ ቁጥር ፣ "የኔ ጎርጊስ አዛዬን ነቀለልኝ" በማለት በሽንጋይ ፈገግታ ይቀበሉና ፣ "ደህና ነህ ወይ? ምነው መሰንበቻውን ጠፋህ?" ይሉታል ።

ሆኖም ፣ በሦስትና በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ፣ ዐይን ከጣሉባቸው የአካባቢው ወንዶች መካከል ያወቀበት እግሩን አስልቶና ጊዜውን አጢኖ ጐራ ማለት እንደ ጀመረ ፣ ወ/ሮ ደጅ—ይጥኑ ጠባቂያቸውን በጣፈጠ ፍርፋሪና ባደረ ቅራሪ እየሸነገሉ ፣ ምላሱን ቀየዱት ። ቀኛዝማች ሲጠይቁት ግን ፣ "እኔ እንዲህ ያሉ ሴት አይቼም አላቅ! እንኳን ሰው ወፍ ዝር አይልም" ብሎ የሴትዮዋን ታማኝነት ይገልጽላቸዋል። እሱ ግን ፣ 'እንደ ገበያ አህያ ዐሥሯን ሲያሸቱ ዕድሜያቸውን ፈጁት' ይላል በልቡ ።

የገጠር ደመወዙ እስከ ረፋድ የማታቆይ ማሳ ስትሆን ፣ ያቺንም ከመጋዞ መሬት ጋር የሚያርሳት ልጁ ነበር ።



# ምዕራፍ ዐርባ ሰባት

ምንዳዬ ሁለተኛ ዓመቱን እንደ ጨረሰ ፣ የግርግሬ አንጋሬ እምታሀል ልሙጥ ቆርቆሮ ፣ የሸራ ወይም የጐማ ቅዳጅ ያነጥፍና ከተበላሸ መኪና ሥር ፣ በጐኑ ወይም በጀርባው ተኝቶ የላላውን አጥብቆ ፣ የተሰበረውን ቀይሮ ብቅ ሲል ፣ የተለበለበ እንጨት ይመስላል ። እንደተቀጠረ ሰሞን ያደረገው ድርጊትና የፈጸመው ስሕተት ሁሉ ትዝ ሲለው ብቻውን ይንከተከታል ። ሠራተኞቹ በዘበኝነቱና ከዚያም ወዲህ መፍቻ አቀባይ ሆኖ ሲሠራ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን የቶሎ ዐውቄ ልመስገን ጥድፊያ እያስታወሱ ሲሥቁበት እሱም አብሮ ጦሽ ይላል ። በተለይም አንድ ጊዜ አንዲት ተጠግና የቆመች ፊያት 1500ን በውሃ አጥቦ በናፍታ እንዲወለውላት ታዝዞ ሲሠራ ፣ ሠራተኞቹ ሆን ብለው ይጠቃቀሱና መኪናይቱን ከበስተኋላ ሲገፏት ቀስ ብላ መንሸራተት ትጀምራለች ። ምንዳዬ ደንግጦ እመር ብሎ ከውስጧ ይወጣና ፣ ከፊት ለፊት ቀድሞ ሊያቆማት ይሞክራል ። ቦታው ትንሽ ቁልቁለታማ ስለነበር ፣ ከአቅሙ በላይ ትሆንበታለች ። ሠራተኞቹ ከያቅጣጫው ሲሥቁ ፣ "አንድ መላ በሉዩ ፣ እኔ ልለቅላችሁ ነው" ይላል ።

"በርትተህ ያዝ እንጂ ! ብትጋጭስ?"

"ምንዳ! ዐይኑ እያዬ — — ይዳጥላችኋል ! መልቀቄ ነው!" ሲል፣ እየተሣሣቁ ይረዱታል ። ያን ዕለት ማታ አብሮ ሲሥቅ አመሸ ።

ከሥራ ሰዓት ውጪ አብዛኛዎቹ የያዙትን ይዘው በየመጠጥ ቤቱ ይሰገሰጋሉ ። ቀን ጉልበታቸውን በሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ሲያስመጥጡ ይውሉና ፣ ማታ ማታ ደግሞ ገንዘባቸውን በየመሸታ ቤቱ ሲከሰክሱ ያመሻሉ ። ንዴትና ብሶታቸው በመጠጥ የሚቃለል ይመስላቸዋል ። ንግግራቸው ሁሉ አጭርና ቁርጥ ያለ ሆኖ ፣ ከወደዱ መሬት ፣ ከጠሉ ሬት ናቸው ። የበቀላቸው ክንድ አያላውስም ።

ምንዳዬ ከልዩ ልዩ ሠራተኞች ጋር ባወራ ቁጥር ፣ አንዱ ስለሌላው ዐመል እየነገረው ፣ ካሚታና ካሉባልታው ፣ ከቀልድና ከጨዋታው ስለ አካባቢው ሰዎች ጠባይ አያሌ ነገር አወቀ ። ሲኞር ካርሎና ወኪሎቹ የሚያቀርቡና የሚያርቁት ፣ የሚጠቅሙና የሚጎዱት ሠራተኛ እንዳለም ተገነዘበ ። ከሠራተኞቹም መካከል እነ ማን በጐሪጥ እንደሚ

መራ ይሔድና ከከተማው በስተሰሜን ትንሽ ወጣ ብሎ ፣ በአንድ ኢጣሊያዊ የጡብ ፋብሪካ ውስጥ በቀን ሃምሳ ሳንቲም ይቀጠራል ።

ኑሮ እየመረረውና ጭቆና እያንገሸገሸው ብዙ የሥራ ቦታ ቀያየረ። በኋላም ጋራዥ ውስጥ ተቀጥሮ ጥቂት ዓመታት ከሠራ በኋላ በ1954 ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ ጋራዥ ተቀጠረ ። ይህንና ሌሎችንም የመከራና የደስታ ትዝታዎቹን ለምንዳዬ አጫውቶታል ። "ወዬ ጉድ! ለካ ከኔም የባሰ አለና! እህ! ካሉ ስንት ጉድ ይሰማል" ብሎ በአዘኔታ ራሱን ነቅንቋል ።

ጊዜ እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ ፣ ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ ። — — —



# ምዕራፍ ዐርባ ስምንት

ስንሰለቱ እንደ ከረረና ፣ ቀንበሩ እንደ ከበደ የሠራተኛው የድካም ውጤት ሰተት ብላ ወደምትገባበት ትገባለች ። አራሹም ፣ ቀጥቃጩም ከሞፈርና ከሞተር ጋር ይተናነቃሉ ።

ሠዐረ 'የሠራተኛ ማኅበራትን ከሚያቋቁሙ ሰዎች ጋር በድብቅ እየተገናኘ ይመሳጠራል' የሚል የስሚ—ስሚ ወሬ ከአሠሪ ወኪሎች ዘንድ በመድረሱ ፣ 'ሳይዘገይ እርፍደሃል ፣ ሳይለግም ሥራ በድለሃል ፣ ሲጠግን መሣሪያ ሰብረሃል ፣ አለቆችህን ገላምጠሃል' በሚል የሐሰት ክስና በሥልጣን ኃይል በመጠቀም ፣ ደመወዙን እየቆረጡ አበሳጩት። ቅጣቱ እየጨመረና ጥቃቱ እየከረረ ሔደ ።

ክፉኛ በተበሳጨበት አንድ ዕለት ፣ ከምንዳዬ ጋር ወደ መጠጥ ቤት ይሔዱና ሠዐረ አከታትሎ ይጠጣል ። ያም ቢሆን አልሰነፈ ። እየተዘዋወሩ ሲጠጡ ካመሹ በኋላ የሞቅታቸው ደረጃ ከፍ እንዳለ ፣ አዘውትረው ወደሚገቡበት ቡና ቤት ይገባሉ ። ይጨምሩበታል ። በመኻሉ ሠዐረ ወዳጁ ከሌላ ወንድ ጋር ስትሣሣቅና ስትዳራ በማየቱ ደሙ ይፈላና አፉ እንዳመጣ መሳደብ ይጀምራል ። ምንዳዬም አብሮ ደሙ ፈላ ። የሠዐረ ደም እንደፈላ አልቀረም ። ግብግብ ገጠመ ። ሁለት—ሁለቱ ተዬ በደህና ቡጢ እንደ ተዳቁ ፣ ሠዐረ የተጣዩን አንገትጌ ይዞ ከወደራሱ ወደ ጐንና ወደ ኋላ እየተለጠጠ ፣ በጭንቅላቱ የሰውዬውን አፍንጫና ከንፈር ሁለት ሦስቴ አላትሞ ሲያደማው ፣ ሰውዬውም ያንኑ ያህል ደህና አድርጎ መደወተው ። ሠዐረ እያጠቃ ሰውዬው እየተከላከለ ሲናረቱ ፣ የዚያኛው ሁለት ባልንጀሮች ገላጋይ መስለው ተቀላቀሉ ። ዳር—ዳር ሲል የቆየው ምንዳዬ "አባ ገላግሌ !" ብሎ እንደ ቀትር እባብ ሲወረወር በቅድሚያ አንድ ቡጢ ቀመሰ ። ወገቡን ሰበር ፣ አንገቱን ቀርቀር አድርጎ ፣ በሚያውቀው የትግል ዘዴ ሰውዬውን ሽቅብ አጉኖ ከመሬት ደባለቀው ። አልተነሣም ። ሌላው ሰውዬ ግን ፣ የዋዛ ዱለኛ አልነበረም ፣ በቡጢ አጣደፈው ። ምንዳዬ የሚያዋጣው መስሎት በዚያቹ በዘዴው ሽቅብ አጉኖ ከመሬት ሊደባልቀው ሲል ፣ እላዩ ላይ ተጣብቆ ሙጭጭ አለበት ። ጎንበስ ብሎ አራገፈውና እላዩ ላይ ተከመረበት ። ጥቂት እንደ ተቦጣቦጡ ፣ በትርምሱ መኻል የተንከባለለች የቢራ ጠርሙስ ምንዳዬ እጅ ገባች ። ደህና አድርጎ ተጠቀመ

ካቦው በዝግታ ተራምዶ እነ ምንዳዬ አጠገብ ቆመና፣ “ጩብጠኝ! ብራቦ! የኛ ካስየስ ክሌይ! ሶኒ ሊስተን!” ብሎ በትዕቢት እየማቀ እጁን ዘረጋ።

“ቫይ ቪያ! ዲስክራሲያቶ!” አለ ሠዐረ።

“ዋ! ዛሬ ቀን! ወጊድ ብየሃለሁ ሰውዬ! አሳር እንዳይከተልህ!” ብሎ ምንዳዬ ቡጢውን አዘጋጀ።

“ምን ግበሩ ትለናል! አንተ ሰውዬ የምታመጣ ነገር አለ ዛሬ ቀን! ወዲ ካኔ!”አለ ቱግ ብሎ።

“ምነው አንተ ብትተው! ደህና ሰው አልነበርክም እንዴ?” አሉ አንድ ሽማግሌ ቢጤ ካቦውን።

“ዝምበል! የቡሃቃ ሌባ! ሐድና ማድቤት ለማድቤት ሊጥህን ድፋ! አጁዛ !!” አላቸው ዘወር ብሎ። አልመለሱም።

ካቦው፣ “በል ተወው፣ ረጋ ብለን እንጫወታለን! ይቺን የሽሮ ድንፋታ እናውቃታለን” ብሎ ተመልሶ ተቀመጠ። አንዳንድ ሞገደኛ ሰው ሲያጋጥም፣ አረጋግቶና ተመራርጦ በመደብደብ፣ ምናልባት የደ በቀው ገንዘብ ካለም ፈልፍሎ ማውጣት፣ አለበለዚያም በማግስቱ እንዲ ያስመጣ ቃል ማስገባት የተለመደ ዘዴ ነው።

እንደገና ጸጥታ ሆነ።

ከእስረኞቹ መኻል አንዱ፣ “ለምን የሻማ ክፍላችሁ በሰላም አትተኙም” አለ።

“አሁን ከየት ናመጣል?”

“የነበረንን እኮ አስረክቡ ተብለን አስረክበናል — የት አለን!” አለ ምንዳዬ በቁጣ።

“ምን ያስቆጣሃል ታዲያ? ደርቲ! ጢት እናመጣለን አትሉም!!” አለ ሌላው።

“አይትሳደብ! እዚህ ሁላችን ሐደ ኢና! ኢቐራንቲ!”

“ቀድሞ ነገር ማ እናግሮን! ከውጪ ዱላ ከግቢ ዱላ?!”

“ተአብ አታብዛ! — —ገንዘብ አስመዝግባችኋል?!” አለ አንድ ባለ ሰላላ ድምፅ።

“ጢት ስንት — ስንት ትከፍላላችሁ?” አለ ሌላ ቃጭል ቢጤ።



“የምን ጥያቄ ማብዛት ነው፣ ካደረ ባለቀፎዋን ነዋ! አምስት ገቢሬ!”

“እንዲህ በወጉማ መጠያየቅ ያባት ነው። እናንተ ታዲያ በየት?” አለ ምንዳዬ።

“የሻማ እንደሚከፈል አታውቅምና ነው?! ጉረኛ !!” አለ ሌላው በንቀት።

“አፋ! እባካችሁ ዝም በሉ! እንተኛበት!! አያስቸኩልም!!” አለ ሰባራ አንኮላ መሳይ ጉሮሮ።

ምንዳዬና ሠዐረ እንደ ቆሙ፣ ሁሉም እግሩን ወደ ቤቱ መኻል እየ ዘረጋ ተኛ። በግድግዳው ዙሪያ ካርባ በላይ ጭንቅላቶች፣ እቤቱ መኻል ከየልብሱ ሥር ብቅ—ብቅ ያሉ ከሰማንያ በላይ እግሮች። በእግሮቹ ጣልቃ—ጣልቃ ወደ ተለያዩ አቅጣጫ የተኙ ሰዎች። የአብዛኛዎቹ ጸጉር ተንጨብሮ የተቆጣጠረ፣ የገላቸው ላይ ፉከት መስመር፣ በየጥ ፍራቸው ስፋት መጠን የተሰበጣጠረ፣ ጭቅቅት የጠገበ ሸሚዝና ካና ቴራ፣ የብብትና የገላ ቅርናት፣ ክፍል ውስጥ የሚሸናበት ገረወይና ግማት፣ የልዩ ልዩ ሰዎች ትንፋሽና ላብ ድብልቅልቅ ክርፋት፣ እስኪ ለመድ ቅልብሽ ከሚያሰኝ ሁኔታው ጋር ራስ ይመታል። ግድግዳው ላይ የተገደሉት ቱኋኖች ደም መጠኑ የተለያየ የቃለ—አጋኖ ምል ክት መስሎ ጠቋሯል።

የእስረኞቹ ካቦ፣ ሌሊት በነምንዳዬ ላይ የሚፈጽመውን በቀል እያሰላሰለ፣ ከሌሎቹ በተሻለ ደባደቦ ላይ ተንጋሎ ጣራ ጣራውን ያያል። እነ ምንዳዬ፣ እዚያው ማዕዘኑ ጋ ትንሽ ቦታ አግኝተው ጠጋ ሲሉ የሽንት ገረወይና አፉን ከፍቶ ተቀበላቸው። ምንዳዬ ተናነቀው።

“ማ!እንታይ ዝአመሰለ ዕላጅ’ዩ!” አለ ሠዐረ። አንዱ ማቀበት።

“ማ እባቱ ነው እሚሥቀው!? ምናለ ብትተዉን?!” አለ አንዱ እየተነፋነፈ።

“የሰው አባት አትሳደብ እከካም!” ብሎ መለሰለት።

“ዛሬ እያንዳንድሽን ነው እምረግጥሽ!” አለ ካቦው።

“አህያውን ፈርቶ ዳውላውን” ሳይል አልቀረም አንዱ በልቡ።

ምንዳዬ የደረሰበትን ጉዳት ሲያሰላስል እንቅልፍ ባይኑ አል ዞረም። ሠዐረ ወለሉ ላይ ዘርፈጥ ብሎና ግድግዳውን ተደግፎ፣ ጭንቅ ላቱን ጉልበቱ ላይ አሳርፎ ያንጎላጃል። ካቦው እነሱን ለመበቀልና ሽንት ፉት ለማሰኘት፣ ዘሎ ጉብ የሚልባቸውን ደቂቃ ይጠባበቃል።

# ምዕራፍ ሃምሳ

ሽዋርካብሽ ካንድም ሁለት ሦስት ቤት ተቀጥራ ስትሠራ ፣ ተያዥ ሆኖ ያስቀጠራትና ፣ ስታጠፋ ወቅሶ ፣ ስትበደል ተከራክሮ አይዞሽ በርቺ የሚላት ያው ምንዳዬ ብቻ ነበር ። እንዳቅምቲ አጠረቃቅማ በገዛችው ልብስ ፣ አለባበሷ እየተሻሻለ ፣ አረማመድና አነጋገሯ እየተለወጠ ፣ ሥቃ ስትጫወት ማራኪ ሆነች ። የምንዳዬም ልብ መደንገጥ ጀመረ ። "እንዴት አማረባት እባካችሁ" ይላል እየከጀላት ። የኋላ ኋላማ ዓይኑ መቀላወጥ ፣ ልቡ መናፈቅ ጀመረ ። እሷም ቢሆን ገባት ። እንደ ተጓጉ አልቀሩም ። "አሁን ብትቋጥር ምን አባቴ ይውጠኛል፣ —— አውጣኝ ጌታዬ" ይላል ከየግንኙነታቸው በኋላ ።

በመጨረሻ አንስተኛ ቡና ቤት ውስጥ ለቤት ጠራጊነት ፣ ለዕቃና ለልብስ አጣቢነት ተቀጠረች ። በየዕለቱ ጧት የቡና ቤቷን ባለቤትና ሦስት ሴት አዳሪዎች ቁርስ አብልታና ቡና አጠጥታ ቀሪ ሥራዋን ትጀምራለች ። ጥቂት ወራት እንደ ሠራች ፣ በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወንዶች ዐይናቸውን ጣሉባት ። አለፍ ስትል ጐታቿ ፣ ጠጋ ስትል ጐንታይዋ በዛ ። በዚህም ምክንያት 'ይቺ ደህና ገበያ ታስገኛለች' ተብሎ ወደ አሻሻጭነት ተዛወረች ። በሴት አዳሪነትዋ ምክንያት ከብዙ ሰዎች ጋር ተወዳጀች ። ሆቴሎችና ቡና ቤቶች እንዴት እንደሚቀጥሩም ዐወቀች ። በተጨማሪም ስለ አለባበስና አረማመድ ፣ አፈጋገግና አስተነጋገድ ፣ ስለ ውድ መጠጦች አሻሻጥና አብሮ ስለ መጋበዝ ፣ ብዙ ወንዶችን ቀጥሮ ሲያስጠጡ ስለ ማምሸት —— ——

ምንዳዬም እጅ—እግራቸው የሚናገር በሚመስል ደላሎች ተተካ ።

* * *

የወይዘሮ ዶጅ—ይጥኑ ቡና ቤት የመክፈት ወሬ ከቀኛዝማች ጆሮ የደረሰው ፣ ጉዳዩ ከተጠናቀቀ በኋላ ነበር ። በነገሩ ክፉኛ ተናደው ሆድ ሆዳቸውን ቢበላቸውም ፣ ብስጭታቸውን ዋጥ አድርገው ፣ "ምነው እኔንስ ቀደም ብላችሁ ብታማክሩኝ ፣ ላወቀበትና ለበረታ ሰውኮ ቀላል መተዳደሪያ አይደለም" በማለት ውስጣቸው ቆስሎ ላያቸው ፈገግ አለ ። "አሁንማ የምቀኝነት ያስመስልብኛል" በማለት መራቁንም

“እውነትክን ነው፣ ቀድሞውንም ቢሆን አንተና እሳቸው ኮከባችሁ ግጥም ነው”ብላ ወደ ምድጃዋ ሔደች። ከዚያም እንጀራ ቀርቦ እንደ ተበላና ቡና እንደ ተጠጣ ጨለመ።

አረጋሽ ልጅዋን አዝላ እንደመጣች ምንዳዬም የቸርነትን የበኩር ልጅ አቅፎ ሲጫወቱ አመሹ። ሲተኙ አቅራቢያ ቸርነት ጠመንጃውን ምንዳዬ ትራስጌ አስደግፎለት ወጣ። ከአዲስ አበባ የወሰደው እንሶላ፣ በጠፍር አልጋ ቁርበት ላይ ተነጥፎ፣ ባልና ሚስቱ አዲስ ብርድ ልብስ ደርበው ሲተኙ፣ ልጆቹም መደባቸው ላይ ለሽ አሉ።

በማግሥቱ ጧት ከቁርስ በፊት ፣ ምንዳዬ ለባለቤቱና ለልጆቹ፣ ለቸርነትና ለአረጋሽ የወሰደውን ልብስ ከሻንጣ እያወጣ ሰጣቸውና ለሰባት ወሯ የቸርነት ልጅም በግምት የገዛውን ጥብቆ አለበሳት። ሁሉም አዳዲስ ለብሰው ሲታዩ ማማራቸው!

መሬት ሞቅ እንዳለም ቸርነት ለጓደኛው መስተንግዶ አንድ ወጠጤ አረደለትና አረጋሽ ሕፃኗን አዝላ፣ ልኬለሽ ልጆቿን እየላላከች ምሳ ሲሠሩ፣ ወንዶቹ ጠላቸውን በገንቦ ይዘው ወደ ሰበሰብ ወጡ።

*   *   *

ቀኛዝማች፣ አረጋሽን በጣም ይወዷታል። እሷ ያየችና ያወቀችው ንብረት አይጠፋም፣ አይደፈርም። እሷ ብቅ ስትል ወሬኛ ወሬውን፣ አሚተኛ ምላሱን ይሰበስባል። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ግን፣ እንኳን በድብቅ በግልጽ ቢዝቁ፣ ያሻቸውን ቢሳደቡና ቢናገሩ ፣ “እሳቸው እንዲህ እየለፉና መከራቸውን እያዩ እሱ ለማንም የማጀቱ ሴት እየዛቀ ሲሰጥ ምን ያርጉ?” በማለት ወሬ ማቀበሏን ከተወችው ብዙ ጊዜ ሆኗታል። ሴትዮዋ ግን እመስግነዋት አያውቁም። በጣም እንዲጠሏት ያደረገቻቸው ግን ሸዋርካብሽ ነበረች። እሷ ቸርነትን ፣ እሱ ግን አረጋሽን በመውደዱ፣ “እሱም የሷ ቢጤ ያገልጋይ ልጅ ነው መሰል፣ በደህናው እንዲህ አልወደዳትም። ዕድሜ ለኛ ይበል፣ አቦ! ሲል መጣና ሠለጠነ” ብላ ጠመደችው። ባረጋሽም ላይ ዘመተችባት።

ከቁመናዋ አጠር፣ ከአካሏ ደልደል ብላ፣ ከጠይምነት ይልቅ ወደ ጥቁረት የምታመዝነው አረጋሽ፣ ጎረድረድ ያለች ደም—ግባታም ነች። ቸርነት ሲወዳት አይጣል ነው። እቆጡ ላይ የተኛ መስሎ አድፍጦ ያመሽና፣ ሌሊት ጭር ሲልለት ይወርዳል። ያዳራሹን በር ‘ቋ’ ሲያደርግ ትከፍትለታለች። ዶሮ ደጋግሞ ሲጮህ ወደ ቆጡ ይመለሳል።

“ቀኛዝማች አንድ ቀን ባገኙህና ባሯሯጡልኝ” ሲለው ምንዳዬ፣ “እኔ የተለየ አልያዝኩ!? እሳቸውስ ማጀቴ ድረስ እሚሔዱት ግሼን ማርያም ሊስሙ መሰለህ? በሱስ አይጨክኑብኝም — ጣምናውን ያቁታል” ይለው ነበር። በዚህ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ዐለፈ። ቀኛዝማች ወደ አዲስ አበባ ሔደው፣ አረጋሽ ያጉቷን ንብረት እየጠበቀች እንደ ልቧ በሆነች ሰሞን፣ ቸርነትም ቀስ በቀስ ቆጡን ተወና አረጋሽ ዘንድ አዘወተረ። ወሬውም ከቀኛዝማች ጆሮ ደረሰ። ተይ ብሎ መከልከል የማይቻል ስለ ሆነባቸው በርጋታ አነጋገሯት። ባታፍረጠርጠውም ገለጸችላቸው። “ተያይዘው ከሚኮበልሉ እዚሁ እንዳሻቸው እየሆኑ ያገልግሉ” በማለት ዝም ስላሏት ፈቃዳቸው መሆኑ ገባት። ቸርነት ቀርባ መጠየቋን እንደሰማ፣ ኃፍረትም ፍርሃትም ይዞት ነበር። ግልምጫም ጥላቻም ባለማየቱ ቀለለው። ቀኛዝማችን አስፈቅዶ ካጥር ውጪ አነስ ያለች ጎጆ ሲቀልስ ሣር አምቦች ጉድ አሉ። ያን አውርተው ሳይጨርሱ አረጋሽና ቸርነት ጎጆ ወጡ።

*   *   *

ምንዳዬና ቸርነት ጠላቸውን እየጠጡ ሲጫወቱ፣ “ጥኢት ቀን ትሰነብታላችሁ ፣ ወይስ ቶሎ ትመለሳላችሁ?” ሲል ጠየቀው።

“አንድ 15 ቀን ያህል ሳንቆይ አንቀርም፣ እሳቸውማ ብዙ ሥራ አለባቸው”

“ትንግዲህ ወዲያ ደሞ ምን ያረጋሉ?”

“እንደገና እኮ ሊወዳደሩ ነው! በያራት ዓመቱ አይደል!።”

“ያንተ ያለህ! ገና ነውና አሳራቸው፣ አሁን ደሞ እንዲህ አስደርግላችኋለሁ ሲሉ ሊከርሙ ነው በለኛ! ያቺ ሁሉ ያኗትኮ አንዷም አልተፈጠመች።”

“ሁሉንም አጠቃልዬ አስፈጽምላችኋለሁ ይላሉዋ!” ብሎ ምንዳዬ ሣቀ። ከዚያም ስለ አዲስ አበባ ኑሮው አንዳንድ እያለ ሲያጫውተው፣ ቸርነት እየተከፋም ፣ እየተደሰተም አዳመጠውና፣ “ያም አለ፣ ያም አለ አንተ እንደ ምንም እጅህን አውጥተሃል” አለው። እሱም በበኩሉ ስለ ትዳሩና ስለ ልጁ፣ ስለ ልኬለሽ ብርታትና ስለ ልጆቹ ሁናቴ፣ እንዲሁም ስለ አፈሣ አጫወተው።

“አስቸግሯችሁ ያውቃል እንዴ?” አለ ምንዳዬ ኮስተር ብሎ።

“አሁንማ ልኩን ዐውቋል! አስቸግራለሁ ቢልስ ማ ይለቀዋል? የሱ ነገር ምን መላ አለው፣ ሁለዬ አስጉዳዉ ይገባና ሲዝረጠረጥ ይገ

"ማባቱ !! ይበሏ! ዕድሜ ላንድ ሰው! ተንግዲህም አንተ አለህ !!" አለና ድንገት ቆመ ።

"አምናና ሐቻምና ፣ ሲፈትሉ ሲገምዱ ፣
መጓጉዋው ጠፍቷቸው ፣ መሾሚያ ምንገዱ ።
አሉ ሙቱ ሲሉ ፣ — — አጅሬው ገሥግሠህ ፣
እጐራው አናት ላይ እንዳሞራ ታየህ ፣
አባ ዝናብ ወንዱ ፣ ቆፍጣኔ በላይነህ ።
እርር ድብን ይበል ፣ ጠላት ቁርጡን ይስማ ፣
ሹመቱ የኛ ነው ፣ ለከርሞም ባርላማ" እንዳለም ፣ 'ይበል! ይበል! ለካ! ለካ! — — —ጎሽ!' ጎሽ! የሚል ድምፅ ተሰማ ። ካንጀት ተሥቆ ፣ ከልብ ተጨበጨበ ።

ቾርነት በዚያው ቀጠለ ።

"እንግዲህ ምን ይበል ፣ የዞን አምብ ጓዳ ፣
ወዳጅና ጠላት ፣ ዘመድና ባዳ ፤
አህያ ቀርቅቦ አጋሰስ ሲነዳ ፣
መኪና አግለብላቢው ይኸው መጣ ምንዳ !" ብሎ ሲቀመጥ ሁሉም ተንከተከቱ ። ሌሎች ሁለት ሰዎችም ፎከሩ ።

ቀስ በቀስ ሁሉም ተዳክሞ ፣ አንድ ባንድ ወደየመኝታው አዘገመ ። ምንዳዩና ቾርነት ከሆቴሉ በስተጀርባ ካለው መኝታ ክፍል አደሩ።

በማግሥቱ ማታ ቾርነት ቤት ተሰብስበው ራት ሲበሉ ፣ የትላንትናው ስካርና ቀረርቶ የተነገራቸው ልኬለሽና አረጋሽ ሲንከተከቱ አመሹ ።

ቀኛዝማች በመወዳደሪያ ክልላቸውና ውጪ ፣ በምኑም በምኑም ይጠቅማሉ ብለው ወዳመኑባቸው ሰዎች ሁሉ በበቅሎና በመኪና እየተጓዙ በማነጋገር ፣ እጅ — እጃቸውን ለሚያየው ገንዘብ ፣ ዝምድና ፣ ለሚቢቃው አደራ ፣ ውለታ ለሚጠብቀው ተስፋ ሰጥተው እንዳገባደዱ ፣ ቀሪውን ለሌላ ጊዜ አስተላልፈው ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ተነሡ ።

የምንዳዩም የዓመት ፈቃድ በማለቁ ፣ እሱም ለሥራው ቸኩሏል ። ልኬለሽ ቀኑ ፈጠነባት ። የመለየት ሥጋት በዳበሳት ቁጥር ፈገግታዋ ይጠወልጋል ። ዳግመኛ የሚለያዩባትን ዕለት ክፉኛ ጠላቻት ። ዳሩ ምን ይደረጋል ፣ የቀትር ፀሐይ መጥለቋ ፣ ውብ አበባ መጠውለጓ እንደ ማይቀር ፣ ጠላቻትም ፈራቻት የምንዳዬ መነሻ ቀን ደረሰች ።



"ልኬ?" አላት ምንዳዬ ፣ ለሱዉ መሸኛ የታረደችውን ልበ— ወርቅ ዶሮ ስትገነጣጥል ፤ "ከእንግዲህ ወዲያ እዚህ የምትቆዩት ለተወሰነ ጊዜ ነው ። ሦስት ዓመት ሙሉ ተለያይተናል ። አንደዬ'ንኳ ብቅ ብዬ ያላየኋችሁ ፣ ገና ሳልደላደል በማለት ነበር ። እንዳጫወትኩሽ አሠሪዎቻችን የዋዛ ሰዎች አይምሰሉሽ ። አብዛኛውን ጊዜ ጥቃቅን ስሕተት እየፈለጉ ከሥራ ያባርራሉ ። በተለይማ ችሎታው እንደ ነገሩ የሆነውን በቀላሉ ያስወጡታል ። እኔም ከጥሩ ጥሩ ሰዎች ጋር ጠጋ ጠጋ ስላልኩ ነው ብዙ ነገር የተማርኩት ። በዚያ ላይ ለምኑም ፣ ለምኑም አጋርና ዘመድ ያስፈልጋል ። አሁን እንደ ምንም ጥርሴን ነክሼ ራሴን ችያለሁ ። አንደዬ ሚስቴ አንደዬ ልጆቼ እያልኩ ወለም—ዘለም ባበዛማ ኖሮ ፣ ሥራ አይወድም ብለው ያፈናቅሉኝ ነበር ።"

"ኧረ ደግ አረክ! ይኸ ታዲያ የጥላቻ አዶል! አንተም እሰው አገር ሔደህ ከምትንከላፈት ጥሩ አርገሃል ። በሁለት እግር ቆሞ ነው ወግ ማውጋት ። እጅ ያጠረህ ዕለት ማንም እኔ አለሁልህ አይልህም ። ሁሉም አለሁ አለሁ ቢል የምር አይምሰልህ ፣ ሁኔታህን እያዩ ነው ። ያው ዐይንህ ነውዪ ፣ እጅህ አልራቀን ። ችግር ይሉ ነገር ነክቶን አያውቅም ። አሻጋሪም እርፍ ጨብጧል ፣ በያላይ ደሞ ቾርነት እያለ ቤታችን አይቀዘቅዝም ። ለኛ ምናምኒት አታስብ" ብላ ጥንካሬን የሚገልጽ ገጽታ አሳየችው ።

"እኔም አሳቤን ጥዬ የተቀመጥኩት እንደማይቸግራችሁ ስለማውቅ ነው ። ሥጋት ቢኖርብኝማ ኖሮ ፣ መች እንዲህ እንደልቤ እቀመጥ ነበር !።"

ስለ ሌሎች ጉዳዮች በማውራት ላይ እንዳሉ ፣ ቾርነት ገንቦውን በአሻጋሪ አሸክሞ ፣ አረጋሽም ልጅዋን አዝላ ተከታትለው ገቡ ። ሁሉም ሽከናቸውን ጨብጠው በኅብረትና በተናጠል አዳዲስና ትዝታ ነክ ጨዋታ ጀመሩ ። ወሬው እንደ ጣማቸው የልኬለሽ ዶሮ ወጥ በነጭ ጤፍ እንጀራ ታጅባ ቀረበች ። መላ ቤተ—ሰብ ዙሪያውን ከበው ቅር ጥፍጥፍ አደረጓት ። ያን ለታ ማታ ለልጆቹ የተለየ መዓድ አልተሠራላቸውም ። ድስቲቱ የታጠበች መሰላ ተነሣች ። የኩራዚቱ ላምባ እያለቀ የምድጃው እሳት ላንቃ ሲያጥር ቾርነትና አረጋሽ ወደየቤታቸው ሔዱ ። ነገ ጧት ቅርብ ናት ።

ልኬለሽ ጋደም ከማለቷ ሐሳብ ገባት ። ዶሮ ደጋግሞ እንደ ጮኸ ከእንቅልፏ ነቅታ ውሃ ጣደች ። ሲኮክሉ ካደሩት አውራ ዶሮዎች መካከል ምንዳዬ አንዱን ገብስማ አርዶት ተመልሶ ተኛ ። የፀሐይ መውጫ ቀይ አለላ እንደ መሰለ ድስቱ ወረደ ።

ወይዘሮ እልፍ—ይከንዱም ቅቤው ተንጣሎ ሽታው ዙሪያ ገባውን ያወደ የዶሮ ወጥ ሠርተው ፣ ማግሹን ባገልግል ቋጥረውታል ።

ረፋዱ ላይ ቀኛዝማች እንደተለመደው ታጅበው ሲወጡ ፣ ምንዳዬም ባለቤትና ልጃቹን ፣ እንዲሁም አረጋሽን አስከትሎ ብቅ አለ ። ጥቂት እንደ ተጓዙ አረጋሽ አጐቷን ተሰናብታ ወደ ምንዳዬ መለስ አለችና ፣ "እንደዚህ ቀደሙ ጥፍት አትበል ፣ መጣ—መጣ እያልክ ጠይቀኝ" አለችው እንባዋ ተንቆርዞ ።

"ተንግዲህስ እመጣለሁ ፣ እንደተዚህ ቀደሙ አልቆይም" አላት ፈገግ ብሎ ። ከነልጅዋ ስሞ ሲሰናበታት ሆዱ ባባ ።

እኩለ ቀን ላይ ማጀቴ እንደገቡ የቀኛዝማች ኮተት ካህዮች ላይ ተራግፎ ላንድሮቨር ላይ ተጫነና ሰውዬው አጃቢዎቻቸውን አስከትለው በገቢያው መኻል ዐለፉ ።

የማጀቴ ገቢያ ዙሪያውን በልብስና በሸቀጣ—ሸቀጥ ሱቆች ፣ በሻይ ፣ በጠላና በጠጅ ፣ በሥጋና በቡና ቤቶች የተከበበ ሲሆን ፣ ገበያተኛውን ከጉብታ ላይ አሽቆልቁሎ ለተመለከተው ፣ በሰፊ ጉድጓድ ቦታ የሚርመሰመስ ዝንጉርጉር ፍጥረት ይመስላል ።

ምንዳዬ በኩራትና በላላይ—ላላውቅ ስሜት መኪናይቱ ውስጥ ገብቶ ሞተር በመቀስቀስ አስጓራት ። ሞተሩን ሳያጠፋ ወርዶም ኮፈኑን ከፈተና አንዳንድ ነገሮችን አጠባበቀ ። ልኬለሽ እየገረማት ተደሰተች ። ልጆቹም ከናታቸው ጐን ቆመው ፈዘው ያያሉ ።

ቀኛዝማች ተመልሰው ሲመጡ ፣ ምንዳዬ ከፊቱ ፈገግ ፣ ከመንገዱ ገለል ብሎ ተቀበላቸው ። የልኬለሽ ዐይን እንባ አዝሎ የልጆቹ ፊት ተንቀረበበ ።

"እኔ ነኝ ጥፋተኛው ፣ እዚያው ሜር—እምባ ብሰናበትሽ ኖሮ" አላት በማስመሰያ ቁጣ ።

"ምናረኩ? ለምን መጣሽ ብለህ ነው?" አለች አቀርቅራ ።

"መምጣትሽንማ ወድጄዋለሁ ፣ አንቺ ግን ልቅሶሽ በየት — —"

"ግድ የለህም! ፈርቼ መሰለህ? እንኳንና ዛሬ ያኔዬም አልፈራሁ — —"

"ቢሆንም ! እያለቀሱ መሸኘት ጥሩ አይደለም ። እንደማትፈሪማ ዐውቃለሁ" ብሎ ትከሻዋን ያዘና ፣ "ቢቃ! ከእንግዲህ ብንለያይ ለጥቂት ጊዜ ነው" አላት ደርበብ ብሎ ቀዝቀዝ ያለ ፊቷን እያየ ። በመጠኑ ፈገግ አለች ።



ቀኛዝማች ከቤተሰባቸውና ከአምስት ሰዎች ጋር ላንድሮቨሯ ውስጥ ገቡ ። ምንዳዬ ፣ ልኬለሽንና ልጆቹን ፣ እንዲሁም ቸርነትን ስሞ መኪናይቱ ውስጥ ገባ ። መደዳውን ቆመው ካይናቸው እስኪሰወር አዩት ።

ላንድሮቨሯ ካራቆሬ ከተማ እንደ ደረሰች ፣ ቀኛዝማች እህታቸውን ለመሰናበትና በሰበቡም የጀመሩትን የዝና ማስፋፋት ወሬ ለመነስነስ ወደ ወ/ሮ ጌጤነሽ ታፈሰ ቤት ሔዱ ። ሴትዮዋ ወንድማቸውን ለማስደሰትና ወሬውም ባካባቢው እንዲወራላቸው በማሰብ እንግዶቹን እንዲያድሩ ጠየቋቸው ። ተስማሙ ።

ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ወዳጅ ፣ ዘመድ ጥየቃ ፣ ልጆቹ ባልንጀሮቻቸውን ፍለጋ ሲዘዋወሩ ዋሉ ። የወ/ሮ ጌጤነሽና የባለቤታቸው ግብዣ ሲበላና ሲጠጣ ሌሊቱ ተጋመሰ ። በማግሥቱም ረፋዱ ላይ መስተንግዶው ቀጥሎ ጐረቤቶችም ተጋበዙ ።

ከዚያም መኪናይቱ የትም ሳትቆም ዘጠኝ ሰዓት ላይ አዲስ አበባ ደረሰች ። ቡና ተጠጥቶ ጥቂት እንዳረፉ ፣ ቀኛዝማች አብረዋቸው የመጡትን እንግዶች 'ከተማ ላስጐብኛችሁ' ብለው ወደ ካዛንቺስ ይዘዋቸው ገሠገሡ ።

ቀኛዝማች ካንገታቸው ቀና ፣ ካረጋገጣቸው ኮራ ብለው ወደ ይፋት ቡና ቤት ሲገቡ ፣ ወ/ሮ ዶጅ—ይጥኑ ዳሌአቸውን አቅፎ ቂጣቸውን እንደ ትልቅ ወታቦ ካድበለበለው ደጋናማ የብረት ወንበር ላይ ተቀምጠው ፣ ካንድ ወንድ ጋር እየተሣሣቁ ይዝናኑ ነበር ። ድንገት ስለ ተደረሰባቸው ሴትዮዋ ደንገጥ ሲሉ ፣ ቀኛዝማች ነደዳቸው ። ሆኖም ልብ ያላሉ መስለው ፣ ምንዳዬንና እንግዶቹን አስከትለው ወደ ውስጥ ዘለቁ ። ወ/ሮ ዶጅ—ይጥኑ ፈጠን ብለው ተከተሏቸው ።

"ምነው ቶሎ እመለሳለሁ ብለሁ ፣ ይህን ያክል ጥፍት ማለትሁ ?" እያሉ ከመኝታ ክፍላቸው ፊት ለፊት ያለውን በር ከፍተው አስገቧቸው ። ከመኝታ ቤታቸው ጋር የተያያዘው ይህ የሰበሰብ ክፍል ፣ የእንግዳ መቀበያ ሲሆን ፣ ከቡና ቤቱ ጀርባ ዐሥር ርምጃ ያህል ወደኋላ ፈቅ ይላል ። መኻል ላይ አጠር ብሎ ልከኛ ስፋት ያለው ጠረጴዛና ስድስት ወንበሮች ተደርድረዋል ። ከውጪ የመኝታ ቤቱ በር የተጋረደበት ጌጠኛ መጋረጃ ረዝሞ ዘርፋ ወለል ያስሳል ።

ቀኛዝማች ፣ የተቀዳላቸውን ዊስኪ ፣ ሌሎቹ የቀረበላቸውን ቢራ እየጠጡ ስለ ውሏቸው ሲያወሩ ፣ ሴትዮዋም ደንበኛቸውን ሸኝተው ተቅላቀሉ ። የወ/ሮ ዶጅ—ይጥኑ የመስተንግዶ መዐድ ቀርቦ ከተበላና

ደብተራ ፣ ጠንቋይ ፣ ዘማዊ ፣ ዋልጌ ፣ ሠራተኛ ፣ ገበሬ ፣ ወታደር ፣ ተማሪ ፣ ሁሉም ታመሱ ። በጊዜ መስኖ እየፈሰሱ! ተናነቁ ፣ ላይላቀቁ ።

ቀኛዝማች 'ሰው በድያለሁ ፣ ኃጢአት ሠርቻለሁ' ብለው ባያምኑም ፣ "ሳናውቅ በስሕተት ፣ ስናውቅ በድፍረት የሠራነውን ኃጢአት ይቅር ይበለን" እየተባለ የሚነገረው በዘፈቀደና በከንቱ አይደለም በማለት ፣ የየዕለቱ ጸሎትና ይቅር በለኝ አቤቱታቸው ፣ ያለፈውን ኃጢአት ሁሉ የሚደመስስላቸው ስለሚመስላቸው ፣ የሠሩትን ሠርተውና የበደሉትን ቢበድሉም የንጹሕነት ስሜት ይሰማቸዋል ። ይህ የብዙዎቹ ቢጤዎቻቸው ባሕሪ ነው ።

አንድ ቀን እንደ ተለመደው ማለዳ ተነሥተው ፣ ሰበሰቡ ላይ የጸሎት መጽሐፋቸውን ሲያነቡ ፤

"ትክክለኛ አገዛዝ እንዲህ አይደለም! ከዘር ማንዘር የወረደ ፣ ጂኒ ቁልቋል ፣ በእግዚአብሔር የተሠየምኩ እያሉ ማወናበድ ያታላዮች ሥራ ነው! ኢድየትስ! የይሁዳ ዝሆን ፣ የሰሎሞን ወርንጭላ! እያሉ ባገር ላይ መጋለብ! — — ባስታርድስ! ተዝቢ አይደለም! ዘመድ ! አልጋ! ዙፋን! ቱጋን! ቤሽቲያ! እናቱን! ቢፈልግ እኔ እበቃዋለሁ! ሶኖ ኢዮ አቾዮ ዲ ፌሮ!" እያለ የሚጮህ ድምፅ ይሰሙና ፣ ንባባቸውን ያቋርጣሉ ። አላስችል ስላላቸውም ፣ የአጥሩን በር ከፍተው ብቅ ይላሉ ።

ዳለቻ ኮት ለብሶ ፣ ካኪ ሱሪ የታጠቀ ፣ የሸሚዙ አዝራሮች ተበጥሰው ፣ ደረቱ የተገለጠ ፣ ረዘም ያለ ጸጉረ እንጭብር ወንዳወንድ ወጣት ፣ ባዶ እግሩን ጐዳናው መሐል ቆሟል ።

"እኔ ደሃ መስሎኝ ነበር ። ለካ ይኸ ሰው እብድ ነውና! እንዲህ እንደ ልቡ ዘውድና ንጉሥ ሲሳደብ እንዴት ዝም አሉት?" አሉና ስለ ዘውዱና ንጉሡ ተናደዱ ።

"ጨቋኝና ግፈኛ ሁሉ ቀብሮ ነው ። ቀብሮ በግ ትበላለች ። እነሱ ሰው ይበላሉ! ጅቦች! ሞንስተርስ! እናታቸውን! እኛ እናስብላችኋለን ፣ እኛ እናውቅላችኋለን እያሉ ያታልላሉ! 'ግሬት ቶከርስ አር ግሬት ላየርስ' አለ ያ ፈረንጅ! አብሮት ያለው ሁሉ ቀፈታም ነው ። ቦርጫቸውም በሰዎች ነፍስ ተሞልታለች! ነፍሶቹ ሲፈራገጡ ይታዩኛል! ጉሮሯቸውን አንቄ አስተፋቸዋለሁ! እኔ ሮኪ ማርሲያኖ! 'ሰዎች ይወዱሃል የምንልህ እኛ ነን እንጂ ፣ ሕዝቦችስ ሞትህን ይመኛሉ አይሉትም!' የይሁዳ አንበሳ አንተ ንጉሣችን እየተባለ ይዘመራላ! ዐፈር—ድሜ! ሕዝቦች የሚያጨበጭቡልህና እልል የሚሉልህ ሳይወዱና



ሳያውቁ ነው በሉት! ላላላላ! ቡም! — — ቡቡቡቡም! ነግሬሻለሁ ፣ ፍቅር ይዞኛል! የራሷ ጉዳይ !"

"የሊቀ—መላኩ ያለህ! ዛሬስ ምኑን አሰማኸኝ! የእብዶች ማሰሪያና ማከሚያ አለ እየተባለ እንዴት ዝም ይሉታል!" ብለው እየተናደዱ ወደ ቤት ገቡ ። ንዴቱ ሳይበርድላቸው ዋሉ ።

ከዚያን ቀን በኋላ ፣ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች አዩት ። ስድብና ዘለፋው እያናደዳቸውም ክፉኛ ጠሉት ። መኖሪያው ባቅራቢያቸው ስለ ነበር ፣ "የኪራይ ቤት ምን የማያመጣው ጉድ አለ!? ከእብዱ ያከራዮቹ ስለ ከነዘመዶቹ ነበር ወስዶ ማሰር" አሉ ተናደው ። ቀስ ብለው ነገሩን ሲያጣሩ ፣ በአእምሮ ሕመም ምክንያት ትምህርቱን ያቋረጠ የዩኒቨርስቲ ተማሪ መሆኑን ዐወቁ ።

"ቢሆን ነው! ሌላ ሰው እንዲህ አጥንት የሚሰብር ነገር አይናገርም ። እዚያስ ሥር ሥሩን ስንትና ስንት መዘዘኛ አለ አሉ ። ወይ ነዶ!" ብለው ትክን አሉ ። የሚሰሙና የሚያዩት እያደር በዛ ። አብዱል ከተ ሰዎችም አንደበት ፣ ለየት ባለና በተለባበሰ መልክ መስማት ጀመሩ ። አንዳንድ የምክር ቤት እንደራሴዎችም ፣ ውስጥ—ውስጡን በግልጽ ፣ ባደባባይ ግን ፣ በዘዴ ፣ የአገዛዙን ሁኔታዎችና ስልት እየነቀፉና እያጥላሉ እንደሚናገሩ እያደር ታወቃቸው ። መሻሻልና መለወጥ አለበት የሚባለው ሁሉ ከነከናቸው ። ከሚወዱት የሚጠሉት በዛ ።

በየጊዜው ስለ ገጠር መሬት ፣ ጭሰኛና ባለርስት ፣ አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ፣ እሳቸው መጠንና ባሕሪውን የማያውቁት ዲሞክራሲ ፣ ነጻነት ፣ መጻፍ ፣ መናገር መሰብሰብ ፣ መደራጀት የሚባሉ ጉዳዮች በዙባቸው።

ሠልፍ — አቤቱታ — እምቢታ — ሽብር — ግድያ — እስራት — ስደት — ሞት — ሙብት — ፍትሕ — ርትዕ — ለውጥ ፣ ለውጥ!! እዚህም — እዚያም — የትም!

ቀኛዝማች እየናቁና እያጥላሉ ፣ ችላ ሲሉ ፣ ጊዜ ፣ እንደ መስኖ ውሃ ፈሰሰ ፣ ሁሉም እየታመሰ ።

## ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

ትንሽ የእሳት ፍንጣሪና — — —ገሥጋሽ ማዕበል

ልደታ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ለዕለተ ሰንበት ጸሎት የተሰበሰቡት ምዕመናን ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥና ውጪ ፣ ወጋግራውን ፣ ግንቡን ፣ ዛፉን ፣ ምርኩዝና መቋሚያ እየተደገፉ ፣ ሰሚ ለሚሉት መልአክ ጸሎትና ልመናቸውን ያቀርቡ ነበር ።

አንዳንዶቹ አንጋጠውና አቀርቅረው ፣ ሌሎች በቁማቸው ወዳንድ ወገን ዝልስና ዘምበል ብለው ፣ ቢቃላቸው እያነበነቡ ወይም ከመጻሕፍት እያነበቡ ይጸልያሉ ። ሁሉም ከየራሱ ምኞትና ችግር አኳያ በተለያየ የሕሊና ምጥቀት ወደ ወሰን የለሹ ሰማየ—ሰማያት ቃለ ጸሎቱን ይልካል ።

የማለዳዋ ፀሐይ ገና ለጋ ስለ ነበረች አየሩ ለብ አላለም ። ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የካህናት ቅዳሴና ዝማሬ ፣ ከውጪ ቆማጦች ፣ ዐይነ— ስውራን ፣ መፃጉአን ፣ ሽባዎች ፣ ደንቆሮዎች ፣ ወዘተ . . . በተለያየ የልመና ዜማና ቃና የዕለቱን ታቦት እየጠሩ ይለምናሉ ። ዐይነ—ስውሩን ቆማጣው እየመራው ፣ ሽባውን ዲዳው እየተሸከመው እየዞሩ ፣ እየቆሙ ፣ እየተንፏቀቁና በሽታ ያለበትን ገላቸውን እያሳዩ ። ድህነት ፣ ሕመም ፣ እጦት ፣ ረኃብና እርዛት! ከሰማይም ከሰውም ይለምናሉ ።

ካህናቱ ወደ ሰንበቴ ቤት ሔዱ ። የቸኮሉ ምዕመናንም ወደየቤታቸው ።

መስበኪያው ማማ ላይ አንድ በብረት ዘንግ መስቀላቸው ላይ ትንሽ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ያበቱ ፣ ከወዝ—ጠገብ ቡናማ ቆዳ ልብሳቸው ሥር ደረታቸው ላይ ካምስት ዙር በላይ ሰንሰለት የታጠቁ ፣ የተለያየ መጠን ባላቸው ማኅደሮች መጻሕፍት ያነገቱ ፣ ትልቅ የነሐስ መስቀል ደረታቸው ላይ ያንጠለጠሉና ፣ ዐፈር ከሚመስለው ቆባቸው ሥር ጥቀርሻ የጠገበ ቁጥርጥር ገመድ የሚመስል ረጂም ጸጉራቸው አንገትና ትከሻቸው ላይ የሚንከባለል ፣ መጫሚያ የለሽ ባሕታዊ ቆመው ይሰብካሉ ።

"ሰማይና መሬት ያልፋል ! ቅዱስ ቃሉ ግን አያልፍም ! የዚህ ዓለም ማንኛውም ሀብትና ንብረት ፣ ዕውቀትና ጥበብ ሁሉ ፣ ጠፊና

## ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት

ቀኛዝማች ፣ በመወዳደሪያ ክልላቸው ውስጥ ፣ ከድሆች ጭራሮ በር እስከ ሀብታሞች ልግ ማንቃ ፣ ከቤተ ክርስቲያን ደጇ—ሰላም እስከ ጋለሞታ ጓዳ ፣ ከተራ መሸታ እስከ አካባቢው ትልቅ ቡና ቤት ፣ ዓርማቸው ተለጥፎና ዝናቸው አድጎ ፣ ያልሠሩት ሥራ ተጋንኖ ተወርቷል ። ዐልፎ ዐልፎ ፣ "ኢዲያ!ቢመረጡ ባይመረጡ ፣ ለኛ ምን ሊፈይዱልን ነው ? ያው በገሌ አለች ድመት" ቢባልም ፤

"ደሞ ዛሬም ፣ በበሬ ተምሳሌት መመጣቱ ለምን ይሆን? እያረሳችሁ ወዲህ በሉት ለማለት ይሆን? እንዲህ አረግላችኋለሁ ፣ እፈጥምላችኋለሁ እየተባለ ሲቦተለክብን ተከረመና ፣ ያው ለራሳቸው ቁና—ቁና ብር ቲዝቁብን ከረሙዪ ፣ ለኛ ምን ጥብ ያለልን ነገር አለ? እኛ መች አጣነውና ዓመት የለፋንበትን ይገፋፍፉንና ባንድ ቀን መብል እንደ ልላችሁ ይሉናል" ቢሉም ፤

"ዘንድሮማ አፍ—ለቆባቸዋል ፣ ያንን ለምድ እሚያከል ኮቶግራፋቸውን እየበሬእችን ግንባር ላይ ሊለጥፉት ጥኢት ነው የኸራቸው ! የኛ አገር ሹሞች እያ ሸዋ እሚሉ አገር ደርሰው ቲመጡ ይብሰባቸቸዋል!" ቢባልም ፣ ቀኛዝማች ከምክር ቤት አባላት በሰሙት የንግግር ልምድና ፣ ከልዩ ልዩ ሰዎች ጋር በተገናኙ ቁጥር በቀሰሙት አንዳንድ የአነጋገር ፈሊጥ በመጠቀም ፣ አጠር ወይም ረዘም ያለ ንግግር በማድረግ ፣ የአብዛኛውን ተራ ሰው ቀልብ በተስፋ ቃላት ሸነጋግለው ፣ በድጋሚ የሕግ መምሪያ ምግር ቤት አባል ሆነው ከተመረጡ ስምንት ወራት አልፈዋል ።

የጉዳዩ መሳካት ብዙዎቹን የቀኛዝማች ዘመዶችና ደጋፊዎች ያረካ ቢሆንም ፣ በተለይ ግን ፣ "አሁን ከኔ ሌላ ማንን ፈጥረሃል ? ምቀኞቼን ሁሉ ጠራርገህ ለዚህ አበቃኸኝ ፣ እስቲ አሁን ያንተን ውለታ በምን ይመልሷል" ያሉትን ወ/ሮ እልፍ—ይከንዱን ፣ በምርጫው ወቅት ባሳየው ትጋትና በኦረጋሽ በኩል በቋጠራት የሥጋ ዝምድና ሰበብ አንድ ጥማድ የሚያውል ማሳ የተሰጠው ቸርነትንና ፣ በወ/ሮ እልፍ—ይከንዱ ግፊትና በእርሱም አባባል የተሰበረ ስሙን ለማደስ ባደረገው መሯሯጥና ባሳየው ትሕትና ከቸርነት እኩል ማሳ የተፈቀደለትን አፈሣን ፣ የምርጫው ውጤት በጣም አስደስቷቸው ነበር ።

* * *

ሆኖም ፣ አፈጻጸሙ በአዳዲስ ምክንያትና የቢሮ ስልት ተንተተ። ንዋይ ከሕግ በላይ ፣ ፍትሕ ከጥቅም ግርጌ ዋሉ ። የኋላ—ኋላም ፣ “ሁለቱ ሰዎች ወደ ሥራ ገበታቸው ቢመለሱ ፣ ሌሎች ሠራተኞችን በስውር እያሳደሙ ሥራ ስለሚያዳክሙ ፣ ከድርጅቱ ውጪ ቆይተው ደመወዛቸውን ቦርዱ ጽ/ቤት ድረስ እየቀረቡ ይቀበሉ” በሚል የአሠሪ አቤቱታ ፣ የቀድሞው ውሳኔ በሌላ የጓዳ ችሎት ተገዝግዞ ጉዳዩ እንደገና ተዳፍኖ ተድበሰበሰ ። ሠራተኞቹ በደላቸውን ለማሰማት ወደ ልዩ ልዩ ባለሥልጣኖች ቢቀርቡም ፣ ሕሊናቸውን ሸንግሎ ፣ ቅስማቸውን የሚሰብር እንጂ ፣ ተስፋቸውን የሚያለመልም ሹም አጡ ። እየመሸ ሲነጋ ፣ ለማይገኝ ፍትሕ ፍለጋ — — —



## ምዕራፍ ሃምሳ አምስት

ምንዳዬ ፣ ካንድም ሁለት ሦስቴ በመመላለሱ ፣ ከቅዳሜ ገበያተኛ ጋር ወደ ሣር—አምባ ሲሻገር እንደ በፊቱ ብዙ ሰው አጀብ—ከበብ አላደረገውም ነበር ። ልኬለሽ እንደ ምኞቷ ሴት ልጅ ወልዳ ማጥባት ከጀመረች ሦስት ወር አልፏታል ። ዛሬም ደስ አላት ። አመሻሽ ላይ ከቆላ የገባው ቸርነት የባልንጀራውን መምጣት ሰምቶ ከነባለቤቱ ሲሔድ ፣ የነምንዳዬ ጎጆ በሚዋደዱ ሰዎች ሣቅና ፈገግታ ተሞላች ። በተከታታይ ሦስት ቀናት እስከ ውድቅት እያወሩ ናፍቆታቸውን ተወጡ ።

* * *

“ይኸው እስከዛሬ ድረስ ተለያይተን ኖርን ፣ ከእንግዲህ ብቻሽን መቀመጥ የለብሽም ። ከዚህ ቀደም ስንት ዓመት ተንገላታሽ ፣ መምሬ ተክለ ጎርጊስ እንኳ ‘ለሁሉም ጊዜ አለው’ እሚሏት ጥሩ ፊሊጥ አለቻቸው” አላት ፀሐይ እየሞቁ ሲያወሩ ።

“ኧረ እኔ አልተንገላታሁም ፣ ምን ጐሎብኝ ምን አጥቼ! ስለኔ አትጨነቅ ።”

“አሁንማ ደህና ራሴን ችያለሁ ፣ ትላንትም ከትላንት ወዲያም አጫውቸሻለሁ ፣ ከእንግዲህ እዚህ አትኖሪም — —”

“ወዴት እንሔዳለን?”

“አዲሳባ!”

“መገን ያንተ ነገር! ቤቱን ለማን ጥዬው?”

“የትኛውን ቤት ልኬ? ቤታችንማ ዞን አምባ ፈርሶ ቀረ! ይህ እኮ ሳባ ዐይኔና ደግበረሊላ አይደለም ። ይኸ የመቆረር አገር ነው ፣ የመቆያ ቤታችን ነው ።”

“እኔ እኮ እምልህ ፣ ፍየሎቹ ፣ አህያውና በሮቹስ?”

• “ግድየለሽም ሁሉም ቀላል ነው ፣ ፍየሎቹን እቤቶችሽ ጋ ዞን አምባ እንልካቸዋለን ፣ በሮቹም ይሸጣሉ ፣ ሌላ ምን አለ ? ይኸው ነው ።”

ፈላጊው በዛ ። እያሌ ወራት የተጓተቱ የጋራ ስምምነቶች ወር በማይ ሞላ ጊዜ ተጠናቀው ተፈረሙ ። ሲኞር ካርሎ ቤርናርዲኒ የቃጣው ሳይመታና ዛቻው ፈር ሳይዝ ፤ እያሌ ነገሮች ምስቅልቅላቸው ወጣ ። የነካርሎ የጠራራ ዱለታ ፤ ወደ ውድቅት ሲለወጥ ፤ ሠራተኞቹ ጋራዡ ግቢ እየተሰበሰቡ መወያየት ጀመሩ ። የሸኹ ጠጋ—ጠጋ ፤ የተዳከሙ ጠንከርከር አሉ ። ያቸፍቻፊዎች ምላስ እየጠወለገ ወሬ እያቀበሉ ማራኮት ዋጋ አጣ ።

እናም ፤ ጊዜው እንደ መስኖ ውሃ እየፈሰሰ — — ቀናት እንደ ናዳ ድንጋይ እየተንደረደሩ — — የተነሣው ሞገድ እያፈረጠና እያላጋ ፤ ይብስ ማጥለቅለቁን ቀጠለ ። የይሁዳው አንበሳ ግርማ ሞገስ ተገፎ ፤ ሰለሞናዊው ዘውድ ሲንኮታኮት ፤ ቀኛዝማች በሽብር ተንገርግበው እናቱን እንደ ተመታ ዘንዶ ተወራጩ ።

ወራቱ ሲጨምርም ሥጋትና ብስጭታቸው በዛ ። ወርኃ—የካቲት ላይ የተሰነዘረው ግዙፍ ሰይፍ ፤ ቀኛዝማችን አወራርዶ ፤ የጭሰኞቻቸውን የድግር—እላቂ አሳከላቸው ። ሕሊናቸው እየሚሸሸ ፤ ነፍሳቸው ተንገላታች ። ከነጠር ጋር የተያያዙበት ወፍራም የጥቅም ደም ሥራቸው ድንገት ተጎመደ ። የጉማጇን እርባና ቢስ ጫፍ ከሩቁ ጨብጠው ቀሩ ።

ቀኛዝማች አውርተው ከማያባሩ ፤ ለፍልፈው ከማይሰለቹ ሰዎች ጋር ቤት ዘግቶ መዶለትን አዘወተሩ ። ወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ፤ "ዘንድሮ እኚህ ሰውዬ እንጃላቸው ፤ ያዳሜን ወሸካታ እየሰበሰቡ ጉድ ሳያመጡብኝም አይቀሩ ፤ ከዚህ ሁሉ ያንኑ ሚካኤላቸውን ቢለማምኑ ይሻላቸው ነበር" ይላሉ ጓዳ ለጓዳ ።

ቀኛዝማች ግን ፤ ካንዳንድ የመኝታ ቤትና የሳሎን ውይይት በኋላ ፤ ልባቸው ተስፋ ቢጤ ሲያጎነቁል ፤ "እረዲያ ! ምንም ቢሆን ከዘንድሮ ጎፈሬ ያንበሳ ሙላጣ ይሻላል" ይሉና ፤ ቤት ለቤት ሲንጎራደዱ ልበ—ሙሉነት ይሰማቸዋል ። በእንደዚያ ያለው ወቅት በሙቶና በሺህ የሚቆጠር ጀሌ አስከትለው ፤ ጠላትና ምቀኛዬ ነው የሚሉትን ሁሉ ረፍርፈው እንደ ልባቸው ሲጎማለሉ ይታያቸዋል ።

የወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ሐሳብ ከቅናት ወደ ሥጋት ፤ "ከራሳቸው ጉዳይ ወደ ምነው ጠፉና" ፤ በመጨረሻም "እኚህ ሰውዬ አንድ ነገር ሆነውብኝ ይሆን እምላኬ? የማር እምባው አባቴ አትርሳኝ ፤ አታጋልጠኝ" ወደ ማለት አጋደለ ።

የሰውዬው ተለዋዋጭ ጠባይ ካንድ ውሳኔ ወደ ሌላ ውሳኔ እየተሸጋገረ ፤ አንዱ ሐሳብ በሌላ ሐሳብ እየተሻረ ቁም ስቅላቸውን አዩ ።



የኋላ ኋላ ግን ፤ ከሚመክሩት ጋር መክረውና ያዛልቃል የሚሉትን ብልሃት መርጠው ወሰኑ ። ጊዜም አሳባከኑ ። ሚስትና ልጆቻቸውን ይዘው ፤ መኪናና ቤት ንብረታቸውን ከሣር እምባ ላመጧቸው የቤት ሠራተኞችና ዘበኞች ፤ "በርትታችሁ ጠብቁ ፤ አገር—ቤት ደርሼ እመለሳለሁ" ብለው ፤ በአውቶቡስ አጣዬ ከተማ ሲገቡ ቀለል ቢላቸውም ልባቸው አላረፈም ። ስለ አካባቢው ሁኔታ ወሬ እያጠያየቁ ሁለት ቀን ዘመድ ቤት ውለው አደሩ ። ደስ ስላላቸውም እሞታቸው ፈሰሰ ።

ሐምሌ 18 ቀን አመሻሽ ላይ ካራቆሬ እህታቸው ቤት ሲገቡ ፤ ሁሉም ነገር ቀዝቅዞና ተዳክሞ ፤ አገር ምድሩ ግርማ—ሞገሱ ተገፎ የተከዘ ስለ መሰላቸው ፤ ራሳቸውን በአዘኔታ ነቀነቁ ። የተደረገላቸው የመስተንግዶ መጠን ግን አልቀነሰም ። ይሻል ይሆናል ብለው የገመቱት አካባቢ ይብስ ፍሞ ስለ ቆያቸው ጋደም ብለው ሁኔታውን ሁሉ አሰላሰሉት ። ከማያዳፍኑት እሳትና ከማይጋፈጡት ሞገድ ፊት—ለፊት ቆመው ፤ አሻግረው ተስፋ ይዘራሉ ።

ሳይበላቸው እንዳከኩና ሳይቆረቁራቸው እንደ ተገላበጡ ነጋ ። ጧት ወደ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱም ከእማቻቸው በቀር ሌላ ሰው አልተከተላቸውም ። ከገረገራ ውጪ ቆመው በመጸለይ ላይ እንዳሉ ፤ አንድ ድምፅ አወካቸው ። ከአብሮ አደጋቸው ዜማ ይልቅ ፤ አየሩን ሰንጥቆ የሚሰማው የሬዲዮ ድምፅ ቀልባቸውን ሰለበው ። ድምፁ ወደሚሰማበት ቤት ለመሔድ ልባቸው ቆመ ። እማቻቸውን አስቀድመው እየተፍገመገሙ ቁልቁል ሲወርዱ ፤ ጉልበታቸው ራደ ።

እማችዬው ፤ "እንዴት አደራችሁ እየሀ ቤቶች?" ብለው ገቡ ። ቀኛዝማች እውጪ ቆመው አስፈሰፉ ። ወዲያው እግሩ የተጣመመ አግዳሚ ተጠርጎላቸው ገብተው ተቀመጡ ። በማርሽ እየታጀበ የሚስገመገመውን ሙዚቃ ፤ ወደፊት ለመጥ ፤ ወደኋላ ለጠጥ ፤ ፊታቸውን ቋጠር ፤ ፈታ ፤ ቅጭም እያደረጉ በንቃት አዳመጡ ። የቤት ኪራይ ጥገታቸው ነጠፈች ። እንኳን ሰዉን ፤ የሚረግጡትን መሬት ፈሩት ። እህታቸው ቤት እንደ ደረሱም ማንንም ሳያናግሩ ፤ ሕመሙ እንዳገረሸበት ሰው ጥቅልል ብለው ተኙ ። ደፍሮ ያናገረ አልነበረም ። ቃል ሳይተነፍሱና እህል ውሃ ሳይቀምሱ ውለው አደሩ ።

ገባ ወጣ የሚለውን የጐረቤት ሰው ሁሉ ስለ ጠሉት ፤ ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ ማጀቴ ሔዱ ። የሚያውቋቸው ሁሉ በአክብሮት ተቀበሏቸው ። ከዘመድ ቤት በተገኙ በቅሎዎች ሣር እምባ ሲገቡ ፤ መምጣታቸውን ያየና የሰማ ፤ "እንኳን ደህና መጡ" እያለ እጅ ነሣ ። መስተንግዶውም አልተጓደለ ። ደስ አላቸው ። አንዳንዶቹ ግን ፤ "ደሞ ተንግዲህ ወዲያ ለሱ ማ ጉብ—ቂጥ ይላል" እያሉ ቀሩ ።

ቀኛዝማች ዋል—አደር እንዳሉ ፤ የቀድሞዋ ሣር አምባ ፡ ያዘዙና የነዱባት ፤ የቀጡና የገረፉባት ፤ ያማሩና የተከበሩባት ፡ የተፈሩና ዓለማቸውን ያዩባት ሣር አምባ ቀረቀረቻቸው ። ይኸነዬ "ምናባቱ !" ብለው መላ ሙቱ ! እንደልብ በፏለሉበት አገር እንደ ሽለመጥማጥ እየተሹለኮለኩ ደባ መተብተብ ያዙ ። ወኔ ለመቋጠርና ከጉልበታቸው በታች የወረደውን ሱሪያቸውን ከፍ ለማድረግ ፤ ሥር—ሥሩን መቅበዝበዝና ቢጫዎቻቸውን ማነፍነፍ ጀመሩ ። አጃቢ ጀሌአቸውን መልምለው እንዳበቁ ፤ አቅጣጫቸውን አምታተውና ዓላማቸውን ሰውረው ከሣር አምባ ወጡ ።

* * *

በዋናው የሠራተኞች ማኅበር ጽ/ቤት በኩል የለውጡን ተፃራሪዎች የሚፋለሙ ሠራተኞች ከየድርጅቱ ሲመረጡ ፤ ምንዳዬ በጋለና አማረ ንጋቱ በፈቃደኝነት ተመዝግበው ማስልጠኛ ገቡ ። ከልዩ ልዩ ፋብሪካዎች የሔዱ ሠራተኞች ለ፫ ወራት ያህል ወታደራዊ ልምምድ ተሰጣቸው ። ሁለቱ ሠራተኞች በሾፌርነትና በሜካኒክነት አያሌ አውራጃና ወረዳዎችን እንዳዳረሱ ፤ ሰሜን ሸዋ ውስጥ የሚካሔደው ፍጥጫና ቁርቁስ በመካረሩ ፡ ወደዚያው አመሩ ። የነምንዳዬ ክፍል ከፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባላት ጋር መንዝና ግሼን ፡ ይፋትና ጥሙጋን እያሰሰና እየተዋጋ ዋናው ምሽግ ከነበረበት አካባቢ ደረሰ ።

ከአካባቢው ወረዳዎች የዘመቱ አያሌ ገበሬዎች ፤ ሠራተኞችና የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባላት ፤ የማጥቂያና የመከላከያ ወረዳቸውን ይዘው ፤ ለትንቅንቅ ሲዘጋጁ ፡ ልዩ ልዩ የነፍስ ወከፍና የቡድን ጦር መሣሪያ የያዙ የለውጡ ተፃራሪዎችም ጀሌዎቻቸውን አስቀድመው እያስመሸጉ አመቺ የውጊያ ቀጣናቸውን ይዘዋል ። የጉዳትን መጠን ለመቀነስ ሲባል ፤ አለአግባብ ቸኩሎ የማጥቃቱ ሁኔታ ዘግይቶ ፡ በቅድሚያ የጠላትን አቅም በሽምቅና በስለላ ስልት ማዳከም አስፈላጊ መሆኑ ስለ ታመነበት ፤ እስከዚያው የነምንዳዬ ጦር ቦታ መርጦ ሠፈረ ።

* * *

እሳቱ ባቄላ ምድር ላይ ቦግ ብሎ ነደደ ። ተራራና ገመገሙ ፤ ሸለቆና ስርጓጉጡ ፡ በተኩስ ድምፅ ተናጋ ። ጥይት እንደ በረዶ እየፈላቀቀ ረፍዶ ጠረረ ። ወግያው ተጧጧፈ ። ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ የሕዝቡ ጦር አይሎ ከፍታ መሬቶችንና ምሽጎችን ቢያስለቅቅም ፡ የለውጡ ተፃራሪዎች ጦር መሬት ልሶና ድንጋይ ነክሶ እስከ መጨረሻው



ተዋደቀ ። ፀሐይ ስታዘቀዝቅ ግን ፤ ተንዶ ተፈረካከሰ ። ወዲያው በጉርሻ የተገዛ ሎሌ ፡ በስብከት የተነዳ ጀሌ ፤ በሥጋ ዝምድና የተደለለ አሽከር ፡ ሀብት ያተበተው ባለርስትና ምኞት የቀተተው ከበርቴ ፤ በየቋጥኙ ሥር ሲረፈረፍ ፤ ቀሪው እጁን እየሰጠና እየተማረከ ገባ ።

ፀሐይ እንደ ጠለቀች ፤ ምርኮኞቹ በሙሉ ለጥበቃ ቅርብና ምቹ በሆነ ቦታ ላይ እንዲሰበሰቡ ተደረገ ። በየገደላ—ገደሉ ሲወድቁና ሲነሡ ፤ ሲዘሉና ሲንከባለሉ የዋሉት ምንዳዬና አማረ ፤ ራታቸውን በልተው ጋደም አሉ ።

ድል አድራጊዎቹ እየሸለሉ ሲያቅራሩ ፤ ተሸናፊዎቹ አንገታቸውን ሰብረው ሲተክዙ አጥቢያ ኮከብ ታየች ።

"ምነው አንተ አለመሸለልህ ምንዳ?" አለው አማረ ጉመኔ ብርድ ልብሱን ደርቦ ሜዳው ላይ በጀርባው እንደተኛ ።

"ምን እባክህ ፤ የከተማ ሰው ሆኜ ሰውነቴ ባልጎ ፤ እንደ ዱሮውማ ቢሆን አባቱ ነበርኩ— —"

"እኔስ ትንሽ ታሰማኛለህ ብዬ ነበር ለጉራ እንዲመቸኝ" አለ እየሣቀ ።

"ከእንግዲህ ወዲያ ውጊያ የለም ብለህ ነው — — ያኔዬ እፎክራለሁ!"

"ላንተ ቀረብህ እንጂ ፡ እኔማ እስኪበቃኝ ሰምቻለሁ ።"

"እሱስ ለኔም ለራሴ ቢሆን ጥሩ ነበር ፤ ወገን ያበረታል ፤ ወኔ መቀስቀሱስ ቢሆን ቀላል መሰለህ ? ቆይ ለወደፊቱ" ብሎ ከት ብሎ ሣቀና ፡ "አማረ ?" አለው ።

"አቤት!"

ንግግሩ በሣቅ እየተቆራረጠ ፤ "አሁን ያንን ካርሎን እዚህ ብታገኘውስ?"

"አይ አንተ! በምን ትገዘ አለህ? እሱን ብቻ አልነበር? — — አለ እንጂ! ኧረ ስንቱ!"

"ባትልም ሞልተውልሃል! እንደኔ ደረስ ብለህ ባየኻቸው!" አለ ራሱን እየነቀነቀ ።

አማረና ምንዳዬ ፤ የሁለት ምርኮኞች ስም ለማስመዝገብና የማረኩትን መሣሪያ ለማስረከብ ወደ ማስመዝገቢያው ቦታ ሲጓዙ ፡ ከየት

"በኔ የተነሣ አይወድህም ነበር እኮ! ማን አስታረቃችሁ?"

"ማ ያስታርቀናል! እኛው እስበሳችን እያደር ነገሩ ሲገባን ፣ ተነጋገርን ።"

"እስቲ ሙት በለኝ?"

"ፍቅርህን!"

"አሁን ምንዳዬን እዚህ አገኘሁት ብትለው ምን ይላል?"

"ምን ይላል ብለህ ነው? ሰው በዋለበት ውሃ በፈሰሰበት አይደል?"

"ወየ ጉድ! እንዴት እሚገርም ነገር ነው! በላ! በል ሒድ ንገ ረውና ከኔም ጋ አገናኘን ። ድሮውንም ቢሆን ሁላችንም ከውቀት እጦት ነው ። አሁንማ ጉዳዩ እየገባን ነው ።"

"ኧረ እሱ እሚለውን በሰማህ! አለማወቅ እያለ ፣ ሁለዜ እንደ ተን ገበገበ ነው ። ከወ/ሮ እልፍ ይከንዱ ጋ እማ ዐይንና ናጫ ሆነዋል! በወሬ ወሬ ያንተን ነገር ቲያነሡበት ፣ ምነው አሁን ባገኘሁትና እግሩ ላይ ወድቄ በታረቅን ሲል በሰማኸው !"

"ታዲያ አብረን ሔደን እናነጋግረው እንዴ? ወይ አንተ ሔደህ ትነግረውና . . ."

—"ለማንቻውም እኔ ሔጄ ልንገረው ፣ እየሁ ቆዩኝ — —" ብሎ ሊሔድ ሲል ፣

"እኔ እንደሁ በጣም ነው ደስ ያለኝ ፣ አሁንማ ያንዳችንን ደም አንዳችን እያፈሰ እንዴት ጠላት እንሆናለን?" እንዳለ ቸርነት ሔደ ።

ልዩ ልዩ ሰዎች ምርኮኛና መሣሪያ በግንባር እያስጠሩና እያቀ ረቡ አስመዝግበው ሲመለሱ በነአማረ አጠገብ ያልፋሉ ።

ቸርነት ፣ አፈሣንና ሌሎች ሁለት ሰዎችን አስከትሎ ሲመለስ ፣ ምንዳዬ ገና ከሩቁ ፈገግ ብሎ ጠበቃቸው ። የሁሉም ከንፈር ተላቀ ፣ የሁሉም ፊት ፈገገ ። ምንዳዬ ያነገተውን መሣሪያ ለአማረ ሰጥቶ ሁለት እጁን ሲዘረጋ ፣ ቸርነትም የአፈሣን ጠበንጃ ተቀበለው ። እያሌ ዓመታት እንደ ተለያዩ ባልንጀሮች ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። ከከፍተኛ የጥላቻ አዘቅት ወጥተው ፣ ፈጽሞ ይሆናል ብለው ባልጠበቁት ጊዜ በቀላሉ ሲገናኙ ፣ ሁሉንም ደነቃቸው ። ከግማሽ ሰዓት በላይ ሲያወሩ የቀድሞወን ባይረሱም ፣ አላወሱም ።



ሁሉም ባንድነት የማረኩትን መሣሪያ ለማስረከብ ፣ ወደ ማስመ ዝገቢያው ቦታ አመሩ ። ሠራተኞቹ አንዳንድ ፣ ገበሬዎቹ ሁለት— ሁለት ምርኮኞች አስጠርተው አስመዘገቡ ። ባካባቢው ቆመው አላፊ አግዳሚውን ሲመለከቱ ፣ የተመዘገቡ ምርኮኞች ባጠገባቸው እያለፉ በዚያው ይመለሳሉ ። አንድ መሣሪያ ያነገተ ደልዳላ ጐልማሳ ፣ ምር ኮኛውን ለማስመዝገብ ጮክ ብሎ ተጣራ ። ደስ እንዳለው ከቁንጥና ጤውና ከገጽታው ያስታውቃል ።

እነ ምንዳዬ ፣ የቅርብ ወዳጁን መርዶ እንደ ሰማ ሰው ክው ብለው ደንግጠው እርስ በርስ ተያዩ ። አንድ ረዘም ያሉ ገብስማ ጸጉራቸው የተንጨበረረ አዛውንት ፣ ወፈር ያለ አካላቸውን እያርገደገዱ አቀርቅ ረው ባጠገባቸው ዐለፉ ። ካኪ ሱሪያቸው ከወደ ግርጌው ተተርትሮ ፣ ኮትና ሸሚዛቸው ትከሻና ጀርባቸው ላይ ተዘንጥሎ ገላቸው ይታያል ። ዐፈር መስለዋል ። ከምንዳዬ ይልቅ እነ ቸርነት ዐይናቸውን ትክል አድርገው አዩ ። ምኑን ከምን ይጠራጠሩት ። እሳቱን ውሃ ፣ ተራራውን ሜዳ አይሉት ። ያዩትም ፣ የሰሙትም እውነት ነው! አይቶ ካረጋገጠ ዐይን የበለጠ ማን ይታመን! ሁሉም ወደፊት ተጠጉ ። ሰውዬው ድን ገት ቀና ብለው ዙሪያውን ሲመለከቱ ዐይናቸው እነ ቸርነት ላይ በማረፉ ከመቅፅበት ደንግጠው አቀረቀሩ ። መንፈሳቸው ተሸብሮ አካላቸው ራደ ። እንደገና ቀና ብለው ሲመለከቱ ከምንዳዬ ጋር ተያዩ ። ሕልማዊ ትዕይንት መሰላቸው ።

ትኩር ብለው ሲያዩት ፣ "የኔ ነገር በቃው ፣ ተሸንፌአለሁ ፣ ምር ኮኛህ ነኝ" የሚሉት መሰለው ። ሹክክ ብለው ባቅራቢያው ሲያልፉ ፣ ትኩር ብሎ አያቸው ። እምብዛም ሳይርቁ ከምርኮኞቹ ጋር ተቀላቅ ለው በስተዳር ተቀመጡ ። የእምነታቸው አቅጣጫና ባሕሪ ቢለያይም ፣ የአወዳደቃቸው ፍጻሜ አሳዘነው ። ሰው ፣ ኑሮ ፣ ከፍና ዝቅ ማለት ይኸው ነው?" አለ ለራሱ ።

እነ አማረን ቆዩኝ ብሎ ሻንጣውን ወዳስቀመጠበት ሔደ ። ከሸራ ሻንጣው አንድ ኮት አውጥቶ ወደ ምርኮኞቹ አካባቢ ተመለሰና ፣

"አንድ ምርኮኛ ለማነጋገር ፈልጌ ነበር?" አለው መዝጋቢውን ።

"ለምን? ምን ልትለው ?"

"የምላቸውንማ እኔ ዐውቀዋለሁ ።"

"ምን ታነጋግረዋለህ! አዬ ! 'እርጎ መስሎሽ እርሾ ጥልቅ' እንዳ ይሆን! ይልቅ አትሞኝ ፣ ጠላትህን ጐርፍ ሲወስደው ምራቅህን አክል በት ይባላል ። ሊገልህ የመጣን ጠላት አትዘንለት" ብሎ ምንዳዬን በንቀት አየው ።

“እኔ ይኸን መች አጣሁት ! ያሸነፈውን የሚገል ዐውሬ ነው ! ስለ በቀሉ ግድ የለህም ! እዮ ሌላ ፡ ወዮ ሌላ !”

“ከፎከረ የጠረጠረ ብዬ ነዋ! ይኸንዬ አንተ ተማርከህ ቢሆን ፡ እግር—ተወርች ታስረህ ነበር!”

“እዩዩዩ ! ‘ለቀባሪው አረዱት’ አሉ ! ያንዬ መጥተህ ታየኛለህ !” ብሎ ያለ ፈቃድ ጥሎት ወደ ምርኮኞቹ ሲሔድ ፡ እነ ቸርነትም ተከተሉት ።

“ቀኛማች በላይነህ !” አለ ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ።

“አቤት!” ብለው ቀና ሲሉ ፡ የያዘውን ኮት አለበሳቸው ። ትኩር ብለው አዩትና ዐይናቸው እንባ አቀረረ ።